አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የድህረ ምረቃ ትምህርት መርሃ ግብር
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል
የኢትዮጵያ ሥነጽሑፍና ፎክሎር

የአርጎባ ብሄረሰብ የቤት ውስጥ መገልገያና የማጌጫ ቁሶች፤ በአማራ ክልል፣ ደቡብ ወሎ ዞን፣ አርጎባ ልዩ ወረዳ

በ
ዐቢይ አስማማው

ሰኔ፣ 2000 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የድህረ ምረቃ ትምህርት መርሃ ግብር
የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል
የኢትዮጵያ ሥነጽሑፍና ፎክሎር

የአርጎባ ብሄረሰብ የቤት ውስጥ መገልገያና የማጌጫ ቁሶች፤ በአማራ ክልል፣ ደቡብ ወሎ ዞን፣ አርጎባ ልዩ ወረዳ

በኢትዮጵያ ሥነጽሑፍና ፎክሎር የኤም.ኤ.ዲግሪ
ለማግኘት ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት

በ
ዐቢይ አስማማው

አማካሪ
ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ

ሰኔ፣ 2000 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

የአርጎባ ብሄረሰብ የቤት ውስጥ መገልገያና የማጌጫ ቁሶች፤ በአማራ ክልል፣ ደቡብ ወሎ ዞን፣ አርጎባ ልዩ ወረዳ

በ

ዐቢይ አስማማው

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍለትምህርት

የድኅረምረቃ መርሐግብር

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

አማካሪ	ፊርማ
የውስጥ ፈታኝ	ፊርማ
የውጭ ፈታኝ	ፊርማ

ምስጋና

በመጀመሪያ ሁሉን ማድረግ ለሚችል እግዚአብሔር ምስጋና ይሁን።

ይህ ጥናት ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ ውድ ሰዓታቸውን ሰውተው ጽሑፌን በማንበብ፣ ስህተቶችን በማረምና አቅጣጫ በመጠቆም እንዲሁም የቁሳቁስ እርዳታ በማድረግ ድጋፋቸው ላልተለየኝ ለአማካሪዬና ለመምህሬ ለዶ/ር ፈቃደ አዘዘ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ይህንን ጥናት ማድረግ እችል ዘንድ የትምህርት ዕድል ለሰጠኝ የትግራይ ክልል ትምህርት ቢሮ፣ በመረጃ ማሰባሰቡ ወቅት አስፈላጊውን ትብብር ላደረጉልኝ እንዲሁም መረጃዎችን ላቀበሉኝ የአርጎባ ልዩ ወረዳ የቢሮ ኃላፊዎች፣ የአካባቢው ነዋሪዎች፣ የቀበሌ ተጠሪዎች፣ የልማት ጣቢያ ሠራተኞችና መምህራን እንዲሁም የጥናት ተሞክሮዎቻቸውን ላካፈሉኝ ግለሰቦች ላቅ ያለ ምስጋና ይገባቸዋል።

በትምህርት ቆይታዬ ወቅት ምክራቸውና ድጋፋቸው ላልተለየኝ መምህሮቼ አቶ ዘሪሁን አስፋው፣ ዶ/ር ዮናስ አድማሱ፣ ዶ/ር ሲቨንጉድ ማርክ፣ አቶ መስፍን መሰለ፣ አቶ ጌታቸው እንዳላማውና አቶ መ.ሰ.ሰው አስራቴ የከበረ ምስጋናዬ ይድረሳቸው።

የትምህርትን ጥቅም በአዕምሮዬ ከመቅረጽ ጀምሮ አስፈላጊውን ነገር ሁሉ በማሟላትና ቤተሰባዊ ፍቅራቸውን በመለገስ እዚህ ደረጃ እንድደርስ ለረዱኝ ለአባቴ ለአቶ አስማማው ንጋቱ፣ ለእናቴ ለወ/ሮ ውባሉ ጌጡ እንዲሁም ለወንድሞቼና ለእህቶቼ፣ ኃይለየሱስ፣ መ.ሰ.ጌታ፣ ደሳለኝ፣ ሃናና ቤተልሔም አስማማው፣ አገኘሁ ካሳሁንና ፋንታነሽ ግርማ ዕድሜና ጤናን ይስጥልኝ።

ይህንን ጥናት በማደርግበት ወቅት ፈርጀ ብዙ ትብብራቸውን የለገሱኝን ዘመዶቼን (ወ/ሮ የሺ ታደሰ፣ ወ/ሮ አስካል ፀሃዬ፣ ወ/ሮ እታለማሁ አበባውና ቤተሰቦቻቸውን) እና ጓደኞቼን (መ.ሰ.ነሽ መልኬ፣ አስቴር መ.ሰ፣ ደስታ አማረ፣ ሃና ጌታቸው፣ ንጉሡ አቦሰጥ፣ አብርሃም መብራት፣ ሃብታመ እንግዳው፣ ያብባል መ.ሰ.ዓለም፣ መስፍን ማናዜ፣ ሃብታመ ዘሪሁን፣ ቴዎድሮስ አለነ፣ ወርቃለማሁ ዳኛቸው፣ መልከሜዴቅ መ.ሴ፣ መስፍን አባተ፣ ታምሩ ተረዳ ሌሎችም) ሳላመሰግን አላልፍም።

ማውጫ

አርዕስት ገጽ

ምስጋና i

የአርዕስት ማውጫ ii

የቃላት መፍቻ v

አጠቃሎ vi

1. መግቢያ 1

1.1. የጥናቱ ዳራ 1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት 4

1.3. የጥናቱ ዓላማ 6

1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ 7

1.5. የጥናቱ ወሰን 8

1.6. የመረጃ መሰብሰቢያና መተንተኛ ዘዴዎች 9

1.6.1. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ 9

1.6.1.1. ቀዳማይ መረጃዎች የተሰበሰቡበት ዘዴ 9

1.6.1.1.1. የቃል መጠይቅ 9

1.6.1.1.2. ምልከታ 10

1.6.1.1.3. የጽሑፍ መጠይቅ 11

1.6.1.1.4. የተተኳሪ ቡድን ውይይት 11

1.6.1.1.5. ናሙና ጥናት (Case Study) 12

1.6.1.2. ካልኣይ መረጃዎች የተሰበሰቡበት ዘዴ 12

1.6.2. የመረጃ መተንተኛ ዘዴ 12

1.7. የመስክ ተሞክሮ 13

1.8. ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች 15

1.9. የጥናቱ አደረጃጀት 17

2. ክለሳ ድርሳን 19

2.1. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት 19

2.2. የትውሮች ቅኝት 21

2.2.1 ቱሳዊ ባሕል ምንድን ነው? 21

2.2.2. የቱሳዊ ባህል ዓይነቶች 24

2.2.2.1. ሃገረሰባዊ የእጅ ሥራ 24
2.2.2.2 ሃገረሰባዊ ሥዕል 25
2.2.2.3 ሃገረሰባዊ ምህንድስና 26
2.2.2.4 ሃገረሰባዊ ልብስ 26
2.2.2.5 ሃገረሰባዊ የምግብ አሠራር 26
2.2.3. የቁሳዊ ባህል መገለጫ ባህርያት 27
2.2.3.1. ዘመን ተሻጋሪነት 28
2.2.3.2. ቀዳማይነት 28
2.2.3.3. ተጨባጭነት 28
2.2.3.4. ተወካይነት 29
2.2.3.5. የተፈጥሯዊና የተሰጣፊ ጸጋ ባለቤትነት 29
2.2.4. ቁሳዊ ባህልን የመመደቢያ መስፈርቶች 31
2.2.5. ቁሳዊ ባህልን የመተንተኛ ሞዴሎች /አንጻሮች/ 33
2.2.6 ቁሳዊ ባሕልን የመተንተኛ ሂደቶች 34
2.2.6.1 ገለፃ 34
2.2.6.2 ትርጓሜ 35
2.2.6.3 ጥቅማ 35
2.2.7 ቁሳዊ ባህሎች እንዴት ይሰበሰባሉ? እንዴትስ ይሰነዳሉ? 35
3. የተጠኚ አካባቢውና የነዋሪ ብሄረሰቡ ዳራዊ መግለጫ 39
3.1. የተጠኚ አካባቢው ዳራዊ መግለጫ 39
3.2. የአርጎባ ብሄረሰብ ዳራዊ መግለጫ 39
3.2.1. ጥንተ አመጣጥና አሠፋፈር 40
3.2.2. ባህላዊ፣ ማህበራዊና ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች 42
3.2.2.1. በሉ 42
3.2.2.2. ጋብቻ 45
3.2.2.3. ፋጢማዬ 50
4. የእጅ ባለሙያዎች ሙያና ሕይወት 55
4.1. ጥናቱ ያተኮረባቸው የእጅ ባለሙያዎች ትውውቅ 55
4.2. የእጅ ባለሙያዎች፣ የአሰራር ጥበባቸውና ውጤቶቻቸው 56
4.3. የእጅ ባለሙያዎቹ ሙያውን የለመዱበት መንገድ 58
4.4. የእጅ ባለሙያዎቹ ያጋጠሟቸው ችግሮች 61

5. የናሙና የቤት ውስጥ መገልገያና የማጌጫ ቁሶች ትንተና 64
5.1. የናሙና የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶች ትንተና 64
5.2. የናሙና የማጌጫ ቁሶች ትንተና 76
6. ማጠቃለያና የይሁንታ ሀሳቦች 90
6.1. ማጠቃለያ 90
6.2. የይሁንታ ሀሳቦች 91

ዋቢ መጻህፍትና ጽሁፎች
አባሪዎች

የቃላት መፍቻ

ሆሳ	=	ዋጋ የሌለው ነገር፤ የማይረባ።
መናም	=	ሕልም። መናም አየሁ = ሕልም አየሁ።
መቅዳድ	=	በእጅና በማሽን የሚሠራ ባሕል እንፀባራቂ የሆነ የሴቶች (ቀይ) መቀነት።
ሱቢ	=	«ንጋት ላይ» እንደማለት ነው። ሰዓት አመላካች፤ በእስልምና ሃይማኖት ሕግ መሠረት የእምነቱ ተከታዮች የእለቱን የመጀመሪያ ስግደት የሚሰግዱበት ሰዓት።
ሲላ	=	«ታዲያ» እንደማለት ነው።
ሸህ	=	የእስልምናን ሃይማኖት ትምህርት የተማረ የሃይማኖት መሪ።
ቲያስ	=	በተፈጥሮ ወይም በሰው አማካይነት የሚደርስ ችግር (በደል)።
ቃዲ	=	በእስልምና ሃይማኖት ታላቅ ቦታ የሚሰጠውን ኪታብ (የቁርዓንን) ትዕዛዛት መሰረት በማድረግ የጋብቻ ውልን የሚያስፈጽም ሰው።
በሌ	=	ባሕላዊ የዕርቅ ስርዓት። አንድም በበሌው ስርዓት የሚምለው ሰው የሚጨብጠው ቁስ።
ቦለቅያ	=	ወይባ፣ መልሆና ቀጋ የተሰኙትን የእንጨት አይነቶች በማጨስ ውበትን ለመጠበቅ የሚታጠኑት የወላፈን እጥበት፤ ቦለቅያ የሚለው ቃል የመታጠኛ ቁሱንም ያመለክታል።
ተርቲብ	=	የአንድ አካባቢ ሰዎች በየተራ ቡና እያፈሉ የሚጠራሩበትና በአንድነት የሚጠጡበት ስርዓት።
ኒካ	=	የጋብቻ ውል፤ ኒካ ማሰር = ለመጋባት መዋዋል፤ ሰማንያ መፈራረም እንደማለት ነው።
አርሂብ	=	ወደቤት ግባ፤ ጎራ በል፤ እኛን ምሰል እንደማለት ነው።
አበጋር	=	በሌ በተሰኘው የዕርቅ ስርዓት ዳኝነቱን የሚሰጡት የሀገር ሽማግሌዎች፣ አስታራቂዎች። በማሕበረሰቡ ዘንድ የተከበሩ ከመንግስትም እውቅና የተሰጣቸው ሰዎች።
ወቂት	=	የክብደት መለኪያ፤ 1 ወቂት = 1 ጠገራ ብር (ማር ትሬዛ) = 28 ግራም = 4 ፈረንካ (የአጼ ኃይለስላሴ ዘመን 50 ሣንቲም)።
የዘመድ ዳኛ	=	በሌ በተባው ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓት ፍርዱን ከሚሰጡት የተመረጡ ታላላቅ ሰዎች (አበጋሮች) ጋር አብሮ በፍርዱ ሂደት የሚመክርና በከሳሽና በተከሳሽ ስምምነት የሚመረጥ (ለሁለቱም አማካይ የሆነ) ዳኛ።
ዘየረ	=	በእጁ ሰላምታ ሰጠ። በእጁ ጨበጠ።
ጠፍ	=	የእርሻ መሬትን ለምነት የሚገልጽ ቃል። ጠፍ መሬት = ለም መሬት።
ፋጢማዬ	=	ልትወልድ ለተቃረበች ሴት (9ኛ ወሯ ላይ) በሰላም እንድትወልድ የሚከወን የፀሎት ስርዓት።

አጠቃሉ

ይህ ጥናት «የአርጎባ ብሄረሰብ የቤት ውስጥ መገልገያና የማጌጫ ቁሶች፤ በአማራ ክልል፣ ደቡብ ወሎ ዞን፣ አርጎባ ልዩ ወረዳ» በሚል ርዕስ ሲዘጋጅ የብሄረሰቡን የቤት ውስጥ መገልገያና የማጌጫ ቁሶች የመለየትን፣ በናሙና ቁሶች ላይ በማተኮር ቁሶችን ከቁስነታቸው አንድም ከባህል መገለጫነታቸው አንጻር ትንታኔ የማቅረብን ወዲያውም በቁሶችና በባለቤት ብሄረሰቡ መካከል ያለን ግንኙነት አጉልቶ የማሳየትን ዓላማ ይዞ ነበር።

እነዚህንም ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ፣ አጥኚው፣ የቃል መጠይቅንና ምልከታን በዋነኛ የመረጃ ማሰባሰቢያነት፤ የጽሁፍ መጠይቅን፣ የተተኪሪ ቡድን ውይይትንና ናሙና ጥናትን (Case Study) በአጋዥነት ተገልግሏል።

በተጠቀሱት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተገኙት መረጃዎችም በምዕራፍ ሁለት ከተከለሱት የተለያዩ ድርሳናት አንፃር የተተነተኑ ሲሆን ፤ የትንታኔውም ውጤት የሚከተለው ነው።

በናሙናነት የተመረጡትና ለትንታኔ የቀረቡት «11» ቁሶች ናቸው። ከእነዚህም ውስጥ «5ቱ» የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶች ሲሆኑ ብሄረሰቡ በአካባቢው በቀላሉ ከሚያገኛቸው ንጥረ ቁሶች (ቆዳ፣ እንጨት፣ ድንጋይ፣ አፈርና ቅል) የተሠሩ ሆነው ተገኝተዋል። ቀሪዎቹ «6ቱ» ደግሞ የማጌጫ ቁሶች ሲሆኑ ከብር፣ ከነሃስ፣ ከኒኬልና ከሸማ የተሠሩ ናቸው። ከሚውሉበት የሰውነት ክፍል አንጻርም፣ የአንገት፣ የእጅ፣ የወገብና የእግር ተብለው ተመድበዋል።

በጥናቱ የተተነተኑት ቁሶች በብሄረሰቡ አባላት ዘንድ አገልግሎት ላይ በሚውሉበት ጊዜ ቀድሞ ከተሠሩለት ዓላማ ባሻገር ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደረጃን የሚያመላክቱ፣ የእርስ በርስ መስተጋብርን የሚያሳዩ ናቸው። ከዚህም ባሻገር ከ'Schelereth' የ«አገልግሎት ሰጪነት»፣ የ«መዋቅራዊነት»፣ የ«ተምሳሌታዊነት»፣ የ«ባህላዊነት»፣ የ«አካባቢያዊነት»፣ የ«ባህርይ አመላካችነት» እና የ«ማህበራዊነት» ሞዴሎች አንፃር የሚተነተኑ፣ አንድም፣ ሞዴሎቹን ለማብራራት በአስረጅነት የሚቀርቡ ሆነው ተገኝተዋል።

ከላይ የተጠቀሱትን የጥናቱን ግኝቶችና የአካባቢውን ነባራዊ ሁኔታዎች መነሻ በማድረግም፣ አጥኚው፣ የልዩ ወረዳው የባህልና የማስታወቂያ እንዲሁም የጥቃቅን ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮዎች የብሄረሰቡን ቁሶች በመለየቱና በመሠነዱ፣ የእጅ ባለሙያዎችንም በመደገፉ ረገድ ሥራዎችን ቢሠሩ የሚሉ የይሁንታ ሀሳቦችን ሠንዝሯል። ከዚህም ባሻገር፣ የቁሳዊ ባህል ጉዳይ የሚመለከታቸው ተቋማት የውይይትና የምርምር ሥራ መርሃ ግብሮችን ቢቅርፁና መስኩን ቢያበለጽጉት የሚል ተጨማሪ ሀሳብ አቅርቧል።

1. መግቢያ

ይህ ክፍል ዘጠኝ ንዑሳን አርዕስተ ጉዳዮችን ያካተተ ሲሆን፤ በዋናነት የጥናቱን የትኩረት አቅጣጫና የአጠናን ዘዴ ለማስተዋወቅ ተዋቅሯል።

1.1. የጥናቱ ዳራ

የአርጎባ ብሄረሰብ በኢትዮጵያ ከሚገኙት በርካታ ብሄረሰቦች አንዱ ሲሆን መገኛውም የስምጥ ሸለቆን ምዕራባዊ ጫፍ ተከትሎ በአራት የተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች እንደሆነ ጥናቶች ይጠቁማሉ (Stitz, 1973:185፤ ነጋሽ፣ 1981:13፤ Weeks, 1984:50፤)። እነዚህም፣ የአማራ፣ የሐረር፣ የኦሮሚያና የአፋር ብሔራዊ ክልሎች እንደሆኑ ልብ ይሏል። ከዚህም አንፃር፣ የአርጎባ ብሄረሰብ ከአማርኛ፣ ሐረሪ፣ ኦሮምኛና አፋርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ሕዝቦች ጋር ተቀላቅሎ እንደሚኖር መገንዘብ ይቻላል።

የአርጎባን ብሄረሰብ ታሪካዊ አመጣጥና አሰረጫጨት በተመለከተ Weeks ሦስት አከራካሪ መላምቶች እንዳሉ አትቷል (1984:50-51)። *የመጀመሪያው* መላምት፣ «ቤኒ ኡማያ» (ኋላም-አርጎባ) የተሰኘው የአረብ ጎሣ (ለማብራሪያው ከታች ሦስተኛውን አንቀጽ ይመለከቷል) በ750 ድኅረ ልደተ ክርስቶስ (A.D) አካባቢ ከነበረበት የአረብ ግዛት ሲፈናቀል በሰሜን የኢትዮጵያ ክፍል እንደሠፈረ የሚገልፅ ነው። *ሁለተኛው* ደግሞ፣ በ13ኛውና 14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አካባቢ በኢትዮጵያ የተከሰቱትን የሃይማኖት ጦርነቶች የሚያወሳ ሲሆን፤ ቀደም ሲል በሰሜን አካባቢ ይኖር የነበረው *የወላስማ*[1] ሥርወ መንግስት ቀስ በቀስ በሰስ ቀንቶት ወደ መካከለኛው የኢትዮጵያ ክፍል በመምጣት ይፋት አውራጃ ላይ ጠንካራ የእስላሞች ግዛት እንደመሠረተ ይናገራል። በኋላ ግን፣ በዓፄ ዳዊት (ቀዳማዊ) እና በዓፄ ይስሃቅ ሠራዊት አማካይነት ድል ተደርጎ ወደ ቀይ ባህር አቅጣጫ በመሸሽ በአዳል አካባቢ መስፈሩን ይተርካል። *ሦስተኛው መላምት*[2] እንደ ሁለተኛው ሁሉ የጦርነትን ታሪክ መነሻ ያደረገ ሲሆን፤ ያቀረበውም ማስረጃ በግራኝ አህመድና በክርስቲያን ገዥዎች መካከል የነበረውን ግጭት ነው። ግጭቱ የተቀሰቀሰው በግራኝ የጅሃድ ጦርነት አወጃ ምክንያት ሲሆን፤ ከግራኝ ሞት በኋላ ግን የተፈጠረው ክስተት ለአርጎባዎች መሰደድ ምክንያት እንደሆነ ጠቁሟል። እንደምን ቢባል፣ መሪው የተገደለበት ሕዝብ ከአዳል-ሐረር ወደ «ደናኪል በረሃ» በመሰደዱ። አንድም፣ በዚህ ወቅት በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ አካባቢ የነበረው የኦሮሞ ሕዝብ የታሪክ አጋጣሚውን

---

[1] የታሪክ ጸሃፊው አለቃ ታዬ «ወላስማ» የሚለው ቃል ከዓረብ አገር ሸሽተው የመጡን ዘሮች እንደሚያመለክት ለመጠቆም የሚከተለውን ማስታወሻ አስፍረዋል። «... በይፋት ያሉ አርጎባዎች የዚህ የዓሊ ገዳይ የአብዱራሒማን ዘሮች ናቸው። ... ስማቸው ወይም አበጋዛቸው ወላስማ ነው። ወላስማ ማለት ወላ እስላም ማለት ነው። ወላ እስላም ማለትም እስላም ያይደለ ማለት ነው። አባታቸው ዓሊን ስለገደለ ይህን ስም ከዓረቦች ተቀበሉ ይባላል» (የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ፣ 1964:69፤ አጽንኦቱ የእኔ ነው)።

[2] ይህ መላምት እንደሁለተኛው ሁሉ አርጎባዎችን ከቀደምት ጀምሮ በኢትዮጵያ ይኖሩ እንደነበር የማመላከት አንድምታ ይስተዋልበታል።

ተጠቅሞ ወደ ሰሜኑ ክፍል ግዛቱን ማስፋፋት በመጀመሩ የአርጎባ ብሄረሰብ ራሱን ከጥቃት ለመከላከል መኖሪያውን እየለቀቀ በከፍተኛ ቦታዎች (በተራራዎች) መስፈር ግድ ሆኖበታል።

ከፍ ሲል ከተጠቀሱት የአርጎባን ብሄረሰብ ታሪካዊ አመጣጥና አሰረጫጨት ከሚያሳዩት መላምቶች፣ ከመጀመሪያው ጋር በተያየዘ መልኩ «አርጎባ» የሚለው ሥያሜ እንደተገኘ Weeks፣ ሃጂ በሽር የተሰኙ የ97 ዓመት አዛውንትን በዋቢነት ጠቅሶ አስገንዝቧል (1984:50)። አዛውንቱ እንዳሉትም፣ «ቤኒ ኡማያ» የተባለው የዓረብ ጎሣ ቀደምት መኖሪያውን ለቆ ወደ ኢትዮጵያ በሚገባበት ወቅት ሰዎች ተመልክተው «አረብ ገባ» ሲሉ ተናግረዋል፤ ይህ ንግግራቸውም በጊዜ ሂደት «አርጎባ» ወደሚል የብሄረሰቡ ወዲያውም የቋንቋቸው መጠሪያነት ተቀይሯል።

ሥያሜው፣ አንድም የብሄረሰቡን ሃይማኖትና የመተዳደሪያ ሥልት አመላካች እንደሆነ Stitz (1973: 188) ጠቁሟል። ከዚህም አንፃር፣ «አርጎባ» ማለት ሃይማኖቱ እስልምና የሆነ[3]፣ በግብርና፣ በሽመና ወይም በንግድ ሥራ የሚተዳደር ብሄረሰብ እንደሆነ በአካባቢው ማኅበረሰብ ዘንድ ይታመናል። ከዚህም ባሻገር፣ «አርጎባ» የሚለው ሥያሜ የብሄረሰቡን መኖሪያ አካባቢ (በይፋት አውራጃ የሚገኝ ወረዳ) ሊያመላክት እንደሚችል ከሣቴ ብርሃን ተሰማ ጠቁመዋል (1951:720)።

የአርጎባን ብሄረሰብ ቋንቋ ዐቢይና ንዑስ ትኩረታቸው አድርገው ያጠኑ ምሁራን እንደገለፀት፣ ብሄረሰቡ «አርጎባ» የተሰኘ ቋንቋ አለው፤ ምድቡም፣ በኢትዮጵያ ከሚገኙት የሴም ቋንቋዎች ሲሆን ከአማርኛ ጋር ዝምድና ይስተዋልበታል (Ullendorff, 1960: 126፤ ዮናስና ሌሎች፣ 1966:44፤ Hetzron, 1969:5፤ Bender, 1976: 33)።

ስለ አርጎባ ቋንቋ ሲነሳ አብሮ ሊታይ የሚገባው ጉዳይ ቋንቋውን ባጠኑት ምሁራን መካከል የሚስተዋለው ወጥ ያልሆነ የድምዳሜ ሃሳብ ነው። እነ Leslau (1952:251)፣ Stitz (1973: 185)፣ ነጋሽ (1981:7) የአርጎባ ቋንቋ ላለመጥፋቱ እርግጠኞች ሆነው በሌሎች ቋንቋዎች ተጽዕኖ ላይ መውደቁን ግን ሳይጠቁሙ አላለፉም። በአንፃሩ፣ እነ Ullendorff (1960:126)፣ ዮናስና ሌሎች (1966:44)፣ Weeks (1984:50) ደግሞ የቋንቋውን በአገልግሎት ላይ መገኘት በመጠራጠር ገልፀዋል።

የቋንቋውን ጎልውና አስመልክቶ በተመራማሪዎቹ የተሰጡ ሁለት የተለያዩ ድምዳሜዎች ቢኖሩም፣ ቋንቋው ጎልው መሆኑን፤ ነገር ግን በሌሎች ቋንቋዎች ተጽዕኖ ሥር መውደቁን የሚገልፀው ሃሳብ ሚዛን እንደሚደፋ ልብ ይሏል። ለዚህም ብሄረሰቡ ሰፍሮባቸው

---

[3] የአርጎባ ብሄረሰብ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ለመሆኑ የተለያዩ አጥኚዎች (Leslau, 1952፤ Weeks, 1984) ያስገነዘቡ ሲሆን፣ አለቃ ታዬም ጉዳዩን አስመልክተው እንዲህ ብለዋል፡- «ወደ ኢትዮጵያ የገቡ እስላሞች አራት ዓይነት ናቸው። መጀመሪያ ሀምርያ ... ሁለተኛ፣ ትገሬ ... ሦስተኛ አርጎቦች ናቸው። አራተኛ...» (የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ፣ 1964:70፣ አጽንኦቱ የእኔ ነው)።

ባሉት አካባቢዎች በቋንቋው የሚገለገሉ ሰዎች (ሕፃናት፣ አረጋውያን - በተለይም ሴቶች) መገኘታቸው[4] ተጨባጭ ማረጋገጫ ነው (Stitz 1973:189፤ ነጋሽ፣ 1981:7)።

ወደዚህ ጥናት የትኩረት አቅጣጫ ስንመጣ፣ ከፍ ሲል ስለቀደምትና የአሁን ጊዜ መገኛው (its location)፣ ስለሥያሜው፣ ስለሃይማኖቱ ስለ ቋንቋውና ስለአኗኗሩ በአጭሩ የተጠቀሰለት የአርጎባ ብሄረሰብ ምን ዓይነት «ቁሳዊ ባህል» እንዳለው ለመፈተሽ አልሞ የተነሳ ነው።

«ቁሳዊ ባህል» የሚለው ቃል የእንግሊዘኛውን "material culture" የተሰኘ ቃል ይተካል ሲሉ ፈቃደ የተገለገሉበት ሲሆን (1991:15)፤ ከፎክሎር የጥናት ዘርፎች (genres of folklore) አንዱ እንደሆነ ምሁራን ይጠቅሳሉ (Dorson ውስተ ፈቃደ፣ 1991:15፤ Bartis, 2002:4)። ምንነቱንም አስመልክተው ምሁራኑ ተመሣሣይ ብያኔ ያቀረቡ ሲሆን ለአብነት ፈቃደ የሚከተለውን ገለፃ በመፅሃፋቸው አስፍረዋል።

> *'ቁሳዊ ባህል' በዓይን የሚታየውን፣ በእጅ የሚዳሰሰውን፣ ከዘመናዊ ኢንዱስትሪ በፊት ጀምሮ የሰው ልጅ የተገለገለባቸውን ቁሳቁሶች፣ እነዚህ ቁሳቁሶች የተሰሩበትን ዘዴ ወይም ቴክኒክ፤ የልዩ ልዩ ምግቦችን አሠራር፣ የቅመም አቀማመም ብልሃትን፤ የልብስ፣ ቤት፣ የአጥር ወዘተ. አሠራርን፤ ሰዎች ልዩ ልዩ ሥራዎችን የሚያከናውኑባቸውን መሣሪያዎችንና ሌሎች ተመሣሣይ ጉዳዮችን ያጠናል (1991:15)።*

ከፍ ሲል ከቀረበው ጥቅስ፣ «ቁሳዊ ባህል»፣ መንፈሳዊውን ወይም ሃሳባዊውን ሳይሆን ቁሳዊውን ወይም ሊታይ፣ ሊዳሰስና ሊጨበጥ የሚችለውን[5]፤ አንድም ኢንዱስትሪ ሰራሽ ወይም ዘመን አመጣሽን ሳይሆን የእጅ ሥራ ውጤት የሆነውንና ባህላዊውን ጉዳይ[6]፤ መሠረት አድርጎ «ቁሶች፣ ከምንና እንደምን ባለ ብልሃት ወይም ጥበብ ይሠራሉ?» ሲል የሚጠይቅና የሚመረምር የጥናት መስክ እንደሆነ መረዳት ይቻላል። ከመረዳትም አልፎ ደግሞ ወደ ተግባሩ በመሸጋገር ጥናቱን የአካባቢ ወይም የአገር ዓውድ አስይዞ ለመሥራት መነሳሳት በቀዳሚነት የባለጉዳዩ «የፎክሎረኛው»[7] ተልዕኮ ነውና እኔም ይህንን ዓላማ ይገፍ የአርጎባ

---

[4] ይህንን ጉዳይ እኔም ብሆን በነሐሴ /1998 ዓ.ም ባደረግሁት ቅኝት አረጋግጫለሁ። ቅኝቱም፣ የአርጎባ ልዩ ወረዳ ጊዜያዊ መቀመጫ በሆነው በሀርቡ ወረዳና በአካባቢው ባሉ ቀበሌዎች የተማከለ ነበር።

[5] Glassie ምንም እንኳ Material Culture በሚል ርዕስ መጽሀፍ ቢያዘጋጅም፣ ቃሉ ወይም ስያሜው ግን ግራ የሚያጋባ መሆኑን "It is an odd term, material culture" (1999:41) ሲል ገልጿል። ምክንያቱም፣ የባህል ጽንሰ ሃሳብ በተፈጥሮ፣ በአዕምሮ ያለ ውቅርን (pattern in mind)፣ ውስጣዊና ሊታይ የማይችልን (inward and invisible)፣ እንዲሁም ተቀያያሪ (shifting) እንጂ በአንድ ቅርጽ የማይፀናን ነገር አመላካች መሆኑ ነው። እናም የባህልን ቁሳዊነት የተጠራጠረ ይመስላል።

[6] ጉዳዮቹም፣ ሀገረሰባዊ ዕደጥበብ፣ ሀገረሰባዊ ምህንድስና፣ ሀገረሰባዊ ልማድ፣ ሀገረሰባዊ ሥዕልና ሀገረሰባዊ ምግብ ናቸው (Dorson ውስተ ፈቃደ፣ 1991:15)

[7] ቃሉን በተደጋጋሚ ጊዜ የሚጠቀሙበት ፈቃደ አዘዘ (ዶ/ር) ሲሆኑ ፎክሎሪስት (Folklorist) የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል ይተካል፣ የፎክሎር አዋቂ ለማለት።

ብሄረሰብ ካሉት ቁሳዊ ባህሎች መካከል ናሙና የቤት ውስጥ መገልገያና የማጌጫ ቁሶችን ተተኳሪ በማድረግ ጥናቱን አስኪጀዋለሁ።

ጥናቱን ለማድረግ ስነሳም፣ እኔ ከመረጥኩት ብሄረሰብና ርዕሰ ጉዳይ ጋር በቀጥታ የሚዛመድ ቀዳሚ ሥራ ባያጋጥመኝም በተዘዋዋሪ መልኩ የሚዛመዱ ጥቂት ጥናቶችን ተመልክቻለሁ። የመረጥኳቸውንም በምዕራፍ ሁለት (2፡1ን ይመለከቷል) «የተዛመጅ ጥናቶች ቅኝት» ስር ከልሻቸዋለው።

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

«... ባይገርምህ እንደዚህ ያለ ባህል' ኮ አርጎባዎችም አላቸው!»
(ንጉሡ አቦሰጥ[8]፣ ታህሳስ 26 /1998)

ከላይ የተጠቀሰውን የጓደኛዬን የአቶ ንጉሡ አቦሰጥ ንግግር ያስቀደምኩበት አንድ ዐቢይ ምክንያት አለኝ። ይኸውም፣ አሁን ላጥናው ብዬ ያቀድኩትን የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ ርዕስ በአዕምሮዬ ቀርጬ እንድይዝ የገፋፋኝ ጥቆማ መሆኑ ነው።

ነገሩ እንዲህ ነው። ታኅሳስ 26/1998 ዓ.ም ረቡዕ ዕለት የEtLi 621 (Folklore) የትምህርት ክፍለ ጊዜ ተከታትዬ ወደ ምሣ በምሄድበት ጊዜ ከአቶ ንጉሡ አቦሰጥ ጋር መንገድ ላይ እንገናኛለን። ሠላምታ ከተለዋወጥን በኋላ የ«ትምህርት እንዴት ነው?» ጥያቄን ያቀርብልኛል። እኔም፣ በተለይ በዕለቱ ትምህርት መደሰቴን እነግረዋለሁ። ስለምን ጉዳይ እንደተማርኩ ይጠይቀኛል። ወደ ዝርዝሩ ከመግባቴ በፊት ቦርሳዬ ውስጥ የያዝኩትን «ኮፒ» የተደረገ ጥናታዊ ጽሑፍ አሳየሁት። "The Sauna: An Expression of Finnish-American Identity" (Yvonne R. Lockwood) ይላል ርዕሱ። ማብራሪያዬንም ቀጠልኩና ስለምንነቱ አጠር አድርጌ ነገርኩት። በጨዋ ደንብ ካዳመጠኝ በኋላ *«... ባይገርምህ እንዲዚህ ያለ ባህል' ኮ አርጎባዎችም አላቸው!»* አለኝ። ከዚያም፣ ወደ ውጭ ትቼ ወደ ውስጥ መመልከት ጀመርክ፤ ፊኒሽ አሜሪካዎችን ሳይሆን የሃገሬን አርጎባዎች አሰብክ፤ የዕለቱን ትምህርቴን በሃገሬ አውድ ለመመልከት፤ አንድም ለቀጣይ ጥናት በማቀድ። እናም፣ ስለአርጎባዎች ማንነት ይበልጥ ለማወቅ ወሰንክ። ስለእነሱም የተሣሉ ጥናቶችንና ሌሎች ጽሁፎችን ማንበቡን ተያያዝኩት። ብዙም ባይባልም፣ በሰሜን ሸዋ የሚገኙትን አርጎባዎች (በተለይ) ተተኳሪ ያደረጉ የሥነ ልሣን፣ የታሪክና የሥነ ሰብ ጥናቶች በቀደምት ተመራማሪዎች ተዘጋጅተዋል። በጽሑፎቹ ከተካተቱት ይዘቶች መካከል ደግሞ የብሄረሰቡን ቋንቋ በተመለከተ የቀረቡት ነጥቦች የአንባቢን ትኩረት የመያዝ ብቃት አላቸው።

ከአጥኚዎቹ መካከል ከፊሎቹ የቋንቋውን ጎልው መሆን አምነው በሌሎች ቋንቋዎች ተዕዕኖ ስር መውደቁን አያይዘው ገልጸዋል። ሌሎቹ ደግሞ በቋንቋው ጎልውና ጥርጣሬ

[8] አቶ ንጉሡ አቦሰጥ ከዲላ ዩኒቨርሲቲ በታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪውን በአሁኑ ጊዜ ደግሞ በኢ.ኢ.ዩ. በስነ-ሰብ ጥናት የሁለተኛ ድግሪውን ተቀብሎ በአንድ መንግስታዊ ባልሆነ ድርጅት ውስጥ እየሰራ ይገኛል።

አድሮባቸዋል። ቋንቋቸው በሌላ ቋንቋ ተውጦ ወይም «ጠፍቶ» ከሆነ ደግሞ የብሄረሰቡ አባላት የሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎች እየሆኑ ነው ወይም «ሆነዋል» ሊያስብል ይችላል። ይህ ሁኔታ ደግሞ «ባህላቸውስ?» የሚል መሠረታዊ ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል።

ጥያቄውን በአዕምሯችን እንደያዝን፣ በ1998 ዓ.ም. ሁለተኛ መንፈቀ ዓመት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት፣ በአዋጅ ቁጥር 130/1998 የተላለፈውን ውሳኔ ስንመለከት፣ የአርጎባ ብሄረሰብ ራሱን ችሎ በልዩ ወረዳነት እንዲዋቀርና የራሱን የአስተዳደር ሥልት እንዲከተል ታውጇል[9]።

አዋጁ፣ ከፍ ሲል ያነሳነውን ጥያቄ፣ አንድም ጥርጣሬ፣ በጥልቀት እንድንመረምር ብሎም እንድናረጋግጥ የሚጋብዝ ነው[10]። ምክንያቱም፣ እስከ 1998 ዓ.ም. ሁለተኛ አጋማሽ ድረስ ብሄረሰቡ በራሱ ሳይሆን በሌሎች የአስተዳደር ጥላ ሥር ተጠልሎ ለመቆየቱ አስረጂ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የራሱ የሆኑ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ ተፅዕኖዎች እንደነበሩት አጠያያቂ አይሆንም[11]። እናም፣ ሌሎቹን ጉዳዮች ለሌሎች ትቼ፣ ቁስ-ተኮር የሆነ ባህላቸውንና የማንነት መገለጫቸውን ለማየት ወዲያውም ዓላማዎቼን ከግብ ለማድረስ ተነሳሳሁ። እዚህ ላይ ግን፣ «ከአርጎባዎች ሁለመና ቁሳዊ ባህላቸውን ለማጥናት ለምን ወሰንክ?» የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። አምስት መሠረታዊ ምክንያቶችን በመጥቀስ ለማብራራት እወዳለሁ።

የመጀመሪያው፣ «ቁሳዊ ባህል» ከሌሎች የፎክሎር ዘርፎች (አንባራዊ በሆነ መልኩ) ሳይቀየር የመቆየት አቅም ስላለው ነው (Bronner, 1986: 202)። «ለምን?» ቢባል፣ ቁሶች፣ ባለሦስት ጎን ቅርፅ ያላቸው ነገሮች ናቸው። እነዚህን ነገሮች ለመቀየር ደግሞ፣ ባለሙያው ቁሶቹ ይዘውት የነበውን ቅርፅ መሉ በመሉ በመቀየር አዲስ ቅርጽ የማስያዝ ወይም በነበረው ላይ አንዳች ማስተካከያ ወስዶ አዲስነትን የማላበስ ችሎታው ይኖረው ዘንድ የግድ ነው። ይህ ደግሞ አስቻጋሪ ከመሆኑ የተነሳ ብዙ ጊዜ ቁሶች የያዙትን ቅርጽ ይዘው ለረኽርም ጊዜ ይቆያሉ። በአንጻሩ ቃላዊውን የፎክሎር ዘርፍ ብንመለከት፣ በከፍተኛ ሁኔታ የመለወጥ አባዜ የተጠናወተው ሆኖ እናገኘዋለን። እንደቁሶቹ ሁሉ ለመለወጥ የባለሙያውን (የተራኪውን - ለቃላዊው) ችሎታ አይጠይቅም፤ መርሳትም ለመለወጥ ምክንያት ነው። እናም፣ የአርጎባን ብሔረሰብ ቁሳዊ ባህል መርጬ ማጥናቴ፣ ብሄረሰቡ ከሌሎች ብሄረሰቦች ጋር ተቀላቅሎ የሚኖር ቢሆንም እንኳ ፣ ቁሶቹ ሳይቀየሩ የመቆየት ባህሪው አላቸውና ስጋቴን ሊቀንሱልኝ ይችላሉ ብዬ አምናለሁ።

ሁለተኛው፣ ቁሳዊ ባህል በዓይን የሚታይና በእጅም የሚዳሰስ በመሆኑ ስለባለቤት ብሄረሰቡ (ቁሱን የሚሰሩትን እና/ ወይም ቁሱን ገዝተው የሚጠቀሙትን ጨምሮ) ማንነት፣

---

[9] መረጃውን የሰማሁት ከኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የዜና ሥርጭት ሲሆን፣ በኋላ ግን በክልል ምክር ቤቱ የወጣውን አዋጅ በማየት የአዋጅ ቁጥሩን ለማጣቀስ ችያለሁ።

[10] ይህ ሁኔታ የእኔን ጥናት ወቅታዊና መታሰብ ባለበት ጊዜ የታቀደ ያደርገዋል ብዬ አምናለሁ።

[11] በቅኝቴ ወቅት ይህንን ድምጸት ያዘለ የተወላጆችን ንግግር መስማቴ እርግጠኛ ሆኜ እንድናገር አስችሎኛል።

እምነት (belief) እና ርዕዮት (view) ለማጥናት ተጨባጭና አስተማማኝ መረጃን ስለሚያስገኝ የሚለው ነው (Dunkan, 1981 ውስተ Internet)።

ሦስተኛው ምክንያቴ፣ የሰው ልጅ ሆነ ብሎ ቁሶችን ከራሱ ባህርይ ጋር ለማመሳሰል የሚያደርገው ጥረት ነው (Bronner, 1986:204)። ለአብነት፣ ወንበርን፣ ጠረጴዛንና አልጋን ብንመለከት እግር እንዳላቸው ተደርገው ነው የሚገለጹት። ከዚህም ባሻገር እንስራ - ጆሮ፣ ብርሌም - አንገት፣ መርፌ ደግሞ ዓይን እንዳላት ተደርጎ ይቆጠራል። እንግዲህ ይህ በአሰያየም (በአጠራር) የሚፈጠረው ምስስሎሽ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ልዩነቱ ለጥናት አመቺ እንደሆነ ልብ ይሏል፤ ለአብነት «ሰዎች ምስስሎሹን መፍጠራቸው ለምን አስፈለገ?» ብሎ መጠየቁ አንዱ መንገድ ነው።

አራተኛው ምክንያቴ፣ (ወደመጥፎው ጥግ ሄደን እናስብና) በአጋጣሚ በመስክ ቆይታዬ መረጃ አቀባይ ባላገኝ እንኳ ቁሶቹን ተመልክቼ፣ ዳስሼና ይገር ቢያንስ የግል ግንዛቤዬን በማስታወሻዬ ላይ ማስፈር እችላለሁ ብዬ አምናለሁ። ለምሳሌ፣(የፎክሎር ዕውቀቴን መሠረት በማድረግ) ለቁሶቹ ቅርፅና መጠን እንዲሁም መሠሪያ ጥሬ ነገርና አገልግሎት ትኩረት ሰጥቼ በማየት፣ በመለካትና በመገመት ነጥቦችን እይዛለሁ። ከዚህ ላይ የአርኪዮሎጂ ተመራማሪዎችን የአሰራር ሂደት ማስታወሱ ሳይበጅ አይቀርም፤ ቅሪተ አካሎችን ተመልክተው ወይም አጢነው ስለባለቤት ማህበረሰቡ አንዳች መላምት ይሰነዝራሉና። በእርግጥ ይህ ስልት ብቻውን የተሟላ መረጃን ያስገኛል የሚል እምነት የለኝም። ችግር ብልሃትን ይፈጥራል ብዬ እንጂ። አንድም፣ ቁሶች በራሳቸው መልዕክትን መሸከም መቻላቸውን ለመጠቆም፤ «ቁሶች እንደ ቋንቋ ሁሉ ተግባቦትን ይፈጥራሉና» (Musello, 1992:38)።

ለጥናቴ ሰበብ የሆነኝ አምስተኛው ምክንያት Silverman የሰነዘረው ትዝብት አዘል ቃል ነው። ይህ ምሁር ኢትዮጵያ የአፍሪካ፣ የመካከለኛው ምስራቅና የሜዲተራንያን አካባቢ ሰዎች ወዲያውም ባህል መፍለቂያና መናኸሪያ እንዲሁም የበርካታ ብሄረሰቦችን ልዩ ልዩ ባህሎች አዋህዳ የያዘች አገር ብትሆንም፣ የቁሳዊ ባህል ምርምርን በተመለከተ እስካሁን በአጥኚዎች መነጽር ዕይታ ውስጥ የገቡት (በአንጻራዊ መልኩ) በየአብያተ ክርስቲያናቱ የሚገኙት የስዕል ጥበቦች ብቻ ናቸው ሲል ገልጿል (1995:5)። እናም «ጋን በጠጠር ይደገፋል» እንዲሉ ይህች ጥናት ከትዝብት ባታድንም ከምንም ትሻላላች በማለት ለሥራው የአቅሜን ታጥቄ ተነስቻለሁ። ከዚሁ ጋር ተያይዞ፣ Weeks የአርጎባን ብሄረሰብ ባህል አስመልክቶ « ...no ethnography of the group has ever been carried out »(1984:49) ሲል አስምሮ ያለፈበት ጥቆማ ሌላው አነሳሽ ነጥብ እንደሆነ ለመግለጽ እወዳለሁ።

1.3. የጥናቱ ዓላማ

ይህ ጥናት፣ የአርጎባን ብሄረሰብ ማንነት፣ ከቁሳዊ ባህሎቻቸው አንጻር ለማጥናት ወዲያውም መረጃዎችን በጽሁፍ ከትቦ ለማስቀመጥ አልሞ የተነሳ ነው። ከብሄረሰቡ ቁሳዊ ባህሎችም፣

ናሙና የቤት ውስጥ መገልገያና የማጌጫ ቁሶች የጥናቱ ዋነኛ ተተኳሪዎች ሲሆኑ፤ እነዚህ ቁሶችም ከቁስነታቸው አንድም ከባህላዊ ገጽታነታቸው አንፃር[12] ይጠናሉ። ከዚህም አንፃር፤

- አርጎባዎች ምን ምን የቤት ውስጥ መገልገያና የማጌጫ ቁሶች እንዳሏቸው መለየት፤
- የተመረጡ ናሙና ቁሶች፣ በማን፣ ከምንና እንዴት እንደሚሠሩ፤ መቼ፣ ለምንና እንዴት አገልግሎት ላይ እንደሚውሉ፤ ምን ዓይነት ቅርጽ ለምን ምክንያት እንደተቀረፀባቸው ማሳየት፤ በዚህም መነሻነት፣
  - የብሄረሰቡን የፈጠራ ችሎታ ማመላከት፤
  - በብሄረሰቡና በቁሶቹ መካከል ያለን ግንኙነት ማሳየት[13] የሚሉት ነጥቦች በዝርዝር ዓላማነት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ

የቁሳዊ ባህል ጥናት ተልዕኮ ናቸው ሲል Bruce (1987) የጠቀሳቸው ሦስቱ ነጥቦች፣ በዚህ ጥናት ውስጥ ተተግብረው ሥራው የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ይሰጣል ተብሎ ይታመናል፤ (ጠቀሜታዎቹ ከተልዕኮዎቹ እንደተጠለፉ ልብ ይሏል)።

እነዚህም፦

- ተተኳሪ ብሄረሰቡ፣ ምን ምን ቁሶችን ሰርቷል? ምንንስ ሊሰራ ይችላል? የሚለውን ያሳያል።
- ብሄረሰቡ የቁሶቹ ባለቤት (ሰርቶ ወይም ሸምቶ) በመሆኑ ምክንያት ምን የተለየ ባህርይ (ባህል) እንደተላበሰ ያመላክታል።
- ሁኔታዎች ሲፈቅዱም፣ የተተኳሪ ብሄረሰቡን (በተለይም የእጅ ባለሙያዎችን) ኑሮ የተሻለ ለማድረግ ሃሳቦችን ይሠነዝራል። ለአብነት፣ የማስተዋወቅ ስራን በመስራት ጎብኝዎች ብሄረሰቡ ወደሚገኝበት ቦታ እንዲሄዱና ባህሉን እንዲመለከቱ ይጠቁማል፤ ቁሶቹን የሚሰሯቸው ባለሙያዎች በቡድን ተደራጅተው የተሻለ የማምረት አቅም እንዲኖራቸው፣ ምርቶቻቸውን ለሽያጭ ያቀርቡ ዘንድም ገበያዎች እንዲመሠረቱ ሃሳቦችን በተገኘው አጋጣሚ ይሠነዝራል።

---

[12] ቁሶቹን ከቁስነታቸውና ከባህላዊ ገጽታነታቸው አንጻር እመለከታለሁ ስል Schlereth "Object centered" እና "Object driven" በማለት የመጀመሪያው አንጻር (approach) የቁሱን አሠራር /ተፈጥሮ፤ ሁለተኛው ደግሞ ከዚሁ በስተጀርባ ማህበረሰቡ ለቁሱ የሚሰጠውን ዋጋ (values and meanings) እንደሚመለከት የገለጸውን መነሻ አድርጌ ነው።

[13] ጉዳዩን ለማጤን፣ ብሄረሰቡ ለቁሶቹ የሚሰጣቸውን መጠሪያ ስያሜና ዋጋ (value) መነሻ በማድረግ፣ በቁሶቹ አማካይነት ራሳቸውን፣ አካባቢያቸውንና ዓለምን እንዴት እንደሚመለከቱ (the societies own self, environmental, and worldview through the objects) ለመመርመር እሞክራለሁ።

ከዚህም ባሻገር፣ ይህ ጥናት፣ ለተለያዩ አጥኚዎች መረጃን የማቅረብ ጥቅም ይኖረዋል ተብሎ ይታመናል። ለአብነት፣

- ለቤተመዘክር አጥኚዎች በስብስቦቻቸው ውስጥ ሊያካትቷቸው የሚገቡ አዳዲስ ቁሶችን ይጠቁማል።
- ለሥነ ትምህርት አጥኚዎች፣ በመማሪያ መጻሕፍት ዝግጅት ወቅት ቁሳዊ ባህል ነክ የሆኑ ይዘቶችን (ስለቁሶች ምንነት፣ አሠራርና አገልግሎት ወዘተ) በማቅረቡ ረገድ አጋዥ ይሆናል።
- ለአርኪዎሎጅስቶች ደግሞ፣ የዚህ ጥናት ተተኳሪ ብሄረሰብ ከመገልገያ ቁሶቹ ጋር ያለውን ግንኙነት በማሳየቱ ረገድ ፍንጭ ይሰጣል ተብሎ ይታመናል።

1.5. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ከቦታና ከርዕስ ጉዳይ አንጻር ወሰኑ የተገደበ ነው። ከቦታ አንጻር፣ (በጥናቱ ዳራ እንደተመለከተው) የአርጎባ ብሄረሰብ በተለያዩ ታሪካዊና ማኅበራዊ አጋጣሚዎች የተነሳ በአንድነት መኖር አልቻለም። በመሆኑም፣ በአራት ዓበይት ሥፍራዎች መቀመጥ የግድ ሆኖበታል። በአማራ፣ በሐረር፣ በኦሮሚያና በአፋር ክልሎች። ታዲያ፣ ምንም እንኳ በአራቱም አካባቢዎች የአርጎባ ብሄረሰብ አባላትን ብናገኝም፣ ጥናቱንም ማስኬድ ብንችልም፣ ይህ ጥናት ግን በአማራ ክልል የአርጎባ ብሄረሰብ ከሚገኝባቸው ሦስት ዞኖች[14] የደቡብ ወሎዎችን አርጎባዎች (አርጎባ ልዩ ወረዳ) በሁለት መሠረታዊ ምክንያቶች በተተኳሪነት መርጧል። የመጀመሪያው ምክንያቱ፣ የአርጎባዎችን ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ የመስፈር ሁኔታን ወይም እንቅስቃሴን አጥኚዎች (Stitz, 1973:191 እ Weeks, 1984:50) እንዳመለከቱት አንድም በመስክ ቆይታዬ ታሪክ አዋቂዎች እንዳረጋገጡልኝ (3.2.1ን ይመለከቷል) ከሰሜን ወደ ደቡብ ዓይነት አቅጣጫን የተከተለ የሚመስል ነውና ምናልባትም ቀደምት ሠፋሪዎቹ በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል የሚገኙት ሳይሆኑ አይቀርም ከሚል መላምት የተነሳ፣ ቅድሚያ ለቀደምቶቹ ትኩረት ልስጥ የሚለው ሃሳብ ሲሆን እ ሁለተኛው ምክንያቴ፣ በ1998 ዓ.ም ክረምት ወቅት ያሰብኩትን የጥናት ርዕስ ይገፍ መቀጠል መቻል/አለመቻሌን ለማረጋገጥእ ወዲያውም ስለብሄረሰቡ ከራሱ ከብሄረሰቡ መነሻ ዕውቀትን ለማግኘት ቅኝት ማድረግን ሳቅድ አመቺ ሆኖኝ ያገኘሁት የደቡብ ወሎውን የአርጎባዎች አሰፋፈር በመሆኑ ነው።

ከርዕሰ ጉዳይ አንጻር፣ ምንም እንኳ ጥናቱ የቁሳዊ ባህል ጥናት ቢሆንም፣ በቁሳዊ ባህል ጥናት ሥር ደግሞ እንደ ሀገረሰቡዊ የእጅ ስራ፣ ሀገረሰባዊ ምህንድስና፣ ሃገረሰባዊ ሥዕል፣ ሀገረሰባዊ ልማድና ሃገረሰባዊ ምግብ የመሳሰሉት ጉዳዮች ሊፈተሹ ቢችሉም (Dorson ውስተ ፈቃደ፣ 1991:15፣ Bartis, 2002:4) ይህ ጥናት ግን በሃገረሰባዊ የእጅ ስራና

[14] በቅኝቴ ወቅት ባደረግሁት ኢ-መደበኛ ቃለ መጠይቅ (ከአቶ ጀማል መሐመድ - የልዩ ወረዳው ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት ም/አስተዳዳሪ ጋር) መሠረት በአማራ ክልል የአርጎባ ብሄረሰብ ሠፍሮባቸው የሚገኙት ሦስቱ ዞኖች ደቡብ ወሎ፣ ሰሜን ሸዋና ኦሮሚያ ልዩ ዞን ናቸው።

ሀገረሰባዊ ልብስ ላይ ትኩረቱን አድርጓል ፤ ለዚያውም፤ የብሄረሰቡን ናሙና የቤት ውስጥ መገልገያና የማጌጫ ቁሶችን ብቻ ታሳቢ ባደረገ መልኩ። «ለምን?» ቢባል (የጥናቱን ትኩረት ማጥበብ የግድና ተገቢ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ) የተመረጡት ቁሶች የባለቤት ብሄረሰቡ የእለት ከዕለት መገልገያ መሳሪያዎች ናቸውና ስለተተኳሪ ብሄረሰቡ ማንነት በቂ መረጃን (አንጻራዊ በሆነ መልኩ) ይሰጣሉ ተብሎ በመታመኑ ነው።

1.6. የመረጃ መሰብሰቢያና መተንተኛ ዘዴዎች

ይህ ክፍል ሁለት ርዕሰ ጉዳዮችን ለማብራራት ተዋቅሯል። እነዚህም የጥናቱ መረጃዎች የተሰበሰቡበትና የተተነተኑበት ዘዴዎች ናቸው።

1.6.1. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ

የዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ዋና ዓላማ የአርጎባ ብሄረሰብ በቤት ውስጥ የሚገለገልባቸውንና የሚያጌጥባቸውን ናሙና ቁሶች ከቁስነታቸውና ከባህል መገለጫነታቸው አንጻር ማጤንና የተገኙትን መረጃዎች መሰነድ እንደሆነ በ1.3 ተገልፏል። ይህንንም ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚከተሉት ዘዴዎች በመረጃ ማሰባሰቢያነታቸው ተመርጠዋል።

1.6.1.1. ቀዳማይ መረጃዎች የተሰበሰቡበት ዘዴ

ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑ ቀዳማይ መረጃዎች በተለያዩ ዘዴዎች በመታገዝ የተሰበሰቡ ሲሆን፤ዘዴዎችንም በመረጃ ማሰባሰቡ ወቅት ከነበራቸው አስተዋፅኦ አንጻር በሁለት ጎራ ከፋፍዬ ለማሳየት እወዳለሁ። የመጀመሪያዎቹ «ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች» ያልኳቸው ሲሆኑ፤እነዚህም የቃል መጠይቅና ምልከታ ናቸው። ሁለተኛዎቹና በአጋዥነት የተገለገልኩባቸው ዘዴዎች ደግሞ የጽሁፍ መጠይቅ፤ የተተኳሪ ቡድን ውይይትና የናሙና ጥናት (Case Study) ናቸው።

1.6.1.1.1. የቃል መጠይቅ

ይህ ክፍል በቃል መጠይቁ የተሳተፉ መረጃ አቀባዮች እንዴት እንደተመረጡና የቃል መጠይቁ እንዴት እንደተተገበረ የሚገልፅ ነው።

እንደ *Jackson* አገላለጽ፤ፎክሎር በሰው ልጆች የእለት ከዕለት ሕይወት ውስጥ ያለውን አስተዋፅኦ ከፍተኛነት አስካልዘነጋን ድረስ ማንኛውንም ሰው በፎክሎር ጉዳዮች ዙሪያ ለማነጋገር በመረጃ አቀባይነት ልናጭ እንችላለን (1987:42)። ይሁን እንጂ አንድ ሰው በፎክሎር ከሚካተቱት ጉዳዮች መካከል በአንደኛው ወይም በተወሰኑት የተለየ የህይወት ተሞክሮ እና/ወይም የላቀ የአገላለጽ ብቃት ባለቤት የሚሆንበት አጋጣሚ ብዙ ነውና አንዱን ከአንዱ በማበላለጥ መምረጡ የግድ ይሆናል።

የዚህ ጥናት አቅራቢም ይህንኑ መርህ በመከተል መረጃ አቀባዮቹን መርጧል። የተመረጡትም መረጃ አቀባዮች፦

- በእጅ መ.ያ ዕውቀት የተካነና በመ.ያው ለረዥም ጊዜ የቆዩ፤
- በአካባቢው ማኅበረሰብ ዘንድ የባህልና የታሪክ ዕውቀታቸው የተመሰከረላቸው፤
- በናሙና ቁሶቹ ተገልጋይ የሆነ፤
- ከናሙና ቁሶቹ ጋር የተለየ ቁርኝት (የሕይወት ገጠመኝ) ያላቸው፤ እንድም፤ በአጋጣሚ የተመረጡ፤ ማለትም፤ መንገድ ላይ ወይም በሌሎች ቦታዎች በተፈጠሩ መስተጋብሮች የተካተቱ መረጃ አቀባዮች አሉ።

ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑት መረጃዎች ከተሰበሰቡበት ዘዴዎች አንዱና ቀዳሚው የቃል መጠይቅ ሲሆን በሁለት መንገድ ተከናውኗል። የመጀመሪያው እኔና ቃል አቀባዮቹ ለመጠይቁ ከመገናኘታችን በፊት ጥያቄዎቹ ቀድመው ተዘጋጅተው የተተገበረው /Structured Interview/ ሲሆን ይህንን መንገድ (በተለይ) የእጅ ባለመ.ያዎችንና ታሪክ አዋቂዎችን ሳነጋግር ተጠቅሜበታለሁ። ከዚህ ባሻገር በድንገት ተፈጥረው የማያቸውና የምሰማቸው ሁኔታዎች ለጥናቴ አስፈላጊ ሆነው ሳገኛቸው ወዲያውኑ ወደ አዕምሮዬ የመጡትን እንዲሁም ከአቀባዮቹ ምላሽ የሚፈልቁልኝን ሌሎች ጥያቄዎች አካትቼ ሁለተኛውን ዓይነት የቃል መጠይቅ /Unstructured Interview/ ከውኛለሁ።

የቃል መጠይቁን በማደርግበት ወቅት (በዋናነት) መቅረጸ ድምጽን (ቴፕ) የተገለገልኩ ሲሆን (10 ካሴቶችን ተጠቅሜያለሁ) ቦታውን በተመለከተ እንደተጠያቂዎቹ ማንነት ሰፊር ውስጥ ባሉ የእደ ጥበብ መሥሪያ ቦታዎች፤ በመኖሪያ ቤት ውስጥ፤ በማምለኪያ ቦታዎች (መስጊዶች) ፤ቁሶቹ በሚሸጡበት ገበያዎች እንዲሁም የማያልፉ አጋጣሚዎች በተፈጠረባቸው ቦታዎች (ለአብነት መንገድ ላይ፤ የቡናና የዕርቅ ሥርዓት ላይ ወ.ዘ.ተ.) ተከናውኗል።

1.6.1.1.2. ምልከታ

ይህ ክፍል አጥኚው በምልከታው የመረጣቸውን ናሙና ቁሶች እንዴት እንደመረጣቸውና ምልከታውን እንዴት እንደተገበረው የሚያሳይ ነው።

ይህ ጥናት የአርጎባን ብሄረሰብ ናሙና የቤት ውስጥ መገልገያና የማጌጫ ቁሶች ጉዳዬ ብሎ እንደሚመለከት በ1.3 ተጠቅሷል። ናሙና ቁሶችም የተመረጡበት ምክንያት ቁሶቹ መ.ሉ በመ.ሉ ወይም በዋናነት ተተኳሪ ብሄረሰቡን ገላጭ ከመሆናቸው አንጻር ነው።

ይህም ሲባል፤ በጥናቱ ሂደት አንድ ቁስ በናሙናነት የተመረጠው፤ ቁሱ በብሄረሰቡ የእጅ ባለመ.ያዎች በመሠራቱ እና /ወይም ብሄረሰቡ ቁሱን (ባይሠሩትም እንኳ) ከሌላው ብሄረሰብ (አጥኚው በመጠኑም ቢሆን ከሚያውቃቸው) በተለየ መልኩ ከተገለገለበት፤ አንድም፤ ቁሱ ብሄረሰቡን በአንዳች መንገድ የመግለጽ ባህርይ ካለው መሆኑን ያስተውሏል። ይህንንም ለማድረግ፤ አጥኚው፤ ከባለቤት ብሄረሰቡና ከቃል አቀባዮቹ (ቁስ ሰሪ የእጅ ባለመ.ያዎች፤ በቁሱ ተገልጋዮች እንዲሁም ባህልና ታሪክ አዋቂ ሰዎች ወ.ዘ.ተ.) አንደበት ካገኛቸውና «እነዚህ ቁሶች የእኛ ባህላዊ ቁሶቻችን ናቸው፤ እነዚህኞቹ ግን ከሌሎች ብሄረሰቦች

ዘንድ ያመጣናቸው ናቸው!» የሚሉ ቀዳማይ መረጃዎችን እርስ በርስ በማናበብ በአጋዥነት ተገልግሏል። ከዚህም ባሻገር አጥኒው በተለያዩ አጋጣሚዎች (በዕድገት፣ በትምህርትና በሥራ ቆይታ) ያገኘውን መጠነኛ የሆነ የብሄረሶች ባህል ዕውቀት (የባህል ተመሳስሎና ልዩነት) በናሙና ቁሶች መረጣ ወቅት ተገልግሏል። ይህንንም ዕውቀት ለመገልገል የወሰነው Jackson የተባለ ምሁር Webb et. al.ን ጠቅሶ ያሰፈረውን ትውር እንደ አንድ አጋዥ ዘዴ በመቁጠር ሲሆን ሃሳቡም የሚከተለው ነው።

> *A fieldworker is 'more likely to report on phenomena which are different from those of his own society or subculture than he is to report on phenomena common to both (Jackson, 1987:60).*

ምሁሩ የተጠቀሰውን ትውር በጽሁፉ ያቀረበው፣ አንድ የባህል አጥኚ በመስክ ቆይታው ምልከታን እንደዘዴ ተገልግሎ መረጃዎቹን በሚሰበስብበት ጊዜ የእርሱን ናሙናዎች ለመምረጥ ሊገለገልበት እንደሚችል ለመጠቆም ነው። እኔም ይህንኑ ሀሳብ ከመጋራት አልፌ በተግባር ተገልግዬበታለሁ።

ምልከታ፣ ሁለተኛው የመረጃ መሰብሰቢያ መንገድ ከመሆኑ ባሻገር በቃል መጠይቁ ላገኘኋቸው (ቃላዊ) መረጃዎች ማረጋገጫነትም ተገልግዬበታለሁ። ይህ ዘዴ በፎቶ ግራፍ (17 የታተመ ምስሎችና 4 ሲዲ ያልታተመ ፊልሞች)፣ በቪዲዮ (4 ቪሲዲ ካሴቶች) እና በጽሑፍ (ማስታወሻ በመያዝ) የታገዘ ሲሆን ፣ናሙና ቁሶቹ በሚሰሩበት ቦታ የአሰራር ሂደቱንና ጥበቡን ለማጤን ፣ እንዲሁም በገበያ ላይ ደግሞ የሚሸጡበትን ዋጋ ለማወቅና በሻጮቹና በገዥዎቹ መካከል የሚፈጠረውን መስተጋብር ለማጤን ተግባራዊ ሆኗል።

1.6.1.1.3. የጽሑፍ መጠይቅ

የጽሁፍ መጠይቁ የተዘጋጀበት ዋነኛ ዓላማ በልዩ ወረዳው በኃላፊነት የተቀመጡ ባለሙያዎች ስለብሔረሰቡ ቁሳዊ ባህል ያላቸውን ዕውቀት ለመፈተሽ፣ ለእጅ ሙያና ባለሙያዎች ያላቸውን አመለካከት ለመገንዘብ ነበር። ይህንንም ማድረጌ ቁሶችን ለመጠበቅም ሆነ የእጅ ባለሙያዎቹን ኑሮ ለማሻሻል በመንግስት ደረጃ ባለፉት ጊዜያት ምን እንደተደረገ፣ በአሁኑ ጊዜ ምን ዓይነት እንቅስቃሴ እንዳለና ወደፊት ምን ለማድረግ እንደታቀደ ለማወቅ ችያለሁ። መረጃዎቹንም የ«ይሁንታ» ሃሳቦችን ለማዘጋጀት ተገልግየባቸዋለሁ።

የጽሑፍ መጠይቁ «17» ጥያቄዎችን አካቷል። ከእነዚህም ውስጥ 4ቱ «ዝግ» (closed-ended) ጥያቄዎች ሲሆኑ 13ቱ «ክፍት» (open - ended) ጥያቄዎች ናቸው ።

1.6.1.1.4. የተተኳሪ ቡድን ውይይት

ይህ ዘዴ፣ጉዳዩ የሚመለከታቸውንና ከሁለት በላይ የሆኑ መረጃ አቀባዮችን በአንድ ላይ አድርጌ ያወያየሁትን ይመለከታል። በውይይቱ የተሳተፉት የሽመና ሰራተኞች (በቁጥር 4)፣ የሸክላ ሰሪዎች (በቁጥር 4) እና ጌጣጌጥ አንጥረኞች (በቁጥር 4) (በተናጠል) ሲሆኑ፣ ውይይቱም (በተለይ) በጋራ የመስራትንና ችግር የመቅረፍን ባህል እንዲያዳብሩ፣ የተሻለ

ገበያን እንዲያገኙ፣ ባህላቸውን አዕንተው እንዲይዙ ወዘተ. ግንዛቤን ሊያጭሩ የሚችሉ ነጥቦችን በርዕስነት ያካተተ ነበር። የቡድን ውይይቱ ከፍ ሲል ከተጠቀሱት የእጅ ባለሙያዎች ባሻገር በተጠኝው አካባቢ ታሪክ ያውቃሉ የተባሉ የሀገር ሽማግሌዎችንም ተተኳሪ አድርጓል። ይህንንም ያደረገው ስለ ብሔረሰቡ ጥንተ አመጣጥና አሰፋፈር መረጃዎችን ለማግኘት ነው።

1.6.1.1.5. ናሙና ጥናት (Case Study)

ይህንን ጥናታዊ ጽሁፍ በመረጃ ለማበልጸግ ናሙና ጥናቶች (case studies) በአጋዥነት ተካትተዋል። ለናሙና ጥናቱ የተመረጡት ሰዎች የእጅ ባለሙያዎች ሲሆኑ ሙያውን ከማን እንደተማሩት፣ እንዴት እንደተማሩት፣ በሙያው ምን ያህል ተጠቃሚ እንደሆኑ፣ ለምን ያህል ጊዜ በሙያው እንደቆዩ፣ በቆይታቸውም ምን ችግር እንደገጠማቸውና ምን ዓይነት መፍትሄ እንደወሰዱ ለማወቅ በአጥኚው ለተሰነዘሩ ጥያቄዎች የተሰጡትን ምላሾች አካትቷል።

ናሙና ጥናቱ፣ ከእጅ ባለሙያዎች ባሻገር ከተጠኚ ናሙና ቁሶቹ ጋር በተያያዘ የተለየ ተሞክሮ ያላቸውንና *ተሞክሮዎቻቸውንም ለመተረክ ፈቃደኛ የሆኑትን* ሌሎች ሰዎች ለማካተት ጥረት አድርጓል።

1.6.1.2. ካልኣይ መረጃዎች የተሰበሰቡበት ዘዴ

ለዚህ ጥናት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ጠቃሚ የሆኑ ካልኣይ መረጃዎች ከተለያዩ ምንጮች የተሰበሰቡ ሲሆን ዘዴውም የንባብና ማስታወሻ የመያዝ ዘዴ ነው። ከይዘት ረገድ መረጃዎችን በሁለት መክፈል ይቻላል። ትውሮችና ብሄረሰቡን የሚመለከቱ የተለያዩ ጥሬ መረጃዎች በማለት። ምንጫቸውን በተመለከተ፣ የታተመ መጻህፍት፣ ያልታተመ ጥናታዊ ጽሁፎች፣ ዓለም አቀፋዊ የመረጃ መረቦችና መንግስታዊ አዋጆች ይገኙበታል።

1.6.2. የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

በ3.1 በዝርዝር ለመግለፅ እንደተሞከረው ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑ ቀዳማይም ሆኑ ካልኣይ መረጃዎች በተለያዩ ዘዴዎች ተሰብስበዋል። እነዚህም መረጃዎች የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ባነጣጠረ መልኩ የተተነተኑ ሲሆን ትንተናውም በሚከተለው መንገድ እንደተከወነ ልብ ይሏል።

በትንተናው ሂደት በመጀመሪያ ያደረግኩት ነገር ቢኖር የመስኩ ምሁራን እንደሚመክሩት (2.2.3ን ይመለከቷል) ናሙና ቁሶችን በምድብ በምድብ ማስቀመጥ ነበር። ከዚህም አንፃር የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶችን ከተሰሩበት ጥሬ ቁስ መስፈርትነት (ከሸክላ፣ ከቆዳ፣ ከእንጨት፣ ወዘተ. የተሰሩ በሚል) የማጌጫ ቁሶችን ደግሞ ለጌጥነት ከሚውሉበት የሰውነት ክፍል አንፃር (የአንገት፣ የእጅ ፣የእግር፣ ወዘተ ጌጦች በማለት) ከፋፍያቸዋለሁ። እንደዚህም እንድከፋፍል ያስቻለኝ Bedaux (2000: 110) እንደመከረው የብሄረሰቡ አባላት ለቁሶቹ (በተለይም ለጌጦቹ) የሚሰጡትን ምደባ መነሻ አድርጌ ነው።

የመመደቡን ስራ ከከወንኩ በኋላ በምዕራፍ ሁለት የተነሱትን ትውሮች በተለይም የSchlerethን ዘጠኝ ሞዴሎች (2.2.5ን ይመለከቷል) በአዕምሮ በመያዝ ናሙና ቁሶችን ለመተንተን ሞክሬያለሁ። ትንተናውም ከአንድ በላይ ሞዴሎችን (መረጃዬ እስከፈቀደልኝ) መሰረት ያደረገ ሲሆን Prown ባቀነቀነው ሶስት የመተንተኛ ሂደቶች (2.2.6ን ይመለከቷል) ለማለፍ ጥረት አድርጌያለሁ።

1.7. የመስክ ተሞክሮ

ለጥናት ይዥው የተነሳሁት ርዕሰ ጉዳይ በባህርይው የመስክ ሥራ ላይ የተመረኮዘ በመሆኑ ወደ ተጠኚ ብሄረሰቡ በተደጋጋሚ ጊዜ (በቁጥር ሦስት ጊዜ) በመሄድና የተለያዩ ዘዴዎችን በመገልገል አስፈላጊ መረጃዎችን አሰባስቤያለሁ። ከዚያ በፊት ግን ሁለት ዐበይት ተግባራትን ከውኛለሁ።

የመጀመሪያው፣ ስለአካባቢው እና/ወይም ስለተጠኚ ብሄረሰቡ ዕውቀት ያላቸውን ሰዎች አፈላልጎ ተሞክሯቸውን እንዲያካፍሉኝ መጠየቅ ነበር። ለዚህም፣ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ዶ/ር መሐመድ ኃቢብን፣ ከቅርስ ጥናትና ጥበቃ ቢሮ ዶ/ር ዮናስ በየነንና አቶ ተሰፋዬ ኃይሉን እንዲሁም ከግለሰቦች ጀርመናዊውን የቋንቋ (ሥነ ልሳን) አጥኚ Mr. Andreas Wetterን በአካል እና/ወይም በe-mail በማግኘት በተለይም ስለተጠኚ ብሄረሰቡ ማንነት መጠነኛ ግንዛቤን ጨብጫለሁ።

ሁለተኛው ሥራ፣ ለቅድመ ዝግጅት የከወንኩት የቅኝት ሥራ ሲሆን ቅኝቱ ከነሐሴ 23/1998 እስከ ጳጉሜ 4/1998 ዓ.ም. ድረስ ተከናውኗል። በዚሁ ቆይታዬም «የበጋ መሻገሪያህን በክረምት ተመልከት» እንዲሉ የወደፊቱን ሥራዬን የተቃና ለማድረግ ከልዩ ወረዳውና በሥሩ ከሚገኙት ሰባት ቀበሌዎች የባህልና ማስታወቂያ ቢሮ ሠራተኞች ጋር በሰፊው ተዋውቄያለሁ፤ ዓላማዬንም አብራርቼ ገልጫለሁ። ከዚህም ባሻገር ለእኔ ጥናት አስፈላጊ መረጃን ሊሰጠኝ የሚችሉ ባህልና ታሪክ አዋቂ የመረጃ አቀባዮችን ስምና የመኖሪያ አድራሻ ዝርዝር በማስታዎሻዬ ይዣለሁ። እንዲሁም ብሄረሰቡን ከሚገልፀው ቁሳዊ ባህሎች መካከል የእኔ ጥናት የትኞቹ ላይ ማተኮር እንዳለበት ለመወሰን ሞክሬያለሁ። ውሳኔዬም በናሙና የቤት ውስጥ መገልገያና የማጌጫ ቁሶች ላይ አነጣጥሯል።

ቀደም ሲል የጠቀስኳቸው የቅኝት ሥራዬን ለመስራት ባሰብኩበትና በምሰራበት ወቅት ያሳለፍኳቸው ተሞክሮዎች ሲሆኑ በሁለተኛውና በዋናው የመረጃ መሰብሰቢያ የመስክ ቆይታዬ ከሚያዚያ 17 እስከ ግንቦት 28/1999 ዓ.ም. ድረስ ደግሞ የሚከተሉትን ተግባራት ከውኛለሁ።

በመጀመሪያ፣ ከትምህርት ክፍሌ ያዛኩትን የትብብር ደብዳቤ ወደሚመለከታቸው የወረዳው ቢሮዎች በማቅረብና በምላሹ ለየቀበሌዎቹ የትብብር ደብዳቤ እንዲፅፉልኝ በመጠየቅ ደብዳቤውን በእጄ አስገብቻለሁ ። ከዚያም በየደረስኩበት ቦታ ሁሉ ይህንኑ ደብዳቤ እያሳየሁ የመረጃ ማሰባሰብ ሥራውን ሰርቻለሁ።

መረጃውን በማሰባሰብበት ወቅትም፣ እንደ አመቺነቱ፣ አንዳንድ ጊዜ ከመረጃ አቀባዮቼ ጋር ቀጠሮ በመያዝ ከውኛለሁ። ለዚህም በዋናነት የሚጠቀሰው ከእጅ ባለመ·ያዎች እና

ከታሪክ አዋቂ ሰዎች ጋር የነበረኝ ቆይታ ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት የእጅ ባለሙያዎች ሙያውን በሚሰሩበት ቦታ በመሄድ የአሰራር ሂደቱን መመልከቱ የግድ ስለነበር ሲሆን ታሪክ አዋቂዎቹ ደግሞ በጉዳዩ ዝግጅት አድርገው እንዲጠብቁኝ በማሰብ ነው። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ መረጃ የምፈልግበትን ዐውድ እንዲፈጥሩልኝ የማድረግ ሥልትንም ተጠቅሜያለሁ። ለአብነት፣ ስለቁሶቹ የሚነገሩ ቃልግጥሞችን ለማግኘት ወጣቶችን (ወንዶችንም ሆነ ሴቶችን) በማሰባሰብና «እስኪ በሠርግ ወቅት የምትዘፍኗቸውን ዘፈኖች ዝፈኑልኝ!» በማለት መረጃዎችን አግኝቻለሁ። ከዚህም ባሻገር ድንገት የሚፈጠሩ ክስተቶችን በመንተራስ የመረጃ ማሳባሰቡን ሥራ ከውኛለሁ። ለአብነት፣ መንገድ ላይ ስሄድ የማያቸውንና የምሰማቸውን ነገሮች የወይይት መነሻ ርዕስ አድርጌያለሁ።

መረጃዎችን በምሰበስብበት ወቅት የተለያዩ አጋዥ መሳሪያዎችን ተጠቅሜያለሁ። እነርሱም፣

- ሜትር - የቁሶቹን ርዝመትና ወርድ ለመለካት፣
- ሚዛን - የቁሶቹን ክብደት ለመለካት፣
- ፎቶ ካሜራ - የቁሶችን ምስል ለመቅረጽ፣
- ቪዲዮ ካሜራ - የቁሶችን የአሰራር ሂደት እንዲሁም የሽያጭ ሁኔታ ለመቅረጽ፣
- መቅረጸ-ድምፅ - በቃል መጠይቁ ወቅት ቃላዊ መረጃዎችን ለመሰነድ፣
- ማስታወሻ ደብተር - በምልከታውና በመጠይቁ ወቅት ግላዊ ስሜቶቼን ለመክተብ።

ከፍ ሲል በተጠቀሰው መልኩ መረጃዎችን ካሰባሰብኩ በኋላ ወደ አዲስ አበባ በመመለስ ፎቶ ግራፎችን አሳትሜያለሁ፣ በካሴት የተያዙ ቃላዊ መረጃዎችን ደግሞ ወደ ዕሁፍ ቀይሬያለሁ። እንዲሁም በማስታወሻዬ የያዝኳቸውን የተለያዩ ነጥቦች (የቁሶችን ርዝመትና ክብደት፣ በቃል መጠይቁና በምልከታው ወቅት የተሰሙኝን ግላዊ ስሜቶች) ለትንታኔ በሚያመቸኝ መልኩ አዘጋጅቻለሁ። ወዲያውም የትንታኔውን ሥራ የመጀመሪያ ረቂቅ ጽሬ አልተሟሉም ያልኳቸውን መረጃዎች ለማሟላትና የቪዲዮ ቀረፃውን ለመስራት ከተመረጡ ቃል አቀባዮቹ ጋር ቅድሚያ ቀጠሮ በመያዝ ለሶስተኛ ጊዜ ወደ መስክ ሄጃለሁ።

በዚሁ በሦስተኛው የመስክ ቆይታዬ (ከታህሳስ 17 እስከ ጥር 10/2000 ዓ.ም. የእጅ ባለሙያዎች (ጌጣጌጥ፣ ሽክላና ሽመና ሠራተኞች) በየመስሪያ ጎጆዎቻቸው የሚከውኗቸውን የተለያዩ ጥበቦች፣ አጋዥ የሚያደርጓቸውን መሳሪያዎችና የእጅ ሙያ ውጤቶቻቸውን እንዲሁም በገበያ ቦታ ላይ የቁሶችን የሽያጭ ሁኔታ የሚያመለክት የቪዲዮ ቀረጻውን ሥራ ሰርቻለሁ። በወቅቱም ያጋጠመኝን የመሳሪያ አለመገኘትና የባለሙያዎች ወደ ቦታው ለመሄድ ፈቃደኛ ያለመሆን ችግር *በሕይወቱ እንዲጋጠመኝ መጥፎ አጋጣሚ* የምጠቅሰው ሲሆን፣ ችግሩንም፣ ከመቅረጫ መሣሪያው ጋር ትውውቅ በማድረግና የአቀራረፅ ጥበቡን በመለማመድ ፈትቼዋለሁ።

የመስክ ቆይታ ዘገባዬን ከመቋጨቴ በፊት ካላሰፍኳቸው ተሞክሮዎች የሚከተሉትን ሁለት ነጥቦች አንባቢ ትኩረት ሰጥቶ እንዲመለከታቸው አፈልጋለሁ።

የመጀመሪያው፣ አንድ በመስክ ሥራ ታግዞ ጥናታዊ ጽሁፉን የሚያዘጋጅ ተመራማሪ በማያውቀው አካባቢና በማያውቃቸው ማህበረሰብ ዘንድ መሥራቱ የሚፈጥርበት ሥነ ልቦናዊ ጫና እንዳለ ሆኖ ውጤታማ የሚሆንባቸው በርካታ ሁኔታዎች እንዳሉ ልብ ሊባል ይገባዋል። የእኔን ተሞክሮ ለመጥቀስ ያህል፣ ለዚህ ጥናት ተተኳሪ አድርጌ የወሰድኩትን አካባቢ በምንም አጋጣሚ አላውቀውም ነበር። በመሆኑም «ለአገሩ እንግዳ ሰሰው ባዳ!» የምባል ዓይነት ነበርኩ። ይህም፣ እያንዳንዱን የብዜረሰቡን እንቅስቃሴ (በተለይም እኔ ካደግኩበትና ከኖርኩባቸው አካባቢዎች የተለየውን) በአንክሮ እንድመለከት አስችሎኛል። አንድም፣ ትንታኔየን ባገኘኋቸው መረጃዎች ላይ ተመርኩዤ (ከአድልኦ ነጻ በመሆን) እንድሰራ አድርጎኛል።

ሁለተኛው፣ አንድ መስክኛ መረጃን ለመሰብሰብ ወደ ተጠኚ ቦታው ከመሄዱ በፊት አካባቢውንና ነዋሪ ማኅበረሰቡን የሚያውቁ ሰዎችን (በተለይም አጥኚዎችን) አግኝቶ ስለተሞክሯቸው ቢጠይቅ እንዲሁም የተባሉ ጽሁፎችን ቢያነብ፣ ከዚህም ባሻገር የቅኝት ሥራን ቢያደርግ የመረጃ ማሰባሰቡን ሂደት የተቃና ያደርግለታል። ይህንንም ለማለት የደፈርኩት የተጠቀሱትን ስራዎች በማከናወኔ በመረጃ ማሰባሰቡ ወቅት እጅጉን ስለተጠቀምኩ ነው።

1.8. ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች

የመረጥኩትን ርዕስ በአዕምሮዬ ይዤ የቅኝት ሥራውን ለማድረግ በተጠኚው አካባቢ ከደረስኩበት ጊዜ ጀምሮ ጥቂት የማይባሉ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን አላልፈያለሁ። ከእነዚህም ውስጥ የሚከተሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

በመስክ ተሞክሮዬ እንደገለጽኩት፣ ለአገሩ እንግዳ በመሆኔ የመጀመሪያው ሥራዬ ከልዩ ወረዳው የባህልና የአስተዳደር ቢሮ ሠራተኞች ጋር እንዲሁም ከየቀበሌ ተጠሪዎችና ባህል አዋቂ ታላላቅ ሰዎች ጋር መተዋወቅ፣ ዓላማዬን ማሳወቅ እና ስለ ነዋሪ ማህበረሰቡና ስለአካባቢው ነባራዊ ሁኔታ የተለያዩ ጥያቄዎችን በማንሳት ግንዛቤን መጨበጥ ነበር። በዚህ ጊዜ ታዲያ አካባቢውን በተመለከተ የሚያነሱልኝ ሃሳቦች (በተለይ) የመስራት ሞራልን የሚያደበገዙ ዓይነት ነበሩ። ለአብነት፣ የመኖሪያ ቀበሌዎቹ ከከተማ ያላቸውን ርቀት፣ የትራንስፖርትን አለመኖር፣ የዓየሩን ሁኔታ (በጣም ሞቃታማ)፣ የመልክዓ ምድሩን ሁኔታ (በጣም ተራራማ) ወ.ዘ.ተ. እየጠቀሱ «ሲላ አንተ ከተማ ይህን ሁሉ ችግር እንዴት ትዛለቀዋለህ?! ... እኛም የእናትና የአባት ርስት ሆኖብን ነው እዚህ እምንኖረው!» (ዘይኑ ዑመር፣ ነሐሴ 24/1998፤ ሃርቡ) የሚሉት ቀዳሚ ተጠቃሽ ችግሮች ናቸው። በእንባሩ፣ «... ስለኛ ልታጠና ነው ካዲሳባ የመጣኸው?!... አላህ ይባርክህ አቦ!» (አቶ ሲራጅ ኢብራሂም፣ ነሐሴ 25/1998፤ ሃርቡ) የሚሉትና «... መልካም አስበሃል ልጄ! ... አንተን ያቁምልን፣ አላህ የኛ ወኪል ያድርግህ!...» (ሸህ አብዱራህማን መሐመድ፣ ነሐሴ 25/1998፤ ሃርቡ) የመሳሰሉት

አበረታች የምስጋና ቃላትም ነበሩና እነዚህኞቹን ወደ ውስጤ እያስገባሁ ፈታኝነቱን ለመታገስ ወስኛለሁ።

ሁለተኛው የመስክ ጉዞ ዋነኛው የጥናቴ መረጃ መሰብሰቢያ ጊዜ እንደመሆኑ መጠን በየቤቱ በመግባት መገልገያና ማጌጫ ቁሶችን የመመልከቱ፣ ስለ እነሱ የመጠየቁ ስራ መሰራት ነበረበትና ይህንን ስከውን፣ ለተጠኚ ቁሶቹ ዝቅተኛ ዋጋ ከመስጠት አንድም የጥናቱን ዓላማ በውል ካለመገንዘብ የተነሳ «ይህ 'ሆሣ' ነገር ምን ሊያደርግልህ ነው?» በማለትና ቁሶቹ ምንም ዋጋ እንደሌላቸው በማመን ለዕይታ የመከልከሉ፣ በፎቶ ግራፍ ለማንሳት ስፈልግም «የኛን ጥላሸት ከማቡነን በደሴና በከሚሴ ስንት ወርቅ ወርቅ የመሰለ እቃ በየሱቁ አለልህማይደል?... 'ሲላ' ተይህ ምን አለፋህ!... መገን ሥራ ማጣት!» (ስመ-ን ለመጥቀስ ያልፈቀደ ጎልማሳ ሚያዚያ 28/1999፣ ጮምዬ) የሚሉ ለስራዬ አሉታዊ ተጽዕኖ የነበራቸውን ሃሳቦች ለማስተናገድ ተገድጃለሁ። ከዚህም ባሻገር፣ ከሁለት አስርት ዓመታት በፊት የነበረን ክስተት በማውሳት «በሰባ ሰባት እንዲህ እንዳንተ ገጠር ለገጠር እየዞሩ ለቃቅመው ነው ከነጥሪት እንኳ ሳንይዝ የቤት ዕቃዎቻችንን እንድንሸጥ ያደረጉን፣ ... መቼም ተወደ ከተማ የምትመጡ ሰዎች...!» (ስማቸውን መጥቀስ ያልፈቀዱ አዛውንት፣ ግንቦት 23/1999፣ ጎበራ) የሚሉ በአንድ ወገን ለባህላዊ ቁሶች ያለን ልባዊ ተቆርቋሪነት የሚያመለክቱ፣ በሌላ ወገን ደግሞ በእኔ ጥናት ላይ ዕምነት ያለመኖርን የሚያሳዩ ሃይለ ቃላት ተሠንዝረውብኛል። ይሁን እንጂ፣ እንደዚህ የሚናገሩ ሰዎችን ቁጭ አድርጎ በማወያየት፣ የጥናቱን ዓላማና ጠቀሜታም በሰፊው በማብራራት ችግሮቹን ፈትቻለሁ።

በጥናቱ ሂደት ካጋጠመኝ ችግሮች በጣም-ን ፈታኝ የሆነብኝና ሳልጠቅሰው የማላልፈው ነገር ቢኖር መረጃዎቼን በቪዲዮ ፊልም ለማስደገፍ ባቀድኩት ወቅት የተፈጠረው ችግር ነው። የቪዲዮ ቀረጻውን ሳስብ ሁለት መንገዶችን በአማራጭነት ይገቼ ነበር። የመጀመሪያው፣ ከወረዳው ማስታወቂያ ቢሮ ትብብር በመጠየቅ መሳሪያውን መዋስና ባለሙ-ያውን የቀን አበል በመክፈል ማሰራት ሲሆን ፤ ሁለተኛው፣ በአካባቢው ያሉና በቪዲዮ ቀረፃ ሥራ የተሰማሩ ባለሙ-ያዎችን በክፍያ ማሰራት ነበር። ይሁን እንጂ፣ የመጀመሪያው መንገድ ከአንዱም ሁለት ሦስት ጊዜ መሳሪያው ብልሽት ስላጋጠመው ሊያስኬደኝ አልቻለም። የሁለተኛውን አማራጭ ለመጠቀም ስሞክርም፣ አካባቢው ከከተማ ያለውን ርቀት፣ የአየሩን ሁኔታና መልክዓ ምድራዊ አቀማመጡን በመፍራት አንድም ሰው እንኳ ፈቃደኛ ሊሆንልኝ አልቻለም ነበር። በመሆኑም፣ ሁለቱም አማራጮች ሊያስኬዱኝ ባለመቻላቸውና ሥራው ደግሞ መቅረት ስላልነበረበት በመጨረሻ ያደረግኩት ነገር ቢኖር የቪዲዮ መቅረጫ መሳሪያውን ከግለሰበች በመከራየትና የአቀራረፅ ስልቱን በመለማመድ እኔው ራሴ መቅረፅ ነበር። ችግር ብልሃትን ያስተምራልና በተፈጠረው ክስተት ብዙ ተምሬበታለሁ። በዚሁ አጋጣሚ ግን፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ ትምህርት ክፍል ለሥነጽሁፍና ፎክሎር መርሃ ግብር ተከታታይ ተማሪዎች ማገገሪ የሚሆኑ የ«ኤሌክትሮኒክስ» መሳሪያዎች ቢኖሩትና ተማሪዎች በትምህርት ቆይታቸው ወቅት የስነጻ ሥራን በተመለከተ ከእነዚሁ መሳሪያዎች ጋር የሚተዋወቁበትን መንገድ ቢያመቻች ተገቢ ነው ለማለት እወዳለሁ።

በዕርግጥ ይህ ተሞክሮ ከአሁን በፊት እንደነበር አማካሪዬ አጫውተውኛል። ይሁን እንጂ ተጠናክሮ መቀጠል ሲገባው አልቀጠለበትም።

ከላይ ከተጠቀሱት ችግሮች በተጨማሪ ተጠኚ ናሙና ቁሶችን በተመለከተ የሚነገሩ ፎክሎሮችን (ቃል ግጥሞች፣ ምሳሌያዊ ንግግሮች፣ ተረቶች ወዘተ) ማግኘቱ አስቸጋሪ ነበር። ለዚህም ሁለት ነጥቦች በምክንያትነት ሊጠቀሱ ይችላሉ። የመጀመሪያው፣ እነዚህ ቃላዊ ትውፊቶች በዐውድ ወይም አንዳንድ ጊዜ በአጋጣሚ እንጂ ታስቦባቸው ወደ አዕምሮ የሚመጡ ባለመሆናቸው ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ አንዳንድ መረጃ አቀባዮቼ «እኛኮ እስላሞች ነን፤ እስላም ደግሞ በ'ሰቢ' ተነስቶ አላህን ተማመስገንና ወደ ሥራ ተመደፋት ሌላ ተረት መተረት፣ ቧልት ማብዛትና መዝፈን ሃራመ ነው!» (ስማቸውን ለመጥቀስ ያልፈለጉ የሽመና ባለሙያ አዛውንት፣ ግንቦት 22/1999 ጎበራ) በማለት ጉዳዩን ከሃይማኖታቸው ባህርይ አንፃር መመልከታቸው ነው። ይህንን ችግር ለመቅረፍ ታዲያ በተዘዋዋሪ መንገድ በሠርግ ወቅት ወጣቶች የሚዘፍኗቸውን ቃል ግጥሞች እንዲከውኑልኝ በመጠየቅ ከሰማኋቸው መካከል የምፈልጋቸውን መርጬ ለትንታኔዬ ተገልግዬባቸዋለሁ። ሌላው አስቸጋሪ ሁኔታ፣ ተጠኚ ወረዳው አዲስ «ጎጆ ወጭ» ከመሆኑ አንፃር አካባቢውን በተመለከተ የተሟላና የተደራጀ መረጃ ባለቤት አለመሆኑ ነው። ይህም፣ መረጃን በማፈላለግ የወረዳው ቀበሌዎች ቀድመው ይተዳደሩበት ወደነበሩባቸው ከተሞች መሄድን የግድ ያደረገው ሲሆን፤ እንደዚያም ሆኖ ግን ያልተገኙ አጋዥ መረጃዎች «ለአብነት የተጠኚ አካባቢው የተሟላ ካርታ) እንዳሉ ለመጥቀስ እወዳለሁ።

1.9. የጥናቱ አደረጃጀት

ይህ ጥናት በጠቅላላው ስድስት ምዕራፎች አሉት። የመጀመሪያው ምዕራፍ፣ የጥናቱን የትኩረት አቅጣጫና የአጠናን ዘዴ የሚያስተዋውቁ ነጥቦችን አካትቷል። በምዕራፍ ሁለት፣ ሁለት መሠረታዊ ጉዳዮች ትኩረት ተሰጥቷቸዋል። እነርሱም ፣ የተዛማጅ ጥናቶችና የትውሮች ቅኝት ናቸው። ይህ ክፍል፣ ከጥናቱ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ተዛማጅነት ያላቸውን ቀደምት ጥናቶች ሂሳዊ ሆኖ በመፈተሽ፣ ማን ምን እንደሰራ፣ የተሰራው ስራም ከዚህ ከአዲሱ ጥናት ጋር ምን ተመሳሰለ፣ ምን ልዩነት እንዳለው፣ አዲሱ ጥናትም ቢሆን ከነባሮቹ ጥናቶች ግኝት የተለየ ምን ነገርን ሊያመጣ እንደሚችል በዝርዝር ለማሳየት ረድቷል። አንድም፣ በመስኩ ምሁራን የተደረሱ ትውሮች የተከለሱበት ክፍል ነውና ቁሳዊ ባህልን የሚመለከቱ ጽንሰ ሃሳቦችን ለመበየን፣ ከአጠናን አንጻሮች ጋር ለመተዋወቅ፣ ብሎም የመረጃ መሰብሰቢያና የመተንተኛ ዘዴዎችን ለመካን ወዘተ. አገልግሏል። በምዕራፍ ሶስት ተተኳሪ አካባቢውንና ብሄረሰቡን የሚገልፀ ዳራዊ መረጃዎች ተዳስሰዋል። በምዕራፍ አራት ደግሞ የእጅ ባለሙያዎች ሙያና ሕይወት ተቃኝቷል። ቅኝቱም ፣ ባለሙያዎቹን ከማስተዋወቅ አልፎ ሙያቸውን፣ የሚሠራቸውን ቁሶች ዝርዝር፣ ሙያውን የለመዱበትን መንገድና ያጋጠሟቸውን ችግሮች አካትቷል። በምዕራፍ አምስት የጥናቱ ዋናኛ ተተኳሪ የሆኑት ቁሶች ተተንትነዋል። ትንተናውም ናሙና የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶችን በአንድ

ክፍል፣ ናሙና የማጌጫ ቁሶችን ደግሞ በሌላ ክፍል ይዞ ቀርቧል። በመጨረሻው ምዕራፍ ፣ በምዕራፍ ስድስት ደግሞ፣ በቀዳሚዎቹ የጥናቱ ክፍሎች የተነሱት አንኳር አንኳር ነጥቦች በግኝትነት የተወሰ ሲሆን፤ ከእነዚህም ነጥቦች በመነሳት፣የአጥኚው የ«ይሁንታ»[15] ጥቆማዎች ተያይዘው ቀርበዋል።

[15] «ይሁንታ»፣ ቃሉን ያገኘሁት ከአማካሪዬ ከፊቃደ አዘዘ (ዶ/ር) አንደበት ሲሆን Recommendations የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል እንደሚተካ ልብ ይሏል።

2. ክለሳ ድርሳን

ይህ ክፍል ሁለት መሠረታዊ አርዕስተ ጉዳዮችን ለማካተት የተዘጋጀ ነው። የመጀመሪያው ንዑስ ክፍል (2.1) ከእኔ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ቀደምት ጥናቶች የተቃኙበት ሲሆን፤ ሁለተኛው ንዑስ ክፍል (2.2) የያዝኩትን ርዕሰ ጉዳይ (ቁሳዊ ባሕልን)[16] በተመለከተ በመስኩ ምሁራን ዘንድ የተደረሱ ትውራዊ ሃሳቦች ቀርበውበታል።

2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በቁሳዊ ባሕል ጥናት ሥር ሊዳሰሱ የሚችሉ አርዕስተ ጉዳዮችን እና/ወይም እኔ የመረጥኳቸውን ብዜረሰቦች ተተኳሪ በማድረግ የተሠሩ ጥናቶች በቁጥር ብዙ ባይባሉም ለእኔ ጥናት መነሻ ሃሳብን ያገኘሁባቸውና የአሠራር ሥልትን የቀሰምኩባቸው ጥቂት ጥናቶችን አግኝቻለሁ። በተዛማጅነታቸውም ቃኝቻቸዋለሁ።

ቅኝቱ፣ በእኔ ጥናትና በሌሎች ጥናቶች መካከል ያሉን ምስስሎሽና ልዩነቶች የሚያመላክት ሲሆን፤ ጥናቶቹ ምንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ አልመው ተነሱ? እና የእኔ ጥናትስ ከእነሱ በተለየ የትኛውን ክፍተት ለመመላት አስቧል? የሚሉትን ጥያቄዎች በአዕምሮ በመያዝ ተከናውኗል።

ጥናቶቹ በቁጥር አምስት[17] (ሦስቱ በአማርኛ፣ ሁለቱ በእንግሊዝኛ የተዘጋጁ) ሲሆኑ ከእኔ ጥናት ጋር ካላቸው ዝምድና አንጻር በሁለት ከፍዬ ቃኝቻቸዋለሁ። የመጀመሪያዎቹ፣ ከተተኳሪ ብዜረሰቡ ወይም ከተጠኚ አካባቢው አንፃር ዝምድና ያላቸው ሲሆኑ፤ ሁለተኛዎቹ ደግሞ ከያዝኩት ርዕሰ ጉዳይ አንጻር ዝምድና ያስተዋልኩባቸው ናቸው።

ከተተኳሪ ብዜረሰቡ ወይም ከተጠኚ አካባቢው አንጻር ከተዛመዱልኝ ጥናቶች የነጋሽ[18] (1981 ዓ.ም.) ቀዳሚ ተጠቃሽ ነው።

ይህ ጥናት፣ ምንም እንኳ የአርጎባን ብዜረሰብ ተተኳሪ ያደረገ ቢሆንም፣ ዋነኛ ዓላማው፣ በተለያዩ አጋጣሚዎች (ለአብነት፣ በቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜያት፣ በመገናኛ ብዙኃን ፕሮግሞች፣ በጥናታዊ ጽሁፎች ወዘተ) የሚቀርቡና አርጎብኛ ቋንቋ እንደሞቱ አድርገው የሚገልፀው ሀሳቦች እውነታነታቸው የት ድረስ እንደሆነ ማረጋገጥ ከመሆኑ አንጻር ከእኔ ጥናት የተለየ ነው። ይህ ልዩነት መኖሩም የብዜረሰቡን ናሙና ቁሶች ተተኳሪ በማድረግ እንድሰራ አስችሎኛል።

---

[16] በዚህ ጽሑፍ ውስጥ «ቁሳዊ ባህል» ስል የሚጠኑትን ቁሶች ለማመላከት ሲሆን፤ ስለነሱ የቆመውን የጥናት ዘርፍ «የቁሳዊ ባህል ጥናት» በማለት ለመለየት ሞክሬያለሁ።

[17] በተዛማጅነት ከቃኘኋቸው አምስቱ ጥናቶች ጋር ተመሣሣይ የሆኑ ሌሎች ጥናቶች (ብርሃነ ትንሳኤ ወልደሰንበት (1963)፣ ተሾመ ፎርሲዶ (1993)፣ ብርሃኑ ይዘንጋው (1996)፣ ... ቢኖሩም ጎልቶ የሚታይ ልዩነት ስለሌላቸው ድግግሞሽን ለማስቀረት ስል በቅኝቱ ከማካተት ተቆጥቤያለሁ።

[18] በጽሁፌ ውስጥ፣ ለውጭ ሀገር ጸኃፊዎች «አንተ/አንቺ» የሚሉትን ተውላጠ ስሞች፣ ለሃገር ውስጦቹ ደግሞ እንዳስፈላጊነቱ «አንተ/አንቺ» እና «አንቱታ»ን ተጠቅሚያለሁ።

ከተጠኚ አካባቢው አንጻር ዝምድና የተስተዋለበት ሌላኛው ጥናት የውብሸት (1978 ዓ.ም.) ነው። ይህ ጥናት ከተጠቀሰው ነጥብ ባሻገር ከርዕሰ ጉዳይ አንጻርም ዝምድና ይታይበታል። ምክንያቱም አልባሳትና ጌጣጌጦች የጥናቱ ዋነኛ ተተኳሪዎች ናቸውና።

የውብሸት ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር በሁለት መልኩ ቢዛመድም የእኔ ጥናት በጣም ውስን ቦታ ላይ በማተኮሩ፣ በአማራ ክልል ከሚገኙትም የተለያዩ ብሄሮች አርጎባን ብቻ በመመልከቱ ልዩነት ይስተዋልበታል። ከዚህም ባሻገር፣ የእሱ ጥናት ከአልባሳትና ከጌጣጌጦች አልፎ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶችን ባለመመልከቱ ልዩ ነው። በተጠቀሱት ልዩነቶች አማካይነት የሚታዩትንም ክፍተቶች መሙላት የእኔ ጥናት የትኩረት አቅጣጫ እንደሆነ ልብ ይሏል።

ከርዕሰ ጉዳይ አንጻር ዝምድና አላቸው ስል የቃኘኋቸው ጥናቶች፣ የአሰገደች (1986 ዓ.ም.)፣ የNahu (1998 G.C.) እና የSophia (2004 G.C.) ናቸው።

የአሰገደች ጥናት ዋነኛ ዓላማ በመረጠቻቸው አካባቢዎች የሚኖሩ የኦሮሞ ብሄረሰብ ተወላጆች ለባህላዊ ቁሶቻቸው የሰጧቸውን ስያሜዎች ከአማርኛ አቻዎቻቸው ጋር ማነጻጸር ሲሆን ይህንንም ማጤኗ ባህላዊ ቁሶቹ በስም እንዳይረሱ በማድረግ ረገድ ጠቃሚታ እንዳለው ገልጻለች።

ይህ ጥናት፣ ከቁሳዊ ባህል ጥናትነቱ ይልቅ ወደ ማኅበረሰባዊ ሥነ-ልሣን /Sociolinguistics/ ጥናት ያደላ ከመሆኑ አንፃር ከእኔ ጥናት ይለያል የሚል ዕምነት አለኝ። ለዚህም ማስረጃዬ፣ ጥናቱ፣ ብሄረሰቡ ለባህላዊ ዕቃዎቹ ሥያሜን እንዴት እንደሚሠጥ መመልከትን ዋነኛ ትኩረቱ ማድረጉ ነው። የሥያሜ ጉዳይ ደግሞ ይበልጡን በማኅበረሰባዊ ሥነልሣን የጥናት ዘርፉ የሚጠና ጉዳይ ነው።

ከዚህም ባሻገር፣የቁሶችን መደበኛ አገልግሎት ከመግለፅ አልፋ ባህላዊ ገጽታቸውን አለማመልከቷ፣ ስለቁሶች የተነገሩ ሥነቃሎችን አለመዳሰሷ፣ እንዲሁም፣ የቁሶችን ፈጣሪ (ባለሙያዎቹን) ሕይወት በጨረፍታም ቢሆን አለመመልከቷ ከእኔ ጥናት ጋር ላሉት ልዩነቶች ተጠቃሽ ነጥቦች ናቸው። ሌላው፣ ባህላዊ የቤት ቁሶችን መመልከታችን ቢያመሳስለንም እሷ የማጌጫ ቁሶችን አለመመልከቷ እኔ ደግሞ የእርሻ መሣሪያዎችን አለማካተቴ ይለያየናል።

የNahu ጥናት፣ በዓላማነት ይዞት የቀረበው ነጥብ በመረጠው አካባቢ የሚኖሩ የእጅ ባለሙያዎች በምን ዓይነት ማህበራዊና ባህላዊ የአኗኗር ዘይቤ እንደሚገኙ ማሳየት ሲሆንኔ የእጅ ባለሙያዎቹ ከተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ተገልለው እንደሚኖሩና የኢኮኖሚና የማህበራዊ ደረጃቸው ሲታይ በግብርና ከሚተዳደሩ ሌሎች ሰዎች ያነሰ እንደሆነ አመልክቷል።

ጥናቱ፣ በዋነኛነት የእጅ ባለሙያዎችን ሕይወት ከመመልከቱ አንጻር ከእኔ ጥናት ይለያል። በእርግጥ የእሱ ዋነኛ ጉዳይ በእኔ ጥናትም ተፈትሿልና በመካከላችን ምስለሎሽ አለ ሊባል ይችላል። ይሁን እንጂ፣ የትኩረት መጠኑ በእኔ ጥናት ውስጥ ያነሰ ነው። ከዚህም ባሻገር፣ የእኔ ጥናት የማጌጫ ቁሶችን መመልከቱ ለልዩነታችን አንዱ ተጠቃሽ ነጥብ ነው።

ሌላኛው ጥናት የSophia ሲሆን የ«ሚኒማሊዝም ትውር» (theory of minimalism) በ«ኢትኖግራፊያዊ ጥናት» (ethnographic research) ውስጥ እንዴት እንደሚሰራ ለማሳየት የታቀደ ነው። ይህንን ዕቅዷንም ዳር ለማድረስ የመረጠችው ተጠኚ ብዜረሰብ በደቡብ ኢትዮጵያ የሚገኘው የማሌ ብዜረሰብ ሲሆን ናሙና ቁሶቿም ብዜረሰቡ የሚኖርባቸው ባህላዊ ቤቶችና በቤቶቹ ውስጥ የሚገኙት የተለያዩ መገልገያ ቁሶች ናቸው።

አጥኚዋ ካቀረበችው ትንታኔ በመነሳት የማሌ ብዜረሰብ በአካባቢው በቀላሉ የሚያገኛቸውን የተለያዩ ጥሬ ዕቃዎች ተገልግሎ የሚያስፈልጉትን የተለያዩ ቁሶች ይሠራል፤ ቁሶቹም፣ ብዜረሰቡ በሚከውናቸው ባህላዊና ዕምነታዊ ሥርዓቶች ላቅ ያለ ሚና አላቸው፤ ለአብነት፣ ማህበራዊ ደረጃንና ኢኮኖሚያዊ ደረጃን ያመላክታሉ በማለት ገልፃለች። ይህም፣ እሷ ላነሳችው ጉዳይ (የሚኒማሊዝም ትውር በኢትኖግራፊያዊ ጥናት) ዓይነተኛ ማረጋገጫ እንደሆነ አጽንኦት ሰጥታ ገልጻለች።

የSophia ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር ሲነጻጸር ከመረጥናቸው ናሙና ቁሶች አንጻር ልዩነት ይስተዋልበታል። እኔ፣ የቤት ውስጥ መገልገያዎችንና የማጌጫ ቁሶችን በናሙናነት ስመርጥ እሷ ግን ከእነዚህ በተጨማሪ ባህላዊ ቤቶችንና የእርሻ መሳሪያዎችን አካትታለች።

2.2. የትውሮች ቅኝት

ይህ ክፍል፣ ባነሳሁት ርዕስ ጉዳይ ዙሪያ የመስኩ ምሁራን ምን ምን ትውሮችን ደርሰዋል? እኔስ ከድርሳናቱ ምን ምን የመነሻ ሃሳቦችን ይገቼ ነው ጥናቱን ያስኬድኩት? ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ ይሠጣል።

2.2.1. ቁሳዊ ባሕል ምንድን ነው?

የቁሳዊ ባሕልን ምንነት ከመግለጼ በፊት በሥያሜው ዙሪያ ያለን አከራካሪ ጉዳይ አስመልክቼ አንድን ነጥብ ለመጠቆም እወዳለሁ። ይኸውም፣ Glassie እና Prown ያነሱት ነጥብ ነው።

Glassie፣ "Material Culture" («ቁሳዊ ባህል»- ፈቃደ እንደተረጎሙት (1991: 15)) የሚለው ሥያሜ ግራ የሚያጋባ ነው (1999:41)፣ ሲል ይስተዋላል። ግራ አጋቢነቱንም ያመጣው የ«ባሕል» ጽንሰ ሃሳብ በተፈጥሮ፣ በአዕምሮ ያለ ውቅርን ውስጣዊና ሊታይ የማይችልን እንዲሁም ተቀያያሪ እና በአንድ ቅርፅ የማይፀናን ነገር አመላካች መሆኑ ነው (Glassie, 1999: 41)።

Prownም በበኩሉ፣ "Material Culture" የሚለው ሥያሜ ከአመቺነቱ አንፃር ቀድሞ ለመጠሪያነት አገለገለ እንጂ ጥያቄ የማያስነሳ ሆኖ አይደለም፣ እንዲያውም እርስ በርስ የሚጣረሱ ጽንሰ ሃሰቦችን ይዟል" ሲል "despite its concision and aptness, the term material culture seems unsatisfactory, indeed, self contradictory" (1982: 2) በማለት በአጭሩ አመልክቷል።

የሁለቱንም ምሁራን ቅራኔዎች ካቀረቧቸው የመሞገቻ ነጥቦች አንፃር፡ ስንገመግም በዕርግጥም ሥያሜው «ጥያቄ የሚያስነሳ!» ወይም «ግራ የሚያጋባ!» ሆኖ እናገኘዋለን። ቢሆንም ግን በሥያሜው አማካይነት ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት ሊሸከም የሚችል ቃል/ሃረግ እስካልተገኘ ድረስ መደነጋገሩን በማብራሪያ እየፈታን ከሥያሜው ይልቅ ወደ ይዘተ ነገሩ ማምራቱ ይመከራል። ምሁራኑም ያደረጉት ይህንኑ ነው። ደግሞም ማንኛውንም ሥያሜ ብንወስድ የተወከለለትን ነገር በበቂ ሁኔታ ይገልፃል ብሎ መናገሩ የሚያስደፍር አይደለም።

ወደ ብያኔው ስንመጣ፣ «ቁሳዊ ባሕል» በበርካታ ምሁራን ዘንድ በተለያየ መልኩ ተበይኖ እናገኘዋለን። ብያኔዎቹንም በሁለት ጎራ[19] ከፍለን መመልከት እንችላለን። አንደኛው ጎራ፣ ቁሳዊ ባሕልን እንደተጠኚ ቁስ ወይም የቁሶች ስብስብ የሚመለከት ሲሆን፣ ሌላኛው ደግሞ፣ ቁሳዊ ባሕልን እንደ አንድ የጥናት ዘርፍ የሚቆጥር ነው።

ቁሳዊ ባሕልን እንደተጠኚ ቁስ/የቁሶች ስብስብ ስንወስድ፣ «ሰፊ፣ ነገር ግን ድንበር የተበጀለትን የቁሶች ዓለም [material world] ያካልላል» (Prown, 1982: 2)። ክልሉም፣ ሰዎች በዕለት ከዕለት ደፋ ቀናቸው የሚፈልጉትን ነገር ለመከወን ሲሉ በእጃቸው የሚሠሯቸውን [objects made by man]፣ ሠርተውም የሚገለገሉባቸውን ማንኛቸውንም ዓይነት ቁሶች/የቁሶች ስብስብ [the things or the stuff] ይመለከታል (Prown, 1982:2፤ Glassie, 1999:41። አንድም፣ ተፈጥሯዊ ሆነው ነገር ግን መሻሻል/መለወጥ የታየባቸውን [objects modified by man] ይጠቅሳል (Prown, 1982: 2)። ከዚህም ባሻገር (በEtLi 621-Folklore እንደተማርኩት) የማሽን ውጤቶች ሆነውም ባህልን አጉልተው የሚያሳዩ ወይም የአንድ ማኅበረሰብ የተወሰኑ ቡድኖች መገለጫ መሆን ከቻሉ በቁሳዊ ባህል ሊጠቃለሉ ይችላሉ።

ብያኔዎቹን በምሣሌ አስደግፎ ለማሳየት ያህል፣ የሸክላ ድስት፣ የጣት ቀለበት፣ የሸማ ልብስ፣ ወ.ዘ.ተ. በሰው እጅ ከተሠሩት ቁሳዊ ባሕሎች፤ ከቀንድ የተሠራ ዋንጫ፣ ሽልማት የተበጀላት ቅል፣ የተነቀሰ ገላ፣ ወ.ዘ.ተ. ደግሞ ወደ ባሕላዊ ቁስነት ከተቀየሩት ተፈጥሯዊ ነገሮች፤ ነጭ ጋዋን (የጤና ባለሙያዎችና የመምህራን መገለጫ) እና ሬንጀር ልብስ (የወታደሮች መለያ) ደግሞ ማሽን ሠራሽ ሆነው ነገር ግን የተወሰኑ ቡድኖች መገለጫ ከሆኑት ቁሳዊ ባህሎች በአብነት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

ቁሳዊ ባሕልን እንደተጠኚ ቁስ ሳይሆን ራሱን እንደቻለ እንደ አንድ የጥናት ዘርፍ መቁጠር እንደሚቻል ከፍ ሲል ተጠቅሷል። ከዚህም አንፃር፣ ቁሳዊ ባሕል እንዲህ ሊበየን ይችላል።

---

[19] ይህንን አስመልክቶ Prown (1982:2) እንዲህ ብሏል - "The term material culture thus refers quite directly and efficiently, if not elegantly, both to the subject matter of the study, material, and to its purpose, the understanding of culture."

'ቁሳዊ ባሕል' በዓይን የሚታየውን፣ በእጅ የሚዳሰሰውን፣ ከዘመናዊ ኢንዱስትሪ በፊት ጀምሮ የሰው ልጅ የተገለገለባቸውን ቁሳቁሶች፣ እነዚህ ቁሳቁሶች የተሠሩበትን ዘዴ ወይም ቴክኒክ፣ የልዩ ልዩ ምግቦችን አሠራር፣ የቅመም አቀማመም ብልሃትን፣ የልብስ፣ የቤት፣ የአጥር ወዘተ. አሠራርን፣ ሰዎች ልዩ ልዩ ሥራዎችን የሚያከናውንባቸውን መሣሪያዎችንና ሌሎች ተመሣሣይ ጉዳዮችን ያጠናል (ፊቃደ፣ 1991:15)::

ይህንን ጥቅስ ስንመረምር፣ ቁሳዊ ባሕልን እንደ አንድ የጥናት ዘርፍ ወስዶ ዘርፉ ምን ምን ነጥቦች ላይ ትኩረቱን እንደሚያደርግ በዝርዝር የሚያሳይ ነው:: ከብያኔውም፣ «ቁሳዊ ባሕል»፣ መንፈሳዊውን ወይም ሀሳባዊውን ሳይሆን ቁሳዊውን ወይም ሊታይ፣ ሊዳሰስና ሊጨበጥ የሚችለውን፣ ባህላዊው ቁስ ተጠኚ አድርጎ «ቁሱ፣ ከምንና እንደምን ባለ ብልሀት/ዘዴ ይሰራል?» ብሎ የሚጠይቅና የሚመረምር የጥናት ዘርፍ እንደሆነ እንረዳለን::

ዘርፉ፣በ Glassie ደግሞ እንዲህ ተበይኗል::

የቁሳዊ ባሕል ጥናት በተፈጥሮና በባሕል [nature and culture] መካከል ያለን ልዩነት በአዕምሯችን የምንስልበት ወዲያውም በዕለት ከዕለት እንቅስቃሴያችን ውስጥ ፍላጎታችንን መሪ አድርገን ተፈጥሮን መልሰን መላልሰን የምንለዋወጥበትንና አዲስ ቅርፅ የምናስይዝበትን መንገድ የምናጤንበት ዘዴ ነው፣ ... አንድም፣ የቁሳዊ ባሕል ጥናት፣ ታሪክን ከጥበብ ጋር አዋህደን የምንመለከትበት መነጽር ነው (1999:1)::

ከ Glassie ብያኔ ሁለት መሠረታዊ ነጥቦች የአንባቢን ትኩረት እንደሚስቡ ልብ ይሏል:: የመጀመሪያው፣ ሰዎች ፍላጎታቸውን መሠረት አድረገው ከተፈጥሮ ጋር የሚያደርጉትን መስተጋብር፣ ኋላም የሚፈጥሩትን ባሕል፣ «ቁሳዊ ባሕል» የተባለው የጥናት ዘርፍ ጉዳዬ ብሎ እንደሚመለከተው የሚገልፀው ሲሆን፤ ሁለተኛው ነጥብ ደግሞ፣ የቁሳዊ ባሕል ጥናት፣ ቁሶች እንዴት እንደሚሠሩ ይመለከታልና «ጥበቡን»፤ ቁሶች ለባለቤት ማኅበረሰቡ የሚያስታውሱትን ያለፈ ተሞክሮንም ይዳስሳልና[20] «ታሪክን»፤ በድምሩ፣ ጥበብ ከታሪክ ጋር በአንድነት በዘርፉ ሊጠኑ እንደሚችሉ የሚጠቁመው ነው::

ቁሳዊ ባሕልን እንደ አንድ የጥናት ዘርፍ የተመለከተው ሌላኛው ምሁር፣ ዘርፉ፣ ከአርኪዮሎጂ፣ ከታሪክና ከሥነ-ሰብ የጥናት መስኮች የሚነሳው ሥጋ እንዳለው አውስቶ፣ የሰው ልጆችን ከሚያመርቱት ምርት፣ ከሚጠቀሙት ፍጆታ እና ከሚገነቡት ማኅበረሰባዊ ውቅሮች አንፃር ለመመልከት ያለመ ነው (Tilley, 1991: ገጽ አልተሰጠውም) ሲል ይገልፀዋል::

---

[20] ይህንን ሃሳብ ለማስረገጥ የሚከተሉትን ሁለት ገለፃዎች ለመጥቀስ እወዳለሁ፣

- "each object has a story to tell, a story shaped by human use" (Waugh ውስተ Internet –URL:http://www.chnm.gmu.edu/ worldhistorysources/ unpacking/ objetsmain. html).
- "every family has objects that have emotional and historic meaning associated with them" (Illinois State Museum ውስተ Internet – URL:http://www. museum. state.il.us/ muslink/ art/htmls/ hh.html.

ብያኔው፣ አንድ የቁሳዊ ባሕል አጥኚ ለጥናት ከመሰማራቱ በፊት ከየትኞቹ ተዛማጅ የጥናት መስኮች ጋር መተዋወቅ እንደሚገባውና በጥናቱም፣ ለየትኞቹ ነጥቦች ትኩረት መስጠት እንዳለበት የሚጠቁም ነው።

በመጨረሻ፣ Prown የሰጠውን ብያኔ መጥቀስ እወዳለሁ። እንደ Prown አገላለፅ «ቁሳዊ ባሕል» ማለት ቁስን/ቁሶችን በቀዳማይ መረጃነት ይዞ፣ የቁሶቹ ባለቤት የሆነው ማኅበረሰብ በአንድ በተወሰነ ጊዜ በቁሶቹ አማካይነት ምን ዕምነት፣ ሃሳብና አመለካከት እንደሚያስተላልፍ የሚፈትሽና ትንታኔን[21] የሚሰጥ የጥናት ዘርፍ ነው (1982፡ 1)።

ይህ ብያኔ ሦስት ቁምነገሮችን አቅፎ እንደያዘ ልብ ይሏል። የመጀመሪያው፣ «በቁሳዊ ባሕል ጥናት ዋነኞቹ መረጃዎች እነማን ናቸው?» ለሚለው ጥያቄ ምላሽ አቅርቧል፣ ቁሶቹ በራሳቸው። ሁለተኛው፣ በቁሳዊ ባሕል ጥናት የጊዜ/የዘመን ጉዳይ ትኩረት ሊቸረው እንደሚገባ ጠቁሟል። በሦስተኛ ደረጃም ተጠኚ ቁሶቹ የባለቤት ማኅበረሰቡን ምን ምን ጉዳዮች አጉልተው ሊያሳዩ እንደሚችሉ በዝርዝር አመልክቷል። በዚሁ ወደ ቀጣዩ ርዕስ እናልፋለን።

2.2.2. የቁሳዊ ባህል ዓይነቶች

ቁሳዊ ባህል፣ ፎክሎር ከሚያካትታቸው አራት የጥናት ዘርፎች ማለትም፣ ከሥነቃል፣ ከቁሳዊ ባህል፣ ከሃገረሰባዊ ልማድና ሃገረሰባዊ ትውን ጥበቦች (ፈቃደ፣ 1991:15) አንዱ ሲሆን በሥሩም አምስት[22] መሠረታዊ ነጥቦችን ያቅፋል (Dorson ውስተ ፈቃደ፣ 1991:15)። እነዚህም አምስት ነጥቦች በዚህ ክፍል ሥር «የቁሳዊ ባህል ዓይነቶች» በማለት የምመለከታቸው ናቸው።

2.2.2.1. ሃገረሰባዊ የእጅ ሥራ

ሃገረሰባዊ የእጅ ሥራ በቁሳዊ ባህል ጥናት ሥር ከሚዳሰሱት ነጥቦች አንዱ ሲሆን፣ የሰው ልጆች አካባቢያዊ በሆነ ዕውቀት ተመስርተው ለዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያቸው አጋዥ

---

[21] Prown ፣ ምንም እንኳ የቁሳዊ ባህል ጥናት ቁስን በቀዳማይ መረጃነት ወስዶ በመተንተን ለባህል ትርጓሜ ይሰጣል ብሎ ቢናገርም ጥናቱ ለቁሶች ትንታኔን ላይሰጥም ሊከወን እንደሚችል አያይዞ ገልጿል። ለአብነት፣ የቁሶችን ሥርጭትና የመሰራጫ መንገድ ለማጥናት ቁሶችን ለትንታኔ ማቅረቡ አስፈላጊ አይደለም (1982:1)።

[22] Dorson በአምስት ክፍል የመደባቸውን የቁሳዊ ባህል ዓይነቶች Bartis አራት አድርጓቸዋል፡ እነርሱም፣ Artifacts, Cultural Landscapes, Crafts and Trades እና Folk Art ናቸው። (Bartis, Peter. Folk life and Fieldwork፣ A layman's Introduction to Field Techniques. Washington; Library of Congress.2002. PP.4).

በአንጻሩ፣ Prown ደግሞ በስድስት የመደባቸው ሲሆን ዓይነቶቹም፣ Art, Diversions, Adornment, Modifications of the Landscape, Applied Arts እና Devices የሚሉት ናቸው (Prown, J. David. "Mind in Matter: An Introduction to Material Culture Theory and Method." Onlineat, URL:http://ww.jstor.Jstor.org/about/ terms. html

ማስታወሻ፣ የቁሳዊ ባህል ዓይነቶችን ለማሳየት የ"Dorson"ን ምደባ የመረጥኩበት ምክንያት፣
1ኛ. ሌሎቹ ምሁራን በየምድቦቻቸው የዘረዘሯቸው ምሣሌዎች ግልጽነት የጎደላቸው መስሎ ስለተሰማኝና (ለአብነት፣ ድግግሞሽ ይታይባቸዋል) እና
2ኛ. የ"Dorson"ን ምደባ በክፍል ውስጥ በተደጋጋሚ ጊዜ ስለተማርኳቸው ነው።

እንዲሆኗቸው በማሰብ በእጅ የሚያበጇቸውን የተለያዩ ቁሶች ይመለከታል (Roberts ውስተ Dorson፣ 1972፡ 233)። ለአብነት፣ የሽክላ፣ የሽመና፣ የአንጥረኝነት ወዘተ. ሥራና ውጤቶቻቸው ሊጠቀሱ ይችላሉ። ከዚህም በተጨማሪ፣ ሃገረሰባዊ የእጅ ሥራ፣ በባለሙያዎችና በሌሎች ሰዎች መካከል ያለውን መስተጋብር ያካትታል (Yodor ውስተ Vlach እና Bronner, ዘመኑ አልተጠቀሰም፣ 38)።

እንደ Roberts እምነት፣ ቁሶቹ፣ አካባቢያዊ ዕውቀትን መሠረት በማድረግ በእጅ የሚሠሩ ከመሆናቸው አንፃር የባለቤት ማህበረሰቡን ባህል ፍንትው አድርገው ሊያሳዩ ይችላሉ (እንደላይኛው፣ 233)።

2.2.2.2 ሃገረሰባዊ ሥዕል

የሰው ልጆች (በተለይም የእጅ ባለሙያዎች) የተለያዩ ምክንያቶችን መነሻ በማድረግ ቁሶችን ይሠራሉ። ከምክንያቶቹም መካከል የሚከተሉት ሦስቱ በ"Toelken" (1991) ዘንድ መሠረታዊዎቹ ናቸው። የመጀመሪያው፣ ባለሙያዎች ለጥቡበ/ለውበት ያላቸው ግለሰባዊና ውስጣዊ ፍላጎት ሲሆን፤ ሁለተኛው፣ ባለሙያዎች የአካባቢያቸውን ማህበረሰብ መደበኛ ቁሳዊ ፍጆታ ለማሟላት ማሰባቸው ነው። በአንፃሩ ሦስተኛው ደግሞ፣ ባለሙያዎቹ የሚኖሩበት ባህል (ባህሉ በራሱ) እንዳይጓደሉ የሚፈልጋቸው ቁሶች መኖራቸው ነው (Toelken፣ 1991:11)።

ቁሶቹ የሚሠሩበት ምክንያት ምንም ይሁን ምን አንዳች አገልግሎትን ለመስጠት ይሠራሉ። አገልግሎታቸውም የአንዱ ከሌላው የተለየ ነው። ይህንንም የአገልግሎት መለያየት መነሻ አድርጎ Glassie በእንግሊዝኛ «አርቲፋክትስ» የምንላቸውን የቁሶች ስብስብ በሁለት ጎራ ይከፍላቸዋል (Glassie ውስተDorson፣ 1972፡ 253)። የመጀመሪያዎቹ አገልግሎታቸው ለባለቤት ማህበረሰቡ «ተግባራዊ አገልግሎትን» መስጠት ሲሆን «ሃገረሰባዊ የእጅ ሥራ» /Flok Craft/ የሚልን መጠሪያ ሰጥቷቸዋል። ሁለተኞቹ ደግሞ ከተግባራዊው ይልቅ ለባለቤት ማህበረሰቡ የደስደስ ሥሜትን የማጫር አገልግሎት የሚሰጡት ናቸው። እነዚህኞቹን «ሃገረሰባዊ ሥዕል» /Folk Art/ በማለት ይጠሯቸዋል (እንደላይኛው፣ 253)።

የ "Glassie" ን ብያኔ መሠረት አድርገን ለሃገረሰባዊ ሥዕል የተለያዩ ምሣሌዎችን ማቅረብ እንችላለን። ለአብነት፣ የተለያዩ ቀለማትን ቀብተን የሸለምናት ቅል፣ የተለያዩ ቀለማት ያላቸውን ክሮች ተጠቅመን የጠለፍነው ጥልፍ (የቀሚስ፣ የነጠላ፣ የመቀነት፣ ወዘተ.)፣ የጎጇችን ግድግዳ ላይ የነደፍናቸውና የጭቃ ቀለም የቀባናቸው ሥዕሎች ወዘተ. ተጠቃሾች ናቸው።

እነዚህን ምሣሌዎች ስንመለከት፣ ሁሉም ለአዕምሯችን የተለየ ሥሜትን የመፍጠር ኃይሉ አላቸው። የምንመዝናቸውም ይህንኑ የተለየ ባህርያቸውን ግንዛቤ ውስጥ አስገብተን ነው።

2.2.2.3 ሃገረሰባዊ ምህንድስና

ሦስተኛው የቁሳዊ ባህል ዓይነት ሃገረሰባዊ ምህንድስና ሲሆን በባህላዊ መንገድ የሚሠሩ ማንኛቸውንም ዓይነት የምህንድስና ሥራዎች ይመለከታል (Roberts ውስተ Dorson፤ 1972: 281)። ለምሣሌ፤ የሰዎች መኖሪያ ቤት፤ የከብቶች ማደሪያ በረት፤ ዳስ፤ የጭስ ቤት፤ ወ.ዘ.ተ. በአስረጅነት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

ሃገረሰባዊ ምህንድስና ከላይ በምሣሌው የተጠቀሱትን ባህላዊ የምህንድስና ሥራ ውጤቶችን ብቻ አይደለም የሚመለከተው። ይልቁንም፤ ውጤቶቹ የተገኙበትን (የተሠሩበትን) ንጥረ-ቁስ፤ በሥራው ሂደት አጋዥ የነበሩ የተለያዩ መሣሪያዎችን፤ እንዲሁም የአሠራር ጥበቡን፤ ወ.ዘ.ተ. አብሮ ይመለከታል (እንደላይኛው፤ 281)።

2.2.2.4 ሃገረሰባዊ ልብስ

የመጀመሪያውን የሰው ፍጥረት፤ አዳምን፤ ዋቢ አድርገን ስንመለከት፤ የሰው ልጆች በአካባቢያቸው የሚያገኟቸውን ተፈጥሯዊ ነገሮች (ለአብነት-ቅጠል) ተጠቅመው ዕርቃናቸውን ይሸፍኑ ነበር። ይህ ነገር በጊዜ ሂደት እየተሻሻለ መጥቶ ሰዎች ተፈጥሯዊውን ነገር ለወጥ በማድረግ ልብስን መሥራት ጀምረዋል።

የልብሱ ዋነኛ ዓላማ ከላይ እንደተጠቀሰው የተራቆተ ገላን ለመሸፈን ቢሆንም ቅሉ ከዚህ ባሻገር ግን ለተለያዩ አገልግሎቶች ይውላል። ይህንን ነጥብ አስመልክቶ Yodor «ሃገረሰባዊ ልብስ፤ የሰዎችን አፋኣዊ ማንነት ለአካባቢያቸው ማህበረሰብ እና/ወይም ከአካባቢያቸው ራቅ ብለው ለሚኖሩ ለባዕድ ወገኖች ገልጦ የሚያሳይ መለያ ነው» (Yodor ውስተ Dorson፤ 1972:295) ይላል። በመሆኑም፤ ልብሱ፤ የለባሹን ሰው ዖታ፤ ዕድሜ፤ የመኖሪያ አካባቢ፤ ብሄር፤ የሥራ መስክ፤ ማኅበራዊ ደረጃ፤ ወ.ዘ.ተ. ለተመልካቹ የመንገር ባህርይ አለው (እንደላይኛው፤ 304)።

እንደ Yodor ገለፃ ሃገረሰባዊ ልብስ በአንድ አካባቢ የመወሰን ባህርይ አለበትና ከቋንቋ ዘዬ ጋር ይመሳሰላል (እንደላይኛው፤ 295)። ምክንያቱም፤ ለቋንቋ አካባቢያዊ ዘዬ እንዳለው ሁሉ ለልብስም አካባቢያዊ ልብስ አለና፤ ይህም «ሃገረሰባዊ ልብስ» ያልነው ነው።

2.2.2.5 ሃገረሰባዊ የምግብ አሠራር

ሃገረሰባዊ የምግብ አሠራር፤ ከቁሳዊ ባህል ዓይነቶች አንዱ ሲሆን ሰዎች በአካባቢያቸው የሚያመርቷቸውን ጥሬ ነገሮች ተገልግለውና አካባቢ በቀል በሆነ ዕውቀት ተመርኩዘው ለዕለት ጉርሳቸው የሚያዘጋጁትን ምግብ ይመለከታል (Yodor ውስተ Dorson፤ 1972:325)።

ሃገረሰባዊ ምግብን ጉዳዩ ብሎ የሚያጠና ተመራማሪ በጥናቱ ሂደት፤ ምግቡ ከምንና እንዴት እንደሚሠራ፤ መቼና በምን መልኩ ለምግብነት እንደሚውል፤ በምን ባህላዊ ዘዴ ለረዥም ጊዜ መቆየት እንደሚችል፤ ምግቡ ለባለቤት/ለተጠቃሚ ማኅበረሰቡ የሚሰጠው ማኅበራዊና ሥነ አዕምሯዊ ጥቅም ምን እንደሆነ፤ ከምግቡ ጋር ተያይዘው የሚወሱ ቃላዊ ትውፊቶች ምን ምን እንደሆኑ ወ.ዘ.ተ. ትኩረት ሰጥቶ ሊፈተሽ ይገባዋል (እንደላይኛው፤ 325)። ከዚህም ባሻገር፤ ማኅበረሰቡ፤ ምግቡን ባህላዊ እሴቱ አድርጎ የወሰደበት

(የጠበቀበት) መነሻ ምክንያት ምን እንደሆነ አብሮ ሊያጤን ይገባዋል። ለአብነት፣ አንዳንድ ሃገረሰባዊ ምግቦች ሃይማኖታዊ መነሻ ሊኖራቸው እንደሚችል ልብ ይሏል (እንደላይኛው፣ 338)። ሃይማኖታዊ መነሻውም በማህበረሰቡ ዘንድ በሁለት መልኩ ተዕዕኖ ሊያሳድር ይችላል። አንደኛው ተዕዕኖ አምንታዊ ተዕዕኖ ሲሆን ምግቡን እንድንጠቀም ያስችለናል። ለአብነት፣ የቡሄ በዓል መ.ልመ.ል ዳቦን፣ የግቡት ልደታ ደግሞ ንፍሮን እንድንጠቀም ምክንያት ይሆኑናል። በአንፃሩ፣ ሁለተኛው ተዕዕኖ አሉታዊ ሲሆን «ምግቡን» ከመጠቀም እንድንቆጠብ ያደርገናል። ለአብነት፣ የክርስትና ሃይማኖት ሽኮና የሌላቸው እንስሳት በምግብነት እንዲውሉ አይፈቅድም። በተመሣሣይ መልኩ፣ የእስልምና ሃይማኖት ደግሞ የሚያስክር መጠጥን ይከለክላል።

በዚህ ክፍል (በ2.2.2) በመጠኑ ከቀረበው ዳሰሳ የቁሳዊ ባህል አጥኚ አምስት መሠረታዊ ጉዳዮችን (የቁሳዊ ባህል ዓይነቶችን) በጥናቱ ሊመለከት እንደሚችል እንረዳለን። ከዚህም መነሻነት የእኔ ጥናት በሃገረሰባዊ የእጅ ሥራና ሃገረሰባዊ ልብስ ምድብ ሥር የሚካተቱትን ናሙና ቁሶች ተተኳሪ አድርጓል። ይህንንም ያደረግኩበት ምክንያት የተመረጡትን ቁሶች በመስክ ቆይታዬ ስመለከታቸው የባለቤት ብዛረሰቡን ባህል ይበልጥ ይገልፀልኛል ብዬ በማመኔ ነው። ለተጨማሪ ማብራሪያ የጥናቱን ወሰን ያስታውሷል።

2.2.3. የቁሳዊ ባህል መገለጫ ባህርያት

ቀደም ሲል በ2.2.1. እንደተጠቆመው፣ የባህል ጽንሰ ሃሳብ፣ በአዕምሮ ውስጥ ያለ ውቅርን፣ ውስጣዊና ሊታይ የማይችልን፣ እንዲሁም፣ ተቀያያሪና በአንድ ቅርፅ የማይፀናን ነገር አመላካች ነው (Glassie, 1999:41)። ይህ ሆኖ እያለ፣ «ቁሳዊ ባህል» [Material Culture] የሚል ሥያሜ መበጀቱ ብሎም እንደ አንድ የጥናት ዘርፍ ተወስዶ ቁሶችን ለቀዳማይ መረጃነት [Prown, 1982:1] ማጨቱና ባህልን አጉልተው ያሳያሉ ብሎ ማሰቡ ከምን አዕምሮ የመጣ ነው? የሚልን ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል። ጥያቄውን በሌላ መንገድ ለመግለፅ፣ የሰው ልጅ፣ ከአንደበቱ በሚያወጣቸው፣ አንድም ወረቀት ላይ (ወይም ሌላ) በሚከትባቸው ቃላት ማንነቱን፣ ታሪኩን፣ ባሕሉን ብሎም ሁለመናውን መግለጽ እየቻለ፣ «ግዑዛን ቁሶችን» ለጥናት መረጃነት መውሰዱ ለምን አስፈለገ? ቁሶቹ የትኛውን ሃሳብ ለማስረገጥ ምስክርነት ሊጠሩ ነው? የትኛውንስ ሊቃወሙ? ወይንም ደግሞ ካለው ነገር ላይ ምን ተጨማሪ መረጃ ሊያቀርቡ? ይህ ክፍል ለእነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት (የቁሶችን መገለጫ ባህርያት ለማሳየት) የቀረበ እንደሆነ ልብ ይሏል። ወዲያውም፣ እኔ የመረጥኩትን ተጠኚ ብዛረሰብ ከቁሳዊ ባህሎቹ አንጻር ለመመልከት እንድወስን ያበቁኝን ምክንያቶች።

በቁሳዊ ባህል ጥናት ትኩረት ተችሯቸው የሚታዩት ቁሶች የተለያዩ መገለጫ ባህርያት አሏቸው። የሚከተሉት በመስኩ ምሁራን ዘንድ የሚታመንባቸው ነጥቦች ናቸው።[23]

---

[23] ነጥቦቹም፣ ዘመን ተሻጋሪነት /Longevity/፣ ቀዳማይነት /Data precedence/፣ ተጨባጭነት /Tangibleness/፣ ተወካይነት /Representativeness/ የተፈጥሯዊና የተለጣፊ ጸጋ ባለቤትነት /Inherent and Attached Value/ የሚሉት ናቸው።

2.2.3.1. ዘመን ተሻጋሪነት

ቁሶች፣ ለረጅም ዕድሜ (አንፃራዊ በሆነ መልኩ) የመቆየት ባህርይ አላቸው [Schlereth,1985:24]። ይህንን ነጥብ ለማብራራት ከቃላዊው ባህል ጋር ማነፃፀሩ ነገሩን በይበልጥ ግልፅ ያደርገዋልና እናነፃፅር። ማንኛውም ተረት ከዋኝ (ተራች) ቢሆን ከደቂቃዎች በፊት የከወነውን ተረት ቃል በቃል አስታውሶ ሊደግመው አይችልም። ተራቹ፣ ዘንግቶም ይሁን በሌላ ምክንያት፣ አስቦትም ይሁን ሳያስበው ወይም በአጠቃላይ መቆጣጠር ስለማይችል በታሪኩ ላይ አንዳች ለውጥን ያደርጋል። በተሰይ ተራኪው ሌላ ሰው (ቀድሞ አድማጭ የነበረ) ከሆነማ ተረቱ የቀደመ ትርጓሜውን ሊያጣ ሁሉ ይችላል። ይህ የሁሉም ቃላዊ ትውፊቶች (ማለት ይቻላል) ባህርይ ነው። በአንጻሩ፣ ቁሳዊ ባህልን ከወሰድን «በጊዜ ሂደት አይቀየሩም!» ማለት ባይቻልም ለውጡን በቀላሉ ያለማስተናገድ ብቃቱ ግን አላቸው። ይህንን ባህርያቸውንም መሠረት አድርጎ Prown ቁሶችን «surviving historical events» (1982:3) ሲል ይገልፃቸዋል።

2.2.3.2. ቀዳማይነት

እንደ Schlereth እምነት የሰው ልጆች ስለቁሶች ማውራት ወይም መፃፍ ከመጀመራቸው ቀድሞ ቁሶችን ይሠሩ ነበር፤ ይገለገሉባቸውም ነበር፤ በመሆኑም፣ ቁሳዊ ባህል ከቃላዊው ባህል የላቀ ዕድሜ አለው (1985:23)። ይህንንም ሲያስረግጥ፣

> *Material culture is, without question, humankind's oldest legacy of cultural expression. In fact, some scholars argue that it is the oldest manifestation of our humanness (አንደላይኛው፣23)*

ያሚልን ገለፃ አቅርቧል።

በተጨማሪም፣ የታሪክ ተመራማሪዎች የቀደሙትን ዘመናት የሰው ልጆች ታሪክ ሲያጠኑ ዘመናቱን በወቅቱ ይሠሩ ወይም አልግሎት ላይ ይውሉ ከነበሩት ቁሶች አንፃር መሰየማቸው[24] ያለአንዳች ምክንያት አይደለም ይላል (አንደላይኛው፣23)።

የቁሶች የቀዳማይነት ባህርይ ጥያቄ ሊያስነሳና ሰፋ ላለ ውይይት ሊጋብዝ የሚችል ጉዳይ ቢሆንም ዕውነትነት አይጠፋውም።

2.2.3.3. ተጨባጭነት

ቃላዊ ባህልን ስንወስድ መሠረቱ ቃል ነው፣ ቃል ደግሞ የማይታይ፣ የማይዳሰስና የማይጨበጥ ነገር ነው። በአንፃሩ፣ ቁሳዊ ባህልን ብንወስድ መሠረቱ ቁስ ነው፣ ቁስ ደግሞ ባለ ሦስት ጎን [three dimensional] ቅርፅ ባለቤት ነውና ሊታይ፣ ሊዳሰስና ሊጨበጥ ይችላል [Schlereth,1985:25፤Bronner,1986:202]። ይህም ከቃላዊው ባህል ይለየዋል፤

---

[24] ስያሜዎቹና የሚያጣቅሷቸው ቁሶች የሚከተሉት ናቸው፣- Paleolithic age እና Neolithic age - ድንጋይን፤ Bronze age ብሮንዝን (የመዳብና ቆርቆሮን ቅይጥ - alloy)፣ Iron age ደግሞ ብረትን።

ወዲያውም አንዳች የተአማኒነትን ባህርይ ያላብሰዋል [Schlereth, 1985:25፤ Bronner, 1986:202]።

2.2.3.4. ተወካይነት

ቁሶች «የተወካይነት» ባህርይ አላቸው ሲባል ለሁሉም የሰው ልጆች መገልገያ ከመሆናቸው አንፃር ያገኙት ብቃት እንደሆነ ልብ ይሏል [Glassie ውስተ Prown 1982:3፤ Schlereth, 1985:25]። የናጠጠ ሃብታምም ይሁን መናጢ ደሃ፣ የተማረም ይሁን ያልተማረ፣ በከተማ የሚኖርም ይሁን በገጠር፣ ባለሥልጣንም ይሁን ተራ ሕዝብ፣ ወንድም ይሁን ሴት (ትሁን)፣ አዛውንትም ይሁን ህፃን የሚጠቀመባቸው ቁሶች በዓይነት ይለያዩ እንደሁ እንጂ ሁሉም ቁሶችን ይገለገላሉ።

ከዚህም አንጻር፣ ቁሶችን ለጥናት መረጃነት ብንወስድ፣ «መረጃዎቻችን በዕርግጥ ተጠኚ ቡድኑን ይወክላሉ ወይስ...?» የሚለው ጥያቄ የእኛ የራስ ምታት አይሆንም። በአንጻሩ፣ የተባራ የታሪክ መዛግብትን በመረጃነት ብንወስድ፣ የደሃውንና የተራውን ሕዝብ እሮሮ ሳይሆን የባለሥልጣኑንና የሃብታሙን ድሎት፣ የገጠሩን ሕዝብ ሳይሆን በከተማ የሚኖሩትን ጥቂቶች፣ የሴቶችን ሳይሆን የወንዶችን «ሕይወት»/«ኑሮ» የሚያሳዩ (የሚያዳሉ) ሆነው እናገኛቸዋለን።

2.2.3.5. የተፈጥሯዊና የተለጣፊ ጸጋ ባለቤትነት

አበባ አየሁሽ /ለምለም
አበባ አየሁሽ /ለምለም
....
እናቴን ጥሯት / መድኃኒቴን
እሷን ብታጡ / መቀነቷን
አሸተዋለሁ እሷን እሷን
(«አበባ አየሁሽ» ከሚል ባህላዊ ዘፈን ተቀንጭቦ የተወሰደ ቃልግጥም)

ቁሶች በተፈጥሮ አንድም በሰዎች አማካይነት የአንዳች ጸጋ ባለቤት ሆነው ይታያሉ (Prown, 1982:3)። ለዚህም የተለያዩ ነጥቦች በምክንያትነት ሊጠቁሱ ይችላሉ (እንደላይኛው፣ 1982፣3)።

የመጀመሪያው፣ አንዳንድ ቁሶች የሚሠሩባቸው ንጥረ ቁሶች እንደልብ የማይገኙ ይሆናሉ። ለአብነት፣ ከወርቅ፣ ከብር፣ ከከበረ ድንጋይ፣ ከመሣሠሉት የሚሠሩ ቁሶች መሰሪያ ንጥረ ቁሶቻቸው <u>በተፈጥሮ</u> በማንኛውም ቦታ ካለመገኘታቸው የተነሳ የላቀ ዋጋ ባለቤት ሆነዋል።

ሁለተኛው ምክንያት፣ ቁሶቹ ከሚሠጧቸው መደበኛ ግልጋሎት ባሻገር የጥበብ መገለጫ የሚሆኑበት አጋጣሚ መኖር ነው። ሌላው፣ አንዳንድ ቁሶች የመንፈሳዊ ዋጋ ባለቤትም ናቸው። ለአብነት፣ በክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ መስቀልና ስዕለ አድኅኖዎች ያላቸውን ክብር መጥቀስ ይቻላል። ከሃይማኖት ጋር ባይያያዝም ከላይ ከንዑስ ርዕሱ ግርጌ የተጠቀሰው የባህላዊ ዘፈን ቃልግጥምም አንዳች መንፈሳዊ /አዕምሯዊ/ ዋጋን ለቁሱ (ለመቀነቷ) እንዳለበሰ ልብ ይሏል። ለእናት ተሰጥቶ የነበረን የመፈወስ ፀጋ ለመቀነቷ ሰጥቷል። ይህም፣ ሰዎች፣ ቁሶች ላይ የሚሰጥሩትን ዋጋ በግልጽ አመላካች ነው።

በዚህ ንዑስ ርዕስ (2.2.3.) መግቢያ ላይ ለተነሳው መሠረታዊ ጥያቄ ከላይ በምሁራኑ የተጠቀሱት የቁሶች መገለጫ ባህርያት ምላሽ ይሆናሉ የሚል እምነት አለኝ። በመሆኑም፣ ቁሶች፣ ባህልን መሸከም ይችላሉና ለባህል ጥናት ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን ልናገኝባቸው እንችላለን። ከቁሶች የምናገኘው መረጃም፣ ሁሉንም የሰው ልጆች ወካይ ከመሆኑም በላይ ተጨባጭ/ተኣማኒ ነው። ከዚህም ባሻገር ቀዳማይና ዘመን ተሻጋሪም ነው። ይህ ማለት ግን ከቁሶች የሚገኘው መረጃ የሰው ልጆችን ባህል፣ ታሪክ፣ ማንነት፣ ወዘተ ለማጥናት ብቸኛው ነው ማለት አይደለም፤ ዓይነተኛው[25] ነው ለማለት እንጂ። ብቸኛው ነው ብለን ካሰብን ቃላዊውን ዘንግተናል። ይህ ደግሞ ጥናታችንን ጎደሎ ያደርግብናል። ምክንያቱም፣ ቃላዊውና ቁሳዊው ባህል እርስ በርስ ተደጋግፈው የሚኖሩና በመረጃነትም በጥምረት የሚታዩ እንጂ በተናጠል የሚፈተሹ አይደሉምና[26]።

ከዚሁ ጉዳይ ሳንወጣ ልብ ልንለው የሚገባው ነገር፣ በቁሳዊ ባህል ጥናት ቁሶችን በመረጃነት ስንወስድ ከላይ የተዘረዘሩትን የቁሶች ባህርያት ሽፋን አድርገን በመረጃዎቻችን ልንመዛደቅ አይገባም። ከተመዛደቅን ጥናታችን ከስህተት ሊፀዳ አይችልም። ይልቁንም፣ Schlereth፣ "Material Culture Errors" (1985: 27) ሲል የጠቀሳቸውን ሥህተቶች ወደመፈፀሙ እናመራለን።

ይህ ምሁር የጠቀሳቸው ስህተቶች በቁጥር ሁለት ሲሆኑ፤ የመጀመሪያው የቁሶችን ተወካይነት ይመለከታል። ማለትም፣ ቁሶች፣ በተለይም ዕድሜ ጠገብ የሆኑትና በቅርስነት የተያዙት፣ በተሠሩበትና አገልግሎት ይሰጡበት በነበረበት ወቅት ሁሉንም ሰዎች (ባለመ·ያዎቹንና ተጠቃሚዎቹን) ይወክሉ ነበር ወይ? (ቁሶቹን ይሠሩ የነበሩት ወንዶች ናቸው ሴቶች? ወይስ ሁለቱም ያታዎች? በቁሶቹ ይገለገሉ የነበሩትስ ሁሉም የማህበረሰቡ አባላት ነበሩ ወይስ የተወሰኑት? የተወሰኑት ከሆኑ የትኞቹ? የቀሩትስ ለምን?) ብለን ብንጠይቅ ጊዜው ሩቅ ከመሆኑ የተነሳ ተኣማኒ መረጃ ላናገኝ እንችላለን። እንዲሁም ሆኖ ግን የቁሳዊ ባህል ተመራማሪው «ቁሶቹ ሁሉንም ሰዎች ይወክላሉ!» ከሚል ድፍረት ከተሞላበት ድምዳሜ የሚደርስበት አጋጣሚ አለ። ይህ አንደኛው ስህተት ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ከዓውድ ጋር የተያያዘ ነው።

የቁሳዊ ባህል ተመራማሪው፣ «ተጠኚ ቁሶ ይህንን መልዕክት ያስተላልፋል!» ተብሎ በመረጃ አቀባዮቹ በቃል ሲነገረው መረጃውን በዓውድ ሳያስደግፍ ሪፖርቱን ለመፃፍ ከቸኮለ፣ ዓውዱ ትናንትና ከትናንት በፊት እንጂ ዛሬ ላይ የማይታይ ሊሆን ይችላልና በዚህ መልኩም ስህተት ሊሠራ ይችላል። በዕርግጥ የተነገረው መረጃ ታሪክን ሊጠቁመው ይችላል፤ የዛሬውን ባህላዊ ገጽታ ግን ሊያመላክተው አይችልም።

---

[25] ዓይነተኛነቱን Prown እንዲህ ይገልፀዋል፡- "... although the study of artifacts is only one route to the understanding of culture, it is a special, important, and qualitatively different route. An investigation that ignores material culture will be impoverished. (1982:5 ፣ አጽንኦቱ የኔ ነው)።

[26] ይህንን አስመልክቶ ITO የሚከተለውን ይላል፡- "... the study and understanding of intangible cultural heritage will offer an important basis for the maintenance,, custody, conservation, and repair of tangible cultural heritage." URL: http:// www.international.icomes.org/ victoriafalls2003/papers/

Schlereth የጠቀሳቸውን ስህተቶች የሚፈፅማቸው (በተለይ) በሙዚየም ውስጥ ያሉ ቁሶችን በመረጃነት የሚጠቀም የባህል አጥኚ ወይንም ደግሞ፣ የመስክ አጥኚ ሆኖ ነገር ግን የቁሶቹን ባህላዊ ገጽታ በዓውድ ሳያስደግፍና በዓይኑ ሳያይ በቃል የተነገረውን መረጃ ብቻ ይዞ ድምዳሜ ለመስጠት የሚሞክረው ነው።

የዚህ ጥናት አቅራቢ የተጠቀሱትን ስህተቶች ላለመፈፀም የተቻለውን ሁሉ አድርጓል። ከጥንቃቄዎቹም መካከል፣ መረጃውን ከሙዚየም ሳይሆን ከመስክ ላይ (በየጓዳ ጎድጓዳው) ሰብስቧል። ሲሰበሰብም ከትክክለኛ ዓውድ ለመቅዳት ሞክሯል። በዓውድ ያልታዘቡትንም ቀደም ሲል በአካባቢው ይተገበሩ እንደነበር አሁን ላይ ግን እንደሌሉ አመላክቷል።

2.2.4. ቁሳዊ ባህልን የመመደቢያ መስፈርቶች

አንድ ሊጠና የሚችል ርዕሰ ጉዳይ (ለአብነት - «ቁሳዊ ባህል») በተለይም ሥፋትና ጥልቀትን የተላበሰ ሆኖ ከተገኘ የአጠናን ሥልቱን የቀለለና ሂደቱንም የቀና ለማድረግ ተጨባጭ መስፈርትን ይዞ ጉዳዩን በምድብ በምድብ ማስቀመጡ የሚደገፍ አካሄድ ነው። ይህም ክፍል በቁሳዊ ባህል ጥናት ትኩረት የሚሰጣቸውን ቁሶች (ቀዳማይ መረጃዎች - እንደ Prown 1982:1 አገላለጽ) ከምን ከምን መስፈርት አንጻር መድቦ ማጥናት እንደሚቻል ለማሳየት የቀረበ ነው።

በቁሳዊ ባህል የጥናት መስክ ሊጠኑ የሚችሉ ቁሶችን በምድብ በምደብ ማስቀመጡ በቀላሉ ሊከወን የሚችል ተግባር አይደለም። ይልቁንም ከፍተኛ ጥንቃቄን የሚፈልግ አስቸጋሪ ሥራ እንጂ። አስቸጋሪነቱም ከሁለት መሠረታዊ ምክንያቶች አንጻር እንደሆነ Prown (1982:2) ገልጿል።

የመጀመሪያው፣ የቁሶቹ በቁጥርና በዓይነት ብዙ ሆኖ መገኘት ሲሆን፤ ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ አንድ ወጥ /ሁሉ አቀፍ/ የሆነና ሳንካ አልባ የሚባል የመመደቢያ መስፈርት አለመኖር/ አለመገኘት ነው። እውነታው ይህ ቢሆንም ቅሉ በመስኩ ምሁራን ዘንድ የተጠቆሙ የተለያዩ መስፈርቶች እንዳሉ ግን ልብ ሊባል ይገባዋል።

ለአብነት Prown (1982:2) ከመሰሪያ ንጥሩ ቁስ፣ ከአሠራር ጥበብ እና ከአገልግሎት አንፃር ከፋፍሎ ማየት እንደሚቻል ገልፆ፣ አያይዞ ግን የእያንዳንዱን መስፈርት ኢ-ምሉዕነት ያመላክታል። ይኸውም፣ የመሠሪያ ንጥረ ቁስን መስፈርት ብናደርግ፣ ከአንድ በላይ በሆኑ ንጥረ ቁሶች የተሠሩ ናሙና ቁሶች አሉና መስፈርትነቱ አዋጭነት የለውም። የአሠራር ጥበብንም ብንወስድ፣ ጥበቡ በዘመናት ሂደት የሚለዋወጥ በመሆኑ አንድም በባለሙያዎች የግል ክህሎት ልዩነት መታየቱ መስፈርትነቱን ጥያቄ ውስጥ ይጥለዋል ይልና በመጨረሻ ግን «አገልግሎት»ን የተሻለና ሊያስኬድ የሚያስችል[27] (The most promising) መስፈርት ነው

---

[27] Prown «አገልግሎትን» በመስፈርትነት መውሰድን «የተሻለና የሚያስኬድ» ቢለውም ከችግር ያልጸዳ ለመሆኑ አያጠራጥርም። ለዚህም ማጠየቂያዎቹ፣ ከቁሱ ተጠቃሚዎች /users/ወይም ከቁሱ ጥቅም /use/አንጻር አገልግሎት መቀያየር (functional shift) መኖሩ(Somjee, 1993:86)፤ አንድም ብዙ ጥቅም ያላቸው ቁሶች /multifunctional objects/መኖር /Beals and Harry, 1958:236/የሚሉት ናቸው።

በማለት ይገልፀዋል። ይህንንም መሠረት አድርጎ Prown የራሱን ክፍፍል ያበጃል።

በተመሣሣይ መልኩ (ነገር ግን የመስፈርቶቹን ቁጥር ጨምሮ) Ames (1978:20) የሚከተሉትን ነጥቦች በመስፈርትነት እንድንገለገልባቸው ይመክራል። እነዚህም፤ ቅርፅ፤ አገልግሎት፤ መሠሪያ ንጥረ ቁስ፤ ዘመን፤ ባለሙያ እና ሥልት ናቸው።

ቅርፅ:- ተጠኚ ቁሱ ከአወቃቀር (ከተክለ ቁመና) ረገድ ምን መልክ እንዳለው የሚገልፅ ሲሆን እንደ Georges & Jones እምነት፤ ቁሳዊ ባህልን ከቃላዊው የሚለየውና የተጨባጭነትን ባህርይ የሚያላብሰው ከመሆኑ አንፃር ለክፍፍሉ በቀዳሚነት መታየት ያለበት መስፈርት ነው (1995:94-95)። ይህንንም መስፈርት የሚከተለው ዘዴ "structuralist approach" ይባላል።

ሁለተኛው የ"Ames" መስፈርት፤ **«አገልግሎት»** ነው። አገልግሎትም፤ በዕርግጥ አንድ ቁስ ከአንድ በላይ አገልግሎቶችን ሊሰጥ ቢችልምና መስፈርትነቱን አጠያያቂ ቢያደርገውም /Beals & Harry 1958:236/ ቁሱ በመጀመሪያ ጊዜ የተሰራበትን ምክንያት /intended use/ በመውሰድ ክፍፍሉ ሊሠራበት ይችላል። ይህም ዘዴ /Functionalist Approach/ ይባላል።

ሦስተኛው መስፈርት **«መሠሪያ ንጥረ ቁስ»** ሲሆን ተጠኚ ቁሶች ከምን እንደተሠሩ በማወቅ በምድብ በምድብ ለማስቀመጥ ይረዳል። መስፈርቱን እንደ አንድ አማራጭ መገልገል ቢቻልም፤ አንድ ቁስ ከአንድ በላይ ከሆኑ ንጥረ ቁሶች ተሠርቶ ሲገኝ እክል ሊገጥመን እንደሚችል ሊታወቅ ይገባል (Prown, 1982:2)።

አራተኛው መስፈርት **«ዘመን»** ሲሆን ቁሶቹ የተሰሩበትን ወይም አገልግሎት ላይ የዋሉበትን ወቅት መሠረት በማድረግ «የዚህ ዘመን» ፤ «የዚያኛው ዘመን!» እያሉ መከፋፈልን ይመለከታል። ይሁን እንጂ የቁሶቹን ዘመን በዕርግጠኝነት ማወቅ ካልተቻለ በምድብ በምድብ የማስቀመጡን ሥራ ከችግር ያልፀዳ ያደርገዋል።

ሌላኛው መስፈርት **«ባለሙያው»** ሲሆን የአንዱን ባለሙያ የእጅ ሥራዎች በአንድ የሌላኛውን ደግሞ በሌላ ከፋፍሎ ማስቀመጥን ይመለከታል። ለአብነት፤ የአንጥረኛውን በአንድ፤ የሸማኔውን በሌላ፤ የሸክላ ሠራተኛውን ደግሞ ለብቻ። ይህ መስፈርት ምናልባት በእያንዳንዱ ምድብ ሥር የሚካተቱትን ቁሶች በቁጥር ካላበራከተ በስተቀር በየምድቡ መካከል ግልጽ የሆነ ልዩነትን ይፈጥራል።

Ames፤ በመጨረሻ የጠቀሰው መስፈርት **«ሥልት»** ሲሆን Prown «የአሠራር ጥበብ» ካለው (1982:2) ጋር ተመሳሳይ ነው። ቁሶቹ የሚሠሩበትን ሥልት/ጥበብ ከግምት ማስገባትንም ይመለከታል።

ከፍ ሲል የተዘረዘሩት ነጥቦች በቁሳዊ ባህል ጥናት ቁሶችን በምድብ በምድብ ከፋፍሎ የጥናቱን ሂደት ቀና ለማድረግ የሚያገለግሉ መስፈርቶች ሲሆኑ (እነዚህ ብቻ ናቸው ለማለት አልደፍርም) የየራሳቸው ጠንካራና ደካማ ጎን እንዳላቸው ለመጠቆም ተሞክሯል። በመሆኑም፤ እያንዳንዳቸውን በተናጠል መጠቀሙ ክፍፍሉን ሰንካላ እንዳያደርገው ከአንድ

በላይ መስፈርቶችን ግምት ውስጥ ማስገባቱ ይመከራል። ይህንንም አስመልክቶ Ames "more subtle models may incorporate several of these factors" (1978:20) ሲል አስርግጦ ይናገራል።

2.2.5. ቁሳዊ ባህልን የመተንተኛ ሞዴሎች /አንጻሮች/

ማንኛውም የጥናት መስክ መረጃዎቹን የሚተነትንባቸው የራሱ የሆኑ ሞዴሎች ወይም አንጻሮች አሉት። እነርሱንም በውል መገንዘቡና በተገቢው መንገድ መገልገሉ የጥናቱን ውጤታማነት እውን ያደርገዋል።

በቁሳዊ ባህል ጥናት በዋነኛ መረጃነት የሚወሰዱት ቁሶች /Prown, 1982:1/ ከምን ከምን አንጻሮች መጤን እንዳለባቸው ሲመክር፣ Schlereth[28] (ውስተ ኢንተርኔት)፣ የሚከተሉትን ዘጠኝ[29] ሞዴሎች ቀርፆ አስቀምጧል[30]። በትንታኔው ሂደት ጊዜም አንድና ከአንድ በላይ ሞዴሎችን መጠቀም እንደሚቻል አያይዞ ገልጿል።

ጥበብን አመላካችነት:- ይህ ሞዴል አንዳች ጥበባዊ/መስህባዊ ባህርይን ከተጠኚ ቁሶቹ የሚሻ ሲሆን ያ ባህርይ በገለፃ ጎልቶ መውጣት እንዳለበት ያምናል።

ተምሳሌታዊነት:- ቁሶች ከዘወትራዊ አገልግሎታቸው ባሻገር ለአንድ ነገር ውክልና የመቆም (የመመሰል) ችሎታ አላቸው። ለአብነት፣ ሥልጣንን፣ የሃብት ደረጃን፣ ሃይማኖታዊ ይዘትን፣ ወ.ዘ.ተ. ሊያመላክቱ ይችላሉ። ይህም ሞዴል ቁሶችን በተምሳሌታዊነት ለመፈተሽ የተቀረፀ እንደሆነ ልብ ይሏል።

ባህላዊነት:- ይህ ሞዴል፣ ተጠኚ ቁሶቹ፣ የአንድን የተወሰነ ቡድን፣ ብሄር፣ ክልል ወ.ዘ.ተ. ባህል ያመላክታሉን? ብለን እንድንጠይቅና እንድንመረመር የሚያደርግ ነው።

አገልግሎት ሠጭነት:- ይህ ሞዴል፣ ተጠኚ ቁሶቹ ምን ጥቅም አላቸው?፣ እንዴትስ አገልግሎት ላይ ይውላሉ?፣ ዛሬስ አገልግሎት ይሠጣሉ? ከሰጡ፣ መጀመሪያ ሲሰሩ ለታቀደላቸው ተግባር ነው ወይስ በተለየ መልኩ?፣ ካልሰጡስ ለምን? የሚሉትን ጥያቄዎች እንድንጠይቅ ይጋብዘናል።

መዋቅራዊነት:- ይህ ሞዴል፣ ቁሱ ከምን ተሠራ? እንዴት ተሠራ? በሚሠራበት ጊዜስ የትኞቹ መሣሪያዎች አልግሎት ላይ ዋሉ? ለሚሉት ጥያቄዎች አጥኚው ትኩረት እንዲሰጣቸው ያስገነዝባል።

---

[28] Schlereth, J. Thomas "Understanding the Nine Models of Material Culture Interpretation." Online. Available at – URL: http://www.btnep.org

[29] Schlereth «ዘጠኝ» ብሎ የዘረዘራቸውን ሞዴሎች Fleming (ውስተ Internet) መጠነኛ የሥያሜ ለውጥን በማድረግ ቁጥራቸውን ቀንሶ ወደ አምስት አውርዷቸዋል። እነሱም፡- History, material, construction, design እና function ናቸው URL:http:// www. individual. utoronto.ca/aron_mohr/artfleming.html

[30] ሞዴሎቹን ያስቀመጥኩበት ቅደም ተከተል የፀሃፊውን መሠረት አድርጌ ነው።

አካባቢያዊነት፡- የአንድ አካባቢ መልክዐምድር፣ የአየር ንብረት እንዲሁም የተፈጥሮ ሃብት በቱሱ ላይ የሚያሳድረው አምንታዊም ሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ አለ ወይ? ብለን እንድንጠይቅ የሚጋብዝ ነው። ለአብነት በርሃማ በሆነ አካባቢ ብዙ የእንጨት ቱሶችን ማግኘ ቱ አጠያያቂ ነው።

ባህርይ አመላካችነት፡- ቱሱ ባለበት አካባቢ መኖሩ ወይም አገልግሎት መስጠቱ በማኅበረሰቡ ዘንድ ላይ ያሳደረው ተዕዕኖ አለ ወይ? ወይም ባህርያቸውን በሆነ መልኩ ቀይሯል ወይ? ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ እንድናፈላልግ የሚያደርግ ሞዴል እንደሆነ ልብ ይሏል።

ማሕበራዊነት፡- ይህ ሞዴል፣ በቱሶችና በማኅበረሰቡ መካከል ያለውን መስተጋብር መሠረት አድርገን፣ ቱሶች በማኅበረሰቡ ዘንድ ያላቸውን ሚና አንጥረን እንድናወጣ፤ አንድም፣ ማህበረሰቡ ለአንድ ናሙና ቱስ ያለው አተያይ ተመሳሳይ መሆን / አለመሆኑን እንድናረጋግጥ የሚያነሳሳ ሞዴል ነው።

ማሕበረሰብ ጠቃሽነት፡- ይህ ሞዴል ቱሶቹ በማን ተሠሩ? ንብረትነታቸው ለማን ነው? ከየትኛው ማኅበረሰብ ወይም የማኅበረሰብ ክፍል ፈለቱ? እንዲሁም ከየትኛው ዘመን ማኅበረሰብ? ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ ለማፈላለግ ይረዳል።

2.2.6 ቱሳዊ ባሕልን የመተንተኛ ሂደቶች

በ2.2.5 ቱሳዊ ባህልን ለመተንተን አጋዥ የምናደርጋቸው የተለያዩ ሞዴሎች ቀርበዋል። ተያይዞ እንደተገለፀውም አንዱን ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ሞዴሎችን መርጦ መገልገል ይቻላል። ሞዴሎችን በአጋዥነት መጠቀሙ እንደተጠበቀ ሆኖ በትንታኔያችን ልንከተላቸው የሚገቡ ሂደቶች እንዳሉ ልብ ይሏል።

እንደ Prown እምነት፣ ቱስን መሠረት ያደረገ ትንታኔ በሦስት ሂደቶች ማለፍ አለበት (1982: 7)። እነርሱም፣ «ገለፃ» [Description]፣ «ትርጓሜ» [Deduction] እና «ጥቆማ» [Speculation] ሲሆኑ፤ በእያንዳንዳቸው ሂደቶች ምን ምን ነገሮችን መከወን እንደሚገባን ሲመክር Prown (ገጽ፣ 7-10) የሚከተሉትን ማስታወሻዎች አስፍሯል።

2.2.6.1 ገለፃ

ገለፃ፣ በትንታኔያችን ወቅት የምናስቀድመው ተግባር ሲሆን ናሙና ቱሱን እኛ እንዳየነው አድርገን ያላዩ ሰዎች በአዕምሯቸው እንዲስሉት ማድረግን ይመለከታል። ይህንንም ስናደርግ፣ የቱሱን ቅርፅ፣ የተሠራበትን ንጥረ ቱስ፣ ክብደቱን፣ ርዝመቱን፣ መልኩን (የቀለሙን ዓይነትና መስህባዊ ንድፎቹን)፣ ወ.ዘ.ተ. በአጠቃላይ በዓይን ሊታዩ የሚችሉትን ነገሮች ማካተት ይኖርብናል።

2.2.6.2 ትርጓሜ

ይህ በትንታኔያችን ሂደት የምንፈፅመው ሁለተኛው ተግባር ሲሆን መሉ በመሉ ናመና ቁሱ ላይ የነበረው ትኩረታችን ተከፍሎ በቁሱና በባለቤት ማሕበረሰቡ መካከል ያለን መስተጋብር /interaction/ የምናጤንበት ወዲያውም አንዳች ትርጓሜ የምንሰጥበት ሂደት ነው።

ትርጓሜው፣ በቀዳሚው ተግባራችን (በገለላው) ያካተትናቸውን ነጥቦች መነሻ ሊያደርግ ይችላል። ለአብነት፣ ናመና ቁሱ የተገለፀውን ቅርፅ፣ ክብደት፣ መልክ፣... ለምን እንደያዘ የቁሱን ፈጣሪ እና/ወይም ተጠቃሚ በመጠየቅ። ከዚህም ባሻገር፣ ቁሱ አንዳች ውክልና ወይም የተለየ ዋጋ ካለው ውክልናው ምን እንደሆነ፤ የላቀ ዋጋ ባለቤትም በምን ምክንያት እንደሆነ በመመራመር የትርጓሜው ሥራ ሊሠራ ይችላል።

2.2.6.3 ጥቆማ

«ጥቆማ» አጥኚው፣ የገለላና የትርጓሜ ተግባሩን ከጨረሰ በኋላ የሚከተለው የትንታኔ ሂደት ሲሆን በቀዳሚዎቹ ሁለት ተግባራት የተገኙትን መረጃዎች በአዕምሮው በመያዝ ይከውነዋል። በመሆኑም፣ አጥኚው መሉ በመሉ ከቁሱ ተለይቶ የሚሠራው ሥራ ነው ሊባል ይችላል። በዚህ ሂደት አጥኚው ሁለት ዓበይት ነገሮችን ይሠራል።እንደኛው፣ በጥናቱ ያገኛቸውን መረጃዎች ከቀደምት ትውሮች ጋር ማጣቀስ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ (የግድ ባይሆንም) መረጃዎቹን ተጠቅሞ አዳዲስ ትውሮችን መቀመር ነው።

2.2.7 ቁሳዊ ባህሎች እንዴት ይሰበሰባሉ? እንዴትስ ይሰነዳሉ?

የቁሳዊ ባሕል ጥናት ዋነኛ ዓላማ ቁሳዊ ባሕልን የተመለከቱ መረጃዎችን፣ አቅሙ ሲፈቅድም ቁሶችን በተለያዩ ዘዴዎች መሠብሰብና መሰነድ ነው። ለመሆኑ አንድ ግለሰብ/ተቋም ቁሶችን ለመሰብሰብና ለመሰነድ ቢያቅድ ምን ምን ተግባራትን መከወን ይኖርበታል? ይህ ክፍል ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት የቀረብ ሲሆን Somjee (1993:106-112) የቁሳዊ ባሕል መረጃዎችን በመሰብሰቡና በመሰነዱ ሂደት መተግበር አለባቸው ሲል በዝርዝር ያስቀመጣቸው ነጥቦች ይዳሰሳሉ።

ተግባር አንድ፡- የቁሶቹ ባለቤት ማኅበረሰብ የሚከውናቸውን የተለያዩ ተግባራት ለይቶ ማወቅ። ለአብነት፣ ክብት ማርባት፣ እርሻ ማረስ፣ ዓሣ ማስገር፣ የሽክላ ውጤቶችን መሥራት፣ ወ.ዘ.ተ. ባለጉዳዩ ይህንን ተግባር መፈፀሙ ተጠኚ ማኅበረሰቡ የሚከውናቸውን ተግባራት በየትኞቹ ቁሶች ታግዞ እንደሚሠራ እንዲለይ ያስችለዋል።

ተግባር ሁለት፡- በ«ተግባር አንድ» ላይ ተለይተው የታወቁትን የተለያዩ ቁሶች ስም መዘርዘር፣ ወዲያውም፣ የቁሶችን ምስል በንድፍ እና/ወይም በፎቶ ግራፍ ማስደገፍ። ከዚህም በተጨማሪ፣ መረጃዎችን በምድብ በምድብ የማስቀመጡ ሥራ

ይሠራል። ለአብነት« ለዓሣ ማስገሪያነት የሚያገለግሉትን ቁሶች በአንድ ምድብ፣ ለሸክላ ሥራ የሚውሉትን ደግሞ በሌላ።

ተግባር ሦስት፦ ከዚህ ደረጃ ላይ የደረሰ ሰብሳቢ በአካባቢው ምን ምን ቁሶች እንዳሉ ለይቶ ያውቃልና የሚሠራው ሥራ ቢኖር ቁሶችን ገዝቶ ለመሰብሰብ ዕቅድ ማውጣት ነው። ዕቅዱ በሚከተለው ናሙና ቅጽ መሠረት ሊሠራ ይችላል።

ናሙና የመሰብሰቢያ ቅጽ
[Sample Collection Plan]

የቦታው ሥም _____
ቀን ከ _____ እስከ _____

የቁሱ ምድብ	ብዛት (በዓይነት)	ብዛት (በቁጥር)	ድምር	ዋጋ (በግምት)
- _____ - _____	_____ _____	_____ _____	_____ _____	_____ _____
			ድምር	

Somjee (1993:107) ባቀረበው ቅጽ መነሻነት የተዘጋጀ

ተግባር አራት፦ በዚህ ደረጃ፣ ሰብሳቢው ባዘጋጀው የመሰብሰቢያ ቅጽ ተመሥርቶ የመጀመሪያ ዙር የመሰብሰብ ሥራውን ይከውናል። በዚህም ጊዜ ናሙና የሚሆኑ ቁሶችን (በዕቅዱ ከያዘው ከ10% - 20% ያህሉን) ይገዛል።

ተግባር አምስት፦ ይህ ደረጃ የመሰብሰቡ ሥራ የሚጠናቀቅበት ሲሆን ሰብሳቢው በተግባር አራት ባገኘው ተሞክሮ ተመርኩዞ ዋናውን የመሰብሰብ ሥራ ይከውንበታል። ይህንንም ሲያደርግ የመስክ ላይ የመሰነጃ ቅጽን [Field Documentation sheet] በመሙላት ይሆናል። ቅጹ፣ የሚከተለውን ቅርጽ የሚይዝ ሲሆን እንዳስፈላጊነታቸው የሚጨመሩ / የሚቀነሱ ነጥቦች ሊኖሩ እንደሚችሉ ልብ ይሏል።

ናሙና የመስክ ላይ የመሰነጃ ቅጽ
[Sample Field Documentation Sheet]

የግለሰቡ / የተቋሙ ሥም:- _____
ቀን _____

ሀ. የቁሱ ዓይነት:- 1. _____ የባለቤት ብሄረሰቡ ሥም:- _____ የሰብሳቢው ሥም:- _____
2. _____ ወረዳ:- _____
3. _____ ቀበሌ: _____
ጎጥ:- _____

ለ. የቁሱ አገልግሎት:- 1. _____ የተገልጋዩ ማንነት ስም:- _____
2. _____ ዕድሜ:- _____
3. _____ ዕድሜ:- _____
ቁሱ አገልግሎት የሚሰጥበት ጊዜ:- _____

ሐ. ቁሱ የሚሰራባቸው ንጥረ ቁሶች ዝርዝር:-1. _____
2. _____
3. _____

መ. የባለመብያው ማንነት:- ስም _____ - ባለመብያው ቁሱን የሚሰራበት ምክንያት:- _____
ዕድሜ _____ - የገበያው ሁኔታ: ዋጋ (ሲረክስ): _____
የመኖሪያ አካባቢ _____ ዋጋ (ሲወደድ): _____
ዋጋ (መደበኛው):- _____

ሠ. የቁሱ የአሠራር ሂደት በደረጃ:- በመጀመሪያ ደረጃ ምን? _____
በሁለተኛ ደረጃ ምን? _____
በሦስተኛ ደረጃ ምን? _____

Somjee (1993፣110) ባቀረበው ቅጽ መነሻነት የተዘጋጀ

ከላይ በተመለከተው ቅጽ ውስጥ የሚሞሉት አስፈላጊ መረጃዎች ሰብሳቢው ከተጠኚ ማኅበረሰቡ ጋር በሚያደርገው የቃል መጠይቅና በመስክ ቆይታው በሚያደርገው ምልከታ የሚሞሉ ናቸው::

ቁሶችን በመሰብሰቡና በመሠነዱ የሥራ ሂደት ከዚህ በመቀጠል የሚተገበረው ቁሶችን ለገዙ የማሰናዳቱ ሥራ ነው (Somjee, 1993:109):: ይህም ተግባር የሰብሳቢውን ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚሻ ሲሆን ለተሰባሪና ለማይሰበሩ፣ እንዲሁም ለትንንሽና ለትልልቅ ዕቃዎች ተገቢ ቦታቸውን የማስያዙን ሥራ ይመለከታል::

ከላይ በተጠቀሱት የሥራ ሂደቶች በመመራት መስክ ድረስ ሄዶ ቁሶችን የሰበሰበና ወደሚፈለገው ቦታ ያደረሰ ግለሰብ /ተቋም የሚቀረው ሥራ ቢኖር የመሠነዱ ሥራ ነው:: በእርግጥ የመሠነዱን ሥራ ከመስክ የጀመረው ቢሆንም::

በስነዳው ወቅት፣ የቃል መረጃዎች በካሴት፣ የሚታዩ መረጃዎች በንድፍ፣ በካርታ፣ በፎቶግራፍ፣ (ሲቻልም) በቪዲዮ፣ የጽሑፍ መረጃዎች ደግሞ በበራሪ ጽሑፍ፣ በመጣጥፍ፣ በምርምራዊ ዘገባና በመጽሐፍ መልክ ሊሰነዱ ይችላሉ:: ከዚህ ባሻገር፣ ዋነኞቹ መረጃዎች (ቁሶቹ) ደግሞ የ«መለያ ካርድ» እና «ጠቋሚ ቁጥር» (ስለምንነታቸው ከታች የቀረቡትን ገለጻዎች ይመለከቷል) እየተዘጋጀላቸው ይሠነዳሉ::

የመለያ ካርዱ «Resource Reference Catalogue» የሚል መጠሪያ ሲኖረው የሚከተሉትን ነጥቦች በውስጡ ያካትታል::

ጠቋሚ ቁጥር _____

የፎቶ ግራፍ ቁጥር_____ / የንድፍ ቁጥር_____ / የካርታ ቁጥር_____

የፋይል ቁጥር _____

የካሴት ቁጥር _____

የቁሱ ባለቤት ግለሰብ /ተቋም ስም_____

Somjee (1993:111)

በስነዳው ወቅት ለእያንዳንዱ ቁስ የሚዘጋጀው «ጠቋሚ ቁጥር» /Accession Number/ የሚከተሉትን አራት መሠረታዊ ነጥቦች ይይዛል /Somjee, 1993:111-112)።

- ቁሱ የተገኘበት አካባቢ / ወረዳ፣ ቀበሌ፣ ጎጥ፣ _____
- የቁሱ ባለቤት ብሄረሰብ ሥም፣ _____
- የቁሱ ምድብ፣ _____
- የተሰነደበት ዘመን፣ _____

ለአብነት፣ የዚህ ጥናት አቅራቢ፣ «**መ.አ.ገ.1999**» የሚል «ጠቋሚ ቁጥር» ለአንድ ቁስ ቢያዘጋጅ፣

መ - መዲና	[በአርጎባ ልዩ ወረዳ ሥር ያለችንና ቁሱ የተገኘባትን ጎጥ ሥም ያመለክታል]
አ - አርጎባ	[የቁሱን ባለቤት ብሄረሰብ ሥም ያመለክታል]
ጌ - ጌጣጌጥ	[ቁሱ ከአገልግሎቱ አንፃር የተሰጠውን ምድብ ያመለክታል]
1999 - ዘመን	[ቁሱ በቅርስነት የተሰነደበትን ዘመን ያመለክታል]

በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር ለማመልከት እንደተሞከረው፣ አንድ ግለሰብ /ተቋም በተዘረዘሩት አምስቱ ተግባራት ተመርቶ ቁሶችን ከተለያዩ ቦታዎች ሊያስባስብ ይችላል። ኋላም፣ ለእያንዳንዱ ቁስ የመለያ ካርድና ጠቋሚ ቁጥሮችን እያዘጋጀ የስነዳውን ሥራ ሊያከናውን ይችላል። ይህንንም ማድረጉ፣ በዋነኛነት፣ በተለያዩ አጋጣሚዎች አማካይነት የሚጠፉ ቁሶችን እንዲታደግ ያስችለዋል፤ ወዲያውም፣ ቁሶች በተመልካችና በአጥኚዎች ዕይታ ውስጥ እንዲገቡ ያስችላቸዋል።

3. የተጠኚ አካባቢውና የነዋሪ ብዜረሰቡ ዳራዊ መግለጫ

በዚህ ምዕራፍ፣ ሁለት ርዕሰ ጉዳዮች ትኩረት ተሰጥቷቸው ተዳስሰዋል። እነዚህም፣ የተጠኚ አካባቢውና የነዋሪ ብዜረሰቡ ዳራዊ መግለጫዎች ናቸው።

3.1. የተጠኚ አካባቢው ዳራዊ መግለጫ

የአማራ ክልል በኢትዮጵያ ከሚገኙት ዘጠኝ ክልሎች አንዱ ሲሆን በሰሜንና በመካከለኛው የሃገሪቱ ክፍል ተዘርግቶ ይገኛል። ክልሉ፣ በሰሜን ከትግራይ፣ በደቡብ ከኦሮሚያ፣ በምሥራቅ ከአፋር፣ እንዲሁም በምዕራብ ከቤኒሻንጉል ክልልና ከሱዳን ጋር ይዋሰናል። እንደ 2006 (1987 ዓ.ም.)ቱ የማዕካለዊ ስታቲስቲክ ዘገባ የክልሉ ሕዝብ ብዛት 19,120,005 ነበር (CSA፡ 2006)።

የዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆነው አካባቢ መገኛው ከላይ በተጠቀሰው ክልል ውስጥ ሲሆን በክልሉ ከሚገኙት በርካታ ዞኖች መካከል ደቡብ ወሎ ዞንን መሰረት ያደረገ ነው። ይህ ዞን ካካተታቸው ወረዳዎችም ጊዜያዊ መቀመጫውን «ሃርቡ» ከተማ ላይ ያደረገውን የአርጎባ ብዜረሰብ ልዩ ወረዳ ዋነኛ ትኩረቱ አድርጓል።

የአርጎባ ልዩ ወረዳ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት በመጋቢት 1998 ዓ.ም. በተደረገው ሦስተኛ መደበኛ ጉባዔ በተላለፈ አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 130/1998) መሠረት ልዩ ወረዳ ሆኖ የተቋቋመ ሲሆንኔ በዕሁፍ መጠይቁ ያገኘሁት መረጃ እንደሚያመለክተው ወረዳው፣ ከደቡብ ወሎ ዞን አምስት ቀበሌዎችን (ማለትም፣ ፈጠቆማ-01፣ አሬራ ነችሮ-02፣ ጮምዬ-03፣ አሞዬ ሠርጡ-04 እና ኪልኪሶ-05) ከኦሮሚያ ልዩ ዞን ደግሞ ሁለት ቀበሌዎችን (አሠኔ አገር-06 እና ጎበራ-07) በድምሩ ሰባት ቀበሌዎችን አቅፎ ተመስርቷል።

ልዩ ወረዳው፣ በሰሜንና በምዕራብ፣ ከደቡብ ወሎ ዞን ቃሉ ወረዳ ጋርኔ በደቡብ፣ ከኦሮሚያ ልዩ ዞን ዳዋ ጨፋ ወረዳ ጋርኔ እንዲሁም በምሥራቅ ደግሞ ከአፋሩ ተላላክና ከኦሮሚያው ባቲ ወረዳ ጋር ይዋሠናል።

ከወረዳው ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት የተገኘው መረጃም[31] እንደሚያመለክተው፣ የወረዳው አጠቃላይ የቆዳ ስፋት 6265 ሄክታር ሲሆን 36809 ነዋሪዎችም ሰፍረውበት እንደሚገኙ ይኸው መረጃ አያይዞ ይገልጻል።

3.2. የአርጎባ ብዜረሰብ ዳራዊ መግለጫ

በዚህ ክፍል፣ ከላይ ስለመኖሪያ አካባቢው አጠቃላይ ዳራዊ መግለጫ የቀረበለትና የዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆነው ብዜረሰብ ከየት እንደመጣ፣ የት የት እንደሠፈረ፣ ምን ምን ዓይነት ባህላዊ፣ ማህበራዊና ሃይማኖታዊ መገለጫዎች እንዳሉት በአጭሩ ተመልክቷል።

---

[31] መረጃው፣ «በአ/ብ/ል/ወረዳ ያለ ሕዝብ ብዛትና የአርሻ መሬት መጠን መግለጫ» በሚል ርዕስ በግርጌ ተጽፎና በጽ/ቤት ኃላፊው ቢሮ ተለጥፎ የተገኘ ሥዕላዊ መግለጫ ነው።

3.2.1. ጥንተ አመጣጥና አሠፋፈር

በዚህ ጽሑፍ የመጀመሪያ ምዕራፍ «የጥናቱ ዳራ» ላይ፣ የአርጎባ ብሄረሰብ በኢትዮጵያ ከሚገኙት በርካታ ብሄረሰቦች አንዱ እንደሆነ ተገልጿል። Weeks (1984: 50-51) የተሠኘው ተመራማሪ የብሄረሰቡን ጥንተ አመጣጥ አስመልክቶ የሠነዘረውንም ሃሳብ እውነታነት (ተቀባይነት) በመስክ ቆይታዬ ከታሪክ አዋቂ የብሄረሰቡ ተወላጆች ጋር ካደረኳቸው ሁለት የተለያዩ ውይይቶች በአንደኛው አረጋግጫለሁ።

በአንደኛው ውይይት (ውይይት-1) የተሳተፉት ቃል አቀባዮቼ፣ ሸህ አብዱራህማን መሐመድ፣ ሸህ መሐመድ አህመድ፣ አቶ መሐመድ አሊ፣ አቶ ከማል ሲራጅና አቶ የሱፍ መሐመድ (ሚያዚያ 30/1999፤አሞዬ ሠርጤ) እንደተረኩልኝ፣ የአርጎባን ብሄረሰብ የዘር ግንድ ወደኋላ ተመልሰን ስንመረምር ከአረብ ጎሣ ሃረግ የሚመዝ ሆኖ እናገኘዋለን። ለዚህም፣ የውይይቱ ተሳታፊዎች በማረጋገጫነት ያቀረቡት በ7ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አካባቢ በነቢዩ መሐመድ ትዕዛዝ የተወሰኑ የአረብ ዘሮች ከመካ ተነስተው ወደ ኢትዮጵያ የመጡበትን ታሪካዊ እና/ወይም ሃይማኖታዊ ክስተት ነው። ዘመኑንም አስመልክተው በሁለተኛው ውይይት (ውይይት-2) የተሳተፉት አዛውንት፣ ሸህ መሐመድ አሚን፣ ሳኒያ አረባና ሸህ አህመድ ሁሴን፣ «የጌታው ዘመን!» እንደሚባል ገልፀውልኛል (ሚያዚያ 29/1999፤አሞዬ ሠርጤ)። «ጌታው» የተባሉትም ነቢዩ መሐመድ እንደሆኑ አያይዘው ጠቁመውኛል።

የብሄረሰቡን ጥንተ አመጣጥ አስመልክተው ተወያዮቼ ተመሳሳይ ሃሳብ ቢኖራቸውም ወደ ኢትዮጵያ የገቡበትን በር በተመለከተ ግን ሁለት ዓይነት ሀሳቦችን አቅርበውልኛል።

እንደ ሸህ መሐመድ አሚንና ሌሎች (ውይይት-2) ገለፃ፣ የአርጎባ ብሄረሰብ መነሻው ከአረብ ሲሆን ወደ ኢትዮጵያ የገባውም በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል ነው። ይህንንም ሲያስረዱ የሚከተለውን ብለዋል።

> *... አንግዲህ ቲነሱ ተመካ ነው፤ ተመካ መዲና፤ ሃበሻ ላይ የገቡትም 'ዛመልካይ' ነዎት (ናቸው)። ዘራቸውም፣ የአቂል ዘር፣ የቁሬሽ ዘር፣ የሃሽም ዘር ይባላል። ቲገቡ፣ ቲመጡ ደሞ በሃወዝ ነው ይባላል። በሃወዝ ነው የገባነው፤ ሃወዝ፣ በትግሬ፣ በምጥዋ ውስጥ። የመጡትም ሃበሻን ሊያቀኑ ነው። በመጀመሪያ ያቀኑትም ጎዚን፣ ሾንኬንና አሞዬ ሠርጤን ነው (ሸህ መሐመድ አሚንና ሌሎች፣ ሚያዚያ 29/1999፤ አሞዬ ሠርጤ)።*

ከሸህ መሐመድ አሚንና ሌሎች ንግግር ሦስት መሠረታዊ ነጥቦች ትኩረት እንደሚሹ ልብ ይሏል። የመጀመሪያው፣ የአርጎባ ብሄረሰብ መነሻ «መካ መዲና» መሆኑ ነው። ሁለተኛው ነጥብ ደግሞ ከመካ የተነሱት የአቂል፣ የቁሬሽ፣የሃሽም ዘሮች ወደ ኢትዮጵያ የገቡበት በር በትግራይ በኩል በምዕዋ/ በሃወዝ እንደሆነ ነው። ሌላኛው ነጥብ ደግሞ ሃበሻን ሊያቀኑ የመጡት የተጠቀሱት ዘሮች በቀዳሚነት ካቀኗቸው የኢትዮጵያ ቦታዎች መካከል ቃል አቀባዮቼ የሚኖሩበት አካባቢ፣ አሞዬ ሠርጤ፣ አንዱ መሆኑ ነው።

ሸህ አብዱራህማን መሐመድና ሌሎች (ውይይት-1) ብሄረሰቡ ወደ ኢትዮጵያ የገባበትን አቅጣጫ አስመልክተው ከላይ ከተጠቀሰው የተለየ ሃሳብ የሠነዘሩልኝ ሲሆን፣ አቅጣጫውንም

ለመጠቆም በዚያን ወቅት መጡ ከተባሉት ሰዎች የተወሰኑትን ስምና የዘር ሃረግ የንግግራቸው መነሻ በማድረግ እንደሚከተለው አስረድተውኛል።

> ... ዋናው ተዚያ ተማደ (ከመካ) የመጡት ሰይድ አባድር ይባላሉ። አባዚድ የሚባል ልጅ አለዎት (አሳቸው)። የእኒህ የአባዚድ ልጅ ደሞ አብሳን ይባላሉ፤ የአብሳን ልጅ ደሞ ፊቱ አብሳን ይባላሉ። ፊቱ አብሳን ደሞ ማንን ይወልዳሉ፣ አሊ ሻፊቅን፤ አሊ ሻፊቅ ደሞ አንሷር አሊን፣ ሷዲቅ አሊን የሚባሉ ይወልዳሉ፤ ... እኒህ የኛ የጥንት አያቶች ናቸው። የአቂል ዘር ናቸው። ... እነዚህ አንግዲህ ተአረብ፣ ተመካ ቲነሱ አፈር ቆንጥረው መጡ፤ ቲመጡ ተመጡ..... ሐረር ደረሱና ተሐረር አፈር ጋር ቲመዝኑት አንድ ሆኗ ተዚያ ደሞ ቲመጡ ቲመጡ ... ተዚህ ተላይ በኩል (በጣታቸው እየጠቆሙ) የሀላችን የእርሻ መሬት አለይ፣ እዛች ቲደርሱ አፈሩን ቲመዝኑ ደሞ አኩል ሆኗ አፈሩ አኩል የሆነ ጊዜ 'ማን እንበለው አንግዲህ ይሽን አገር?' አሉ፣ 'አረፈ ልባችን' አለ፤ አሁን 'አረፍ ልቤ' ነው ስሚ ያቺ (በጣታቸው እየጠቆሙ) ጎጥ (ሸህ አብዱራህማን መሐመድና ሌሎች፤ ሚያዚያ 30/1999፤ አሞቤ ሠርጤ)።

ከፍ ሲል (ከሁለቱ ውይይቶች ተውጣጥተው) በተጠቀሱት ንግግሮች መካከል ተመሳስሎ እንዳለ ልብ ይሏል። የመጀመሪያው፣ የአርጎባዎች ዘር መነሻው (ምንጨ) ከአረብ (ከመካ መዲና) እንደሆነ የሚገልጸው ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ፣ ከአረብ የመጡት ዘሮች «የአቂል ዘሮች» እንደሆኑ የተነገረው ነው። ከዚህ ባሻገር ግን፣ በሁለቱ ጥቅሶች መካከል አንድ መሰረታዊ ልዩነት እንዳለ አሌ የማይባል ጉዳይ ነው። ይኸውም፣ የተጠቀሱት የአቂል ዘሮች ወደ ኢትዮጵያ ገቡበት የተባለው በር ነው። አንደኛው ሃሳብ በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል፣ በትግራይ (በሃወዝ፣ በምጽዋ) እንደገቡ ሲያጣቅስ፤ሌላኛው ደግሞ በሐረር እንደገቡ የሚያመለክተው ነው[32]። የዚህ ጥናት አቅራቢም የብሄረሰቡን ጥንተ አመጣጥ አስመልክቶ ታሪክ ያውቃሉ ከተባሉት የብሄረሰቡ ተወላጆች ያገኘውን መረጃ በመረጃነቱ ማቅረብን (መሠነድን) ጉዳዬ ብሏልና እስከዚህ ድረስ መጓዝ ችሏል። ይህንንም ያደረገበት፣ Emerson, et.al. "the task of the ethnographer is not to determine 'the truth' but to reveal the multiple truths apparent in others' lives" (1995:3) ሲል ያቀነቀነውን ሀሳብ መነሻ አድርጎ ነው።

ይህንን ርዕሰ ጉዳይ ከመቋጨቱ በፊት የብሄረሰቡን አሠረጫጨት በተመለከተ ከፍ ሲል የተጠቀሱት ተወያዮቹ ያቀረቡትን መረጃ ለመጥቀስ እወዳለሁ።

እንደ ሸህ መሐመድ አሚንና ሌሎች (ውይይት-2) እምነት የአርጎባ ብሄረሰብ ከአረብ ሀገር፣ ከመካ፣ መነሻውን አድርጎ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ከገባ በኋላ በሃገሪቱ የተለያዩ ቦታዎች የተሠራጨ ሲሆን ለመሰራጨቱ ዋነኛ ምክንያት ነው ያሉትን ነጥብ አያይዘው እንደሚከተለው አብራርተውልኛል።

---

[32] ከዚህ ላይ ሳልጠቅሰው የማላልፈው ነጥብ ቢኖር፣ በእንደኛው ውይይት ከተሳተፉት አንዱ (አቶ መሐመድ አሊ) አርጎባዎች ሁለት ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ እንደመጡ የጠቆሙኝ ሲሆን በመጀመሪያ በሰሜን ኋላም በምስራቅ የሀገሪቱ ክፉል እንደገቡ አያይዘው ገልፀውልኛል።

... አንደኛውን አገር አንግዲህ ዝዜን አትንተው ቲቀመጡ፣ ተዛም አልበዙም፣ እዝህ ወደ ለም አገር፣ ለም ወደሆነው፣ ምላሌ፣ ሠፈራ ምናምን እኮ መንግስቱ እየሰደደ ነው። በጊዜው፣ የመንግስት ሹም ለም ወዳለበት አልሙ፣ ጠፍ ወዳለበት አልሙ እያለ ይወስዳል... አይደለም!? አሳቸውም (የመጀመሪያዎቹ ሠፋሪዎች) በጊዜያቸው 'እስቲ ወደተሸለ አገር' እያሉ እያማረጡ ቲመጡ ሾንኬ ላይ፣ ደሞ ተዛ መተው እዚህ አረፉ፤ ግማሾቹ ተዛው ናቸው። አሁን እኮ የኛ ዘር ይፉት ድረስ ነው፣ ... የኛ ዘር፣ የአርጎባ ዘር የሚባለው እስተ ሐረር ጠቅላላ የኛ ዘር ነው፤ እዛ ተርፈው የኛ አያቶቻችን ደሞ መተው ... 'እስቲ አገር እንሰልል' ብለው ይቺን (በጣታቸው እየጠቆሙ) መንጥረው ነው የገቡባት (ሸህ መሐመድ አሚንና ሌሎች፤ ሚያዚያ 29/1999ኛ አሞዬ ሠርጤ)።

ሸህ አብዱራህማን መሐመድና ሌሎች ደግሞ የብሄረሰቡን አሠረጫጨት አስመልክተው የሚከተለውን ብለዋል።

የአርጎባ ኑሮው በተራራ ነው። በየጎራው ላይ ያሉትም ዋንኛ ምክንያቱ በሽሽት ነው፤ ለመከላከል፤ ይሽ ሚዳ ለሚዳ ያለ አንትን ያስቸገራቸው ጊዜ ... ጦርነት እሚከፍቱባቸው ነበሩ፤ ዝም ብለው ከብት አርቢ ናቸው፤ ... አንዲህ የሆነ ጊዜ አሳቸውም (አነሰም) ተራራ ላይ ወጥተው ካብ ይክባሉ፤ ... አሁን ይህ አገር (አሞዬ ሠርጤ) በሁለት ደጃፍ ነበር፣ በሳንቃ ነበር የሚገባው፣ ሠርጤ ዙሪያውን ካብ ተክቦ፣ ታጥሮ፣ በአንትን ነው፣ በዘበኛ ነበር እየተጠበቁ የሚቀመጠ፤ ... ከብት አርቢ እየተፈራ (ሚያዚያ 30/1999ኛ አሞዬ ሠርጤ)።

ከተጠቀሰው የሸህ አብዱራህማን መሐመድና ሌሎች ንግግር ለአርጎባ ብሄረሰብ አሠረጫጨት በዋነኛ ምክንያትነቱ የተጠቆመው ሃሳብ ከከብት አርቢዎች (በግልጽ ካልጠቀሷቸው) ጋር ከሚፈጠር ጦርነት የሚደረግ ሽሽት ነው። ከዚህም አንጻር፣ ብሄረሰቡ፣ ጦርነትን በመሸሽ ራሱን ለመከላከል በሚችልበት ቦታ፣ በተራራ ላይ፣ ለመስፈር ግድ እንደሆነበት እንረዳለን። የሃሳቡን እውነታነት በመስክ ሥራዬ በነበረኝ ቆይታ ለመታዘብ ሞክሬያለሁ። ከተመለከትኳቸው የልዩ ወረዳው ሰባት ቀበሌዎች ከአንዱ ውጭ (አንዛራዊ በሆነ መልኩ) ማለትም ከፈጠቆማ-01፣ ሌሎች በተራራ ላይ የሚገኙ ናቸው።

3.2.2. ባህላዊ፣ ማህበራዊና ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች

በዚህ ክፍል፣ ተጠኚውን ብሄረሰብ ከሌሎች ብሄረሰቦች የሚለዩት ባህላዊ፣ ማህበራዊና ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች በአጭሩ ተዳስሰዋል። ዳሰሳውም፣ የየሥርዓቶቹን ሂደት ከመግለፀ ባሻገር በየሂደቱ አገልግሎት ላይ የሚውሉትንና የዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆኑትን ባህላዊ ቁሶች ለማሳየት የሞከረ ሲሆን ይህንንም ያደረገው በቀጣዩ የትንታኔ ክፍል (በምዕራፍ አምስት) አንዳንድ ማስታወሻዎችን ለማጣቀስ መነሻ እንዲሆኑ በማሰብ ነው።

3.2.2.1. በሉ

የሰው ልጅ ከመሰሎቹ ጋር በማህበር በሚኖርበት ወቅት ኑሮው የተመቻቸ ይሆንለት ዘንድ በተቻለው መጠን ሠላምን ለማስፈን ይጥራል። በእርሱ፣ በንብረቱ ብሎም በመኖሪያ ቀዬው አንዳች መጥፎ ነገር እንዳይከሰት ይመኛል። ይህም እውን ይሆንለት ዘንድ መክፈል የሚጠበቅበትን ዋጋ ሁሉ ይከፍላል። ይሁን እንጂ፣ ኑሮው ሁልጊዜ እሱ እንዳሰበውና

እንዳለመው አይሆንለትም። በእንዣሩ፣ የሕይወት ሌላኛዋ ገፅታ ትገጥመውና ምኞቱ በእንግልት፤ ደስታው በሃዘን ይተካበታል። በሠላም ይኖር የነበረው ጥልን በልቡ ይቋጥራል። እናም፣ ከራሱ፣ ከሰዎች እንዲሁም ከአባባቢውና ከተፈጥሮ ጋር ይጋጫል። በዚህ ሁኔታ መቀጠሉን ግን ውስጡ አይፈቅደውምና ወዲያውኑ መፍትሄን ያፈላልጋል።

የዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆኑት የአርጎባ ብሄረሰብ አባላት በማህበር በሚኖሩበት ወቅት ለሚከሰት (በተለይም) የአርስ በርስ ግጭት መፍትሄ የሚሰጡበት ባህላዊ የግጭት መፍቻ ዘዴ አላቸው። ይህም «በሌ» ይሰኛል። ይህ ባህላዊ የግጭት መፍቻ ዘዴ የራሱ የሆነ ሥርዓት ያለው ሲሆን በማንኛውም ዓይነት መንስዔ የሚፈጠርን አለመግባባት ለማርገብና ዘላቂ መፍትሄን ለማምጣት ያገለግላል።

የበሌውን ሥርዓት ሂደት አስመልክተው ሼህ መሐመድ አሕመድ የተባሉ ቃል አቀባዬ እንዲህ ገልጸውልኛል።

> *... እንግዲህ አንድ ሰውና አንድ ሰው ይጣላል። ሲጣላ እንግዲህ አበጋሮች ይኖራሉ። ተርቲብ አለ፤ ቡኋ እመስጅድ በተራ የምናፈላው። እዛ ይሂድና 'አያ እገሌ'ኮ በደለኛ፤አቅርቡና አጠያይቁኝ' ይላል። ይጠራል ተመንደር። ያ ይመጣል። 'ይሽ ሰውዬ በደልኝ ይለሃል፤... አንተ፣ ምንድን ነው ቂያሳችሁ?' ይባላል። አሁን ሲያዩት ደካማ ተሆነ (ጉዳዩ) እዛው ያስታርቋቸዋል። ከባድ ተሆነ 'ቀኑን ያዝና አንተ ሁለት ሽማግሌ ጥራ አንተም ሁለት ሽማግሌ ጥራ፤ ይሽን ቀን ይዘናል እንገኛኝ!ይባላል። ያም ዘመድ ይጨምራል፤ ይሽም ዘመድ ይጨምራል። እንግዲህ የተበደለ ተፈት ያወራል፣ ያ ይመልሳል፣ ይሽ ይናገራል፤ ያ ይመልሳል። ከዚያ 'አግሉ!' (ተለዩ) ይባላል፤ ያገላሉ። ሁለቱም ሽማግሌ ያንን ነገር ያዩና 'አንተ ይሽን በድለኸዋል ... ይሽን ነገር እንደበደልከው ነው ያየነው!' ይሉና እሚያስቀጣም ተሆነ ያስቀጣዋል፣ እማያስቀጣም ተሆነ 'እኛ በደል አይተናል፣ አንተ ላይ፣ ግን አንተ ታሁን ጀምረህ ትተወዋለህ፣ ለወደፊት ዘመዳሞይ እናረጋችኋለን፣በል ውደድ!' ይሉታል፤ ... 'እንግዲህ እናንተ ታያችሁት... ' ብሎ ይተዋል። 'በሉ ተዛዩሩ!' ይባላሉ፤ ይዘያየራሉ። እንግዲህ ያ ነገር አይነሳም፤ ይተራል (ግንቦት 5/1999፤ አምዬ ሠርጤ)።*

ከሼህ መሐመድ አሕመድ ገለጻ የአርጎባ ብሄረሰብ ባህላዊ የዕርቅ ሥርዓት ራሱን የቻለና ቅደም ተከተሉን የጠበቀ ሂደትን የተላበሰ እንደሆነ መረዳት ይቻላል። በመሆኑም፣ በዕርቁ ሥርዓት የመጀመሪያው ተግባር በተፈጠረው ግጭት ተበደልኩ ብሎ የሚያምነው ሰው በደሉን ማሳወቅ ሲሆን የሚያሳውቀውም በብሄረሰቡ ዘንድ ታምኖባቸው፣ መንግስትም እውቅና ለሰጣቸው ታላላቅ ሰዎች ነው። እነዚህ ሰዎች «አበጋር» የሚል መጠሪያ ሲኖራቸው ለሃቅ የቆሙ፣ ዘራቸው የተከበረና የሚያስፈራ እንደሆኑ በአካባቢው ነዋሪዎች ዘንድ ይታመናል። ተበዳዩ በደሉን ካሳወቀ በኋላ በዳይ ነው የተባለው ሰው ተጠርቶ ይጠየቃል። አበጋሮችም የሁለቱንም አቤቱታ ከሰሙ በኋላ ፍርድ ለመስጠት ይመካከራሉ። በዚህ ጊዜ ታዲያ ከሳሽም ሆነ ተከሳሽ እንዲሁም የሁለቱ የቅርብ ወገኖች ምክክሩን መስማት ስለሌለባቸው ሁለታቸውንም ሊወክልና በፍርዱ ሂደት አብሮ ሊመክር የሚችል አንድ ሰው፣ ማለትም «የዘመድ ዳኛ» መርጠው ለተወሰኑ ደቂቃዎች ከአካባቢው እንዲርቁ ይደረጋል። ወዲያውም፣ ዳኞቹ የተፈጠረው ችግር የሚረግብበትን መንገድ በማፈላለግ፣ ተከሳሹ ጥፋቱን

ካመነና ጥፋቱም ሊያስቀጣው የሚችል ከሆነ፣ ከበደሉ ቅለትና ክብደት አንጻር (ከፍየል እስከ በሬ) ቀጥተው፤ የማያስቀጣው ከሆነ ደግሞ በቃላት ገስፀው ያስታርቋቸዋል።

ይህ ሳይሆን ቀርቶ፣ በዳይ የተባለው ሰው ጥፋቱን ካላመነና የተጣለበትንም ቅጣት ካልተቀበለ የዕርቁ ሥርዓት ከፍ ሲል ከተጠቀሰው ሂደት በተለየ ሌላ ገጽታ ይኖረዋል። ይኸውም፣ በዳይ የተባለው አለመበደሉን ለማረጋገጥ ቃለ-መሃላ እንዲፈጽም ይደረጋል። ቃለ መሃላውን ከመፈጸሙ በፊት ግን፣ አቶ ዑመር መ·ሃሊ እንደገለፁልኝ፣ ተከላሹ በሃሰት እንዳይምል አበጋሮቹ ቀድመው «የሸሆቹ በሌ ነው!፤ የአባቶቻችን በሌ ነው!፤ ጦር ነው!፤ ሠይፍ ነው!፤ እንዳትቆረጥ ...!» (ሚያዚያ 19/1999፤ አፈራ ነቸሮ) በማለት ያስጠነቅቁታል። በዚህ ጊዜ ተከሳሹ ጥፋት ከሌለበት በውሣኔው ፀንቶ «ዘሬን አላህ ያጥፋው!፤ የውስጥ ገላዬን ተላይ አላህ ይገልብጥብኝ!፤ ...» (እንደላይኛው) በማለት ይምላል። ሲምልም፣ በእንደቡቱ ከሚናገራቸው የመሃላ ቃላት ባሻገር በእጁ እንዲጨብጠው ወይም በአግሩ ተራምዶት እንዲያልፍ የሚደረግ ቁስ አለ። ይህ ቁስ፣ በሃሰት በሚምለው ሰው ላይ አንዳች ቁስል ወይም የጤናን መታወክ ያስከትላል በመባል በብዛረሰቡ ዘንድ የሚታምን ሲሆን ስሙም «በሌ» ፣«ምዝራጥ»፣«አንካሴ» ይባላል። ቁሱ፣ በአንድ ጫፉ ባላ ያለው በትር ሲሆን በሌላኛው ጫፉ ጦር የተሰካበት ነው። በባላውም፣ የማግ ክር፣ አውራ ጫትና መ·ስብሃ (ምንነቱን በምዕራፍ አምስት ይመለከቷል) በአንድ ላይ ይታሰሩበታል።

በበትሩ ባላ ላይ የማግ ክር የመታሰሩ ትዕምርትነት የሚምለው ሰው ሞቱን ወዲያውም ከፈኑን (መከፈኛ ልብሱን) እንዲያስብ የታለመ ሲሆን (የ "Schelereth" ን 2ኛ እና 7ኛ (ገፅ 33 - 34) ሞዴል ያስታውሷል)፤ አውራ ጫትና መ·ስብሃው መታሰራቸው ደግሞ በተጠኚ አካባቢው የሚገኙና ታላላቅ የሚባሉት የሃይማኖት ሰዎች ድዋ (ፀሎት) በሚያደርጉበት ወቅት አውራ ጫቱን በመቃም መ·ስብሃውን ደግሞ በእጃቸው ይዘው በማሻሸት ነውና የሚፈልጉትን አንዳች ነገር እንዲፈፀምላቸው የሚለመኑት ጉዳዩን ሃይማኖታዊ ባህርይ ለማላበስና ክብደት ለመስጠት ሲባል ነው። አንድም፣ በሌው፣ የታላላቅ አባቶችና የሸሆች መሆኑን ለማስረገጥና የሚምለው ሰው በበሌው ላይ የታሰሩትን አውራ ጫትና መ·ስብሃ ሲመለከት የተወከሉለትን ታላላቅ አባቶቹንና የሃይማኖት መሪዎቹን እንዲያስታውስ (የቁሶችን የተወካይነት ባህርይ (ገጽ 29) ያስታውሷል) የታለመ ነው።

በመሃላው ጊዜ፣ ሌላው ሊጠቀስ የሚገባው ጉዳይ፣ የሚምለው ሰው ምንም ዓይነት ብረት ነክ ቁስ (ቀለበት፣ ቀበቶ፣ ጊሌ፣ የልብስ ቁልፍ፣ ሚዶ፣ ወ.ዘ.ተ.) ከሰውነቱ ወይም ከልብሱ እንዲኖር አይፈቀድም። ይህም የሆነበት ምክንያት፣ የሚምለው ሰው ምናልባት በሃሰት የሚምል ከሆነ በእርሱ ላይ ሊደርስ (ሊመጣ) ያለውን አንዳች መርገም ቁሱ ይከላከልለታል ተብሎ ስለሚታመን ነው። ከዚህ ላይ ብሄረሰቡ ለቁሶች የሰጠውን ባህርይ ትኩረት ሰጥቶ ማጤን ይቻላል። ይህም፣ በምዕራፍ 2፣ ንዑስ ርዕስ 2.2.3 ላይ Prown እንደጠቀሰው ቁሶች የአንዳች ተለጣፊ ፀጋ ባለቤት ናቸው የሚለውን ሃሳብ ያስረግጥልናል።

ስለባህላዊ የዕርቅ ሥርዓቱ የቃል መጠይቅ ያደረግኩላቸው ቃል አቀባዮቼ አቶ ዑመር መ·ሃሊ፣ አቶ አብዱ አህመድና አቶ መ·ሐመድ አቡ ሃምዛ እንደገለፁልኝ ይህ ሥርዓት ከጥንት ጀምሮ ሲዳኙበት የቆዩ ሲሆን በአሁኑ ጊዜም የአካባቢው ነዋሪዎች ከመደበኛው

(መንግስታዊው) የፍርድ ቤት አሠራር በላቀ መልኩ ይገለገሉበታል (ሚያዝያ 19/1999፤ አራራ ነቸሮ)። ለዚህም በምክንያትነት የጠቀሱት ጊዜ፣ ገንዘብና ጉልበት ቆጣቢ መሆኑ ነው። አንድም፣ የዳኝነቱ ሥራ ሂይማኖታዊ ነው ብለው ስለሚያምኑ በዳኝነቱ የሚቀርቡትን የመሸምገያ ሀሳቦች ፍፁም ፍትሃዊ አድርገው መቁጠራቸው ነው። ጉዳዩ፣ ተጫማሪ ጥናትንና ምርምርን ሊያሰራ የሚችል ነው ብዬ ስለማምን በዚሁ አጋጣሚ ጠቁሜ ለማለፍ እወዳለሁ።

3.2.2.2. ጋብቻ

የአርጎባ ብሄረሰብ ባህሉን ከሚያንፀባርቅባቸው የተለያዩ ማህበራዊ ክወናዎች መካከል የጋብቻ ሥርዓት አንዱ ነው። በተጠኚው አካባቢ ጋብቻ ራሱን የቻለ ሥርዓት ያለው ሲሆን በተጋቢዎች መካከል ከሚፈጠረው መተዋወቅ ጀምሮ እስከ ሠርጉ ዕለት ድረስ የተለያዩ ባህላዊ ሂደቶችን ያካተተ ነው። በዚህ ክፍልም በጋብቻው ሂደት የሚከወኑትን ዐበይት ሁነቶች በመዳሰስ ሥርዓቱ ምን እንደሚመስል ተመልክቷል።

በጋብቻው ሂደት፣ በመጀመሪያ የሚቀድመውና መሰረታዊው ነገር በተጋቢዎች እና/ወይም በወላጆቻቸው መካከል የሚፈጠረው መፈላለግ ነው። እንደብዬረሰቡ ባህልም፣ ተጋቢዎች በሁለት መንገድ ለአጮኝነት ይበቃሉ።

የመጀመሪያውና በአብዛኛው የሚተገበረው፣ የወንድየው ወላጆች ለልጃችን ትሆናለች ያሏትን ልጃገረድ የሚመርጠበትና የሚያጨበት መንገድ ሲሆን፤ አብዱ ሠይድ የተባለ መረጃ አቀባዬ እንደገለፀልኝ ወላጆች በሁለት አነሳሽ ምክንያት ይህንን ሥራ ሊተገብሩ ይገደዳሉ። «ብኛ ላይ ክፉ በጎ አለ፤ ስለዚህ ለልጃችን ጮኛ እንፈልግለት!» ብሎ በማሰብ፤ አንድም፣ «ይኽ ልጅ መሳደብና መገላመጥ ጀምሯል፤ ስለዚህ ቢታጭለት ሊያርፍ ይችላል!» (ታህሳስ 10/2000፤ ኪልኪሎ) በሚል።

በአንዳሩ ሁለተኛው መንገድ ደግሞ ወንዱ ልጅ በራሱ የሚመርጥበትና በጣም በሚቀርበው የወንድ ጓደኛው አማካይነት ለወላጆቹ አስነግሮ ሃሳቡ እንዲፈፀምለት የሚያደርግበት መንገድ ነው። ታዲያ በዚህ መንገድ የሚያጭ አንድ ጎረምሳ የሴቲቱን ፈቃድ የሚጠይቅበት ባህላዊውን የአጠያየቅ ሥልት ተከትሎ እንደሆነ ጀማል አብዱልቃድር (ታህሳስ 17/2000፤ ጎበራ) ገልፃልኛል። የሚከተለው ቃለ ምልልስም የአጠያየቅ ሥልቱን የሚያሳይ ሲሆን ጎረምሳው ብቻውን ወይም ከሚያቀርበው ጓደኛው ጋር ሆኖ ልጂቱ ወደ ገበያ ወይም እንጨት ለመስበርና ውሃ ለመቅዳት ስትሄድ መንገድ ላይ ጠብቶ በማናገር ይከውነዋል።

ወንዱ: «ጤና ይስጥልኝ!» (በማለት ሠላምታን ይጀምራል)

ሴቷ: «አብሮ ያድርግልን!» (በማለት ለሠላምታው ምላሽ ታቀርባለች)

ወንዱ: «ከዚያስ?» (ሲል በምላሿ አለመርካቱን ገልፆ ለተጨማሪ ምልልስ ይጋብዛታል)

ሴቷ: «ለመንገደኛ ምን አነሰው!» (በማለት በቂና ተገቢ ምላሽ ማቅረቧን አስረግጣ ትገልፅለታለች)

ወንዱ፡ «እኔኳ መንገደኛ ሳልሆን አፍቃሪ ነኝ!፤ ... ደግሞስ የመንገደኛ ደንቡ ሥንት ነው?» (በማለት አፍቃሪነቱን ይገልጻል፤ ወዲያውም፣ መንገደኛ እንኳ ቢሆንም በዚያ መልኩ መስተናገዱ «ደንብ» እንዳልሆነ ይጠቁማታል)።

በዚህ ጊዜ ልቧ ከፈቀደላትና ከወደደችው፣ እንደ ጀማል አብዱልቃድር ገለጻ፣ የእርሷ ተምሳሌት የሆነችን «አሪቲ» የተባለች ጥሩ መዓዛ ያላትን ቅጠል ቆርጣ ትሰጠውና «በትጥምህ አሽትታት፤ ባትጥምህ ጣላት!» በማለት፤ አንድም፣ ለምለም ቅጠል ቆርጣ ለመቀመጫው በመጎዝጎዝ፣ ላቀረበው የ«እጮኛዬ ላድርግሽ!» ጥያቄ ፈቃደኛነቷን ትገልጽለታለች (ታህሳስ 17/2000፤ ጎበራ)።

የእጮኝነት መረጣው ሂደት በልጁ ወላጆችም ይሁን በራሱ በልጁ ከተከወነ በኋላ በመቀጠል የሚተገበረው ሥራ የወንዱ ልጅ አባት ለሴቷ ወላጆች የሚያሳውቁበትና የእነርሱን መልካም ፈቃድ የሚጠይቁበት ሂደት ነው። ሲጠይቁም «አላህ የሰጣችሁን ልጃችሁን አላህ ለሰጠኝ ልጄ ስጡኝ!» በማለት ሲሆን፣ የልጅቱም ወላጆች የእሽታም ሆነ የእምቢታ ምላሽ ከመስጠት ተቆጥበው «... እስኪ መክረን እንነግርዎታለን፣ በዚህን ቀን ይመለሱ!» በማለት ከቤተ ዘመዶቻቸው ጋር ለመመካከር ይመቻቸው ዘንድ አንድም እንደባህሉ ለመጓዝ የቀጠሮ ቀን ቆርጠው ይመልሷቸዋል።

ቀጠሮ የተሰጣቸው አባትም በቀጠሯቸው ቀን «እሽ!» እንደሚባሉ በማሰብ ለልጂቱ የሚያበረክቷቸውን ጌጣጌጦች (ብር ብስ፣ ድንብል፣ ኩክ ማውጫ ፣መቅዳድ የተባለ ቀይ መቀነት) እና «ናርጅ» በተባለች የቅቤ መያዣ ለጋ ቅቤ በመያዝ ወደ ልጂቱ ቤት ይመለሳሉ። ወደ ቤት ሲገቡም አስፈላጊውን ሠላምታ በማቅረብ ቀኝ እግራቸውን አስቀድመው የሚገቡ ሲሆን ፤ ጀማል አብዱልቃድር (እንደላይኛው) እንዳብራራልኝ፣ ቀኝ እግራቸውን የሚያስቀድሙበት ትዕምርትነቱ የልጆቹ የወደፊት የትዳር ሕይወት ያማረና የቀና ይሆናል ተብሎ ስለሚታመን ነው። በዚህ መልኩ ወደ ቤት ጎራ ያሉት የልጁ አባት፣ እንደባህሉ፣ ቀደም ሲል በመጡበት ወቅት ያቀረቡትን ጥያቄ በድጋሚ በማቅረብ ምላሹን በጉጉት የሚጠብቁ ቢሆንም ቅሉ፣ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ምላሽ ሊሰጣቸው እንደሚችል ገና ወደ ቤት ሲገቡ መገመት አያዳግታቸውም። ምክንያቱም የሴቷ ወላጆች ፈቃደኛ ከሆኑ ገብስ ፈትገው፣ አጃ ወቅጠው፣ ዶሮ ወጥ ሰርተውና የሚጠጣ (ቃሪቦ) አዘጋጅተው፣ እነርሱም አጊጠው ለብሰው በአጠቃላይ በቤቱ ውስጥ የሚስብ ድባብ ፈጥረው ነውና የሚቀበሏቸው።

የልጁ አባትም ወገ እንዳይቀር የሴቷ ወላጆች የሚሰጧቸውን ምላሽ ከአንደበታቸው ለመስማት ጥያቄውን በድጋሚ ያነሳሉ። የሴቷ ወላጆችም«አላህ የሰጠንን ልጃችንን አላህ ለሰጠህ ልጅ ሰጥተናል!» በማለት ፈቃደኛነታቸውን ይገልጻሉ። ከዚያም የተዘጋጀውን እህል ውሃ አቀራርበው በደስታና በሃሴት ይመገባሉ። ወዲያውም የልጁ አባት «ልጂቱን አምጡና ምልክት እናድርግ!» በማለት ይጠይቃሉ። የልጂቱ እናትም ልጂቷን ከጓደኞቿ ጋር ይዘው ያመጡና የቤቱ በር ላይ ሲደርሱ ዓይኗን በመሃረብ ሸፍነው (ለልጂቱ ያላቸውን ፍቅርና ስስት ለመግለፅ) ወደ ልጁ አባት ያቀርቧታል። የልጁ አባትም ያመጡትን ቅቤ ከፍለው የልጂቱን

ራስ ይቀቡና የቀረውን ደግሞ ለልጃቸው ትንሽ በማስተረፍ ሌላውን ለልጂቱ እናት ይሰጣሉ። ያመጡትን የጌጣጌጥ ስጦታም ለልጂቱ ያደርጉላትና ለሌላ ቀን ቀጠሮ ይዘው ወደ ቤታቸው ይመለሳሉ። ይህ ለሌላ ቀን የሚያዘው ቀጠሮ «የቅቤ ቀቢ ቀን» የሚል ስያሜ ሲኖረው የወንዱ ልጅ አባት፣ «ቅቤ ቀቢና ነገር ሰው ይመርጣል!» (እንደላይኛው) እንዲል የብሂረሰቡ ብሂል ከተመረጡ አምስት ወይም ስድስት ታላላቅ ሰዎችና ከልጃቸው ሚዜዎች ከሁለቱ ወይም ከሶስቱ ጋር በመሆን የልጃቸውን እጮኛ ቅቤ ለመቀባት የሚሄዱበት ዕለት ነው።

በዚህ ዕለት የወንዱ ልጅ አባት ሁለት ናርጅ *ቦታላቃ* (በአደስና ሌሎች ቅመማት የተዘጋጀ) ቅቤ እና ለስጦታ የሚሆን አምባርና የተለያዩ አልባሳትን ይዘው መሄድ ይጠበቅባቸዋል። ከዚህም ባሻገር፣ ቀደም ሲል በነበራቸው ቀጠሮ መሰጠት የሚገቧቸውን የስጦታ ጌጣጌጦች በወቅቱ ሳይሰጡ ቀርተው ከሆነ በዚህ ዕለት አሟልተው ያመጣሉ። የሴቲቱ ወላጆች ደግሞ ለሚመጡት እንግዶች የሚሆን የምግብና የመጠጥ ዝግጅት (ከላይ እንደተገለፀው) ያደርጋሉ። አስፈላጊው የመቀበያ መስተንግዶ ካለቀ በኋላም ልጂቱ በቅቤ ቀቢዎቹ አማካይነት ከመጣው ቅቤ ትቀባለች፤ የመጡላትን የማጫ ጌጣጌጦችም ከእጮኛዋ አባት ዘንድ ትቀበላለች። የመስተንግዶ ሥርዓቱም እስከ ማግስቱ ድረስ ቀጥሎ የሰርጉን ቀን በመቁረጥ ይጠናቀቃል።

ከዚህ ጊዜ በኋላ በሴቲቱም ሆነ በወንድዬው ወገኖች ዘንድ የሠርጉ ዝግጅት የሚጧጧፍ ሲሆን፣ በሴቲቱ ቤት በተለየ ደግሞ «ለፍጀሌ» የተባለው የሞፊራ ጨዋታ ማታ ማታ ይከወናል። በጨዋታው፣ ማንኛውም የአካባቢው ነዋሪ ድቤ እየተመታ የሚታደም ቢሆንም የሴቲቱ ሚዜዎችና እርሷን ይመኙ የነበሩ አፍቃሪ ኮበሌዎች ጨዋታውን በማድመቁና ሕይወት በመስጠቱ ረገድ ላቅ ያለ ሚና አላቸው። ከሚከውኗቸው ቃል ግጥሞችም የሚከተሉትን በአብነት መጥቀስ ይቻላል።

የልጂቱ ሚዜዎች እርሷን በማድነቁ ረገድ፣

«አካሌ ውቤ ድማሚ
አካሌ ውብ ነሽ የኛው ነሽ»

(መሬም አብዱ፣ አንሻ መሐመድ እና ሌሎች እየዘፈኑ ሲከውኑ የሰማሁት፣ ግንቦት 8/1999፣ ጮምቤ)

በማለት ያሞጋግሷታል። በአንጻሩ ልጂቱን ይመኙ የነበሩና ቀረቤታ የነበራቸው አፍቃሪ ኮበሌዎች ደግሞ፣

«የድንጋይ ሰር ውሃ ይቀዳል በፍኝ
ምነው ባላየሁሽ በቀረሽብኝ»

(እንድሪስ አብዱ፣ መሐመድ ጁሃር እየዘፈኑ ሲከውኑ የሰማሁት፣ ግንቦት 8/1999፣ ጮምቤ)

በማለት እርሷን ይመኙ፣ ያፈቅሩ እንደነበር ይገልጻሉ፤ ወዲያውም እርሷን የማግኘት ተስፋቸው እንደተሟጠጠና እንዳከተመለት በማመን የተዋወቁበትን አጋጣሚ/ዕለት ይረግማሉ። ከዚህም ባሻገር፣

«ማግባቱንስ አግቢ እኔ አልከለክልም
እየመጣሽ እይኝ ናፍቆቱን አልችልም»

(አንድሪስ አብዱ፣ መሐመድ ጁሃር እየዘፈኑ ሲከውኑ የሰማሁት፣ ግንቦት 8/1999፣ ጮምቤ)

በማለት ልጅቱ «የሌላ ሆኛለሁ!» ብላ ከእነርሱ ጋር የነበራትን ጨዋታ እንዳታቋርጥ በማሳዘን ያሳስቧታል። እርሷም ይህንን በሰማች ጊዜ፣

«በቆሎ እበላለሁ በብር ሸምቺ
አንተ ጋር ለመኖር ስፍራው መች ተመቺ»

(መሪም አብዱ፣ አንሻ መሐመድ እና ሌሎች እየዘፈኑ ሲከውኑ የሰማሁት፣ ግንቦት 8/1999፣ ጮምቤ)

በማለት ከእርሱ የተለየችበት ምክንያት በእርሷ ፍላጎት ሳይሆን በነገሮች አለመመቻቸት እንደሆነ ታስገነዝበዋለች። አንድም ከእርሱ ተለይታ የምትኖረው ኑሮ ድሎት (ምቾት) የሌለበት፣ ከሸመታ በቆሎ ውጭ የማታገኝበት እንደሆነ አስተዛዝና ትገልፅለታለች። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ከዚህ ጠንከር ያለን ሀሳብ እንደሚከተለው በመሰንዘር ውስጣዊ ሥሜቷን ትገልጽለታለች።

«ቦርከና ውሃው ሞልቶ ቢነካ ሰማይ
ዘንዶ ቢዘረጋ ከመንገዱ ላይ
ካንተ ጋር መጫወት የሚቀር ነው ወይ!?»

(መሪም አብዱ፣ አንሻ መሐመድ እና ሌሎች እየዘፈኑ ሲከውኑ የሰማሁት፣ ግንቦት 8/1999፣ ጮምቤ)

የቃል ግጥሙ፣ ልጂቱ ለአፍቃሪዋ ያላትን የማይደበዝዝ ፍቅር የሚያሳይ ከመሆኑ ባሻገር የልጁን ተስፋ የሚያለመልም እንደሆነ ልብ ይሏል።

የለፍጆሌው ጨዋታ ከላይ በተጠቀሰው መልኩ እስከሠርጉ ዕለት ድረስ የሚቀጥል ሲሆን በዚሁ ወቅትም የተለያዩ ድርጊቶች ጎን ለጎን ይካሄዳሉ። ለአብነት፣ በሠርጉ ዋዜማ (ይህ ዕለት «አጮምያ» የሚል አካባቢያዊ ስያሜ አለው) የልጂቱ ታላላቅ እህቶች፣ አክስቶች ለአዲሷ ጎጆ ወጪ የሚሆን የስፌት ዕቃዎችን (መዳይ፣ ሌማት፣ ቱና፣ ወ.ዘ.ተ.) ሰፍተው በማምጣት በስጦታ መልክ ያበረክታሉ። በተመሳሳይ መልኩ ልጂቱን ይመኙ የነበሩ ከበሌዎች ደግሞ (በድብቅ) ብርኩማ (የእንጨት ትራስ)፣ መስተዋት፣ ሳሙና፣ ወ.ዘ.ተ. ይሰጣሉ። በአፀፋውም፣ ከሽቦ የተሠሩ ቀጫጭን ቀለበቶችን ከልጅቷ ዘንድ ይቀበላሉ። ዶሮ ታርዶላቸውም ይስተናገዳሉ። ከዚህም በተጨማሪ፣ በዚሁ ዕለት፣ የሴቷ ሚዜዎችና ጓደኞቿ «ሴራ» የተባለውን መዓድ ማብላት ስላለባቸው አውጣጥተው አንድ መዓድ እንጀራና አንድ ወጭት ወጥ ያቀርቡና (የሴቷ ሴራ ይባላል) ለተሰበሰበው ሰው ያበላሉ። ወዲያውም፣ ከወንዱ ወገን ሴራ ተቀበሉ በማለት የወንዱ ሚዜዎች (ተወክለው ለዚሁ ሥራ የሚመጡ) የወንዱን ሴራ እንዲያቀርቡ ያስገድዳሉ። ምክንያቱም ሴራ ማብላት የማይቀር ባህል ነውና። ይህን ካደረጉ በኋላም፣ በሴቷ በኩል ሚዜዎቿ ገላዋን አጥበው፣ አዲስ ልብስ አልብሰው፣ ፀጉሯን ሸርባ ሠርተው እነርሱም አጊጠውና ተውበው የሠርጉን ዕለት ንጋት ይጠባበቃሉ። በወንዱ

ወገን ደግሞ የወንዱ ሚዜዎች ለጫጉላይቱ ቤት ግድግዳ ማስክኪያ የሚሆን ሽንብቆ ያስባስባሉ፤ ከመካከላቸው አንዱም (ዋናው ሚዜ) ጥሩምባና «አኮርባጅ» (የሙሽራ አለንጋ) አምጥቶ ለሙሽራው ይሰጠዋል። ከዚህም ሰዓት በኋላ የሙሽራው ሙሽርነት ይከበራል። ምክንያቱም፣ ጥሩምባው፣ ጋብቻውን የሚያውጅበት ቱስ ሲሆን አኮርባጁ (አለንጋው) ደግሞ ወንድነቱን፣ ተጋራፊነቱን፣ አንድም ሙሽራነቱን (የ"Schlereth"ን 2ኛ ሞደሌ - «ተምሳሌታዊነት» ያስታውሷል) የሚገልፅበት ነውና።

በሠርጉ ዋዜማ ከፍ ሲል የተጠቀሱት ድርጊቶች በወንዱና በሴቷ በኩል የሚከወኑ ሲሆን በሠርጉ ዕለት ደግሞ (ይህ ዕለት «የጥፍር ቆረጣ ዕለት» የሚል አካባቢያዊ መጠሪያ አለው) ሁለቱም በየበኩላቸው እንግዶቻቸውን ያስተናግዳሉ። ከመስተንግዶው በኋላም «ክሌ» ተነጥፎና «ሌማት» ተቀምጦ የጥሎሽ ማሰባሰቡ ሂደት ይፈጸማል። ወዲያውም፣ ከወንዱ ሚዜዎች አንዱ ተመርጦ (ኪዳን - ሽማ ልብስ ያሻ) ወደ ሴቷ ቤት ይላካል። የሚላከው የሴቲቱን ጥፍር ለማስቆረጥ ሲሆን ሲሄድም ኪዳን፣ ሐር ልብስ፣ ሙቅደድ (ቀይ መቀነት)፣ አንድ ናርጅ ቅቤ እና ዕብሪቅ (የውሃ ኮዳ) ይዞ ነው። በቦታው እንደደረሰም ጥፍር ለመቁረጥ ለተመረጡት ሦስት ባልቴቶች የያዛቸውን ቁሶች ያስረክብና የጥፍር መቁረጡ ሥርዓት ይፈፀማል። ይህ ሥርዓት (ይህ ዕለት) የሙሽራዋ የልጅነት አበባ (የልጅነት ጊዜዋ) ያለቀ መሆኑን የሚያሳይ ነው ተብሎ በብዛረሰቡ አባላት ዘንድ ስለሚታመን ጥፍሯ የሚቆረጠው ሙሽራ አምርራ ታለቅሳለች፤ «ወግ ነው ሲዳሩ ማልቀስ» እንዲሉ። የሙሽሪት ጥፍር ተቆርጦ እንዳለቀም ወደ ሙሽራው ቤት በመሄድ የሙሽራውን ጥፍር ይቆርጣሉ። ከዚያም «ሠርገኛ ቁጠሩ!» ይባልና ወደ ሴቷ ቤት የሚሄዱት የወንዱ ወገኖች ይመራረጣሉ። ሲሄዱም፣ ለልጅቷ ጫማ፣ ጥላና *ጉፍታ* (እንደ ሽማ ከላይ የሚደረብ ማሸን ሰራሽ ልብስ) በመያዝ ሲሆን በጭፈራና በዕልልታ ይታጀባሉ። በሴቷ ቤት በደረሱ ጊዜም ከሴቷ ሚዜዎች አንድም ከወንድ ጓደኞቿ (አፍቃሪዎቿ) ጋር ግጭት እንዳይፈጠር ሽማግሌዎች ጣልቃ ገብተው ፀጥታ የማስከበሩን ሥራ ይሠራሉ። ይህ የሽማግሌዎች እንትስታሴ ቢኖርም በሁለቱ ወገኖች መካከል በቃል ግጥም አማካይነት የሚደረገውን በነገር የመጎሻሸም ተግባር ሊያስቆሙት አይችሉም። በሰዓቱ ከሚከወኑት ቃልግጥሞችም የሚከተሉትን በአብነት መመልከት ይቻላል።

በልጂቱ መወሰድ (የሌላ መሆን) ውስጣቸው ያረረው የሰፈር አፍቃሪዎቿ፣

«የኛ ሙሽራ ባለካባ
ወሰዳት ያ ከላባ»

(መሬም አብዱ፣ አንሻ መሐመድ እና ሌሎች አየዘፈኑ ሲከውኑ የሰማሁት፣ ግንቦት 8/1999፣ ጮምዬ)

በማለት እሷ ለእሱ እንደማትገባ የእርሱን ክብር (ማንነት) አንቋሸሸው በነገር ጠቅ ሲያደርጉት፤ የወንዱ ሚዜዎች በዚህ ትንኮሳ በመናደድ፣

«የእመቤትን ወዳጅ ቂጠ ጎፈርን
ልንወሰዳት ነው በሉት ያስጥል እንደሆን»
(እንድሪስ አብዱ፣ መሐመድ ጁሃር እየዘፈኑ ሲከውኑት
የሰማሁት፣ ግንቦት 8/1999፣ ሥምዒ)

በማለት አፀፋውን ይመልሳሉ።

የቃላት ጦርነቱ በዚህ መልኩ ከቀጠለ ወደከረረ ጠብ ሊያመራ ይችላልና ገና በጅምሩ ሽማግሌዎች የልጅቱን አፍቃሪዎች በቃላት ገስጸው ወይም ከአካባቢው አባርረው «የኒካ ማሠር ሥርዓቱን» (የማፈራረም ሥርዓት) ይፈፅማሉ። ሲያፈራርሙም «የልጂቱ ሃቅ ስንት ይሁን?» ብለው ለልጅቱ ዋጋ (በገንዘብ) ይተምናሉ። ይህ ገንዘብ፣ ሴቷ፣ ምናልባት ከጊዜያት በኋላ ከባሏ ጋር ብትፋታ ከቤት ስትወጣ የሚሰጣት እንደሆነ ቃል አቀባዬ ጀማል አብዱልቃድር (ታህሳስ 17/2000፤ጎበራ) ገልያልኛል።

የኒካው ማሠር ሥርዓት እንደተፈፀመ ሙሽራውና ሙሽሪት (ታዝላ / በበቅሎ ጀርባ ተቀምጣ) ከሚዜዎቻቸውና ከሌሎች ቤተዘመዶቻቸው ጋር ሆነው ወደ ሙሽራው ቤት ያመራሉ። በቦታው ከደረሱ በኋላም፣ የሴቲቱ ሚዜዎች ሙሽራዋን በሞቀ ውሃ ያጥቧትና «ሶረሳ» የተባለ ጭስ ያሞቋታል። ወዲያውም ሦስት ባልቴቶች ተመርጠው ይመጡና ልጂቱን ይመርቋታል። ከዚያም ወደ ጫጉላ ቤቷ አስገብተዋት ይመለሳሉ። የዕለቱ ሥርዓት በዚሁ የሚፈፀም ቢሆንም ዝግጅቱ ግን ቀጥሎ እስከ አስር ቀን ድረስ በሙሽራው አባት አዘጋጅነት እየተበላና እየተጠጣ ይቆያል። ከዚያም በአስረኛው ቀን፣ እንደ አካባቢው አጠራር በ«አሰርቱው ቀን» የልብስ አጠባ ሥርዓት ይከወናል። በዚህም ጊዜ ሙሽራው ከሚዜዎቹ ጋር በመሆን በእርሱም ቤት ሆነ በሴቲቱ ቤት የሚገኙትን ልብሶች ሰብስበው ወደ ወንዝ ይወርዳሉ። በአንባሩ፣ ሙሽሪትና ሚዜዎቿ ደግሞ ፀጉራቸውን በመሠራራት በቤት ቁጭ ብለው ይጠብቃሉ። ከዚህም ቀን በኋላ እስከ ሃያኛው ቀን ድረስ አንዱ ሚዜ የአንድ ቀን ድግስ እያዘጋጀ ሚዜዎቹን ሰብስቦ በማብላት የሥርዓቱን ፍፃሜ ያማረ ለማድረግ ይጥራሉ። ሥርዓቱም በዚሁ ፍፃሜን ያገኛል።

ከፍ ሲል፣ የአርጎባ ብሄረሰብ ባህላዊ የጋብቻ ሥርዓት ምን እንደሚመስል በመጠኑም ቢሆን ለማሳየት ተሞክሯል። ከቀረበው ገለጻ የእኔ የጥና ትኩረት የሆኑት ናሙና የቤት ውስጥ መገልገያና የማጌጫ ቁሶች ናቸውና ብርኩማን፣ ከሌን፣ መቅዳድን፣ መቀነትንና አምባርን መርጨ በምዕራፍ ስድስት ተንትኛቸዋለሁ። ከዚህ ባለፈ ግን ጉዳዩ ሠፋ ያለ ጥናትና ምርምርን ሊያሠራ የሚችል ነውና በዚህ ጽሁፍ መነሻነት አጥኚዎች ጉዳዩን ርዕሳቸው አድርገው ቢንቀሳቀሱ የሚልን ጥቆማ ለመስጠት እወዳለሁ።

3.2.2.3. ፋጢማዬ

የአርጎባ ብሄረሰብ ከሚታወቅባቸው ባህላዊ፣ ማሕበራዊ አንድም ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች አንዱ «ፋጢማዬ» ነው። ፋጢማዬ፣ በአርጎባ ብሄረሰቦች ዘንድ የመውለጃ ጊዜዋ ደርሶ ልትወልድ ለተቃረበች ነፍሰጡር ሴት የሚፈፀም ሥርዓት ሲሆን ሥርዓቱ የሚከወንበት ዋነኛ ዓላማ ነፍሰ ጡሯ ያለምንም ጭንቀትና ችግር በሠላም እንድትገላገል ከመመኘት የመነጨ ነው።

ወ/ሮ አንሻ አሕመድ የተባሉ መረጃ አቀባዬ እንደገለፀልኝ፣ በአንድ አካባቢ ልትወልድ የደረሰች ነፍሰጡር ካለች፣ በራሷ አነሳሽነት ወይም በቤተ ዘመዶቿ ወይም ደግሞ በፋጢማዬ ሥርዓት አስፈፃሚዎች (የሃይማኖት ትምህርት የተማሩ፣ ቁርዓን የቀሩ ሴቶች) አማካይነት «ስሟ ይጠራ!» በሚል የመነሻ ሃሳብ ድግስ እንዲዘጋጅ ይታቀዳል (ግንቦት 7/1999፣ ጮምዬ)። ከዚህ ላይ «ስሟ ይጠራ!' የተባለችው ሴት ማን ነች?» የሚልን ጥያቄ አዕምሯችን ሊያጭር ይችላል። ስሟ ይጠራ የተባለችው ሴት ነፍሰ ጡሯ ሴት አይደለችም፤ ከእርሷ ዘመዶች የአንዷም አይደለም፤ ወይንም ደግሞ የሥርዓቱ አስፈፃሚ ወይዘሮ ሥምም አይደለም። ይልቁንም በእስልምና ሃይማኖት ትልቅ ቦታ የሚሠጣቸው የነቢዩ መሐመድ ልጅ የፋጢማ እንጅ። ሥርዓቱ «ፋጢማዬ» የሚል ስያሜም ያገኘው፣ እንደ ወ/ሮ ከሚያ አብዱ ገለፃ፣ በዚሁ መነሻነት ነው፤ የሚዘከረው የፋጢማ ስም ነውና (ግንቦት 7/1999፣ ጮምዬ)።

ሥርዓቱ የአንድ ቀን ዕድሜ ያለው ሲሆን ከንጋቱ 12:00 ሰዓት ጀምሮ እስከ ምሽቱ 12:00 ሰዓት አንዳንዱም ከዚያ ገፍቶ እስከ ምሽቱ 1:00 ሰዓት ወይም 2:00 ሰዓት የሚራዘምበት አጋጣሚ አለ። የፋጢማዬን ሥርዓት ሂደት አስመልክተው ወ/ሮ አንሻ አሕመድ (ግንቦት 7/1999፣ ጮምዬ) እንደገለፀልኝ፣ በመጀመሪያ፣ ነፍሰ ጡሯ ሴት የመውለጃ ጊዜዋን በማሰላሰል ለድግሱ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ታዘጋጃለች። የቤቷን ወለል ታስለቀልቃለች፣ ጉዝጓዝ ታስገዘግዛለች፣ የመቀመጫ ምንጣፍ (ከሌ) እና የመጋረጃ ልብስ (ኪዳን፣ ጉፍታ) ታሰባስባለች። ከዚያም፣ ቀን ትቆርጥና ሴቶች ዘመዶቿን (ወንዶች አይሳተፉም) ፣ ጎረቤቶቿን እንዲሁም አቅሟ እንደፈቀደ የአካባቢዋን ነዋሪዎች በመጥራት ገንፎ አስገንፍታ በቅቤ እና/ወይም በዘይት አጣፍጣ ቁርስ ታበላለች። ከቁርሱም በኋላ፣ ቤቱ በጥሩ መዓዛ እንዲታወድ «አድሩስ» (ሃደሩስ) የተባለውን ጭስ በማስጨስ የቡና መጠጣት ሥርዓትን ታከናውናለች። ከዚያም፣ የመመገቢያና የመጠጫ ቁሶች ወደየቦታቸው ይመለሱና እርሷ ሰፋ ካለና «ኪዳን» በተባለ መጋረጃ ከተጋረደ መደብ ላይ የቤቱን ግድግዳ ተደግፋ፣ «ጉፍታ» የተባለን ልብስ እንደ ሽማ ደርባ፣ ጌጣጌጧን በየዓይነቱ አድርጋ፣ እምራና ተውባ ትቀመጣለች። የፋጢማዬ ሥርዓቱን የሚመሩት ሁለት ወይም ሶስት ሰዎች (አቀንቃኞች/መራቂዎች) ደግሞ ጉፍታ ደርበው ከርሷ ፊት ለፊት (ዓይኗን እያዩዋት) መደቡ ላይ ይቀመጣሉ። በእነዚሁ ሰዎች ቀኝና ግራ እንዲሁም በስተጀርባ ደግሞ ጥሪ የተደረገላቸው ሰዎች (ምርቃት ተቀባዮች/አድማቂዎች) እንደገመድና ቀረቤታቸውና እንደ ዕድሜ ተዋረዳቸው ቦታ ቦታቸውን ይዘው ይቆማሉ። ከዚያም፣ አቀንቃኞቹ፣ ልመናን፣ ምስጋናንና ምርቃትን የሚያስተጋባ ቃልግጥሞን በዜማ ሲከውኑ፣ ተቀባዮቹ፣ «አሜን!» በማለት እንዳስፈላጊነቱም ሌሎች ምላሾችን በመስጠት፣ ድቤ በመምታት፣ በማጨብጨብ እንዲሁም በመደለቅ (በመወዛወዝ) ሥርዓቱ ድምቀት የተላበሰ እንዲሆን ያደርጉታል።

በሥርዓቱ ከሚከወኑት ቃልግጥሞች መካከልም የሚከተሉትን መመልከት ይቻላል። በመጀመሪያ፣ አቀንቃኞቹ «ዛራ ሁን!» የሚለውን ቃልግጥም በማለት ሥርዓቱን ሲጀምሩ ሌሎች ሰዎች (ተቀባዮች) ደግሞ የቃል ግጥሙን ዜማ ሥልት በመጠበቅ እያጨበጨቡ ድምቀትን ለማላባስ ይጥራሉ። ቃልግጥሙ የሚከተለው ነው።

ዛራ ሁን (2 ጊዜ) አመቤቴን ዛራ ሁን
» » ኣሚነትን » »
» » ኣይሸትን » »
» » ፋጢመትን » »
» » ከድጃትን » »
» » መሬማዬን » »
» » ዕሩቅያን » »
» » ዘይነቡትን » »
» » ሱባባዬን » »

(ወ/ሮ አንሻ አሕመድ፤ ግንቦት 7/1999ኛ ጮምዬ)

ከፍ ሲል በቀረበው ቃልግጥም ውስጥ የተዘረዘሩት ስሞች፣ ወ/ሮ አንሻ አህመድና ወ/ሮ ከሚያ አብዱ እንደገለፀልኝ፣ የነቢዩ መሐመድ እናት፣ ሚስት፣ ልጅ እና የልጅ ልጆች ሲሆኑ፣ የእነርሱን[9] ስም መጥራታቸው በረከታቸውና መንፈሳቸው በእኛ ላይ ይደር ለማለት እንደሆነ፣ አንድም፣ የፈለግነውንና የምንለምነውን ነገር የሚፈፅሙልን እነርሱ ናቸው ለማለት እንደሆነ አያይዘው ገልፀውልኛል (ግንቦት 7/1999፣ ጮምዬ)። በቃል ግጥሙም ውስጥ «ዛራ ሁን!» የሚለው ሃረግ ለግጥሙ ዜማ መጠበቅ ሲባል የተጎረደ ሃረግ ሲሆን፣ የተሟላው ሃረግ «ዝዛራ ይሁን!» የሚለው ነው። ትርጉሙም፣ የተቃና፣ የተስተካከለና የለመረ ይሁን እንደማለት ነው።

«ዛራ ሁን!» እየተባለ በአቀንቃኞቹ የተጀመረው የፋጢማዬ ሥርዓት «ግቡ ግቡ!» እየተባለና በአቀንቃኞቹና በተቀባዮቹ ህብረት እየታገዘ እንደሚከተለው ይቀጥላል።

ግቡ ግቡ ፋጢማ (አቀንቃኝ) ግቡ ግቡ ፋጢማ (ተቀባይ)
እንዲሆንልን ቃሊማ » » » »
ግቡ ግቡ ከድጃ » ግቡ ግቡ ከድጃ
እንዲወርድልን ፈረጃ » » » »
ግቡ ግቡ ኣሚነት » ግቡ ግቡ ኣሚነት
የነቢያችን እናት » » » »
ግቡ ግቡ ዕሩቅያ » ግቡ ግቡ ዕሩቅያ
የሠይዳችን ቡቃያ » » » »
.....

(ወ/ሮ አንሻ አሕመድና ወ/ሮ ከሚያ አብዱ ሲያቀነቅኑ፣ ወ/ሪት ኣሚነት አብዱ፣ ሸህ ጀማል የሱፍ እና እኔ ደግሞ ስንቀበል የቀረፅኩት፤ ግንቦት 7/1999ኛ ጮምዬ)

ከቃል ግጥሙ በግልጽ መረዳት እንደሚቻለው ቀደም ሲል «ዛራ ሁን!» በማለት ውሏቸው የተቃናና የሠመረ ይሆን ዘንድ የለመኑት፣ በማስከተል ደግሞ «ግቡ ግቡ! በማለት በእስልምና ሃይማኖት ታላላቅ ቦታ የሚሰጣቸውን የነቢዩ መሐመድን እናት፣ ሚስት፣ ልጅና የልጅ ልጆች እየጠሩ መንፈሳቸው በቤቱ እንዲገባና አንዳች በረከት (ፈረጃ) እንዲያላብሳቸው ይማፀናሉ። አንድም፣ የሚጠሯቸውን ስሞች ማንነት ያስተዋውቃሉ። ለአብነት፣ «ኣሚነት»፣ የነቢዩ መሐመድ እናት እንደሆኑ ተገልጿል፣ «ዕሩቅያ» ደግሞ «ሠይዳችን» (መመኪያችን) የሚሏቸው የነቢዩ መሐመድ «ቡቃያ»፣ ልጅ፣ አገልጋይ፣ እንደሆነች ተጠቁሟል።

የመማፀኛ፣ የመለመኛ ቃልግጥሞቹ ክወና በዚህ የሚቆም አይደለም፣ ይልቱንም «አርሂቡ! አርሂቡ!» በመባል ይቀጥላል።

አርሂቡ አርሂቡ	(አቀንቃኝ)	አርሂቡ አርሂቡ	(ተቀባይ)
አርሂቡ ፋጢማ	(»)	» »	(»)
አርሂቡ ግቡልን	(»)	» »	(»)
አንቱማ ብትገቡ	(»)	» »	(»)
ይገኛል አደቡ	(»)	» »	(»)
አንደዚ ግቡና	(»)	» »	(»)
በሉ ለወሰወሰ	(»)	» »	(»)
አንቱ አይደለሁም ወይ	(»)	» »	(»)
የቀዬው አግማስ	(»)	» »	(»)

(እንደላይኛው)

ከላይ ከቀረበው ቃልግጥም ውስጥ በተደጋጋሚ የቀረበውና እንደ እዝማች የተገለገለበት ቃል «አርሂቡ» የሚለው ቃል የአረብኛ ቋንቋ ቃል ሲሆን «ግቡ!፤ ጎራ በሉ!፤ ወደ እኛ ኑ!» የሚል ትርጓሜ እንዳለው ሸህ ጀማል የሱፍ ገልፀውልኛል። ግቡ የተባሉትም የነቢዩ መሐመድ ልጅ ፋጢማ ሲሆኑ፤ የእርሳቸው (መንፈስ) መግባትና በቤቱ መላወስ አደብን፣ መረጋጋትን፣ ያለጭንቀት መኖርን ያስገኛል ተብሎ በተጠኚው ብሄረሰብ ዘንድ ይታመናል። አንድም፣ ነፍሰ ጡሯ ያለ ብዙ ምጥ በሠላም ትገላገላለች ብለው ያስባሉ። ለዚህም በምክንያትነት ያቀረቡት በቃል ግጥሙ ማብቂያ ላይ እንደተጠቀሰው ፋጢማ የአካባቢው (የቀዬው) አግማስ፣ መመኪያ፣ እንደሆኑ በመጠቆምና ላቅ ያለ ክብር በማቀዳጀት ነው።

ሥርዓቱ ከፍ ሲል በተጠቀሰው መልኩ (ሌሎችንም ክወናዎች አካትቶ) እየተካሄደ ይቆይና በስተመጨረሻም የክወናው መሪዎች (አቀንቃኞች፣ መራቂዎች) የሚከተለውን ቃል ግጥም በማነብነብ ለበዓሉ መቋጫ ያበጁለታል።

አላህ መሶሌ አላህ መሐመዴ
አላህ መሶሌ እንበለውና
በሽተኛም ይሻር ጠማማውም ይቅና
መሐመዴ ያሚን ሠይዴ ምስጠፋ
እስቲ አንደዬ ግቡ እስቲ አንደዬ ግቡ
አንቱ ብትገቡ ይገኛል አደቡ
አንቱ አትገቡም እንጂ ብትገቡልንማ
ይደረብልኋል በሸማ ላይ ሸማ
የነፋጥዬ አባት ደም የዘይነባ
አብሸሪ እንድትሉኝ እቀብር ስገባ
.....

(ወ/ሮ ከሚያ አብዲ፤ ግንቦት 7/1999ኛ ሥምሪ)

ቃልግጥሙ የሥርዓቱ ማስፈፀሚያ ከመሆኑ አንፃር መልዕክቱ ሰፋ ያለ ነው። ልመናው፣ የታመመው ምህረትን እንዲያገኝ፣ የተጣመመውም እንዲቀና የሚያጣቅስ ነው። ከዚህም ባሻገር የአቀንቃኟ ግላዊ መማፀንም የተንፀባረቀበት ነው። ለዚህም በቃል ግጥሙ

የመጨረሻ ስንኝ ላይ «አብሽሪ (አይዞሽ፣ አለሁልሽ) አንድትሉኝ አቀብር ስገባ» የሚለውን በአስረጅነት መጥቀስ ይቻላል።

በሥርዓቱ ማብቂያ ላይ አቀንቃኞቹ ከፍ ሲል የቀረበውን ቃልግጥም ከከወኑ በኋላ «በኸይር (በሠላም) አላህ ያውጣን!፤ ተናግሮ አናጋሪን፣ አብሎ መስካሪን አላህ ይያዝልን!፤ ዛሬ መስሎ ነገ ተማፊር አላህ ይጠብቀን!፤ ተበላው ፎቀት፣ተራህመቱ ዘፈቅ አድርገን!፤...» (ወ/ሮ አንሻ አህመድ፤ ግንቦት 7/1999፤ ጮምዬ) በማለት ምርቃቱን ሲያወርዱት ሌሎች ተሳታፊዎች ደግሞ «አሚን!» በማለት፣ እንዲሁም «ነጊ፣ ናጋ!፤ የነጊ፣ የአማን ቤት ይሁን!፤ ልጅም፣ ከብቱም አማን ይሁን!፤ በኸይር አላህ ይገላግልሽ!...» እያሉ የመልካም ምኞታቸውን እየገለፁ እስከ ግቢው በር ድረስ ይሸኛሉ። ሥርዓቱም በዚሁ ፍፃሜን ያገኛል።

ጉዳዬን ቋጭቼ ወደ ሌላ ርዕስ ከመሻገሬ በፊት፣ በወቅቱ ካየሁትና ከተሰማኝ ሥሜት አንፃር ይህ ሥርዓት ቅፁ ዳጎስ ያለ ጥናታዊ ፅሁፍ ሊያሠራ የሚችል መሆኑን ለመጠቆም እወዳለሁ። አንድም፣ ከፍ ሲል የተጠቀሰው ሥርዓት በተጠኚው አካባቢ የሚፈፀም ሥርዓት ቢሆንም፣ በአሁኑ ወቅት፣ ከሁለት መሠረታዊ ምክንያቶች አንፃር መጠነኛ መቀዛቀዝን እያሳየ በመምጣቱ በቅርብ ያለው የልዩ ወረዳው ባህል ቢሮ ከወዲሁ አንዳች መፍትሄ ቢያፈላልግ ለማለት እወዳለሁ። ለሥርዓቱ መቀዛቀዝም በምክንያትነት የተነሱት ነጥቦች፣ ወ/ሮ ከሚያ አብዱ እንደጠቆሙኝ፣ አንደኛው፣ ለድግሱ የሚወጣውን ወጭ መፍራት ሲሆን፤ ሁለተኛ ውና ለባህሉም መጥፋት ዓይነተኛ አስተዋፅኦ ያለው የፋጢማዬ ሥርዓቱን መምራት የሚችሉት ሴቶች በቁጥር ማነስና ችሎታው በታላላቅ ሰዎች ብቻ ተወስኖ መቅረቱ (የተተኪ አለመኖር ችግር) ነው (ግንቦት 7/1999፤ ጮምዬ)።

4. የእጅ ባለሙያዎች ሙያና ሕይወት

የዚህ ጥናት ዋነኛ ትኩረት የአርጎባ ብሄረሰብ ናሙና የቤት ውስጥ መገልገያና የማጌጫ ቁሶች ቢሆኑም ቅሉ ለቁሶች መፈጠር ምክንያት የሆኑትን የብሄረሰቡን የእጅ ባለሙያዎች በመጠኑም ቢሆን መዳሰሱ ጥናቱን የተሟላ ያደርገዋል በሚል ሀሳብ በዚህ ምዕራፍ ሥር የእጅ ባለሙያዎቹን ሙያ (ጥበብ) እና ሕይወታቸውን በመጠኑ ለመቃኘት ተሞክሯል። ቅኝቱም፣ የእጅ ባለሙያዎችን ከማስተዋወቅ አልፎ፣ ሙያቸውን፣ የሚሠሯቸውን ቁሶች ዝርዝር፣ ሙያውን የለመዱበትን መንገድና ያጋጠሟቸውን ችግሮች አካትቷል።

4.1. ጥናቱ ያተኮረባቸው የእጅ ባለሙያዎች ትውውቅ

ይህንን ጥናት ለማድረግ ካሰብኩበትና ለመጀመሪያ ጊዜ የቅኝት ስራን ለመከወን በተጠኚው አካባቢ ከተገኘሁበት ጊዜ ጀምሮ የብሄረሰቡ አባላት በምን በምን ዘዴ (መንገድ) እንደሚተዳደሩ ለማወቅ ጥሬያለሁ። ከጣርኩባቸውም መንገዶች መካከል በልዩ ወረዳው የመስተዳድር ኃላፊዎችና የባህል ቢሮ ተጠሪዎች እንዲሞላ ባዘጋጀሁት የጽሁፍ መጠይቅ ውስጥ «በየቀበሌዎቹ የሚገኙት ነዋሪዎች የሚተዳደሩት በምን በምን ሥልት ነው?» የሚልን ጥያቄ በማካተት መረጃዎችን ሰብስቤያለሁ። መረጃው እንደሚያመለክተውም፣ የአርጎባ ብሄረሰብ፣ በግብርና፣ በንግድ፣ በሸክላ ሥራ፣ በሽመና ሥራ፣ በብረታ ብረት ሥራና በእንጨት ሥራ እንደሚተዳደር ተገንዝቤያለሁ።

የብሄረሰቡ አባላት ከፍ ሲል በተዘረዘሩት መንገዶች የሚተዳደሩ ቢሆንም ከእኔ የጥናት ርዕስ ጋር የማይሄዱትን ባለሙያዎች በመተው፤ መካተት የሚገባቸውን ደግሞ በማካተት ሙያቸውንና ሕይወታቸውን ዳስሻለሁ። ከዚህም አንፃር፣ በግብርናና በንግድ ሥራ የሚተዳደሩትን ሙሉ በሙሉ በዳሰሳዬ አላካተትኩም። በብረታ ብረት ስራ ከተሰማሩት ደግሞ ጌጣጌጥ የሚሰሩትን ብቻ መርጫለሁ። ሌላው፣ የእንጨት ሥራ ውጤቶችን (ቁሶችን) በናሙና ተጠኝነት ባካትታቸውም፣ በምልከታዬ እንደታዘብኩት በሥራው የተሰማሩ ሰዎች በወቅቱ የነበራቸው እንቅስቃሴ የጎላ ካለመሆኑ አንጻር የመረጃ ዕጥረት ስላጋጠመኝ፤ በተመሳሳይ መልኩ፣ የቆዳ ሥራን በተመለከተ ደግሞ ማንኛውም የብሄረሰቡ አባል ለራሱ ፍጆታ የሚሆኑ የቆዳ ውጤቶችን መሥራት በመቻሉ እነሱን በተመለከተ ዳሰሳዬ ምንም ዘገባ አላቀረበም። ከዚህ ባሻገር ግን፣ የሸክላ፣ የሽመናና የጌጣጌጥ ባለሙያዎችን በተመለከተ ከዚህ በታች ከተነሱት ንዑሳን አርዕስተ ጉዳዮች አንጻር መጠነኛ ማስታዎሻዎችን ለማስፈር ችያለሁ።

4.2. የእጅ ባለሙያዎች፣ የአሠራር ጥበባቸውና ውጤቶቻቸው

ከፍ ሲል በ5.1. እንደተጠቀሰው፣ የአርጎባ ብሄረሰብ በተለያዩ ዘዴዎች የሚተዳደሩ ቢሆንም፣ ይህ ጥናት፣ የሽክላ፣ የሽመናና የጌጣጌጥ ሠራተኞን ሙያና ሕይወት በተመለከተ ገለጻ አቅርቧል።

የሽክላ ሠራተኞች፣ ብሄረሰቡ ከሰፈረባቸው ሰባት ቀበሌዎች በተለይም በአራቱ (01፣02፣03 እና 07) ቀበሌዎች የሚገኙ ሲሆን፤ አብዛኞቹ ዝቅተኛ ኑሮን በመግፋት ላይ ያሉ የብሄረሰቡ አባላት ናቸው። ኑሯቸውም ከእጅ ወደ አፍ ዓይነት ኑሮ ሲሆን፤ ብዙ (ሰፊ) የእርሻ መሬት የሌላቸውና በሚሠሩት የሽክላ ሥራ ውጤት ሽያጭ ብቻ የሚተዳደሩ ናቸው።

ሙያው፣ በዋናነት የሴቶች ሥራ እንደሆነ በአካባቢው ነዋሪዎች ዘንድ የሚታመን ሲሆን፣ ወንዶች (ልጆች ብቻ) በአፈር ቁፋሮውና ስብሰባው ወቅት መጠነኛ ተሳትፎ አላቸው። የአሠራር ጥበቡን (ሂደቱን) በተመለከተ ቃል አቀባዬ ወ/ሮ ከድጃ ይብሬ (ሚያዚያ 29/1999፣ አሞዬ ሠርጤ) እንደገለፀልኝ፣ የመጀመሪያው ሥራ ለሽክላ ሥራ የሚሆነውን የአፈር ዓይነት ከዱር ወይም ከወንዝ ዳር ቆፍሮ ወደ ቤት ማምጣት (በኬሻ ወይም በቆዳ ዘንቢል-በቀርቀቦ) ሲሆን፤ የመጣውም አፈር በድንጋይ ወፍጮ ይፈጭና በወንፊት በመታገዝ ለም አፈሩ ከጠጠሩ ይለያል። የተለየው ለም አፈርም ጉድጓድ ውስጥ ወይም «ዋዳት» በተባለ የሽክላ ቁስ ውስጥ በውሃ ተለውሶ ይቦካል። ከዚያም የተቦካው ጭቃ የተወሰኑ ሰዓታትና ቀናት (ከ1 እስከ 3 ቀናት) ይቆይና ለታለመለት ሥራ ይውላል።

ቁሱ ሲሰራ መጠኑና ቅርፁ በአብዛኛው በባለሙያዎች ፍላጎት የሚወሰን ቢሆንም አንዳንድ ጊዜ ግን በተጠቃሚዎች ትዕዛዝ ሊሆን እንደሚችል ልብ ይሏል። የቅርፅ ማስያዙ ሥራ፣ እንደ ማሰሻ ጨርቅ፣ ስንጥር ሸምበቆና ቆረቆንዳ በመሳሰሉት መሳሪያዎች በመታገዝ ከተሠራ በኋላ «ሸክላ» በተባለ ቀይ አፈር ዙሪያው ተቀብቶ በፀሃይ መሞቅ (ለ2 ወይም 3 ቀናት) እንዲደርቅ የሚደረግ ሲሆን፣ ከዚያም ጥንካሬ ይኖረው ዘንድ ፍግና የጥጥ ፍሬ እየተነሰነሰበት በእሳት ተለኩሶ ወደ ገበያ ይወጣል።

ከፍ ሲል በተጠቀሰው መንገድ የተለያዩ የሽክላ ውጤቶች የሚሠሩ ሲሆን፣ በመስክ ቆይታዬ የተመለከትኳቸውና የብሄረሰቡ የሽክላ ባለሙያዎች የሚሠሯቸው የሚከተሉት ናቸው። ድስት፣ ጀበና፣ ማጨሻ፣ ቶፋ (ጭንቁላ)፣ ወጭት፣ ዋዳት፣ ጋን፣ ጉልቻ፣ ቆሪ፣ ወ.ዘ.ተ.

በአንጻሩ፣ የሽመና ባለሙያዎችን ስንመለከት፣ ከሰባቱ ቀበሌዎች መካከል በተለይ በአራቱ (02፣04፣05 እና 06) ቀበሌዎች ቁጥራቸው በርከት ይላል። አብዛኛዎቹ የሽመና ባለሙያዎችም እንደሽክላ ሠራተኞች ሁሉ ሰፊ የእርሻ መሬት ባለቤት ካለመሆናቸው አንጻር በሙያው የተሠማሩ ሲሆን፤ አንዛራዊ በሆነ መልኩ ከሽክላ ሠራተኞች የተሻለ ኑሮን የሚኖሩ ናቸው።

የሽመና ሙያ፣ ከሽክላ ሙያ በተለየ መልኩ የወንዶችና የሴቶች ሙያ እንደሆነ በአካባቢው ነዋሪዎች ዘንድ የሚታመን ሲሆን፤ ሥራውም፣ የሁለቱንም ፆታዎች (ዕድሜ ሳይለይ) አስተዋጽኦ የሚሻ ነው። የአሠራር ጥበቡንም ስንመለከት፣ አቶ ይማም ሲራጅ

(ግንቦት 15/1999፣ አሠኔ አገር) የተባሉ ቃል አቀባዬ እንደገለፁልኝ፣ መጀመሪያ፣ ባለሙያው «ድር» የተባለውን ጠንካራ ክር በአንድ ጫፉ ከሚሰራው የሽማ ጨርቅ መጠቅለያ ጋር ካለች ዘንግ (የመጠቅለያ ዘንግ) ላይ ያስርና በሁለት «ደንፍ» ተብለው በሚጠሩና ከላይና ከታች በታቀፉ ጥርጥር (ቀጫጭን ሽምበቆዎች) መካከል በማሳለፍ ሌላኛውን የድሩ ጫፍ በተወሰነ ርቀት ከተተከለ እንጨት ላይ ያያይዛል። ከዚያም፣ ሁለት ገመዶቹን ከሁለቱ ጥርጥር ሽምበቆዎች (ከደንፎቹ) ጋር አስሮ ወደታች አንድ ክንድ ያህል ወደተቆፈረ ጉድጓድ ይለቃቸዋል። ይህንንም የሚያደርገው በስራው ወቅት ገመዶቹን ከታች በእግሩ ጣቶች ሳብና ረገብ በማድረግ የደንፎቹን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር ሲሆን ፤ ይህም በመወርወሪያዋ (ቀለም አቃፊ ቱስ) ውስጥ ያለውን ቀለም ወይም ጥለት ወደግራና ወደ ቀኝ እያመላለሰ በሚሰድበት ወቅት ቀለሙ (ጥለቱ) በተዘረጋው ድር እየተጠላለፈ የታለመውን የሽማ ልብስ በድሩና በቀለሙ ውህደት ወይም ጥምረት እንዲሰራ ያስችለዋል። የድሩና የቀለሙ ውህደትም የሽማውን ጥንካሬ የሚወስን ከመሆኑ አንጻር፣ ባለሙያው፣ ደንፎቹን ወደተጠላለፉት ድርና ቀለም በሃይል ሳብ ሳብ (መታ መታ) በማድረግ ሽማው ዘርዛራ እንዳይሆን የሚቆጣጠር ሲሆን ፤ የሽማውን ዓይነት (ከቀለም አንጻር) በመወርወሪያዋ አማካይነት በሚያመላልሳቸው ጥለቶች ምርጫና አጠቃቀም ይወስናል።

በዚህ ጥበብ፣ የሽመና ባለሙያው የተለያዩ የሽማ ውጤቶችን፣ መቀነት፣ መቅዳድ፣ ኪዳን፣ ግልድም፣ ኪታ፣ ቀሚስ፣ ዓይነት፣ ጃኖ፣ ወዘተ. የሚሠራ ሲሆን ፤ ለራሱ ፍጆታም ሆነ ለሽያጭ በማቅረብ የሙያው ተጠቃሚ ይሆናል።

በተጠኚው አካባቢ የሚኖሩ የጌጣጌጥ ባለሙያዎችን ስንቃኝ፣ ከፍ ሲል ከተነሱት ከሸክላና ከሽመና ባለሙያዎች በተሻለ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ መሆናቸውን በመስክ ቆይታዬ የታዘብኩ ሲሆን ፤ ይህም የሆነበት ምክንያት፣ ካላቸው ገበያ አንጻር እንደሆነ ለመረዳት ችያለሁ። ከዚህም ባሻገር፣ በሙያው የሚተዳደሩ የጌጣጌጥ ሠራተኞች በብዛት አለመኖር ተፈላጊነታቸውን በመጨመሩ እንደሆን ልብ ይሏል።

ከሥርጭት አንጻር፣ የጌጣጌጥ ሠራተኞች ከሰባቱ ቀበሌዎች መካከል በሁለቱ (03 እና 04) ብቻ ማለት በሚቻል ሁኔታ በቁጥር አንሰው ይገኛሉ። ለዚህም ቃል አቀባዬ አህመድ መሐመድ እንደምክንያት የጠቀሰልኝ ባንድ በኩል የሙያው አስቸጋሪ መሆን ሲሆን ፤ በሌላ በኩል ደግሞ፣ ጥበቡ፣ በቤተሰብ ብቻ ተወስኖ በምስጢር የመተላለፍ ልማድ መኖሩ ነው (ሚያዚያ 27/1999፣ አሞዬ ሠርጤ)።

የጌጣጌጥ ሥራ ከሽክላ ሠራ በተቃኚው መልኩ የወንዶች ሙያ እንደሆነ በአካባቢው ነዋሪዎች ዘንድ የሚታመን ሲሆን ፤ ሴቶች መጠነኛ የሆነ አስተዋጽኦ አላቸው። ተሳትፏቸውም፣ ለሽያጭ የሚቀርቡ ጌጣጌጦችን በፈላ የሎሚ ውሃ በመዘፍዘፉና በማጠቡ ረገድ የተወሰነ ነው።

የጌጣጌጥ ሥራ ጥበብን ስንመለከት፣ ባለሙያው፣ በመጀመሪያ የሚያደርገው ነገር ቢኖር ለጌጣጌጥ መስሪያ የሚሆኑ የተለያዩ ንጥረ ቁሶችን (ለአብነት፣ ብር፣ ነሃስ፣ ቆርቆሮ፣ ቀጫጭን ሽቦ፣ ኒኬል፣ ሳንቲሞች ወዘተ.) በጥሬ እቃነት ማሰባሰብ ሲሆን ፤ እነዚህን ንጥረ ቁሶች ለሚፈለጉት ዓላማ ለማዋል፣ ባለሙያው፣ የሚቀልጡትን በማቅለጥና በተዘጋጁ (ቅርጽ

በወጣላቸው) የማፍሰሻ ቦታዎች በማፍሰስ ቅርፅ የማስያዙን ሥራ ይሠራል። ሊቀልጡ የማይችሉትን ወይም ሊቀልጡ የማይገባቸውን ደግሞ በእሳት በማጋልና በመዶሻ በመቀጥቀጥ አንድም በጉጠት (በመቆንጠጫ) በመሳብ፣ ወይንም ደግሞ በጋሉት ንጥረ ቁሶች ላይ የቀለጠ ብር ወይም ብረት በማፍሰስና አዲስ ቀርጽ በማስያዝ የተለያዩ ጌጣጌጦችን ይሠራል። እነዚህን ሥራዎች ሲሰራ፣ ባለሙያው፣ ከ«ወናፍ» በሚወጣ ነፋስ በሚግም እሳት ታግዞ ነውና ቀጣዩ ሂደት የሚሆነው ከስለውና ጠቁረው ከእሳት የሚወጡትን ጌጣጌጦች ግለታቸው ሳይበርድ ጥንካሬ እንዲኖራቸውና አብረቅራቂ መልክ እዲይዙ የብረት ብናኝ «ዱቄት» የመነስነሱ ሥራ ነው። ከዚያም የማጽዳቱ ሥራ ይሠራል። ይህም ሥራ የሚሠራው፣ እሳት ላይ ተጥዶ በሚፈላ ውሃ ውስጥ ሎሚ እየተከተፈ ከተጨመረ በኋላ በሎሚው ፍላት ሲሆን፣ ጌጣጌጡ ከተጣዱበት ለአፍታ እየወጡ በፀጉራም ቡርሽ በተደጋጋሚ ጊዜ ይታሻሉ። ከዚያም ፀሐይ ላይ (አየር ላይ) በማቆየት ይደርቁና ለሽያጭ ወደ ገበያ ይወጣሉ።

ከላይ በተጠቀሰው ሂደት፣ የእጅ ባለሙያዎች በቁጥር በርካታ የሚባሉ የጌጣጌጥ ዓይነቶችን የሚሠሩ ሲሆን ውጤቶቻቸውን ራሳቸው ባለሙያዎቹ አንድም ተገልጋይ ብሄረሰቡ በምድብ በምድብ በሚያስቀምጠበት ዘዴ (ጌጦቹ ከሚውሉበት የሰውነት ክፍል አንጻር) ከፋፍዬ እንደሚከተለው ለማሳየት ሞክሬያለሁ።

- ❖ የግንባር (የፀጉር) ጌጥ - ወላባ፣ ወገሮ
- ❖ የጆሮ ጌጥ - ጉትቻ፣ ጨልጨሌ
- ❖ የአንገት ጌጥ - መስብሃ፣ ሣላ ፍሬ፣ ንፍስ (ከዳዋ)፣ ብር ቁርጥ፣ ብር ብስ፣ ብር ገረዴ፣ መሐልቅ፣ ተመን፣ ኩክ ማውጫ፣ ድንብል፣ አሸንክታብ፣ ድሪ
- ❖ የእጅ (የጣት) ጌጥ - አምባር፣ ቀለበት
- ❖ የእግር ጌጥ - አልቦ

4.3. የእጅ ባለሙያዎች ሙያውን የለመዱበት መንገድ

«ያባት ሥራው ለልጅ ገሩ ነው!»
(አህመድ መሐመድ፣ ሚያዚያ 27/1999፣ አምቤ ሠርጤ)

የአርጎባ ብሄረሰብ በተለያዩ የመተዳደሪያ ሥልቶች ተሠማርቶ ሕይወቱን እንደሚመራ ከፍ ሲል በቀረቡት የዚህ ምዕራፍ ክፍሎች ተጠቅሷል። ከመተዳደሪያ ስልቶቹም፣ የእጅ ሙያዎችን፣ ማለትም የሽክላ፣ የሽመናና የጌጣጌጥ ሥራዎችን በተመለከተ መጠነኛ ገለጻ ቀርቧል። በዚህ ክፍል ደግሞ፣ የተጠቀሱት የእጅ ሙያ ባለቤቶች ሙያውን እንዴት እንደተማሩት ወይም እንደለመዱት ለማሳየት የናሙና ባለሙያችን የሕይወት ተሞክሮ በማጣቀስ አቅርቤያለሁ።

Silverman በዝርዝር እዳመለከተው፣ አንድን የእጅ ሙያ በተለያዩ መንገዶች መካን የሚቻል ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ፣ መደበኛ ሥልጠና፣ ምልከታና ተደጋጋሚ ሙከራ በዋናነት ሊጠቀሱ ይችላሉ (1999:16-20)።

የዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆኑት የአርጎባ ብሄረሰብ የእጅ ባለሙያዎች፣ Silverman ከጠቀሳቸው ዘዴዎች በመጨረሻዎቹ በሁለቱ መንገዶች የሙያቸው ባለቤት እንደሆኑ የገለፀ ሲሆን ፤ ጉዳዩን በተጨባጭ ለማየት የሚከተሉትን ከባለሙያዎች አንደበት የተቀዱ የሕይወት ተሞክሮዎች (በምዕራፍ ሦስት "case study" ያልኳቸውን) ማጤን ይቻላል።

ወ/ሮ ከድኛ ይብሬ የ35 ዓመት ጎልማሳ ሲሆኑ በአርጎባ ልዩ ወረዳ፣ በቀበሌ 04 (አሞዬ ሠርጤ)፣ ልዩ ስሟ ስንዴ ሜዳ ተብላ በምትጠራ ጥሮ ነዋሪ ናቸው። ወይዘሮዋ፣ የሽክላ ሥራ ባለሙያ ሲሆኑ፣ በሙያው፣ ራሳቸውን ጨምሮ አሥራ ሁለት ቤተሰቦቻቸውን ያስተዳድራሉ። ይህንን የመተዳደሪያ ሥልት አድርገው የያዙትን የሽክላ ሥራ ሙያ እንደምን እንደተካኑት እንዲነግሩኝ ስጠይቃቸው፣ ሁኔታውን ወደኋላ ተመልሰው በማስታወስ እንዲህ ነበር የገለጹልኝ።

> *... እናቴ ትሠራ ነበር፣ ትሠራለይ መስራት፣ እኔም ያው በልቤ ነውይ በእጅ ከእናቴ አላነሳሁም፤ ዝም ብዬ ወጪ ገቢ ነኝ፤ ትትሰራ አያታለሁ እንጂ ቁጭ ብዬ ከእናቴ ጋር ሁኜ አንዲትም እቃ አልሰራሁ፤ ያው በዛ በዓይኔ ተጠቅሜ ችግር ቀሰቀሰኝ ገባሁበት። አሁን ሌላ ዕውቀት የለኝም፤ ተሰባ ሰባት (ዓ.ም.) ይገሬ እለፋለሁ፤ ለዚሁ ለራሴ ችያለሁ፤ ሰውን አባካችሁ አልልም፤ የሰው አልከጅልም (አጽንኦቱ የእኔ ነው፣ ሚያዚያ 29/1999፣ አሞዬ ሠርጤ)።*

ከፍ ሲል ከተጠቀሰው የወ/ሮ ከድኛ ይብሬ የሕይወት ተሞክሮ (በተለይም አፅንኦት ከሰጠኋቸው ገለፃዎች) እንደምንረዳው የእጅ ሙያ ባለቤት ለመሆን እንደኛው መንገድ ሙያው ያላቸው ሰዎች ሲሠሩ በአትኩሮት መመልከትና የተመለከቱትንም ወደ ተግባር መለወጥ ነው። ወይዘሮዋም ያደረጉት ይህንኑ ነው። እናታቸው ሲሠሩ ተመለከቱ፣ «ያኖሩት እንቅርት ያገለግላል!» እንዲሉ በቸገራቸው ጊዜ ተገለገሉበት።

በተመሳሳይ መልኩ፣ በቀበሌ 02 (አሬራ ነችሮ) ነዋሪ የሆኑትን የሽመና ባለሙያ፣ አቶ አህመድ ሲራጅን፣ «የሙያው ባለቤት ሊሆኑ የቻሉት እንደምን ነው? ከማንስ ነው የቀሰሙት?» የሚልን ጥያቄ አንስቼላቸው ነበር። አቶ አህመድም ሙያውን ከ13 ዓመታት በፊት (የ20 ዓመት ወጣት እያሉ) እንደጀመሩ በማውሳት የለመዱበትን አጋጣሚ እንዲህ ሲሉ አጫውተውኛል።

> *... አይ! ... ይህንን የሽመና ሥራ የቻልኩት አንደኛ በማየት ነው። ስለዚህ እንደዚህ የሚሠሩ ሰዎች ሳገኝ የዚያን ሰዓት ከሚሠሩት ተንስተው ወደ ምሳቸው፣ ወደ ምግብ ቲሄዱ እኔ እገባለሁ፤ ከገባሁ በኋላ ... ገብቼ ደህናም ሠራሁ ሆሳም (የማይረባ) ሠራሁ አጥፍቼም ሆነ እወጣለሁ። ... ስለዚህ በእንደዚህ ምህንያት ነው መልመድ የቻልኩት፤ ትምህርት ቤት ሄጀ ተምሬ አይደለም፤ ያው የዚህ የቅርቤን በማየት ነው አብዛኛው የለመድኩት፤... እንግዲህ ዘመዶቼም ሆኑ አጎቶቼም ሆኑ ይሰራሉ ማለት ነው፤ እገሀም አባቴ ሲሰራም የራሴ ስለሆኑ ዘልሌ እገባለሁ፤ ስለዚህ እንደዚህ ዓይነት ገቢ ምንጭ እያገኘሁ ነው ማለት ነው (ሚያዚያ 19/1999፣ አሬራ ነችሮ)።*

ከቀረበው የአቶ አህመድ ሲራጅ ንግግር «ማየት»/«መመልከት» የእጅ ሙያ ባለቤት ለመሆን ቀዳሚው ተግባር እንደሆነ እንረዳለን። ይህም ተግባር ደግሞ በተደጋጋሚ መከራዎች መታገዝ እንዳለበት ተያይዞ ተመልክቷል። አንድም፣ በእጅ ሙያ ለመዳ ወቅት የቅርብ ሰዎች (አባት፣ አጎት፣ ዘመዶች) ሙያውን ለቀጣዩ ትውልድ ከማስተላለፉ አኳያ ያላቸው አስተዋጽኦ ምን ያህል እንደሆነ ከተጠቀሰው የሕይወት ተሞክሮ ተነስቶ መገመት አያዳግትም። በዚሁ ወደ ሦስተኛው የእጅ ባለሙያ የሕይወት ተሞክሮ እናምራ።

አህመድ መሐመድ የ28 ዓመት ጎልማሳ ሲሆን ለ11 ዓመታት ያህል በጌጣጌጥ ሥራ ዘርፍ ተሰማርቶ ቆይቷል። ይህ ሰው፣ ከአጎቱ ከአቶ ተማም ሃሰን ጋር ሆኖ ሙያውን የሚሠራ ሲሆን በአርጎባ ልዩ ወረዳ «አንቱ» ከተባሉት የጌጣጌጥ ባለሙያዎች ቀዳሚ ተጠቃሽ ነው። ጥበቡን እንደምንና ከማን እንዳገኘው በጠየቅኩት ወቅት «ያባት ሥራው ለልጅ ገሩ ነው!» በሚል አካባቢያዊ ብሂል ንግግሩን ጀምሮ እንደሚከተለው አብራርቶልኛል።

> *... 'ያባት ሥራው ለልጅ ገሩ ነው' ይባል የለ! ... የመማሩ ጉዳይ የሽማዬ (አጎቴ) አባቱ ድሮ በሥራው ላይ ቲሠራ ሳለ ትንሽ ትንሽ ይመለካከት ነበር። ከዚያ አባቱ በትልቅነት ዓይኑን ተያዘ፣ የጀመራቸውን ሥራዎች አልጨረሳቸውም፤ ጅምሩ እንዲሁ ቀረ፤ የሚጨርሳቸው ጠፋ፤ ከዚያ ተማም (የሽማዬ) ዝም ብሎ ብድግ ብሎ ገባባቸው። ከዚያ ይዞ የተሻሻለ ዕውቀት ያዘ፤ ያው እኔም እዚሁ ካለሁ ታየው (ሳየው)፣ ታየው፣ ታየው ያው በቃ እኔም ቅድም እንዳልኩህ 'ያባት ሥራው ለልጅ ...' የሚባል ተረት አለ፣ ያው እሱ እየሰራ ካለ እኔም ዝም ብዬ ገባሁኝ፣ ያው 'ተበራታ መፍራት አያስፈልግም፣ ግማሹንም እያጠፋህ ግማሹንም እያለማህ ነው' እያለኝ እንደዚህ ሆኜ ነው የለመዱኩት፤ አሁን ከቱም ከሞራሌ እያወጣሁ ብዙ ቅርፃ ቅርጾች ይኖሩኛል (ሚያዚያ 27/1999፣ አሞዬ ሠርጤ)።*

ከላይ የሕይወት ተሞክሮዎቻቸውን እንዳየነው እንደሌሎቹ የእጅ ባለሙያዎች ሁሉ የጌጣጌጥ ሥራ ባለሙያ የሆነው አህመድ መሐመድም የሙያው ባለቤት የሆነበት መንገድ ምልከታ ሲሆን፤ የተመለከተውን አካሄድም ተከትሎ አንድንድ ጊዜ እያጠፋ በሌላ ጊዜ ደግሞ እያለማ በተደጋጋሚ መከራዎች በማለፍ ነው።

ከአህመድ መሐመድ ንግግር፣ በዚህ ንዑስ ርዕስ ለተነሳው ጉዳይ አንዳች ምላሽ የሚሆን ሀገርኛ ብሂል እንደተካተተ ልብ ይሏል፣ «ያባት ሥራው ለልጅ ገሩ ነው!» ብሂሉ፣ የእጅ ሙያ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዴት እንደሚተላለፍ አመላካች ነው። ከአባት አንድም፣ ከቅርብ ዘመድ ወደ ልጅ። ምክንያቱም፣ ልጅ ከአባቱ ጋር የሚሆንበት አጋጣሚ በጣሙን ሰፊ ነውና በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ የአባቱን ሥራ በመመልከት ወዲያውም በተደጋጋሚ ጊዜ በመሞከር ሙያውን ሊካነው ስለሚቻል ነው።

4.4. የእጅ ባለሙያዎቹ ያጋጠሟቸው ችግሮች

በቀደሙት የዚሁ ምዕራፍ ንዑሳን አርዕስት፣ ከዚህ ጥናት የትኩረት አቅጣጫ ጋር ተዛምዶ ያላቸው የእጅ ባለሙያዎችና ሙያቸው ተዋውቋል። ከዚህም በተጫማሪ፣ የሙያው ባለቤት የሆኑበት መንገድና በሙያቸው ተመስርተው ሰተገልጋይ የሚያበረክቱት ውጤቶቻቸው በዝርዝር ተመልክተዋል። በዚህ ክፍል ደግሞ፣ ባለሙያዎቹ፣ ሙያውን በመተዳደሪያ ሥልትነት ይዘውት ሲኖሩ በሕይወታቸው ላይ የበለጠ ለውጥ እንዳያመጡና ውጤታማ እንዳይሆኑ እንቅፋት የሆኗቸው ሁኔታዎች ምን ምን እንደሆኑ ተዳስሷል። መረጃው፣ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የእጅ ባለሙያዎች ጋር በተደረገ የቡድን ውይይት እንደተሰበሰበ ልብ ይሏል።

የሸክላ ባለሙያ የሆኑት ወ/ሮ ከድጃ ይብሬ፣ ወ/ሮ አሚነት አብሪ፣ ወ/ሮ ፋጡማ ሁሴንና ወ/ሮ ዚነቱ ሸሀ በውይይቱ እንደጠቆሙት፣ የእነርሱ መሠረታዊ ችግር ለሸክላ መሥሪያ የሚሆነው አፈር በአካባቢያቸው በብዛት ያለመኖር፣ አንድም ያለውንም በመንግስት አካላት (በቀበሌ አመራሮች) አማካይነት መከልከላቸው ነው። የአፈሩ በብዛት ያለመኖር ችግር ሥር-ነቀል መፍትሄ የሚፈልግ ከመሆኑ አንፃር ጉዳዩን በችግርነት ይገፎ ያለውን የተከለከሉበትን ሁኔታ ግን እንዲያስረዱኝ «ለምን?» የሚልን ጥያቄ አንስቼላቸው ነበር። ተወያዮቼ እንደገለፀልኝም፣ የተከለከሉት መሬት፣ ለሸክላ መሥሪያ የሚሆን አፈር ስላለው በተደጋጋሚ ጊዜ እየቆፈሩ ይገለገሉበት ነበር። በሂደት ግን ሰፊ ጉድጓድ በመስራቱ ውሃ ይቋትበት ነበር። በዚህ ጊዜ ታዲያ የቀበሌ አመራሮች፣

> *'... እኒህ ሰዎች አገር አጠፉ አይደል!' ብለው እኛን ከልክለው እነሱ 'ሃሮሮ' (ሆረዮ-የውሃ ማቆሪያ ጉድጓድ) እንዲሠራበት አዘዙ፣ 'ለአገር መጠቀሚያ!' ብለው። ተነተረቱ 'ድህ ወግ ያውቃል፣ የሚያደምጠው ያጣል፤ ውሃ የነሃሴው ይበልጣል፣ የሚጠጣው ያጣል!' ነውና፣ ብንጮህ 'አቤት!' የሚለን ጠፋ። ከቴውም፣ 'ለአገር መጠቀሚያ ነው!' ቲሱን ጊዜ፣ 'አገር ከሚጫንህ ጎራ ከሚጫንህ?' ቲባል ሰውየው፣ 'አገር ቢጫነኝ ማን ያነሳልኛል?፣ ጎራ ቢጫነኝ ግን አገር ያነሳልኛል' እንዳለው፣ አገር ከሚጫነን ብለን ተውነው። ... እንግዲህ አንተው አሳስብልን (ወ/ሮ ከድጃ ይብሬና ሌሎች፣ ሚያዚያ 29/1999፣ አምቤ ሠርጤ)።*

ከላይ እንደተጠቀሰው የሸክላ ሠሪዎች የአፈር ችግር እንዳለባቸው በግልጽ ጠቁመዋል። ከዚህም ባሻገር የመንግስት አካላት ምንም ዓይነት ድጋፍ እያደረጉላቸው እንዳልሆነ መረዳት ይቻላል። እንዲሁም፣ «... እኒህ ሰዎች አገር አጠፉ አይደል!» ከሚለው አገላለጽ የአካባቢው የቀበሌ አመራሮች ለአካባቢው የሸክላ ባለሙያዎች ያላቸው አመለካከት ምን ያህል አሉታዊ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል። ይህ አሉታዊ አመለካከት ደግሞ ሙያውንና የባለሙያዎችን እንቅስቃሴ ምን ያህል ሊያቀጭጨውና ሊገታው እንደሚችል መገመት አያዳግትም።

የሸክላ ባለሙያዎች፣ ከፍ ሲል ከጠቀሷቸው ችግሮቻቸው ባሻገር ለፍተው የሰሯቸውን ሥራዎች (የሸክላ ውጤቶች) ተሸክመው ወደ ገበያ በሚወስዱበት ወቅት በተደጋጋሚ ጊዜ

እንቅፋት እየተመቱና እየወደቁ ሽክላዎቻቸው እንደሚሰበሩ በማውሳት የመጓጓዣ ችግር እንዳለባቸው ጠቁመዋል። ከዚህም ባሻገር፣ የገበያው በየወቅቱ መቀያየር (ከጥቅምት እስከ መጋቢት ድረስ ጥሩ ገበያ የመኖር፣ በሌሎቹ ወራት ደግሞ አነሳሪ መሆን) ሌላው ችግራቸው ነው። ከዚሁ ጋር ተያይዞ፣ በአካባቢው ባሉ ሰዎች ዘንድ ለሽክላ ሠራተኞችና ለሙያቸው ያለው አሉታዊ አመለካከትም ሳይጠቀስ የማይታለፍ ጉዳይ ነው። ይንንም አስመልክቶ፣ በውይይቱ ወቅት መጠነኛ ችግር እንዳለ ለመጥቀስ እንዲህ ነበር የገለፁልኝ፣

... ያገር ችጋር ባዳፈንን ልጆቻችን በየመልካው እየተሰደቡ ነው፤ ... አርግጥም እየተሰደብን ነው፤ ... ግን አለትጥ መጉላት የለውምና፤ ... ጨርሶም አንተ እንደቃጣኸው ባይሆን (በሌሎች አካባቢዎች አለ የሚባሉትንና እኔ የነገርኳቸውን ችግሮች በማውሳት) እንደነገርከንም ባይሆን አለ፤ ጨርሶም 'የለም!' አንልም 'አለምም!' አንል (ወ/ሮ ከድኛ ይብሬና ሌሎች፣ ሚያዚያ 29/1999፣ አምቤ ሠርጤ)።

ከሸማ ባለሙያዎች፣ ከአቶ አህመድ ሲራጅ፣ ወ/ሪት መሬማ ሲራጅ፣ አቶ ሲራጅ አብደላና ወ/ሮ ፋጡማ መሐመድ ጋር ባደረግኩት ውይይት፣ እንደሸክላ ሠራተኞቹ የበዛ ባይሆንም መጠነኛ ችግር እንዳለባቸው ተረድቻለሁ። እንደችግር ያነሱዋቸውም ነጥቦች በቀጥታ እነሱን የሚመለከቱ ሳይሆን፣ ይልቁንም፣ የሽመና ሙያ በአካባቢው ነዋሪዎች ዘንድ እንደትልቅ ሙያ ስለሚቆጠር በሙያው ለመሰማራት የሚፈልጉት ሰዎች የሚገጥሟቸውን የተመለከቱ ናቸው። ነጥቦቹም የሚከተሉት ናቸው።

... እኛ በምንሰራው ሥራ ለመሰማራት በዚህ ባገሩ ብዙ ሰው ይቆላጫል (ይፈልጋል)። ግና ምንድን ነው የመነሻሻ ዕጥረት አለ። ደሞ ቲነሳሱ ሙያውን ሲያጠኑት ይበሳጫሉ፤ ለምንድን? የሚያስተምር ስላጡ። ስለዚህ መነሻ ካጣ፣ አንድ እንቅፋት ነው፤ ከዚያ በኋላ አውቀቱንም አያገኘውም (አጽንኦቱ የእኔ ነው፣ አህመድ ሲራጅና ሌሎች፣ ሚያዚያ 19/1999፣ አሬራ ነቸሮ)።

ከአቶ አህመድ ሲራጅና ሌሎች ንግግር ሁለት ነጥቦች በችግርነት እንደተጠቀሱ ልብ ይሏል። የመጀመሪያው፣ የመነሻ (የወረት) ዕጥረት ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ሙያውን የሚያስተምር (የሚያሰለጥን) ሰው አለመኖር ነው። የተጠቀሱትን ችግሮች በአዕምሮዬ ይዤ ከልዩ ወረዳው የጥቃቅን ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ኃላፊ፣ ከአቶ ኢድሪስ መሐመድ ጋር (የጽሁፍ መጠይቁን በማስሞላበት ወቅት) ለመወያየት (በጨዋታ መልኩ) ሞክሬያለሁ። ሃላፊውም፣ ችግሩ እንዳለ በማመን ወደፊት ለእንደነዚህ ዓይነት ሰዎች የብድር አገልግሎት ለመስጠት እንዳቀዱ ገልጸውልኛል። ስልጠና የመስጠቱን ሁኔታ በተመለከተ ደግሞ የህዝብ አደረጃጀት ቢሮ ኃላፊ የሆኑት አቶ መሐመድ ጀማል ከቃሉ ወረዳ (አጎራባች ወረዳ) ማክሰማ (ማህይም ክህሎት ስልጠና ማዕከል) ድጋፍ ለመጠየቅና ለማሰልጠን እንዳሰቡ ገልጸውልኛል።

በተጠኚ አካባቢው የሚገኙ የጌጣጌጥ ባለሙያዎችንም፣ ማለትም፣ አቶ አህመድ መሐመድን፣ አቶ ተማም ሃሰንን፣ አቶ መሐመድ ሰኢድንና አቶ ሰይዱ ያሲንን፣ ከፍ ሲል ለሌሎች ባለሙያዎች ያነሳሁትን ጥያቄ በመያዝ አወያይቻቸው ነበር። በውይይቱም፣ እንዲህ ሲሉ ሃሳባቸውን ሰንዝረውልኛል።

... ውጤታማ እማያደርጉን አንደኛው ችግር፣ ... አሁን ማርትሬዛ (ብር) እሚባል ነገር አለ፣ አቅልጠን እቃ እምንሠራበት፤ እሱ ታዲያ በስምንት ቀን፣ በሦስት ቀን ባራት ቀን ይጨምራልኝ፤ ዋጋው ማለት ነው። ዋጋ ሲጨምር ታዲያ እኛ እዚህ ገጠር ስለሆን ያው ጫና የሚያደርግብን የግር መንገድ ነው። ቲሌፎን ምናምን የለም፤ ሞባይል የለም፤ ... ስልክ ምናምን ቢኖር የሙያው ዋስትና ማለት ነበር። ... ግን ሆኖም የለም። የግር መንገዱ ደግሞ መኪናው ተገባ ያው ዛሬ ገበያው የዋለበትን ነገ ልናገኘው ይመቻልኝ፤ ስልክም ቢኖር ሚት ማታ ጠይቀን ማግኘት እንችል ነበር። አሁን ግን በዚህ በዚህ ምክንያት ለኛ ትልቅ ችግር ፈጥሮብናል (አህመድ መሐመድና ሌሎች፣ ሚያዚያ 27/1999፣ አሞዬ ሠርጤ)።

ከቀረበው ንግግር፣ የብሄረሰቡን የጌጣጌጥ ባለሙያዎች ውጤታማ እንዳይሆኑ የሚያደርጉ ሶስት ነጥቦች በችግርነት እንደተጠቀሱ ልብ ይሏል። የመጀመሪያው፣ በጥሬ ዕቃዎች ዋጋ ዙሪያ የሚታየው የዋጋ መለዋወጥ ሲሆን፤ ሌላኛው ችግር ደግሞ ጥሬ ዕቃዎቹ በሚገኙበት ቦታ፣ በከተማ፣ ያለውን የገበያ ሁኔታ መረጃ በቀላሉ አለማግኘት ነው። ከዚህም ባሻገር፣ የትራንስፖርት ችግርም አንዱ ችግር እንደሆነ ተጠቁሟል።

በዚህ ምዕራፍ ሥር፣ የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑትን የአርጎባ ብሄረሰብ ናሙና የቤት ውስጥ መገልገያና የማጌጫ ቁሶች አስመልክቶ ትንታኔ ለማቅረብ የቁሶችን ሠሪ ባለሙያዎችና ሕይወታቸውን መፈተሽ ተገቢ ነው በሚል መነሻ ሥጠነኛ መረጃን ለማጠናቀር ተሞክሯል። ጥንቅሩን በዚሁ እንቋጨውና ወደ ዋነኛ ተተኳሪዎቹ፣ ወደ ናሙና ቁሶች ትንታኔ እናምራ።

5. የናሙና የቤት ውስጥ መገልገያና የማጌጫ ቁሶች ትንተና

ይህ ምእራፍ በጥናቱ ዋነኛ ትኩረት የተሰጣቸው የአርጎባ ብሄረሰብ ናሙና የቤት ውስጥ መገልገያና የማጌጫ ቁሶች ቀደም ሲል በምዕራፍ ሁለት በተከለሱት ድርሳናት መነሻነት የተተነተኑበት ነው።

5.1. የናሙና የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶች ትንተና

ይህ ክፍል፣ በምዕራፍ ሦስት (1.6.1.1.2.ን ይመለከቷል) በግልጽ በተቀመጡ መስፈርቶች አማካይነት የተመረጡ ናሙና የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶች የተተነተኑበት ሲሆን ከተሠሩበት ንጥረ ቁስ አንፃር በተለያዩ ክፍሎች ተመድበው ቀርበዋል። ናሙናዎቹ የተመረጡበት የብሄረሰቡ የመገልገያ ቁሶች ስብስብም በአባሪነት (አባሪ 1ን ይመለከቷል) ተያይዘው እንደቀረቡ ለመጠቆም እወዳለሁ።

ከቆዳ የተሠራ ቁስ

ከሌ



የፍየል ከሌ

ከሌ፣ በአርጎባ ብሄረሰብ ዘንድ (በዋናነት) ለምንጣፍነት የሚያገለግል ቁስ ሲሆን፣ ከበግ ውጭ፣ በፍየል (መጠን፣ 70 X 100 ሣ.ሜ.)፣ በከብት (110 X 160 ሣ.ሜ.) እና በግመል (120 X 180 ሣ.ሜ) ቁርበት ሊሰራ ይችላል። ከበግ ቁርበት ውጭ ያልኩበት ምክንያት፣ ተጠኚው አካባቢ

በርሃማ ከመሆኑ የተነሳ በጎች ስለማይረቡበት የበግ ቁርበት አገልግሎት ላይ ሲውል ባለማየቴ ነው። ይህም ጉዳይ የSchelerethን 6ኛ ሞዴል፣ «አካባቢያዊነት»ን (2.2.5ን ይመለከቷል) እንድናወሳ ይጋብዘናል።

የከሌን አሠራር ስንመለከት፣ በተለያዩ አጋጣሚዎች ለዕርድ የሚቀርቡ እንስሳት (ከላይ የተጠቀሱት) ከታረዱ በኋላ ቁርበታቸው በጥንቃቄ ከሥጋቸው ይገፈፍና ወዲያውን በዕርጥብነቱ አፈር እንዳይቅም ተደርጎ በፀጉሩ በኩል መሬት ላይ ይዘረጋል። ከዚያም፣ እንዳይሸበሸብ፣ አንድም ቶሎ እንዲደርቅ፣ ዙሪያውን «መወጠሪያ» ተብለው በሚጠሩ ቀጫጭንና ሹል እንጨቶች (በምስሉ እንደተመለከተው) ይወጠራል። ከዚያም የውሎ ፀሃይ ካደረቀው በኋላ የመወጠሪያ እንጨቶቹ ተነቅለው ወደ ቤት ይገባና በቤቱ ግድግዳ ላይ ተሰቅሎ ለተወሰኑ ቀናት (ከሳምንት እስከ ሁለት ሳምንት) ይቆያል። ይህም የሚሆነው ዓየር በደንብ እንዲያገኝና እንዲናፈስ ሲሆን፤ ከመድረቁ የተነሳ ሲነኩት የመንቋቋት ድምፅ ማሰማት ከጀመረ መደብ ላይ ወይም አልጋ ላይ በመነጠፍ አገልግሎት መስጠት ይጀምራል።

የከሌ ተቀዳሚ አገልጎሎት ምንጣፍነቱ ቢሆንም ለተለያዩ ተጓዳኝ አገልግሎቶች ሊውል እንደሚችል በመስክ ቆይታዬ ተረድቻለሁ። ይኸውም፣ የተለያዩ ቁሶችን ለመስራት በጥሬ ዕቃነት መቅረቡን ይመለከታል። በከሌ አማካይነት ከሚሠሩት ቁሶች መካከልም፣ ድቤ (ከበሮ)፣ ቀርቀቦ (ዘንቢል)፣ ወናፍ፣ ዳውላ (አቅማዳ) አልጋ፣ ወንበር፣ ጠፍር (ገመድ) የመሳሰሉት ለአብነት ሊጠቀሱ ይችላሉ። ከዚህም ባሻገር፣ ከሌ፣ ተፍቶና ተለስልሶ ለመጽሐፍ ማዘጋጃነት (እንደወረቀት) ሊያገለግል እንደሚችል ሼህ አብዱራህማን መሐመድ (ግንቦት 1/1999፣ አሞዬ ሠርጤ) የገለፀልኝ ሲሆን ከከሌ የተዘጋጁ የቁርዓን መጻሕፍትንም (በቁጥር 30 ያህል) በጥንታዊው የሠርጤ መስጊድ ውስጥ አሳይተውኛል።

ከሌ፣ ለተጠቀሰው የመጽሐፍ ዝግጅነት አገልግሎት መስጠት ቢችልም በአሁኑ ጊዜ ግን ከሁለት ምክንያቶች አንጻር እየተሰራበት አይገኝም። እነዚህም ምክንያች፣ እንደ ሼህ አብዱራህማን መሐመድ (እንደላይኛው) ገለፃ፣ ዘመኑ የሥልጣኔ ዘመን ከመሆኑ አንፃር የከሌው አገልግሎት በወረቀት በመተካቱና ከሌውን ፍቶና አለስልሶ በወረቀትነት እንዲያገለግል የሚያደርግ ባለሙያ አለመኖሩ የሚሉት ናቸው። ከተጠቀሱት ሁለት ተጨባጭ ምክንያቶችም ከመጀመሪያው ጋር ተያይዞ፣ ጊዜ (ዘመን) እና ሥልጣኔ በቁሳዊ ባህል ላይ ያላቸውን አሉታዊ ተፅዕኖ በግልጽ መረዳት ይቻላል። አንድም፣ በተዛማጅ ጥናት ትኩቱ ሥር (በ2.1) ያካተትኳቸው አጥኚዎች፣ ውብሸት (1978) እና አሰገደች (1986) እንደገለፀት፣ ባህላዊ ቁሶች በጊዜና በዘመን መለወጥ የተነሳ በሌሎች ቁሶች እየተተኩ ለመምጣታቸው አስረጅ ነው።

ከሌ፣ ከላይ ከተጠቀሱት አገልግሎቶች ባሻገር የብሄረሰቡን ባህል አመላካች እንደሆነ በመስክ ቆይታዬ ታዝቤያለሁ። በመሆኑም፣ በሌሎች አካባቢዎች «ግቡ ቡና ጠጡ!» ተብሎ እንግዶችን መጋበዝ እንደተለመደው ሁሉ፣ በአርጎባ ብሄረሰብ ዘንድ ደግሞ «ግቡ ከሌ ይነጠፍላችሁ!» ይባላል፤ ከዚህም በተጨማሪ፣ በሌሎች አካባቢዎች፣ ወደ ቤት የተጋበዘ እንግዳ የተፈላለትን ቡናና የቡናውን ሥርዓት ተመልክቶ ቢጋገርቹ ዘንድ ምን ያህል እንደተከበረ ወይም እንዳልተከበረ እንደሚረዳው ሁሉ በአርጎቦች ዘንድ ደግሞ የተነጠፈለትን ከሌ ዕዳት (አዲስነት)፣ አንድም ትልቅነት ተመልክቶ ጋባገርቹ ለእርሱ ያላቸውን አክብሮት

ሊረዳ ይችላል። ምክንያቱም፣ አዲስና በመጠኑ ትልቅ የሆነ ከሌ ያለ በቂ ምክንያት ከተሰቀለበት ግድግዳ ሊወርድ አይችልምና።

የአርጎባ ብሄረሰብ አባላት ውስጣዊ ስሜታቸውን በምርቃት ወይም በዕርግማን ለመተንፈስ ሲፈልጉ በንግግራቸው መካከል ከሌን ይጠቅሳሉ። ከዚህም አንጻር፣ የሚወዱትንና የሚያከብሩትን ሰው «ጎንህ ከከሌ አይዋል!» በማለት በአንዳች ደዌ (በሽታ) እንዳይያዝና ጎኑ ከመኝታ እንዳይውል ሲመኙለት፤ በአንጻሩ፣ የሚጠሉትን ሰው ደግሞ «ጎንህ ከከሌ ይዋል!» በማለት ይረግሙታል። ከዚህ አገላለጽ፣ ከሌ፣ አንዳች መጥፎ ሁኔታን ወክሎ እንደቀረበ ልብ ይሏል። ይኸው መጥፎ ሁኔታም ደዌ (በሽታ) እንደሆነ በማብራሪያው ተጠቅሷል።

ከሌ፣ በአርጎባ ብሄረሰብ ዘንድ የሰዎችን ባህርይ አመላካች እንደሆነም ይታመናል። ይህንንም ያልኩበት ምክንያት፣ የተጠኚው አካባቢ ሴቶች የማይታመንን ወንድ ባህርይ ለማጉላት ሲሉ በቃል ግጥማቸው እንደሚከተለው ስለሚቀኙ ነው።

«<u>የውሻ ከሌ ነህ</u> ሳይሰገድብህ፣
ለዚችም ለዚያችም ይዋልላል ልብህ»

(አዕንኡቱ የኔ ነው፣ መሬማ ሁሴን፣ ታህሳስ 17/2008ኧ ዝ/ራ)

በቀረበው ቃልግጥም የተጠቀሰው ተባዕት ምን ዓይነት ባህርይ እንዳለው ለመረዳት የተሰመረበትን ሃረግ ማጤን ይኖርብናል። ሃረጉ በተለዋጭ ዘይቤ የተዋቀረ ሲሆን፣ የከሌውን ባህርይ ለሰውዬው እንዳለበለው ልብ ይሏል። ምክንያቱም፣ ሃረጉ «ነህ!» የሚልን የመሆንን አመላካች ግስ በተዋቃሪነት አካትቷልና። ከዚህም አንፃር፣ ሰውዬው ማለት የውሻ ከሌ ማለት እንደሆነ እንረዳለን። ይህ ማለት ደግሞ የውሻ ከሌ ለመስገጃነት አያገለግልምና ሰውዬውም ለክብርና ለቁምነገር የማያጨት ዓይነት ሰው ነው ማለት ነው። ለክብር ያላበቃው ምክንያትም በቃል ግጥሙ ሁለተኛ ስንኝ ላይ እንደተጠቀሰው ከአንድ በላይ ሴቶችን መመኘቱና አመንዝራነቱ ነው። ይህ ማብራሪያም የSchelerethን 7ኛ ሞዴል፣ «ባህርይ አመላካችነት» ለማጤን በአስረጅነት ሊጠቀስ እንደሚችል ልብ ይሏል።

በአርጎባ ብሄረሰብ ዘንድ፣ ከሌ፣ ለግጭቶች አንዳች መፍትሄን ሊያመጣ የሚችል ቁስ እንደሆነም ይታመናል። ከዚህም አንጻር፣ በሁለት ሰዎች (ለአብነት በባልና በሚስት) መካከል ግጭት ሲነሳ ሦስተኛ ሰው በዳኝነት ገብቶ ነገሩን ለማብረድ፣ በብረሄረሰቡ ብሂል «... (አስኪ) ነገሩን ከሌ ይንካው!» በማለት ያሳስባቸዋል። «ነገሩን ከሌ ይንካው» ማለቱም የተጋጩት ሰዎች በተነጠፈ ከሌ ላይ በሚቀመጡበት ወይም በሚተኙበት ጊዜ የግጭታቸውን መንስዔ በሰከነ አዕምሮ ስለሚያስቡት በግጭቱ ከመቀጠል ይልቅ ወደ መፍትሄው ይመጣሉ ብሎ በማመኑ ነው። አንድም የተጋጩት ሰዎች ነገሩን በአዕምሯቸው ይዘውት ወደ አንድ መኝታ (ወደተነጠፈ ከሌ) መሄዳቸው አይቀርምና በዚያ መፍትሄው ይገኛል ብሎ በማሰቡ ነው። ምክንያቱም፣ የተጋጩት ሰዎች ምንም እንኳ ቢነራረፉም ባልና ሚስት ናቸውና በሚተኙበት ቦታ ፍቅር ሊሰሩ ይችላሉ። የሚሰሩት ፍቅር ደግሞ በልባቸው የቋጠሩትን ቂም አስፈትቶ በፋንታው የመተሳሰብና የመተዛዘን ስሜትን ይሞላበታል። ወዲያውም ያጋጫቸውን ነገር ያስረሳቸዋል። ከዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ጉዳይ፣ ከሌው (ምንጣፉ) በተጠኚው

ብዜረሰብ እምነት አንዳች መፍትሄን ሊያወርድ እንደሚችል ነገር መቆጠሩን ነው። ይህም «ቁሶች የተለጣፊ ጸጋ ባለቤት ናቸው!» በማለት Prown (1982:3) ያቀነቀነውን ትውር እንድናወሳ ይጋብዘናል (2.2.3ን ይመለከቷል)።

ከሌ፣ ዓይነቱ ይለያይ እንጂ በየትኛውም የኢኮኖሚ ደረጃ (ድሃ፣ መካከለኛ ነዋሪና ሃብታም)[33] ላይ ባለ ሰው ቤት ሊገኝ ይችላል። ለዓይነቱ መለያየትም ምክንያቱ የባለቤቶቹ የኢኮኖሚ (የሃብት) ደረጃ እንደሆነ ልብ ይሏል። ይህም ሲባል፣ ዝቅተኛ የሃብት መጠን ያለው ሰው (ድሃው) ከዓመት አንድ ጊዜ እንኳ (ከታላላቅ የሃይማኖት በዓላት በአንዱ) የፍየል ግልገል የማረድ ወይም የፍየል ቅርጫ የመካፈል አጋጣሚውን ስለማያጣ በቤቱ የፍየል ከሌ (አማካይ ዋጋ፣ 25.00 ብር) አይጠፋም። በአንፃሩ፣ የጥጃና የወይፈን ከሌ (አማካይ ዋጋ፣ 65.00 ብር) ብዙም ባይባልም የትልቅ ላም/በሬ ከሌ (አማካይ ዋጋ፣ 90.00 ብር) ደግሞ በመካከለኛ የሃብት ደረጃ ላይ ባለው ሰው ቤት አይጠፋም። ከዚህ ባለፈ፣ የተጠቀሱትን የሁሉንም እንስሳት እንዲሁም የግመልን ከሌ (አማካይ ዋጋ፣ 110 ብር) ጨምሮ ሃብታም በሚባለው ሰው ቤት ማግኘቱ የተለመደ ነው። ይህ ጉዳይ የሰዎች የኢኮኖሚ ደረጃ የቁሶች ባለቤት የመሆንን ወይም ያለመሆንን ነገር ሊወስን እንደሚችል ያስገነዝባል። አንድም፣ Sophia (2004) እንደገለፀቸው (2.1ን ይመለከቷል) በአንድ ቤት ውስጥ ያሉ ቁሶችን ተመልክቶን (አጢነን) የቤቱን ባለቤት የሃብት (የኢኮኖሚ) ደረጃ መገመት እንደሚያስችል አመላካች ነው።

ከእንጨት የተሠራ ቁስ

ብርኩማ (ወንቃፊሎ)

ብርኩማ (ለአንድ ሰው መገልገያ)

ብርኩማ (ለሁለት ሰው መገልገያ)

[33] የሃብት ደረጃ ምደባውን ከብዜረሰቡ አባላት ጋር ተወያይቼ የሰራሁት ሲሆን ፤ በብዜረሰቡ ዘንድ፣ «ድሃ» የሚባለው፣ በጣም አነስተኛ የእርሻ መሬት ያለው፣ ከእርሷም የሚያገኘው ለዓመት ቀለቡ እንኳ የማትበቃው፤ ጉልበቱን በመሸጥ ለተጨማሪ ገቢ ደፋ ቀና የሚለው ዓይነት ሰው ነው። «መካከለኛ ነዋሪ» የሚባለው ደግሞ በጣም ብዙ (የተትረፈረፈ) ሃብት ባይኖረውም ለዓመት ጉርሱ ሊበቃው የሚችል ገቢ ያለው፤ መጠነኛ መሬትና በጣም ብዙ እንስሳት ያሉት ሰው ነው። በአንጻሩ፣ «ሃብታም» የሚባለው ደግሞ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ሃብቱ የሚራቡ እንስሳት ያሉት ሰው ነው። በአንጻሩ፣ «ሃብታም» የሚባለው ደግሞ በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ሃብቱ የተመሰከረለት፣ ሠፊ የእርሻ መሬት፣ የሚታሰቡ ከብቶችና የሚጫኑ ግመሎች ያሉት፤ መርጦ የሚበላና የተሻለ የሚለብሰው ዓይነት ሰው ነው።

ብርኩማ (ወንቃፊሎ)፣ በመባል የሚጠራው ቁስ የእርጎባ ብሄረሰቦች (ሴቶቹም ሆኑ ወንዶች - ዕድሜ ሳይለይ) በሚተኙበት ጊዜ በትራስነት የሚገለገሉበት ቁስ ሲሆን ፤ ከላይ በመስሎቹ እንደተመለከተው ሁለት ዓይነት ቅርጽ አላቸው። ቅርጹም የሚወሰነው ሊጎተራላቸው ባለ የሰው ቁጥር ነው። ከዚህም አንጻር፣ በስተግራ ያለው (20-25 ሳ.ሜ. ከፍታ፣ 25-30 ሳ.ሜ. ርዝመት) ለአንድ ሰው ብቻ አገልግሎት ሲሰጥ በስተቀኝ ያለው ደግሞ (20-25 ሳ.ሜ. ከፍታ፣ 60-80 ሳ.ሜ. ርዝመት) ለሁለት ሰዎች (ለባልና ለሚስት) አገልጎሎት ይሰጣል።

አሰራሩን ስንመለከት፣ በመጀመሪያ፣ በምስሉ ለተመለከቱት ቅርጽ ሊሰማሙ የሚችሉ (ወፍራም ወይም በሁለት በኩል ባላ ያሉት ቀጭን) የወይራ፣የዋንዛ ወይም የዕድ እንጨቶች ከሚገኙበት ቦታ ተፈልገው ይመጣሉ። ከዚያም፣ እንጨቶቹ ሳይደርቁ በሰላ መጥረቢያ እየተጠረቡ (በተለይ በስተግራ ያለው) ቅርጽ እንዲይዙ የሚደረግ ሲሆን ፤ ውበትና ጥንካሬ እንዲኖራቸውም በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ቅባት (ቅቤ፣ ሞራ፣ ዘይት፣ ወ.ዘ.ተ.) ይቀባሉ። ከዚያም፣ ለአገልግሎት የሚበቁ ሲሆን፣ በሽያጭ ከ20.00 ብር እስከ 25.00 ብር ሊያወጡ ይችላሉ።

ብርኩማ፣ በብሄረሰቡ ዘንድ ለትራስነት ከማገልገሉ ባሻገር ባህላዊ የሆኑ አስተሳሰቦችም ይገለፀበታል። ለአብነት፣ ለሁለት ሰዎች አገልግሎት የሚሰጠው ብርኩማ «ፍቅርን ይጨምራል!» ተብሎ እንደሚታሰብ አህመድ መሐመድ (ታህሳስ 20/2000፣ አሞዬ ሠርጤ) ገልፆልኛል። እንዲህም ሊታሰብ የቻለበት ምክንያት፣ እንደ አህመድ መሐመድ ማብራሪያ ፣ቁሱን በትራስነት የሚገለገሉበት ተቃራኒ ፆታ ያላቸው ሰዎች በመሆናቸው፣ አንድም፣ የትራሱ መጠን ብዙም የሚያዝናና ባለመሆኑ፣ የተንተራሱት ሰዎች መቀት መጋራታቸው የግድ በመሆኑ ነው (እንደላይኛው)። መቀት ከተጋሩ ደግሞ በመካከላቸው ከፍተኛ የመፈላለግ ስሜት ይፈጠራልና ፍቅራቸው ይጨምራል።

ብርኩማ ወይም የብርኩማ አጠቃቀም በእናትና በልጅ መካከል ያለን/የነበረን ግንኙነት የማመላከት ችሎታ እንዳለውም በብሄረሰቡ አባላት ዘንድ ይታመናል። ይህም የሆነበት ምክንያት፣ የብርኩማን አጠቃቀም፣ ልጆች (ሴቶችም ሆኑ ወንዶች) ከልጅነታቸው ጀምረው የሚለማመዱት ከመሆኑ አንጻር ሲሆን ፤ በተለይም ሴት ልጅ በእናቷ የእለት ከዕለት ክትትልና ቁጥጥር የምትካነው በመሆኑ ነው። ከዚህም አንጻር፣ ወ/ሮ የውብዳር አሊ እንደገለፀልኝ፣ አንዲት ልጅ፣ የብርኩማ አጠቃቀሟ ታይቶ «እናቷ ቀጥታ ያሳደገቻት!» (ግንቦት 6/1999፣ ጮምዬ) በመባል መገሳ ሊቀርብላት ወዲያውም እናቷን ልታስመሰግን ትችላለች። በአንጻሩ ደግሞ፣ «ያልተቀጣች!፣ ሚዳ ላይ ያደገች!» (እንደላይኛው) ተብላ እራሷንም ሆነ እናቷን ልታስወቅስ ትችላለች። ወንዱ ልጅም እንዲሁ።

ከብርኩማ አጠቃቀም አንጻር የሚሰነዘረው ትችት በተለይም በአማትና በምራት ዘንድ ገንኖ ይታያል። አማት፣ የልጇ ሚስት (ምራቷ) ተቀጥታ ማደግ/አለማደጓን የምታረጋግጥበት ወዲያውም ትችቷን የምትሰነዝርበት አንዱ አጋጣሚ የልጂቱ የብርኩማ አጠቃቀም ነው።

በመሆኑም፣ አማት፣ ምራቷን በቤቷ በምታስተናግድበት ወቅት ማታ ቅቤ ቀብታት ታድራለች። ታዲያ በጠዋት ሲነሱ ያቺ ቅቤ ከልጂቱ ራስና ከትራሱ (ከብርኩማው) አልፋ ምንጣፉን (ከሌውን) ከነካችው «አዬ እናት...! ፤ ... አይ ልጅ አስተዳደግ ...! ተዚችው ቅቤ ብሳ

የከሌ እራት አደረገቻት!» (እንደላይኛው) በማለት ምራቷንና የምራቷን እናት በነገር ሸንቆጥ ያደርጋሉ::

በአርጎባዎች ባህል፣ ብርኩማ፣ እንደሥጦታ የሚቀርብ ቁስ ሲሆን፣ የሚቀርበውም ለሴቶች ነው:: በመሆኑም፣ ሴት ልጅ ትዳር መስርታ የእናቷን ቤት ትታ ወደ ባሏ ቤት ስትሄድ ከእናቷ ዘንድ ሥጦታው ይበረከትላታል:: ከዚህም ባሻገር (በ3.2.2.2. እንደተጠቆመው) ባል ከማግባቷ በፊት በአካባቢዋ ያሉና የምታቀርባቸው ወንዶች ካሉ ከእነርሱ ዘንድም በሰርጓ ዋዜማ (በአጮምያው ዕለት) ሥጦታው በድብቅ ሊቀርብላት ይችላል:: ከዚህም አንጻር፣ ብርኩማ፣ እናቶች ለሴት ልጆቻቸው፣ ወንዶች ደግሞ ለሴት ጓደኞቻቸው ያላቸውን ፍቅር መግለጫ እንደሆነ መረዳት ይቻላል:: የስጦታው ተቀባይ ሴት ልጅም የስጦታውን ሰጭ አካል ሁሌም የምታስታውስበት እንደሆነ ልብ ይሏል::

ብርኩማን አስመልክቶ ከላይ የቀረበው ትንታኔ የSchelerethን 3ኛ፣ 7ኛ እና 8ኛ ሞዴሎች (2.2.5ን ይመለከቷል) ለማጤን በአስረጅነት ሊቀርብ ይችላል:: ምክንያቱም፣ ብርኩማ፣ የብሄረሰቡን ባህል፣ ባህርይና የእርስ በርስ መስተጋብር ያመላክታልና::

ከዚሁ ጋር ተያይዞ፣ ብርኩማ በሥጦታነት የሚበረከተው ለሴት ልጅ በጋብቻዋ ዕለት በመሆኑ Sophia (2004) እንደጠቆመችው (2.1ን ይመለከቷል) ቁሶች ማህበራዊ ደረጃን ሊያመላክቱ ይችላሉ የሚለውን ትውር ያስረግጥልናል:: ምክንያቱም፣ ሴቷ ልጅ የሥጦታው ባለቤት ልትሆን የቻለችው ከአንድ ማህበራዊ ደረጃ (ከህጻንነት ወይም ከሴተ ላጤነት) ወደ ሌላ ማህበራዊ ደረጃ (ባለትዳርነት) በተሸጋገረችበት ሰዓት ነውና::

ከድንጋይ የተሠራ ቁስ

ቀንዲል

ባህላዊ መብራት (ቀንዲል)

ቀንዲል፣ በአርጎባ ብሄረሰብ ዘንድ መብራትን (ብርሃንን) ለማግኘት የሚያገለግል ቁስ ሲሆን፤ ከድንጋይ፣ ከሞራና ከሸማ ገመድ ይሰራል::

የቀንዲልን አዘጋጃጀት ስንመለከት፣ በመጀመሪያ፣ መጠኑ በአማካይ 15 ሣ.ሜ. ወርድ፣ 20 ሣ.ሜ. ርዝመትና 15 ሣ.ሜ. ቁመት የሆነና ሊጠረብ የሚችል ድንጋይ ይፈለግና ይመጣል። ከዚያም፣ በሹል ብረት (መሮ) እና በመዶሻ በመታገዝ የድንጋዩ መሃል ይቦረቦርና ይለሰለሳል። ድንጋዩ በዚህ መልኩ ተቦርቡሮ ክብ ወይም አራት መዓዘን ቅርጽ ከያዘ በኋላ ከሸማ የተሠራ ገመድ ከድንጋዩ መሃል ላይ አቁሞ በመያዝ በዙሪያው የቀለጠ የክብት ሞራ (ስብ) ይሞላል። ከዚያም ሞራው በጎደጎደው ክፍል ፈስሶ ከረጋ በኋላ ገመዷን ደግፎ የሚይዛት ሲሆን ፤ ገመዷም፣ ሞራውን በመጠጣት ለመለኮስ (ለመንደድ) ትዘጋጃለች። ተገልጋዩ ሰውም የሸማ ገመዷን በእሳት በመለኮስ ለረኽርም ጊዜ ሊገለገልበት ይችላል።

የቀንዲል መብራት የአሠራር ጥበብ ከላይ እንደተመለከተው ቀላል ወይም በማንኛውም ሰው ሊሠራ የሚችል ቢመስልም በማንኛውም ሰው ቤት ግን ሊገኝ አይችልም። ይልቁንም፣ በአንዳንድ ሃብታም ሰዎች ቤትና በመስጊዶች አካባቢ እንጂ። ለዚህም፣ አቶ ኢብራሂም እንድሪስ እንደምክንያት የጠቀሱልኝ ሞራውን ማግኘቱ የማይቻል ከመሆኑ አንፃር ሲሆን (ግንቦት 15/1999፤ አሠኔ አገር)፣ ቁሱን ሃብታም እንጂ ድሃ እንደማይጠቀምበት ለማስረዳት «... ድሃውማ እንኳን የሚያበራው የሚበላውስ ከወዴት ያመጣል!» በማለት ገልፀውልኛል (እንደላይኛው)። ከዚህም ገለፃ፣ Sophia (2004) እንደጠቆመችው (2.1ን ይመለከቷል) ቁሶች፣ የባለቤታቸውን የኢኮኖሚ ደረጃ ሊያመላክቱ እንደሚችሉ መገንዘብ ይቻላል።

ቀንዲል፣ በአርኃባ ብዜረሰብ ዘንድ ብርሃንን ለማግኘት የሚረዳ ቁስ ከመሆኑ ባሻገር የተለያዩ መልዕክቶችን ወክሎ በብዜረሰቡ ዘወትራዊ ንግግር ሊቀርብ ይችላል። የሚከተለው ቃልግጥምም ለዚሁ አስረጅ ነው።

«ቀንዲል መብራት ያለው አብርቶ በላሽ፣
እኔ በጨለማ አልጎመጎምኩሽ»

(ታሪኩ ገበየሁ፣ ታህሳስ 26/2000ኧ ሃርቡ)

የቃል ግጥሙ ተናጋሪ ይህንን ስንኝ ሊቋጥርበት የቻለበት ምክንያት (ዐውዱ) የሚወዳትን ነገር ግን መውደዱንና ማፍቀሩን እንኳ ያልገለፀላትን ልጃገረድ በሌላ ሰው በመቀማቱ (በመቀደሙ) ሲሆን ፤ የተቀማበትም ምክንያት፣ ከግጥሙ አማራያዊ ትርጉም አንፃር የቀንዲል መብራት በእጁ ባለመኖሩ ነው። እማሬያዊው ወይም በግልጽ የተላለፈው መልዕክት የቀንዲል መብራት ያለመኖር ችግር ቢሆንም ፍካሬያዊውና በድብቅ ሊተላለፍ የተፈለገው መልዕክት ግን የሃብት፣ የጉልበት፣ የእንደበት፣ ወዘተ. ባለቤት ያለመሆን ችግር ነው። ከዚህም አንፃር፣ የግጥሙ ተናጋሪ መውደዱን ያልገለጸበት ኋላም የሚያፈቅራትን ልጅ የተቀማበት ምክንያት፣ በጨለማ የወከለውንና እርሱ የሚገኝበትን አስቸጋሪ ሁኔታ (ሁለተኛውን ስንኝ ይመለከቷል) የሚያስወግድበት (የሚቀይርበት) አቅም (የገንዘብ፣ የጉልበት አቅም) ስለሌለው ነው። አንድም፣ መውደዱን በውስጡ ያልጎመጎመበት ምክንያት አንደበቱ የረታ ባለመሆኑ እንደሆን ልብ ይሏል። ከዚህም መልዕክት አንጻር፣ ቁሶች፣ ለአንዳች ነገር ውክልና

ሊቆሙ ወይም በተምሳሌትነት ሊጠቀሱ እንደሚችሉ (የSchelerthን የ«ተምሣሌታዊነት» ሞዴል ያስታውሷል) መገንዘብ እንችላለን::

ከአፈር የተሠራ ቁስ

ቦለቅያ

ቦለቅያ (የጭስ መሞቂያ)

ቦለቅያ፣ የአርጎባ ብሄረሰብ ያገቡ ሴቶች ውበታቸውን ለመጠበቅ የሚገለገሉበት የጭስ መሞቂያ ቁስ ሲሆን ፤ ጭሱ «ወይባ ጭስ» በመባል ይታወቃል:: «ወይባ ጭስ» የተባለበትም ምክንያት ሴቶቹ የሚሞቁት «ወይባ» የተባለን እንጨት ፍላጭ በመሆኑ ነው:: የጭሱ ሥያሜ በወይባ ብቻ ይጠራ እንጂ ከወይባ ባሻገር ሚጤ፣ ቀጋና መልሆ የተባሉ እንጨቶችም አገልግሎት ላይ ሊውሉ ይችላሉ::

የቦለቅያን አሠራር አስመልክተው ወ/ሮ ከድኛ ኢብራሂም እንደገለፁልኝ፤ በመጀመሪያ፤ በቤት ጓዳ ውስጥ ጥልቀቱ ከ40-50 ሣ.ሜ.፣ ዲያሜትሩ ደግሞ ከ50-60 ሣ.ሜ. የሚሆን ክብ ጉድጓድ ይቆፈራል:: ከዚያም፣ ከጉድጓዱ ወለል ወደ ላይ አንድ ሥንዝር (ከ20-25 ሣ.ሜ.) ተለክቶ በዚያ ላይ ከ3-5 እንጨቶች (ለእግር ማሳረፊያ) ይረበረባሉ:: በተመሳሳይ መልኩ በጉድጓዱ ከንፈርም (በከፊል ወደ ውጭ ወጥተው፣ በከፊል ደግሞ ገባ ብለው የሚያርፉ) ከ3-7 እንጨቶች ለመቀመጫነት ይረበረባሉ:: በቀሪው የጉደጓዱ ከንፈር ደግሞ ከፍታው ከ40-45 ሣ.ሜ. የሚደርስ የመደገፊያ አንድም ከጉድጓዱ ውስጥ የሚጨሰው ጭስ እንዳይወጣ የመከላከያ ግድግዳ ዙሪያውን ይሠራል:: ይህ ሁሉ ከተደረገ በኋላ የጉድጓዱ የውስጥና የውጭ ክፍሎች በጭድ (በሳር) በተቦካ ጭቃ ይመረጋሉ:: በሂደትም፤ የጉድጓዱ የውስጥ ክፍል ቅባታቸው በወጣላቸው የሰሊጥና የኑግ ድፍድፍ ተለቅልቆ ለአገልግሎት ይውላል::

የበለቅያ አጠቃቀሙን ስንመለከት ደግሞ ሂደቱ የሚከተሰውን ይመስላል። በመጀመሪያ፣ ጭስ የሌለው የከሰል እሳት (ፍም) ይጫርና በጉድጓዱ ወለል መሃል ላይ ይቀመጣል። ከዚያም በቀጫጭኑ የተፈለጠ የወይባ፣ የሚጤ፣ የቀጋ ወይም የመልሆ እንጨቶች እሳቱ ላይ ይማገዳሉ። በመቀጠልም፣ የምትሞቀው ሴት ልብሶቿን አወላልቃ በጉድጓዱ ከንፈር ላይ በመቀመጥ እግሮቿን በጉድጓዱ ውስጥ በተረበረቡት እንጨቶች ላይ ታሳርፋለች። ደረቷን ደግሞ ከፊት ለፊቷ ለመደገፊያና ጭስ እንዳይወጣ ለመከላከያ በተገነባው ግድግዳ ላይ ታስደግፋለች። ከዚያም፣ ከአንገቷ በላይ ብቻ በማስቀረት ሌላውን የሰውነቷን ክፍልና የመደገፊያ ግድግዳውን በመጀመሪያ በኪዳን (በሸማ ልብስ) ከዚያ በላይ ደግሞ በከሌ ትሸፍናለች። ይህንንም የምታደርገው ከጉድጓዱ ውስጥ የሚጨሰው ጭስ ወደውጭ ሳይወጣ ራቁት ሠውነቷን በደንብ እንዲያጥነው ሲሆን፤ በዚህ መልኩ ከሰላሳ ደቂቃ እስከ አንድ ሰዓት ያህል እየሞቀች ልትቆይ ትችላለች። በመጨረሻም፣ ከምትሞቅበት ቦታ ተነስታ ገላዋን በቀዝቃዛ ውሃ በመታጠብ ወይም ደግሞ እንዲሁ ላቧን በማብረድ ልብሶቿን ለባብሳ ወደተለያዩ ስራዎቿ ልትሰማራ ትችላለች።

ከፍ ሲል የተጠቀሰውን ባህላዊ ቁስና የእንፋሎት እጥበት ዘዴ ያገዙ ሴቶች (ቁሶች ማህበራዊ ደረጃን እንደሚያመለክቱ ልብ ይሏል) ሁሉም በማንኛውም ሰዓት ሊገለገሉበት ቢችሉም፣ በተለይ፣ በጫጉላ ቤቷ ያለች ሙሽራና የወለደች ሴት (በአራስነቷ) እንዲያዘወትሩት (በቀን እስከ ሦስት ጊዜ) ይመከራሉ። ይህም የሆነበት ዋነኛ ምክንያት ወ/ሮ አረጋሽ ይመር የተባሉ ቃል አቀባዬ እንደገለፀልኝ የወይባ ጭስ ለሰውነት ጥንካሬን ይሰጣል ተብሎ ስለሚታመን ነው (ሚያዚያ 20/1999፤ አሬራ ነቸሮ)። ጥንካሬን የመስጠት ደረጃውን (አቅሙን) ሲገልፀም፡-

> *... እኛ ባገራችን የቤት ግድግዳችን ጢስ ቲመታው ባሳር (በአሳር) ነው እሚፈነቀለው፤ ይጠነክራል፤ ልፈንቅለው ብትል በጅ አይልህም። ጢስ የመታው ሰውነትም እንደሱ ነው። ማናቸውን ግድግዳ ግን ጢስ ታይመታው ብትነካው ብርግግ ብርግግ ነው እሚለው (እንደላይኛው)*

በማለት ጭስ የሞቀን ሰውነት ጭስ ከጠገበ የቤት ግድግዳ ጋር በማነፃፀር ከወይባ ጭስ የሚገኘውን የጥንካሬ ደረጃ ገልፀውልኛል።

በተመሳሳይ መልኩ፣ ወ/ሮ ዘውዴ መሐሌ የተባሉ ቃል አቀባዬ ደግሞ ከወይባ ጭስ የሚገኘውን ጥንካሬ ሲገልፁ ክብረ ንፅህናዋ የተገሠሠ ሴት ልጅ እንኳ ጭሱን በተደጋጋሚ ብትሞቅ ከመጀመሪያው (ከተፈጥሯዊው) ያልተናነሰ የሰውነት ጥንካሬ ሊኖራት ይችላል በማለት አስረድተውኛል (ሚያዚያ 20/1999፣ አሬራ ነቸሮ)። በዚህ ጊዜ ታዲያ «ወንዶች ለጭሱ ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል?» ብዬ ጠይቂያቸው ነበር። በምላሹም ከፍ ሲል ከጠቀሱት እውነታ ጋር አያይዘው «... ባሎች፣ ሚስቶቻቸው ሁልጊዜ ጭሱን እንዲመቱ ይፈልጋሉ!» (እንደላይኛው) ሲሉ አጫውተውኛል። መፈለጋቸውንም፣ ለጭስ የሚሆነውን እንጨት ከዱር ፈልገው በማምጣት ይገልፀዋል፤ ወይም ደግሞ ጭስ የማይሞቁ ሚስቶቻቸውን በነገር ወረፍ በማድረግ ይገልፀዋል በማለት አብራርተውልኛል። ለአብነትም «ቦለቅያውን ሁሉ ዓይጥ ወለደበት!» በማለት ሚስቶቻቸው የመሞቂያ ቁሱን (ጉድጓዱን)

ካለመጠቀማቸው ወይም ዘወር ብለው ካለመጎብኘታቸው የተነሳ ዓይጥ እንደተራባበት በመግለጽ እንደሚናገሩ ወ/ሮ ዘውዴ መ.ሐ (እንደላይኛው) ጠቁመውኛል።

ለቦለቅያ ወይም ለወይባ ጭስ ወንዶች ያላቸውን አመለካከት ከራሳቸው አንደበት ለመስማት በመፈለግ ጥያቄውን ለአቶ ሠይድ አህመድ አንስቼላቸው ነበር። በምላሹም፣ በአካባቢው እንደተረት የሚጠቀስንና በባልና በሚስት መካከል ተከወነ የሚባልን የቃል ግጥም ምልልስ አንስተው እንደሚከተለው ገልፀውልኛል።

ወይዘሮዋ ከባለቤታቸው ጋር እየተኙ ነገር ግን ባላወቁት ምክንያት ባለቤታቸው ምንም ዓይነት የፍቅር ጨዋታ ሊያጫውቷቸው አልቻሉም። በዚህ ጊዜ ታዲያ ምቹ አጋጣሚ ይጠብቁና፣

«ሲተኛ እንደራሳ ሲበላ እንዳንበሳ
ይሸው ሰባት ቀኔ ተኝቼ ስነሳ»

(ሠይድ አሕመድ፣ ታህሳስ 20/2000፣ ንብራ)

በማለት ባለቤታቸውን በነገር ይወርፉና የውስጣቸውን ይተነፍሳሉ። ይህን የሰሙ አባወራም በምላሹ፣

«እንኳን ሰባት ቀን ቢሆንሽ ሰላሳ
ምነው ባንቺ ጉያስ ጢስ አይጤስምሳ»

(እንደላይኛው)

በማለት ለፍቅር ጨዋታቸው መቋረጥ ምክንያቱ የእርሷ ጭስ አለመሞቅ እንደሆነ ይገልፀላታል። ወዲያውም፣ የቀድሞው የፍቅር ጨዋታቸው እንዲቀጥል ከፊለገች ሰውነቷን በጭስ መመታት እንዳለባት ያሳስቧታል። ይህም ንግግራቸው ወንዶች ለቦለቅያ (ለወይባ ጭስ) ያላቸውን አዎንታዊ አመለካከት አስረጅ ነው የሚል እምነት አለኝ።

የወይባ ጭስ፣ ሰውነትን ያጠራል፣ ንፁህ ያደርጋል፣ ውበትንም ያላብሳል ተብሎም ይታመናል። ይህንን ጉዳይ ለማብራራት ወ/ሮ አረጋሽ ይመር የተባሉ ቃል አቀባዬ በአካባቢያቸው ተከወነ የተባለን ክስተት በአብነት ጠቅሰው እንደሚከተለው ገልፀውልኛል።

... ሴትዮዋ፣ ዘላለም ጢስ ያልሞቀችውንና በነጋ እምትሞቀውን 'ኑ ጢስ ግቡ!' አለቻቸው አሉ። እነሱም በአርጎባ ጢስ ገቡ አሉ። ከሌ ተሸፋፍነው። ተዚያ ሴትዮዋ ቅጠል ያዘችና የዚችንም ላብ በቅጠል ተቀብላ እዚች ታኖራለይ። የዚያችንም ላብ ትቀበልና ተዚያ ታኖራለይ። ተዚያ ቆይቶ ምን ሆነ አሉ፣ ጢስ መቃ የማታውቀው ሴት ላቧ ትል ፈጠረ አለኝ 'ጉድና ጅራት ...' ጢስ በነጋ እምትሞቀው ደሞ ውሃይቱ ኮለል እንዳለይ ተቀመጠይ (ሚያዚያ 20/1999፣ አሬራ ነቸሮ)።

ከላይ የቀረበው ጥቅስ በተጠኚው አካባቢ ስለቦለቅያ ወይም ስለወይባ ጭስ ሲወራ ዘወትር እንደተረት የሚነገር ክስተት ሲሆን ጭስ በሚሞቁና በማይሞቁ ሴቶች መካከል የሚታየውን የሰውነት ንጽህና ልዩነት በግልጽ አመላካች ነው። ክስተቱም፣ ጢስ የሚሞቁት በመሞቁ እንዲቀጥሉ የሚያበረታታ፣ በአንፃሩ፣ የማይሞቁት ደግሞ መሞቅ እንዲጀምሩ የሚያነሳሳ መሆኑን መረዳት ይቻላል።

የወይባ ጭስ የሰውነትን ንጽህና ለመጠበቅ እንደሚያገለግል ሲገልፁ፤ ሌላኛዋ ቃል አቀባዬ፤ «ቤትኽ ተተጠራረገ ሽረሪት፣ ትል ምናምን አያፈራም፤ ሴትም ጢስ ከሞቀይ ሠውነቷ ይጠዳልኧ ጅስሟ (ጤናዋ) ይጠበቃልኧ ምንም ቆሻሻ ነገር አይዛትም» (ወ/ሮ ዘውዱ መሐሌ፤ ሚያዚያ 20/1999፣ አሬራ ነችሮ) በማለት ጭስ የምትሞቅን ሴት የገላ ንጽህና ከተጠረገ ቤት ንጽህና ጋር በማነጻጸር አስረድተውኛል።

የወይባ ጭስ ከፍ ሲል ከተጠቀሱት አገልግሎቶች ባሻገር ህጻናት ከተወለዱ ጀምሮ እስከ ሰባተኛ ሳምንታቸው (ከዚያ በኋላ ምች ያማታቸዋል ስለሚባል አይሞቁም) ድረስ ቢሞቁ ያፋፋቸዋል ተብሎ ይታመናል።

ቦለቅያ፣ ከተዘረዘሩት አገልግሎቶቹ አንጻር፣ በአርጎባ ብሄረሰብ ዘንድ በሁሉም ቤት ማለት በሚያስደፍር ሁኔታ ይገኛል። ከዚህም አልፎ ተርፎ፣ በአጎራባች ከተሞችም፣ ለአብነት፣ ሃርቡ፣ ኮምቦልቻ፣ ደሴ፣ ከሚሴ፣ ወዘተ. አገልግሎት ላይ እየዋለ እንደሆነ ወ/ሮ አረጋሽ ይመር ጠቁመውኛል (ሚያዚያ 20/1999፣ አሬራ ነችሮ)። ይህንን ጉዳይ በሰፊው መመልከት የሚፈልግ አጥኚ፣ በመዲናችን በአዲስ አበባ ከሚደረጉት የእንፋሎት ዕጥበቶች (Steam Bath) እና በፊኒሽ አሜሪካዎች ዘንድ ከሚዘወተረው የሳውና ዕጥበት (Sauna Bath) ጋር በማነፃፀር ሰፋ ያለ ጥናት ማድረግ ቢችልና በ«ይሁንታው» በሚጠቁማቸው ሀሳቦች መነሻነት የሚመለከታቸው አካላት እንቅስቃሴ ቢያደርጉ፣ ቦለቅያ፣ ቱሪስትን በመሳቡና ገቢ በማስገኘቱ ረገድ ብዙ ሊሰራበት ይችላል የሚል እምነት አለኝ።

ከቅል የተሠራ ቁስ

ቅል

የመጠጫ ቅል

የፈሳሽ መያዣ ቅል

ቁሳዊ ባህል፣ ሰዎች በአካባቢያቸው የሚገኙትን ንጥረ ቁሶች ተገልግለውና አካባቢያዊ በሆነ ዕውቀት ተመርተው የሚሠሯቸው (Objects made by man) ወይም ካለመኖር ወደ መኖር የሚያመጧቸው ቁሶች እንደሆኑ ብዙ ምሁራን ይስማማሉ (Prown, 1982:2፤ Glassie,

1994:41፣ Cleary, ዘመኑ አልተጠቀሰም)። የዚህ ብያኔ እውነታነት እንዳለ ሆኖ፣ ሰዎች ተፈጥሯዊ ነገሮችን በማሻሻል ወይም በመለወጥ (Objects modified by man) ቁሳዊ ባህልን እንደሚመሠርቱ (Cleary, ዘመኑ አልተጠቀሰም) ልብ ይላል።

ሰዎች ተፈጥሯዊ ነገሮችን በማሻሻል ወይም በመለወጥ ከሚሠሯቸው ቁሳዊ ባህሎች አንዱ ከላይ በምስሉ የተመለከተው ቅል ነው። ምክንያቱም፣ ቅሉ፣ ተፈጥሯዊ ሲሆን ሰዎች በቀዬአዊ ዕውቀታቸው ተመርተው ባህላዊ ቁስ አድርገውታልና።

ቅል፣ በአርጎባ ብሄረሰብ ዘንድ ብዙ አገልግሎትን የሚሰጥ ቁስ ሲሆን ከአገልግሎቶቹ የተነሳ የተለያዩ ሥያሜዎች ይሰጡታል። ለአብነት እንደ ወ/ሮ የውብዳር አሊ (ግንቦት 6/1999፣ ጮምዬ) ገለጻ፣ የመጠጫ ቅል፣ የመቅቢያ ቅል፣ የማለቢያ ቅል፣ የመግፊያ ቅል ወ.ዘ.ተ. የሚሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

ቅል፣ ከተፈጥሯዊ ቁስነት ወደ ባህላዊ ቁስነት የተቀየረበትን ሂደት (አሠራሩን) ስንመለከት ወ/ሮ አንሻ እንድሪስ (ግንቦት 16/1999፤ አሠኔ አገር) እንደገለፀልኝ፣ በመጀመሪያ ቅሉ ከጓሮ ወይም ከሚገኝበት አካባቢ ተቆርጦ ይመጣና ወዲያውን በአርጥብነቱ ከላይ ከአንገቱ ላይ በቢላዋ ይቆረጣል። ከዚያም፣ ውስጠኛው ክፍል እንዲደርቅና ፍሬው በቀላሉ እንዲወጣ ፀሃይ ላይ (ለሁለት ወይም ሦስት ቀናት) ይቆያል። ከደረቀ በኋላም፣ ውሃ ይሞላና ተከድኖ ለተወሰኑ ቀናት (ለሁለት ወይም ሦስት ቀናት) እንዲቆይ ይደረጋል። ይህም የሚሆንበት ምክንያት የቅሉ የውስጥ ክፍል በተፈጥሮ መራራ ነውና ይህንን ምሬቱን በውሃው አጥቦ ለማስወጣት ነው። ምሬቱ በዚህ መልክ ከፀዳ በኋላ ተገልጋዮቹ አካባቢያዊ ዕውቀታቸውን ተጠቅመው ግራዋና «ምሳና» በተባሉ ቅጠሎች በተደጋጋሚ ጊዜ ያጥኑታል። ወዲያውም ወይራ፣ ጥንጁት፣ ጫባ የተባሉ የሚጨሱ ቅጠሎችንና እንጨቶችን በማጨስና በማጠን ቅሉ ጥሩ ሽታ እንዲኖረው ያደርጋሉ። ከዚያም፣ በየተወሰኑ የጊዜ ሂደቶች ተመሳሳይ የማጠን ተግባሩን እየከወኑ ለተለያዩ አገልግሎቶች ይጠቀሙበታል። እንዳስፈላጊነቱም፣ የቅሉን አፍና መቀመጫ በስፌት በመስፋትና የተለያዩ ቅባቶችን በመቀባት ቅሉ ውበት እንዲኖረው ያደርጋሉ።

ቅል፣ በተጠኚው ብሄረሰብ የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች ሳጤን ከቅርፁ አንፃር የሚወሰን ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ይህንንም ያልኩበት ምክንያት ከላይ በምስሉ እንደተመለከቱት ሰፋ ያለና ሆድ ያላቸው ዓይነት ከሆኑ ለውሃ፣ ለሊጥ (ቡሆ)፣ ለዱቄት፣ ለወተት፣ ለማርና ለቅቤ መያዣነት ሲያገለግሉ፤ በአንፃሩ፣ በመጠን አነስተኛና ከሆድ ይልቅ አንገት ያላቸው ከሆኑ ደግሞ ለውሃና ለሌሎች ቀዝቃዛ ፈሳሾች (ወተት፣ ቡቅሪ፣ ወ.ዘ.ተ.) መጠጫነት፣ አንድም፣ እንጀራ በሚጋገርበት ጊዜ ሊጡን ምጣዱ ላይ ለማስፋት (ለማዞር) ሲያገለግሉ በመመልከቴ ነው።

ቅል ከጓሮ ወይም ከቅርብ አካባቢ ተቆርጦ በቀላሉ አገልግሎት ላይ ከመዋሉ አንጻር በየትኛውም የሃብት ደረጃ (ድሃ፣ መካከለኛ ነዋሪ፣ ሃብታም) ላይ ባለ ሰው ቤት ሊገኝ ቢችልም አገልግሎቱ ግን ከባለቤቱ የሃብት (የኢኮኖሚ) ደረጃ አንጻር የሚወሰን ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ይህንንም ያልኩበት ምክንያት፣ በድሃው ቤት፣ ሆደ ሰፊው ቅል ውሃ፣ ሊጥና ዱቄትን በመያዝ አገልግሎቱ ተወስኖ ሲቀር፤ በሃብታሙና «እላቢ ባለው» (የሚታለቡ ላሞችና ግመሎች ባሉት)

ሰው ቤት ግን ከዚህ አገልግሎቱ ባሻገር ማር፣ ወተት፣ ቅቤና ሌሎች የወተት ተዋጽኦዎችን ሲይዝ በመታዘቤ ነው። ይህም፣ቁሶች በአንድ ግለሰብ በባለቤትነት ከመያዛቸው ባሻገር ከሚሰጡት አገልግሎት አንጻር የግለሰቡን የኢኮኖሚ ደረጃ ሊያመላክቱ እንደሚችሉ አስረጅ ነው።

5.2. የናሙና የማጌጫ ቁሶች ትንተና

ይህ ክፍል ናሙና የማጌጫ ቁሶች በአባሪ 2 ከቀረቡት ስብስቦች ተመርጠው የተተነተኑበት ሲሆን ከሚውሉበት የሰውነት ክፍል አንጻር በተለያዩ ክፍሎች ተመድበዋል።

የአንገት ጌጦች

ሙስቡሃ

የብር ሙስቡሃ

የእንጨት ሙስቡሃ

የፕላስቲክ ሙስቡሃ

The 'whatness' of an object can be learned through the 'whyness' of it ... knowledge about an object is based on understanding or recognizing the causes of that object"

(Turan (1990) ውስተ Osman (2004, ገፅ አልተሰጠውም)

ከላይ ያቀረብኩትን ትውር ያስቀደምኩበት ምክንያት በመስክ ቆይታዬ ከዚህ በታች የተጠቀሰውን ቃልግጥም በሰማሁበት ወቅት መረጃን ለማግኘት ስለተገለገልኩበት ነው።

«ምን ያደርግልሻል የማተብ ድግሉ
አንዱ ይበቃሻል ከጠበቀ ውሉ»

(ሲራጅ አስማኤል፣ ሚያዚያ 18/1999ኛ. ፈጠቆማ)

ይህንን ቃልግጥም የሰማሁት (በአጋጣሚ) ከአቶ ሲራጅ አስማኤል አንደበት ሲሆን፣ በግጥሙ ውስጥ «ማተብ» የሚለው ቃል መጠቀሱ አስገርሞኝ (ተጠኚዎቼ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ከመሆናቸው አንፃር) ማብራሪያን በመሻት ስለ ማተቡ ምንነት

እንዲያስረዱኝ፣ «ቁሱ (ማተቡ) ለምን በግጥሙ ውስጥ ተጠቀሰ? በዚህ አካባቢስ ለምን አገልግሎት ላይ ዋለ? መነሻ ምክንያት አለው ወይ?» የሚሉ የ«ለምን»ን ጥያቄዎች ሠነዘርኩላቸው። ለምላሻቸው መንደርደሪያ እንዲሆንም፣ እኔ ባደኩበት አካባቢ (ጎንደር) አንድ ሰው ባዶ አንገቱን (ያለማተብ) ከሆነ «አስላም አንተ ሆንክ!» እንደሚባል አያይዤ ገለጽኩላቸው።

በዚህ ጊዜ ታዲያ፣ የቃል ግጥሙ ከዋኝ ላይሆኑ አብረውን የነበሩት የልዩ ወረዳው የሕዝብ አደረጃጀት ቢሮ ኃላፊ፣ አቶ መሐመድ ጀማል፣ በግራኝ አህመድ ጦርነት ጊዜ ተከወነ የሚባልን ክስተት በማንሳት ላነሳኋቸው ጥያቄዎች የሚከተለውን ታሪካዊ ማስረጃ አቀረቡልኝ።

> *... በርግጥ አንተ እንዳልከው ማተብ የአስላም ባህል አይደለም። ነገር ግን በዚህ አካባቢ የተለመደበት ምክንያቱ በግራኝ ጦርነት ወቅት አስላሞች በክርስቲያን ታጣቂዎች እንዳይገደሉ ማተብ በአንገታቸው በማሰር ክርስቲያን ይመስሉና ህይወታቸውን ያተርፉ ነበር። መነሻው ይህ ታሪክ ነው። ... ከጦርነቱ በኋላ ምን ሆነ መሰለህ ... 'ማተቡ የክርስቲያን ነው' በማለት አሱን ለመሸፈን በገመዱ ላይ መስብሃ የተባለ ጌጣጌጥ እያስገቡ ማንጠልጠል ጀመሩ፣ ... አሁን ሁሉም ያስረዋል፣ ያጌጥበታል (ሚያዚያ 18/1999ኛ ፈጠቶማ)።*

ከቀረበው የአቶ መሐመድ ጀማል ገለጻ፣ በተጠኚው አካባቢ «ማተብ» በመባል የሚጠራው ቁስ «መስብሃ» የተባለው (ከላይ በምስሉ የተመለከተው) ቁስ እንደሆነና በአካባቢው በባህላዊ ቁስነት አገልግሎት መስጠት የጀመረውም ከግራኝ አህመድና ከክርስቲያኖች ጦርነት ወዲህ እንደሆነ ተጠቁሟል።

መስብሃ በአርጎባ ብሄረሰብ ዘንድ በዋናነት በአንገት ጌጥነት የሚያገለግል ቁስ ሲሆን የሚሠራውም ከብር፣ ከደረቅ ፕላስቲክ እንዲሁም ከእንጨት ከተገኙ ብይ መሰል እንክብሎችና ከገመድ ነው።

አሠራሩን ስንመለከት፣ በመጀመሪያ እንክብሎቹ ብር በማቅለጥና እንጨት በመቅረጽ ይዘጋጃሉ። በአንጻሩ ከደረቅ ፕላስቲክ የሚገኙት እንክብሎች ደግሞ በማሽን የሚሠሩ ስለሆኑ ከሰቅ (ከገበያ) ይገዛሉ። ከዚያም ለማንጠልጠያ የሚሆን ቀጭን ገመድ ይፈተልና በእንክብሎቹ ቀዳዳ በማስገባት የማስካካቱ ሥራ ይሠራል። ከዚያም አንገት ላይ በማጥለቅ በጌጥነት ያገለግላል።

የመስብሃ ጌጥ፣ ሲሠራ ከሚስካኩት እንክብሎች ቀለም አንጻር ቢጫ መስብሃ፣ ቀይ መስብሃ፣ ባሪያ (ጥቁር) መስብሃ ወ.ዘ.ተ. እየተባለ የሚጠራ ሲሆን ከሚሠራበት ንጥረ ቁስ አንጻር ደግሞ የብር፣ የእንጨት ወ.ዘ.ተ. እየተባለ ይጠራል።

መስብሃ ከሚሰራበት ንጥረ-ቁስ አንጻር ስያሜው እንደተለያየ ሁሉ የሚያጌጥበት ወይም የሚገለገልበት ግለሰብም ሊለያይ እንደሚችል ልብ ይሏል። ልዩነቱም፣ በስያሜ ማህበራዊ ደረጃ የሚገለጽ ነው። ማለትም፣ መስብሃው ከፕላስቲክ የተሠራ ሆኖ እንክብሎቹ ትንንሾች ከሆኑ (አማካይ ዋጋ 4.00 ብር) የሚያጌጡባቸው በእድሜንት ደረጃ ላይ ያሉ ሰዎች (ሁለቱም ያታዎች) ሲሆኑ መጠናቸው ከፍ ከፍ ያለው (አማካይ ዋጋ 8.00 ብር) ደግሞ ያገቡ ሴቶች ያጌጡበታል። በአንጻሩ፣ መስብሃው የተሰራው ከብር እንክብሎች ከሆነ (አማካይ ዋጋ

110.00 ብር) ያገቡ ሴቶች በተለይም በጫጉላ ጊዜያቸው የሚያጌጡበት ሲሆን፣ ከዚህም አንፃር «የጫጉላ ጌጥ» በመባል ይታወቃል፣ «መሸለሚያ»ም ይባላል። ሌላው፣ መስቀሃው የተሠራው ከእንጨት ከሆነ (አማካይ ዋጋ 15.00 ብር) የጌጥነት ባህርይው ደብዘዝ ከማለቱ የተነሳ የሚገለገሉበት ታላላቅ ሴቶች (ባልቴቶች) ናቸው። ከዚህም ባሻገር፣ በብሄረሰቡ ዘንድ ከፍ ያለ ማህበራዊ ደረጃ ያላቸው አበጋሮች (ባህላዊ ዳኞች) ይገለገሉበታል። ሲገለገሉበት ግን በጌጥነቱ ሳይሆን በባህላዊው የማስታረቂያ ሥርዓት ሂደት «በሌ» ከተባለው ቁስ ጋር (3.2.2.1ን ይመለከቷል) በአንድነት በማያያዝ መሃላን ለማስፈፀም እንደሆን ልብ ሊባል ይገባዋል። የእንጨት መስቀሃ ከተጠቀሱት ሰዎች በተጨማሪ ታላላቅ የሃይማኖት አባቶችም በዱአ (በጸሎት) ጊዜ በእጃቸው ይዘው በማሻሸት እንደሚገለገሉበት ሳይጠቀስ የማይታለፍ ነጥብ ነው።

ከፍ ሲል ከቀረቡት የመስቀሃ ዓይነቶች መካከል ከፕላስቲክ የሚሰራውና እንክብሎቹ ትንንሽ የሆኑት «ጥይት ጤማ» የሚል ተጨማሪ አካባቢያዊ ሥያሜ ሲኖረው (በደቡብና በኦሮሚያ ክልል «ጨሌ» ይባላል) በእጮኛሞች መካከል እንደስጦታ ሊቀርብ ይችላል። ቁሱ በስጦታነት ሲቀርብ ታዲያ ከሌሎቹ ዓይነቶች በተለየ መልኩ እንክብሎቹ በስጦታ አቅራቢው ሰው ተቆጥረው (ተመጥነው) የሚቀርቡ ሲሆን የሚለካውም በተቀባዩ አንገት ነው። የመለካቱ ምክንያት ደግሞ መምህር አህመድ መሐመድ እንደገለፀልኝ ሥጦታ ሰጭው በተቀባዩ የወደፊት ሕይወት የመወሰን ሥልጣን (ኃላፊነት) እንዳለው ለማመልከት ነው (ሚያዚያ 18/1999፤ ፈጠቆማ)። ቀጣዩ ቃልግጥም ተያይዞ ከቀረበው ማብራሪያ ጋር ይህንኑ ጉዳይ ይበልጥ ያጎላዋል የሚል እምነት አለኝ።

«ያንገትሽ መስቀሃ ላንገቱ ልክ ነው
ከዚያ የተረፈ በጥሶ መጣል ነው»

(አንድሪስ አብዱ፣ መሐመድ ጁሃርና ሌሎች እየዘፈኑ ሲከውኑ የሰማሁት፣ ግንቦት 8/1999፣ ጮምዬ)

የቃል ግጥሙ ተናጋሪ በቀጥታ ሊያስተላልፈው የፈለገው መልዕክት የእንገቱ መስቀሃ ልክ (የዙር መጠን) ከእሷ (ካፈቀራት፣ ካጫት ልጅ) አንገት መስቀሃ ጋር እኩል እንደሆነ በመጠቆም ምናልባት ከልክ ያለፈ ካለ ግን አላስፈላጊ እንደሆነ ማሳወቅ ነው። ቀጥተኛ መልዕክቱ ይህ ይሁን እንጂ በድብቅ ማስተላለፍ የፈለገው መልዕክት ግን በአንገቷ መስቀሃ የተመሰለችው ልጅ በአንገቱ መስቀሃ ለተመሰለው ለእሱ (የSchelerethን የ«ተምሳሌታዊነት» ሞዴል ያስታውሷል) እንጂ ለሌላ ያልተፈጠረች፣ የፍቅሩ እኩያ፣ የፍቅሩ እቻ እንደሆነች ማመላከት ነው። አንድም፣ መልዕክቱ ዛቻ የተቀላቀለበት እንደሆነ ልብ ይሏል። ዛቻውም፣ በእሷና በእሱ የፍቅር ጉዳይ ሌላ ሰው ጣልቃ ከገባ እርምጃ ሊወሰድበት እንደሚችል (የቃል ግጥሙን ሁለተኛ ስንኝ ያጤኗል) የሚያስጠነቅቅ ነው።

ስለ መስቀሃ የቀረበውን ትንታኔ ከማጠቃለሌ በፊት ሁለት ነጥቦችን ለማንሳት እወዳለሁ። የመጀመሪያው ነጥብ ስለመስቀሃ (ማተብ) ታሪካዊ አመጣጥ አቶ መሐመድ ጀማል ያቀረቡት ማስረጃ የSchelerethን 9ኛ ሞዴል (2.2.5ን ይመለከቷል) ለማጤን

በአስረጅነት ሊጠቀስ ይችላል የሚለው ነው። ምክንያቱም «ቁስ (መስቀሃው) ከየትኛው ማህበረሰብ ፈለቀ?» ብለን ብንጠይቅ በግራኝ ጦርነት ጊዜ በተጠኚው አካባቢ የነበሩትን የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች በመረጃነት ያጣቅሳልና።

ሁለተኛው ነጥብ ደግሞ፣ ከፕላስቲክ እንክብሎች የሚሠራውን መስቀሃ (ጌጥ) የሚመለከት ሲሆን፤ ይህ ጌጥ የተሰራበት ንጥረ ቁስ የማሽን ውጤት ቢሆንም የተጠኚው ብሄረሰብ አባላት ግን የእነሱን ባህል አጉልቶ እንዲያሳይ ማድረጋቸውን የሚጠቅስ ነው። ይህም፣ ቁሳዊ ባህል በእጅ የተሰሩትን ቁሶች ብቻ ሳይሆን የአንድን አካባቢ፣ ቡድን (folk group) ወይም ብሄረሰብ ባህል ማጉላት እስከቻሉ ድረስ በማሽን የተሰሩትንም ሊያካትት ይችላል የሚለውን በ"Folklore (EtLi 621)" ትምህርት ያገኘሁትን ዕውቀት የሚያስረግጥ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

ብር ብስ

የአንገት ጌጥ፣ ብር ብስ

በአርጎባ ብሄረሰብ ዘንድ አንዲት ሴት ልጅ ከታጨችበት ዕለት ጀምሮ እስከ ዕድሜዋ መጨረሻ ድረስ ከምታጌጥባቸው የተለያዩ የአንገት ጌጦች መካከል ብር ብስ ተጠቃሽ ሲሆን የሚሠራውም ከብር ነው።

አሠራሩን ስንመለከት፣ በመጀመሪያ፣ የእጅ ባለሙያው «ጠገራ ብር» በመባል የሚታወቀውን ብር (ማርትሬዛ) ከገበያ በመግዛት ያስባስባል። ከዚያም በጠገራ ብሩ ላይ ያለውን ምስል አቀማመጥ (ለዕይታ) በመጠበቅ ከላዩ ላይ የማንጠልጠያ ገመድ ማስገቢያ ቀለበት በቀላጭ ያያይዛል። ይህ በቀላጭ የተያያዘ ማንጠልጠያም ጥንካሬ ይኖረው ዘንድ የብረት ብናኝ «ዱቄት» ይነሰነስበታል። በመጨረሻም በ4.2 በተገለጸው መልኩ አስፈላጊውን

የእጥበት ሥራ ካከናወነ በኋላ ለገበያ የሚያቀርበው ሲሆን በዋጋ ደረጃ በአማካይ 125.00 ብር ያወጣለታል።

ከፍ ሲል በተጠቀሰው መንገድ የተሰራው ጌጥ፣ ለአገልግሎት በሚውልበት ጊዜ፣ በቁጥር ከአንድ እስከ ዘጠኝ የሚደርሱ ብር ብሶች ከጥቁር ሻሽ ቅዳጅ በተገኘ ማንጠልጠያ ገመድ ተሰድረው በአንገት ላይ ይጠልቃሉ። በዚህም ጊዜ፣ ብር ብሶቹ የልጂቱን ውበት ከመጨመራቸው ባሻገር እጮኛዋና የእጮኛዋ ቤተሰቦች በየትኛው የኢኮኖሚ ደረጃ ላይ (ድሃ፣ መካከለኛ ነዋሪና ሀብታም) እንደሚገኙ ሊያመላክቱ ይችላሉ። ይህም የሆነበት ምክንያት ብር ብሱን በስጦታ መልክ የሚያበርክቱላት እጮኛዋና የእጮኛዋ ቤተሰቦች ከመሆናቸው አንፃር የሚያቀርቡት የብር ብስ መጠን (በቁጥር መብዛት/ማነስ) ከሃብት ደረጃቸው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ስላለው ነው። ከዚሁ ጉዳይ ሳንወጣ፣ ልጅቱ የምታጌጥባቸው የብር ብሶች መጠን ማነስ ወይም መብዛት በእጮኛዋና በእርሱ ቤተሰቦች ዘንድ ያላትን ተወዳጅነት ሊያመላክት እንደሚችል ልብ ልንል ይገባል።

ብር ብስ፣ ሴቶች ከታጨቡበት ዕለት ጀምሮ እስከ ዕድሚያቸው መጨረሻ ድረስ የሚያጌጡበት ቁስ ከመሆኑ አንፃር በአርሳባ ብሄረሰብ ዘንድ *በሰፊው* አገልግሎት የሚሰጥ ቁስ እንደሆነ በመስክ ቆይታዬ ታዝቤያለሁ። ቁሱ ለጌጥነት ካለው ተመራጭነት የተነሳ ያልታጩ ሴቶችም ሊያጌጡበት ይፈልጋሉ። ይሁን እንጂ፣ ባህሉ ስለማይፈቅድላቸው በምትኩ በአሁኑ ጊዜ በመገበያያነት አገልግሎት እየሰጡ ባሉት የአንድ እና የሃያ አምስት ሳንቲሞች ላይ የማንጠልጠያ ቀለበት (ጆሮ) እያስቀጠሉ በአንገታቸው በማጥለቅ በጌጥነት ይገለገሉባቸዋል፤ እነዚህም ጌጦች «ተሙን» (አንድ ሳንቲሚ) እና «መሐልቅ» (ሃያ አምስት ሳንቲሚ) የሚል መጠሪያ ያላቸው ሲሆን፤ ከጌጥነታቸው ባሻገር አለመታጨትን ያመላክታሉ።

ብር ብስ፣ በብሄረሰቡ ዘወትራዊ ንግግር (ለአብነት ቃልግጥም) ውስጥ እየተጠቀሰ መልዕክትን አጉልቶ የማሳየት አቅም አለው። ለዚህም የሚከተሉትን ቃልግጥሞች በአስረጅነት መመልከት ይቻላል።

ብር ብሷን አርጋ በአንገቷ ላይ
ካይኔ ጉድፍ ገባ አሻቅቤ ታይ
አሻቅቤ ቤቷን አሻቅቤ እሷን
ምን ወቅት ሥራዬን እሠራው ይሆን

(ታሪኩ ገበየሁ የነገረኝ፣ ታህሳስ 26/2000፣ ሃርቡ)

የዚህ ቃልግጥም ተናጋሪ በብር ብስ ያጌጠችን ልጅ ከተመለከተበት ጊዜ ጀምሮ ከዘወትራዊ እንቅስቃሴው (ስሜቱ) የተለየ አንዳች እንግዳ ነገር መከሰቱን ነው የገለጸው። ልጂቱን ወዷታል፣ በመሆኑም፣ ዓይኑ ለአፍታ እንኳ እሷንና ቤቷን ከማየት እንዲመለስ አልፈቀደም። በአንጻሩ፣ መሉ ትኩረቱ በእሷና በቤቷ ላይ ብቻ መሆኑ ደግሞ ግራ አጋብቶታል። በተለይም ሥራ የሚሠራበት ሽርፍራፊ ጊዜ እንኳ አለማግኘቱ አስጨንቆታል። እናም «ምን ወቅት ሥራዬን እሰራው ይሆን?» በማለት ራሱን ይጠይቃል። ለዚህ ሁሉ እንግዳ

ነገር መከሰት ምክንያት የሆነው የልጅቱ የእንገት ጌጥ፣ ብር ብስ፣ መሆኑን ስናጤን ቁሱ ምን ያህል ውበትን የሚጨምር አንድም የተመልካችን ቀልብ የመግዛት ኃይል እንዳለው እንረዳለን። የሚከተለው ቃልግጥምም ይህንኑ ሃሳብ ለማጉላት በተጨማሪነት ሊጠቀስ ይችላል።

«ብር ብሷን አርጋ ስትሄድ በበላዬ»
አንዳሮጌ ጎታ ፈረሰ ገላዬ»

(አንደላይኛው)

የቃል ግጥሙ ተናጋሪ ማስተላለፍ የፈለገው መልዕክት ብር ብሷን በአንገቷ ላይ አጥልቃ የተመለከታትን ልጅ ባየበት ቅጽበት የተሰማውን ስሜት ነው። ስሜቱንም በአነጻጻሪ ዘይቤ ተጠቅሞ የተነፈሰው ሲሆን፤ ጎታ ባረጀ ጊዜ እራሱን መሸከም አቅቶት እንደሚፈራርሰው ሁሉ የእሱም ሰውነት የተሰማውን ስሜት መቆጣጠር አቅቶት ለፍቅር እንደተልፈሰፈሰ ገልጸታል።

የእጅ ጌጥ

አምባር

ጥርጥር አምባር

ጥምዝ አምባር

በአርጎባ ብሄረሰብ ያገቡ ሴቶች ራሳቸውን (ማህበራዊ ደረጃቸውን) ከሚገልፀባቸው የተለያዩ የእጅ ጌጦች መካከል አንዱ አምባር ሲሆን፣ በአብዛኛው ከብር አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ከኒኬል ሊሠራ ይችላል።

አምባር፣ ሲሠራ ከሚይዘው ቅርፅ አንፃር በሦስት ይከፈላል። እነርሱም፣ ልሙጥ፣ ጥርጥርና ጥምዝ በመባል ይታወቃሉ። የእያንዳንዳቸውን የአሠራር ጥበብ ስንመለከት፣ ልሙጥ የተባለው አምባር ሲሠራ፣ በመጀመሪያ ርዝመቱ በአማካይ 20 ሣ.ሜ. ወርዱ ደግሞ

በአማካይ 4 ሣ.ሜ. የሚደርስ ጠፍጣፋ የብር ወይም የኒኬል ቁራጭ ይዘጋጃል። ከዚያም እርዝመቱ ከሁለት እኩል ይቆረጥና ሁለቱ ቁራጮች በተናጠል በእሳት እየተሞቁና በመዶሻ እየተመቱ የግማሽ ክብ ቅርጽ እንዲይዙ ይደረጋል። በመጨረሻም፣ ሁለቱ ቁራጮች (ግማሽ ክቦች) በአንድ በኩል ይጋጠሙና (ሙሉ ክብ ለመስራት) በሌላኛው በኩል ክፍት ይተዋሉ። ክፍት የሚተውበትም ምክንያት እየተፈለቀቁና መልሰው እየተገጠሙ በእጅ እንዲገቡ ለማድረግ ነው።

በአንዣሩ፣ ጥርጥር የተባለውን አምባር አሠራር ስንመለከት፣ በመጀመሪያ በጥላ ሽቦ ውፍረት ልክ የሚሆኑ የብር ሽቦዎች በአማካይ በ20 ሣ.ሜ ርዝመት ይቆራረጡና በእሳት እየጋሉ ይጠፈጠፋሉ። ከዚያም የተጠፈጠፈፉት ሽቦዎች ክብ ቅርፅ (ቀለበት) እንዲይዙ ይደረግና ለአንድ አምባር በአማካይ 20 የመሆኑ ቀለበቶች ቀልጦ በሚፈስ ብር ይያዛሉ። በሚያያዙበትም ቅፅበት (ቀላጩ ሣይረጋ) የብረት ብናኝ (ዱቄት) እየተነሰነሰባቸው እንዲጠነክሩ ይደረጋል። የተለየ ጌጥ እንዲኖራቸውም በየቀለበቶቹ መጋጠሚያ ላይ የቀለጠ ብር አልፎ አልፎ ጠብ ጠብ በማድረግ፣ እንደተማም ሀሰን አገላለጽ «ገብገብታ ይበጅላቸዋል» (ሚያዚያ 28/1999፣ አሞዬ ሠርጤ)። ከዚያም አስፈላጊው የእጥበት ሥራ ተሰርቶ ለአገልግሎት ይበቃሉ።

የጥምዝ አምባርን የአሠራር ሂደት ስንመለከት ደግሞ፣ በመጀመሪያ አምስት የብር ሽቦዎች በረጅሙ ይጎነጎናሉ። ከዚያም የተጎነጎኑት ሽቦዎች በአማካይ በ20 ሣ.ሜ. ርዝመት ይቆራረጡና የክብ ቅርጽ እንዲይዙ ይደረጋል። በመጨረሻም፣ ሁለቱን ክብ ቅርጽ የያዙ ጉንጉኖች በአንድ ላይ በማደራረብና በመካከላቸው የቀለጠ ብረት በማፍሰስ የማያያዙ ሥራ ይሠራል። የተጋጠሙበት ቦታም ጥንካሬ ይኖረው ዘንድ ብናኝ የብረት ዱቄት ይነሰነስበታል። ከዚያም እየታጠቡ ከፀዱ በኋላ ለአገልግሎት ይውላሉ።

ከፍ ሲል የተጠቀሱትን የአምባር ዓይነቶች መለያ ባህርያት በተናጠል ለመረዳት የእጅ ባለሙያ የሆነው አቶ አህመድ መሐመድ (ሚያዚያ 28/1999፣ አሞዬ ሠርጤ) የነገረኝን የሚከተለውን መግለጫ እንመልከት።

ልሙጥ የሚባለውና ክብር የሚሠራው የአምባር ዓይነት በክብደት ደረጃ (የጥንዶቹ) በአማካይ 16 ወቂት (1 ወቂት = 1 ጠገራ ብር (ማርትሬላ) = 28 ግራም = 4 ፈረንካ (የአፄ ኃይለሥላሴ ዘመን 50 ሳንቲም) የሚመዝን ሲሆን በዋጋ ደረጃ ደግሞ በአማካይ 1800.00 ብር ያወጣል። ከኒኬል የተሠራው ደግሞ በአማካይ 375.00 ብር ያወጣል። ተፈላጊነቱን ስንመለከት፣ ከአምስትና ከአስር ዓመታት በፊት ከሁሉም የበለጠ ተፈላጊነት የነበረው ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ ግን ከጥርጥር አምባር ቀጥሎ በሁለተኝነት ይፈለጋል።

ጥርጥር የሚባለውን የብር አምባር ስንመለከት፣ ከተጠረጠሩት ሽቦዎች አገጣጠምና በየመጋጠሚያዎቹ ከሚበጁት ገብ ገብ ያሉ ቅርፆች (ገብገብታዎች) አንፃር በአሁኑ ጊዜ ከሌሎቹ የአምባር ዓይነቶች በተለየ የላቀ ተፈላጊነት አለው። ክብደቱን ስንመለከት፣ (የጥንዶቹ) በአማካይ 12 ወቂት የሚመዝን ሲሆን ዋጋውም በአማካይ 1400.00 ብር ነው። ከኒኬል የሚሠራው ደግሞ በአማካይ 300.00 ብር ያወጣል።

አምባር፣ ምንም እንኳ ያገቡ ሴቶች ማጌጫ አንድም መለያ ቢሆንም ጥርጥር (ክብር የተሠራው) የተባለው ዓይነት ግን ሴቷ በእጮኝነት ጊዜዋ ልታጌጥበት የምትችልበት አጋጣሚ ይፈጠራል። ይህም የሚሆነው እጮኛዋ ወይም የእጮኛዋ አባት ሃብታም ከሆኑ ጌጡን ገዝተው በስጦታ መልክ ስለሚያበረክቱላት ነው። ይህ ደግሞ የልጂቱ እጮኛና ቤተሠቦቹ ያላቸውን የኢኮኖሚ ደረጃ (ሃብታምነታቸውን) ከመግለፁ ባሻገር ልጂቱ በእጮኛዋ ዘንድ ምን ያህል እንደምትፈቀር ያመላክታል።

ጥምዝ የተባለውን የአምባር ዓይነት ስንመለከት ደግሞ ከሌሎቹ በተለየ መልኩ ክብር ብቻ የሚሠራ ሆኖ እናገኘዋለን። ይህም የሆነበት ምክንያት፣ ኒኬል፣ ጠፍጣፋ (ዝርግ) ከመሆኑ የተነሳ በተፈለገው መልኩ ሊጎነጎን ስለማይችል ነው። ይህ የአምባር ዓይነት በአሁኑ ጊዜ ከሌሎቹ ያነሰ ተፈላጊነት ሲኖረው፣ ተመራጭነቱም በታላላቅ ሴቶች ብቻ የተወሰነ ነው። በክብደት ረገድ (የጥንዶቹ) በአማካይ 18 ወቲት የሚመዝን ሲሆን ዋጋውም በአማካይ 2000.00 ብር ነው።

አምባር፣ በብሄረሰቡ ዘወትራዊ ንግግር በተለይም በቃል ግጥም ውስጥ በመጠቀስ የተለያዩ መልዕክቶችን የሚገልፅ ሲሆን የሚከተሉት ቃልግጥሞች ለዚሁ ጉዳይ በአስረጅነት ሊቀርቡ ይችላሉ።

«አንድ እጇ አምባር አለው አንድ እጇ እንድድ
ልቤን አርጋው ሄደች ምስጥ የበላው ግንድ»

(አንድሪስ አብዱ፣ መሐመድ ጁሃርና ሌሎች እየዘፈኑ ሲከውኑ የሰማሁት፣ ግንቦት 8/1999፣ ጮምዌ)

በቃል ግጥሙ በግልፅ እንደተመለከተው፣ የግጥሙ ተናጋሪ ባያት ልጅ ተማርኳል። እጁንም ሠጥቷል። እጁን መስጠቱንም ያመለከተው፣ ልቡ፣ በምስጥ እንደተበላ ግንድ መሆኑን በመግለጽ ነው። ለዚህ ሁሉ የዳረገው ደግሞ የልጅቱ አጠቃላይ ውበት ቢሆንም ቅሉ በእጇ ላይ ያለው አምባር ትልቁን ድርሻ እንደሚወስድ አፅንኦት ሰጥቶ ገልፆታል። ይህም የአምባር ጌጥ ውበትን ሊጨምር እንደሚችል አመላካች ነው።

ሁለተኛው ቃልግጥም ደግሞ የሚከተለው ነው።

«ፍርድ ቤት ተቃንቶ መታሰር ባልነበር
አንቺን ከነአምባሽ ይዞ አርሂባ ነበር»
(አንደላይኛው)

የሁለተኛው ቃልግጥም ተናጋሪ በፍርድ ቤት ቆሞ እንዲፈረድበትና ወደ ወህኒ ወርዶ እንዲታሰር ባይፈልግም (ልቡ ባይቆርጥለትም) እንደላይኛው ቃልግጥም ተናጋሪ ሁሉ በተመለከታት ልጅ ውበት መማረኩን ገልጿል። የተማረከበትም አንዱ ምክንያት (ምናልባትም ዋናው) በእጇ ላይ ባለው አምባር መስህብነት እንደሆነ ለማመልከት «... ከነአምባርሽ» በማለት

ተናግሮታል። ይህ ደግሞ አምባር አንዳች መስህባዊ ባህርይ እንዳለውና ያጌጠችበትንም ሴት ውበት እንደሚጨምር አመላካች ነው።

አምባር፣ ከላይ በተደጋጋሚ ጊዜ እንደተገለጸው ያገቡ ሴቶች ማጌጫ እንድም መገለጫ ቁስ ነው። ይሁን እንጅ፣ በብሄረሰቡ ባህል ደግሞ በሃዘን ጊዜ ጌጣጌጦችን ማድረግ ከነውር የሚቆጠር ድርጊት ነውና ሃዘን የደረሰባት ሴት ከሁሉም ዓይነት ጌጣጌጧ ትርቃለች። ለአብነት (ባለትዳር ከሆነች) የእጅ አምባሯንና ሌሎች ጌጣጌጧን አወላልቃ ታስቀምጣለች። ይህ ደግሞ ከባህሏ እንዣር የሚደገፍ አካሄድ ቢሆንም በአርሷ ላይ ግን አንዳች ፈታኝ ነገር ሊያመጣባት እንደሚችል ልብ ይሏል።

> *ስሜ እመቤት አህመድ እባላለሁ። ዕድሜ 25 ነው የመኖሪያ ቦታዬ በዝሁ ቀበሌ (አሬራ ነቾሮ) ሥር ነው። .. ኑሮዬ በቃ ... ከስድስት ዓመት በፊት አባል ጋር ስኖር እሱ ገበያ ያመጣል እኔ እሸጣለሁ ... ኋላ እቃ ላምጣ ብሎ እንደሄደ በዚያው ቀረ። ... እኔም ስድስት ዓመት ጠበኩት። አሁን የአባቴም የባሌም ጌጥ (ስጦታ የሰጡኝ) አለ። ሃውልት ነው ብዬ እየቸገረኝ አስካሁን አልሸጥኩም። በዝህ መሃል ግን እህቴ ሙታብኝ ሁለት ዓመት ተደረቅ ቅል አጉራዋለሁ። የዚያን ሰዓት ታያ (ታዲያ) እንወስዳታለን ግብ ግብ ነው። ... ሴት አምባር ታላደረገይ ... በቃ ያስገድዷታል። እህሳ ...እንውሰድሽ ይሏታል። ይጠልፏታል። እኔም ሰንት ተንገላትቻለሁ። ግንሳ ብዙውን 'እህቷ ሙታ ነው!' ስለሚባል ስለዚያ ግን አልተነካሁም። ብዙ ሰው እየጠየቀ 'ዝረ አሏሚ በዝህ ነውይ ኒካዋ አለቀቃት' (ሠማንያዋ አልተቀደደ) እየተባለ እዝህ ደርሻለሁ (አመቤት አህመድ፣ ሚያዚያ 20/199፣ አሬራ ነቾሮ)።*

ከተጠቀሰው የእመቤት አህመድ የሕይወት ገጠመኝ መረዳት እደሚቻለው፣ አምባር እና ሌሎች ጌጣ ጌጦች "Ornaments communicate a meaning" እንዳለው Somjee (1993:49) የሴትን ልጅ ማህበራዊ ደረጃ አጉልተው በማሳየቱ በኩል ላቅ ያለ አስተዋጽኦ አላቸው። ይህንን አስተዋጽኦዋቸውን ደግሞ እነሱ በሌሉበት (ለምሳሌ፣ በሃዘን ጊዜ) በሴቷ ላይ የሚደርሱትን እንግልቶች ስናስብ የበለጠ እንረዳዋለን።

የወገብ ጌጦች

ሙቅዳድ

በእጅ የተሰራ ሙቅዳድ

በማሽን የተሰራ ሙቅዳድ

በአርጎባ ብሄረሰብ አንዲት የታጨች ልጅ ከምታጌጥባቸው የተለያዩ ቁሶች መካከል «መቅዳድ» የተባለው መቀነት አንዱ ነው። ይህ መቀነት በሁለት መንገድ የሚገኝ ሲሆን አንደኛው መንገድ ባህላዊ በሆነው ዘዴ የሽመና ባለሙያዎች በጣም ቀጫጭን የሆኑ ቀይ ክሮችን (ከተወሰኑ ሌላ ቀለም ካላቸው ክሮች ጋር) እንደድርም እንደማግም ተጠቅመው በማዋሃድ የሚሠሩትን ይመለከታል። ሌላኛው መንገድ ደግሞ፣ መልኩ ቀይ ሆኖ እንደ አቡጀዲድ ልብስ ስስ የሆነና በማሽን የሚሠራን ጨርቅ ይመለከታል።

ልብሱ በባህላዊም ሆነ በዘመናዊ መንገድ ይሠራ (ይገኝ) ለተጠቃሚው ብሄረሰብ ተመሳሳይ አገልግሎት ይሠጣል። ማለትም፣ የሚያጌጡበት የታጩ ሴቶች ሲሆኑ ይህንን ማድረጋቸውም መታጨታቸውን ለመግለፅ ነው።

በሁለቱም መንገዶች የሚሰሩት መቅዳዶች፣ እንደ አህመድ ሲራጅ ገለጻ፣ ተመሳሳይ መጠንና ዋጋ ያላቸው ሲሆን ከመጠን አንፃር በአማካይ «ሦስት ክንድ ከሥንዝር» (1.75 ሜትር) ርዝመትና «ክንድ ከሥንዝር» (0.75 ሜትር) ወርድ አላቸው። በዋጋ ደረጃ ደግሞ በአማካይ 15.00 ብር ያወጣሉ። ይህ የመጠንና የዋጋ ተመሳሳሉ ቢኖርም፣ በማሽን የሚሰራው መቅዳድ በአሁኑ ጊዜ የበለጠ ተመራጭነት አለው። ምክንያቱንም በጠየቅኩበት ውቅት ፋጢማ አብዱ የተባለች የቁሱ ተገልጋይ «ለማሠራት ውጣ ውረድ የለውም፣ ሽክሙም ቀሊል ነው!» በማለት መልሳልኛለች።

መቅዳድ፣ የተለያዩ መልዕክቶችን ለማስተላለፍ በብሄረሰቡ ዘወትራዊ ንግግር ሲጠቀስ ይሰማል። ለአብነት፣ የሚከተሉትን ቃልግጥሞች እንመልከት።

«ስጫኝ መቅዳድሽን አንጥፌው ልተኛ
አንቺም መሸራ ነሽ እኔም ሃዘንተኛ»

(ታሪኩ ገበየሁ፣ ጥር 2/2000፣ ሃርቡ)

የዚህ ቃልግጥም ተናጋሪ ያፈቅራት የነበረች ልጅ በሌላ ሰው በመታጨቷ ምክንያት የእሱ ሊያደርጋት አለመቻሉን የገለፀ ሲሆን፣ በመጨረሻም ተስፋ በቆረጠ ሁኔታ መቅዳዷን እንደትሰጠውና ከሃዘን እንዲጽናና ለምኗታል። መቅዳዷንም እንድትሰጠው የለመነው የእሷ ማስታወሻ ይሆነው ዘንድ በማሰብ ሲሆን፣ አንድም ለእሷ ምንም እንደማያደርግላት በማስረገጥ ነው። ምክንያቱም የእጮኝነት ጊዜዋን አሳልፋ መቅዳዷን ወደምትጥልበት የሙሽርነት ጊዜዋ ተሸጋግራለችና።

የሚከለተለው ቃልግጥም ተናጋሪ ደግሞ ከላይኛው ቃልግጥም ተናጋሪ በተለየ፣ ተስፋን በሰነቀ መልኩ እንዲህ ተቀኝቷል።

«አምባሩንም ጣይው ጠበበኝ ቢይና
ክብራውንም ጣይው ሰፋብኝ ቢይና
መቅዳዱንም ጣይው አጠረኝ ቢይና
እገዛልሻለሁ መች ጠገብኩሽና»

(አብርሃም ሙሉጌታ፣ ጥር 4/2000፣ ፈጠቆማ)

ይህ አፍቃሪ ማስተላለፍ የፈለገው መልዕክት የሚወዳት ልጅ የተለያዩ ምክንያቶችን ደርድራ ከእጮኛዋ እንድትርቅና ከእሱ ጋር አዲስ ሕይወት እንደትጀምር ማድረግ ነው። ለዚህም መክፈል የሚጠበቅበትን ዋጋ ለመክፈል መዘጋጀቱን ገልጿል። በግጥሙም ውስጥ አምባር፣ ከብራ (ቀሚስ) እና ሙቅዳድ የሚሉት ጌጦች የተጠቀሱት በአማራው የእጮኛ ጌጦች መሆናቸውን ለማመልከት ቢሆንም በፍክሬው ግን ልጂቱ ከእጮኛዋ ጋር ያላት ግንኙነት ከትግር ያልፀዳ መሆኑን ለመግለጽ ነው።

መቀነት

ከሸማ የተሰራ መቀነት

ከሃር የተሰራ መቀነት

በአርጎባ ብሄረሰብ ያገቡ ሴቶች ከሚያጌጡባቸውና በትዳር መወሰናቸውን ከሚገልፁባቸው ቁሶች መካከል አንዱ መቀነት ነው። መቀነት፣ በተጠኚው አካባቢ በሚገኙ የሽመና ባለሙያዎች የሚሠራ ልብስ ሲሆን መሰሪያ ንጥረ ቁሶቹም ድር፣ ማግና የተለያዩ ቀለማት (ቀይና ጥቁር) ያላቸው ጥለቶች ናቸው።

የመቀነትን አሰራር ስንመለከት በ4.2. የተጠቀሰውን የሽመና አሠራር ሂደት የተከተለ ሲሆን፣ ከሌሎቹ የሽመና ውጤቶች በተለየ መልኩ በባለሙያዎቹ ዘንድ ተመራጭነት አለው። ይህም የሆነበት ምክንያት፣ እንደ አቶ አህመድ ሲራጅ ገለፃ፣ «ተሉ ተጀምሮ ተሉ ስለሚቆረጥ (ቢበዛ በ4 ሰዓት ውስጥ) ነው» (ሚያዚያ 18/1999፣ አሬራ ነቸሮ)። አንድም የመቀነት ተፈላጊነቱ ከአካባቢው ነዋሪዎች አልፎ በአጎራባች ቀበሌዎችና ከተሞችም መኖሩ ነው (እንደላይኛው)። መቀነት፣ ከመጠን አንፃር፣ አማካይ ርዝመቱ ስድስት ክንድ (3 ሜትር) ሲሆን፣ ወርዱ ደግሞ አንድ ክንድ (0.5 ሜትር) ነው። ይህንን አማካይ መጠን ይዞ የሚሸመነው መቀነትም በዋጋ ረገድ በአማካይ 13.00 ብር ያወጣል።

ከተጠኚው ብሄረሰብ ባህል አንጻር፣ መቀነት፣ ወደ ሦስት ጉልቻ የምታመራ ሴት ከሠርጓ ዕለት ጀምሮ በወገቧ በመታጠቅ የምታጌጥበት ቁስ ሲሆን በእጮኝነት ጊዜዋ ትታጠቅበት የነበረን «ሙቅዳድ» የተባለ ቀይ መቀነት የምትቀይርበት ከመሆኑ የተነሳ «ሙቅዳድ አስጥል!» በመባል ይታወቃል። ይኸው «ሙቅዳድ አስጥል» በመባል የሚታወቀው

መቀነት፣ መቅዳድን ተክቶ በሴቷ ወገብ ላይ ሲውል እንዳች ውበት የመጨመር ኃይል እንዳለው ለመግለፅ፣ ብሄረሰቡ በቃል ግጥም እንዲህ ተቀኝቶለታል።

«አርባ መናም አየሁ ባንድ ቀን ሴቲት
መቀነቷን አርጋ ስትገባ እኛ ቤት»

(መሬም አብዱ፣ አንሽ መሐመድና ሌሎች እየዘፈኑ
ሲከውኑ የሰማሁት፣ ግንቦት 8/1999፣ ሥምዩ)

የቃል ግጥሙ ተናጋሪ ማስተላለፍ የፈለገው መልዕክት የትዳር አጋሩ የሆነች ሴት በወገቧ ላይ የታጠቀችው መቀነት ከሚገባው በላይ ውበት እንዳላበሳት በማመልከት ይኸው ጎልቶ የወጣው ውበቷም በእሱ ልብ ውስጥ ሠርፆ በእውኑ ብቻ ሳይሆን በህልሙም (መናም = ህልም) እየተደቀነበት እንደሆነ መግለጽ ነው።

መቀነት፣ ከፍ ሲል እንደተገለፀው፣ ለሴት ልጅ ውበት የሚያላብስ እንደሆነ ቢቀኝለትም በአሁኑ ጊዜ ግን (በመጠኑ ቢሆንም) ልኬታው በአማካይ ሦስት ክንድ (1.5 ሜትር) ርዝመት፣ አንድ ክንድ (0.5ሜትር) ወርድ ባለውና በማሽን በሚሠራ የሃር ጨረቅ እየተተካ ይታያል። ይህ ደግሞ፣ ውብሸት (1978) እና አስገደች (1986) (2.1ን ይመለከቷል) በጥናታቸው ግኝት እንደጠቆሙት፣ በእጅ የሚሠሩ ቁሶች በማሽን በሚሰሩ እቻዎቻቸው እየተተኩ ለመሄዳቸው አመላካች ክስተት ነው።

የእግር ጌጥ

አልቦ

ብቸኛው የእግር ጌጥ፣ አልቦ

በአርጎባ ብሄረሰብ ዘንድ ያገቡ ሴቶች ከሚያጌጡባቸው ወዲያውም ማግባታቸውን (ማህበራዊ ደረጃቸውን) ከሚገልፀባቸው የተለያዩ ቁሶች መካከል አንዱ አልቦ ሲሆን ከሚውልበት የሰውነት ክፍል አንፃር ሲመደብ፣ አቶ አህመድ መሐመድ እንደገለጹልኝ፣ ብቸኛው የእግር ጌጥ መሆኑ ልዩ ያደርገዋል።

አልቦ ከብርና ከኒኬል የሚሠራ ጌጥ ሲሆን አሠራሩን ስንመለከት፣ በመጀመሪያ፣ ባለሙያው ሊቀልጡ የሚገባቸውን ብሮች እንዲሁም ሊቆራረጡ የሚችሉ ኒኬሎችን ከገበያ ወይም ከሌላ አፈላልጎ ያመጣል። ከዚያም፣ የብር አልቦን ለመስራት፣ ብሩን ያቀልጥና ክብና የዲያመንድ ቅርጽ ባላቸው የብር ማፍሰሻ ቁሶች ላይ ያፈላቸዋል። ከዚያም የፈሰሱት ቀላጮች እስኪጠጥሩ በመጠበቅ ቅርጽ የማስያዙን ሥራ ይሰራና በተፈተለ ቀጭን የማግ ክር በማሰካካት በእግር ዙር ልክ እየተለኩ ይቆራረጣሉ። በመጨረሻም፣ በእግር ላይ እየታሰሩ ለጌጥነት የሚውሉ ሲሆን፤ በዋጋ ደረጃ ጥንዶቹ በአማካይ 135.00 ብር ያወጣሉ። በአንፃሩ ከኒኬል የሚሰራውን አልቦ ስንመለከት፣ በመጀመሪያ ኒኬሉ «ቀላጭ» በሚባል መቆንጠጫ ይያዝና በብረት መቀስ ይቆራረጣል። ከዚያም የተቆራረጡት ኒኬሎች እየተጣጠፉ ክብ ወይም የዲያመንድ ቅርጽ እንዲይዙ ይደረጋል። በመጨረሻም፣ በቀጭን የማግ ክር እየተሰካኩ የእግር አልቦው ይሰራና ለጌጥነት ይውላል። በዋጋ ደረጃ ስንመለከት፣ ኒኬል የተባለው ንጥረ ቁስ በርካሽ ከመገኘቱ አንፃር ከብር ከተሠራው አልቦ ጋር ሲነፃፀር ዝቅተኛ ነው። አማካይ ዋጋውም (በጥንድ) 25.00 ብር ነው።ይህ የዋጋ መለያየትም የተጠቃሚዎቹን ማንነት (ከሃብት ደረጃቸው አኳያ) በመወሰኑ ረገድ የራሱ ተጽእኖ እንዳለው ልብ ይሏል። ከዚህም አንፃር፣ በተጠኚው ብሄረሰብ ዘንድ ድሃ የሚባለው ሰው ከብር ከተሰራው ይልቅ በአብዛኛው ከኒኬል የተሰራውን አልቦ እንደሚገለገል ታዝቤያለሁ። በአንፃሩ፣ በመካከለኛ ኑሮ ደረጃ ያሉ እንዲሁም ሃብታም የሚባሉት ደግሞ ከብር የተሰራውን አልቦ ይገለገላሉ።

አልቦ፣ የእግር ጌጥ ከመሆኑና በትዳር መወሰንን ከማመላከቱ አንጻር «የእግር ብረት» (መታሰሪያ) የሚል ተጨማሪ አካባቢያዊ ስያሜ እንዳለው አቶ ተማም ሃሰን (ታህሳስ 26/2000፤ አሞዬ ሠርጤ) ገልጸውልኛል። ይህንን ሥያሜና ከስያሜው ጋር ተያይዞ በተጠኚው ብሄረሰብ የሚንፀባረቀውን ሀሳብ ለመረዳት የሚከተለውን ቃልግጥም እናጢን።

«ሃቻምና በገመድ አምና በሠንሠለት
ዘንድሮ ቁርጥ ነው ገባሽ እግር ብረት»

(አንድሪስ አብዱና ሙሃመድ ጁሃር እየዘፈኑ ሲከውኑ የሰማሁት፣ ግንቦት 8/1999፣ ሥምዩ)

የቃል ግጥሙ ተናጋሪ ወንድና ቃልግጥሙ የተነገረላት ሴት፣ እንደ ሙሃመድ ጁሃር ማብራሪያ፣ በልጅነታቸው ጣፋጭ የፍቅር ጊዜ ያሳለፉ ሰዎች ናቸው። ይሁን እንጂ፣ እነሱ እንዳሰቡትና እንዳለሙት በፍቅራቸው ሊቀጥሉበት አልቻሉም። ይልቁንም፣ ሴቲቱ በሌላ ወንድ በመታጨቷ፣ በዚያችም የሌላ ሰው የትዳር አጋር በመሆኗ ምክንያት ግንኙነታቸው ተቋርጧል። የቃል ግጥሙ ተናጋሪም ሊገልፀው የፈለገው መልዕክት ልጂቱ ከታጨችበት ጊዜ

ጀምሮ እስካገባችበት ጊዜ ድረስ በውስጡ የተፈጠሩትን የፍርሃት ብሎም የተስፋ መቁረጥ ስሜቶች ነው።

በቃል ግጥሙ የተጠቀሱት፣ ሃቻምና፣ አምናና ዘንድሮ የሚሉ ዘመን አመላካች ቃላትና ገመድ፣ ሠንሰለትና እግር ብረት የሚሉት ቁስ አማላካች ቃላት እንዲሁ ግጥሙን ለማዋቀር የታሳሩ የቃላት ክምችት ሳይሆኑ በብሄረሰቡ የጋብቻ ሥርዓት ሂደት (4.2.2.2ን ይመለከቷል) መሠረት እርስ በርስ ለመናበብና አንዳች መልዕክት ለመጠቆም የቀረቡ ናቸው። በመሆኑም፣ «ሃቻምና በገመድ» የሚለው በብሄረሰቡ የጋብቻ ሂደት የመተጫጨጊ ጊዜን የሚያመላክት ሲሆን፣ ገመዱ ልጂቱ ስትታጭ ወገቧ ላይ የሚታሰረውን «መቅዳድ» (ቀይ መቀነት) ወክሎ እንደቀረበ ልብ ይሏል። «አምና በሠንሰለት» የሚለው ደግሞ ሴቷ ልጅ የጋብቻ ቀኑ ከተቆረጠበት ጊዜ ጀምሮ በእጇ የምታሰረውን «ጥርጥር» የተባለ አምባር ይወክላል። በእንዛሩ «ዘንድሮ... እግር ብረት» የሚለው ደግሞ በጋብቻው ሂደት የመጨረሻ የሆነውን የሠርጉን ዕለት የሚጠቅስ ሲሆን፣ እግር ብረቱም የወከለው በዚሁ ዕለት መሸራዋ የምታሰረውን የእግር አልቦ ነው። የእግር አልቦው «የእግር ብረት» የተባለበትም ምክንያት ልጂቱ በትዳር መወሰኗን፣ እንደ ግጥሙ አገላለጽም፣ በብረት መታሰሯን ስለሚያመለክት ነው።

የቃል ግጥሙ ተናጋሪ በተጠቀሰው መልክ የውስጥ ሥሜቱን ሲተነፍስ፣ ያለፍላጎቷ ለሌላ ወንድ የታጨችውና ግጥሙ የተነገረላት ሴት ልጅ ደግሞ በምላሹ እንደሚከተለው በመቀኘት ለእሱ ያላትን ልባዊ ፍቅር ትገልፅለታለች።

«እግር ብረት ብገባ መች አረሳሃለሁ
እስክሰቱ ሞቴ አስታውስሃለሁ»

(አንድሪስ አብዱና ሙሐመድ ጁሃር እየዘፈኑ ሲከውኑት የሰማሁት፣ ግንቦታ 8/1999ኛ ሥምዒ)

6. ማጠቃለያና የይሁንታ ሃሳቦች

6.1. ማጠቃለያ

በመግቢያው (በ1.3) እንደተጠቀሰው የዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ዓላማ የአርጎባን ብሄረሰብ የቤት ውስጥ መገልገያና የማጌጫ ቁሶች በመለየትና በናሙና ቁሶች ላይ በማተኮር ቁሶቹን ከቁስነታቸው፣ አንድም ከባህላዊ ገጽታነታቸው አንጻር ማጤን ወዲያውም በቁሶቹና በባለቤት ብሄረሰቡ መካከል ያለን ግንኙነት አጉልቶ ማሳየት ነበር።

የተጠቀሱትንም ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ፣ አጥኚው፣ በመስክ ቆይታው የቃል መጠይቅንና ምልከታን በዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያነት ተገልግሏል። ከዚህም ባሻገር፣ የጽሁፍ መጠይቅን፣ የተተኳሪ ቡድን ውይይትንና የናሙና ጥናትን በአጋዥነት ተጠቅሟል። በእነዚህ ዘዴዎች የተሰበሰቡት መረጃዎችም በምዕራፍ ሁለት ከቀረቡት የተለያዩ ትውሮች አንጻር የተተነተኑ ሲሆን የትንተናው ውጤትም በሚከተለው መልክ ተጠቃሏል።

ይህ ጥናት በድምሩ «11» ቁሶችን በናሙናነት መርጦ ትንታኔውን አድርጓል። ከእነዚህም ውስጥ «5ቱ» የቤት ውስጥ መገለገያ ቁሶች ሲሆኑ ቀሪዎቹ «6ቱ» ደግሞ የማጌጫ ቁሶች ናቸው።

የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶችን ስንመለከት፣ ተጠኚ ብሄረሰቡ በአካባቢው በቀላሉ በሚያገኛቸው ንጥረ ቁሶች የተሠሩ፣ (ከቆዳ፣ 1፤ ከእንጨት፣ 1፤ ከድንጋይ፣ 1፤ ከአፈር፣ 1፤ ከቅል፣ 1) ሆነው ተገኝተዋል። በአንጻሩ፣ የማጌጫ ቁሶች ደግሞ በአብዛኛው ከብር (ጠገራ ብር) እንዲሁም ከነሃስ፣ ከኒኬልና ከሸማ የተሰሩ ሲሆኑ፣ ከሚውሉበት የሰውነት ክፍል አንጻር የአንገት (2)፤ የእጅ (1)፤ የወገብ (2)፤ እና የእግር (1) ተብለው ተመድበዋል።

የአርጎባ ብሄረሰብ፣ ለትንታኔ የቀረቡትን ናሙና ቁሶች ሲገለገሉባቸው ቁሶቹ መጀመሪያ ከተሰሩለት አገልግሎት ባሻገር አንዳች መልዕክትን አጉልተው እንዲያሳዩም አድርገዋቸዋል። ለአብነት፣ ቦለቅያ፣ መስብሃ፣ አልቦ፣ አምባር፣ መቅዳድና መቀነት በብሄረሰቡ ዘንድ ማህበራዊ ደረጃን አመላካች ናቸው። ከሌ፣ ቅል፣ አልቦ፣ አምባርና ብር ብስ ደግሞ የባለቤታቸውን ኢኮኖሚያዊ ደረጃ ፍንትው አድርገው የሚያሳዩ ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ ብርኩማን ብንመለከት በብሄረሰቡ አባላት ዘንድ (በተለይም በእናትና በሴት ልጇ (ልጆቿ) እንዲሁም በወንዶችና በፍቅረኞቻቸው መካከል) ያለን የእርስ በርስ መስተጋብር አጉልቶ የሚያሳይ ነው።

ይህ ጥናት የመረጣቸውን ናሙና ቁሶች በምዕራፍ ሁለት (2.2.5ን ይመለከቷል) ከተጠቀሱት የSchelereth ዘጠኝ ሞዴሎች አማካይነት ትንታኔውን እንዳደረገ ያስታውሷል። ከዚህም አንጻር፣ ሁሉም ናሙና ቁሶች ከምሁሩ «የአገልግሎት ሠጭነት» እና «መዋቅራዊነት» ሞዴሎች አንጻር ሊተነተኑ የሚችሉ አንድም የተጠቀሱትን ሞዴሎች ለማጤን በአስረጅነት የሚጠቀሱ ሆነው ተገኝተዋል። ይህም የሆነበት ምክንያት ያለአገልግሎትና ያለመዋቅር (ያለ ቅርጽ) የተሠሩ ቁሶች ባለመኖራቸው ነው።

ከዚህም በተጨማሪ የተወሰኑት ናሙና ቁሶች ለአብነት፣ ከሌ እና ቀንዲል ከምሁሩ የ«ተምሳሌታዊነት» ሞዴል አንጻር፤ ብርኩማ፣ ቦለቅያና ከሌ ደግሞ ከ«ባህላዊነት» ሞዴል አንጻር እንዲሁም ከሌ ከ«አካባቢያዊነት» ሞዴል አንጻር የሚተነተኑ ሆነው ተገኝተዋል። ከዚህም ባሻገር፣ ብርኩማና ከሌ የምሁሩን የ«ባህርይ አመላካችነት» ሞዴል የሚያጣቅሱ ሲሆኑ ብርኩማ ብቻውን ደግሞ የ«ማህበራዊነት»ን ሞዴል የሚያወሳ ነው።

ከፍ ሲል የተዘረዘሩትን ግኝቶች እና በጽሁፍ መጠይቁ አማካይነት የተሰበሰቡትን (የተጠኚ አካባቢውን ነባራዊ ሁኔታ የሚያመለክቱ) መረጃዎች መሰረት በማድረግም አጥኚው የሚከተሉትን የ«ይሁንታ» ሀሳቦች ሠንዝሯል።

6.2. የይሁንታ ሃሳቦች

በማጠቃለያው እንደተገለጸው በዚህ ጥናት በናሙናነት ተመርጠው የተተነተኑት ቁሶች ለባለቤት ብሄረሰቡ መጀመሪያ ሲሠሩ ከታለመላቸው አገልግሎት ባሻገር ባህልንም አንልተው የሚያሳዩ ናቸው። አንድም፣ ከምሁራን ትውሮች አንጻር የሚጤኑ ወይም የምሁራኑን ትውሮች ለማብራራት በአስረጂነት የሚቀርቡ ናቸው። ይህ ባህርያቸውም ላቅ ያለ ዋጋ ያሰጣቸዋልና እነርሱን የመለየቱና የመጠበቁ ሥራ ከሚከተሉት የአጥኚው የይሁንታ ሀሳቦች አንጻር ተግባራዊ ቢሆን ለማለት እወዳለሁ።

- የልዩ ወረዳው የባህልና ማስታወቂያ ቢሮ ሠራተኞች ብሄረሰቡ ለባህላዊ ቁሶቹ ያለው ግንዛቤ እንዲዳብር አመላካከቱም አዎንታዊ እንዲሆን ማስተማር ቢችሉ።
- የጽሁፍ መጠይቁን የሞሉት የልዩ ወረዳው የመስተዳድርና የባህል ቢሮ ሃላፊዎች እንደጠቆሙት የሚሊኒየሙን ባህል አከባበር አስመልክተው የብሄረሰቡን ቁሳዊ ባህሎች የመለየት፣ የመሰብሰብና የመሰነድ ሥራውን እንደጀመሩት ሁሉ ተጠናክሮ የሚቀጥልበትን ሁኔታ ቢያመቻቹ። ይህንንም ሲያደርጉ በዚህ ጥናት ሁለተኛ ምዕራፍ (2.2.7.ን ይመለከቷል) ሥር የተጠቀሱትን የቁሳዊ ባህሎች የመሰብሰቢያና የመሰነጃ ዘዴዎች አጋዥ ቢያደርጉ።
- የልዩ ወረዳው የባህል፣ የማስታወቂያና የጥቃትን ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮዎች (የጽሁፍ መጠይቁን በሞሉበት ወቅት ቃል እንደገቡት) ለብሄረሰቡ ቁሳዊ ባህሎች መፈጠር ምክንያት የሆኑትን የእጅ ባለሙያዎች የሙያ ማሻሻያ ሥልጠና በመስጠት፣ ታታሪዎችን በመሸለም፣ ለሥራቸው አስፈላጊ የሆኑ ንጥረ ቁሶችን አትርቦት በማሳደግ፣ ከምንም በላይ ደግሞ እንደፍላጎታቸው ተደራጅተው የሚሰሩበትን ሁኔታ በማመቻቸት እገዛ ቢያደርጉላቸው።
- የልዩ ወረዳው የባህል፣ የማስታወቂያና የጥቃትን ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮዎች የብሄረሰቡን ቁሳዊ ባህሎች ለሌሎች የሚያስተዋውቁበትን፣ የእጅ ባለሙያዎችን በገንዘብ ለመደጎም ገቢ የሚያገኙበትን እንዲሁም ቁሶችን ከተገልጋይ እጅ የሚያደርሱበትን አጋጣሚ፣ ማለትም ዐውደ ርዕይ (ባዛር) በተከታታይ ቢያዘጋጁ።

- የክልሉና የፌደራሉ የሬዲዮና የቴሌቪዥን ማሠራጫዎች ቁሳዊ ባህሎችን በተመለከተ ማብራሪያዎችን በማቅረብ የማስተዋወቅ ሥራዎችን ቢሰሩ::
- የቋንቋና ሥነጽሁፍ ጥናት ተቋማት እንዲሁም የባህልና ማስታወቂያ ቢሮዎች ቁሳዊ ባህሎችን የሚጠቅሱ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን፣ አጫጭር ታሪኮችን፣ ቃል ግጥሞችንና የመሳሰሉትን ቃላዊ ትውፊቶች ሰብስበው ቢሰንዱ::
- በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሥር ያሉና የቁሳዊ ባህል ጉዳይ የሚመለከታቸው የትምህርት ክፍሎች ቁሳዊ ባህሎችን ለማጥናት ተከታታይና ሰፊ የሆነን የምርምር መርሃ ግብር ቀርጸው ጥናት ቢያደርጉ::
- በትምህርት ሚኒስቴር የሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት ክፍል የመማሪያ መጻሕፍትን ይዘት በሚቀርፅበት ወቅት ቁሳዊ ባህልን ·የተመለከቱ ርዕሰ ጉዳዮችን (ለአብነት፣ የባህላዊ ቁሶችን አካባቢዊ ሥያሜ፣ አሠራር፣ ጠቀሜታ፣ ወ.ዘ.ተ.) ቢያካትት::
- ከፍ ሲል በተጠቀሱት ተቋማት (ቢሮዎች) ሥር ያሉ ባለሙያዎች በአንድ ላይ የሚሰበሰቡበትን አጋጣሚ ቢፈጥሩና በቁሳዊ ባህል ጉዳይ ዙሪያ መነጋገር ቢችሉ::

ዋቢ መጻሕፍትና ጽሑፎች

I. የአማርኛ ምንጮች

ታዬ ገብረማርያም (አለቃ)፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ ሴንትራል ማተሚያ ቤት፣ 1964።

ነጋሽ መሐመድ፤ «አርጎብኛና የአርጎቦች ህይወት በሁለት (አልዩ አምባና አዋሽ) ከተሞች ውስጥ»፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሁፍ ክፍል፣ የባችለር ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣ 1981።

አሰገደች አወቀ፤ «በሊሙ ቢልቢሉ ወረዳ የሚገኙ ባህላዊ የቤት ዕቃዎችና የአርሻ መሣሪያዎች መዘርዝር ከነአገልግሎታቸው»፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል፣ የባችለር ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣ 1986።

ከሳቴ ብርሃን ተሰማ ሀብተሚካኤል ግጽው፤ የዐማርኛ መዝገበ ቃላት፣ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1951።

ውብሸት አሰፋ፤ «የወይዛዝርት አልባሳትና ጌጣጌጥ ሥሞች በአማራው ባህል»፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የኢትጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል፣ የባችለር ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣ 1978።

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት፤ ዜና ምክር ቤት፣ የክልል አዋጆች፤ ሦስተኛ መደበኛ ጉባኤ፤ አዋጅ ቁጥር 130/1998፣ 13ኛ ዓመት፣ ቅጽ 1፣ ቁጥር 3፣ ባህር ዳር፣ መጋቢት/1998።

የአርጎባ ብሔረሰብ ልዩ ወረዳ ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት፤ «በአ/ብ/ል/ወረዳ ያለ ሕዝብ ብዛትና የእርሻ መሬት መጠን መግለጫ፤ ሃርቡ፤ ግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት፤ በማርከር ተጽፎና በኃላፊው ቢሮ ተሰጥፎ የተገኘ ሥዕላዊ መግለጫ፣ 2000።

ዮናስ አድማሱና ሌሎች፤ «አማርኛ ለኮሌጅ ደረጃ የተዘጋጀ፣» ቀ.ኀ.ሥ. ዩኒቨርስቲ፣ አርትስ ፋካልቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ ክፍል፣ ያልታተመ፣ በስቴንስል ተባዝተዉ የተጠረዘ፣ 1966።

ፈቃደ አዘዘ፤ የሥነ ቃል መምሪያ፤ አዲስ አበባ፣ ኢንተርናሽናል ጀርመናዊ የጎልማሶች ትምህርት መረዳጃ ተቋም፣ 1991።

II. የእንግሊዝኛ ምንጮች

Ames, L. Kenneth. "Meaning in Artifacts: Hall Furnishings in Victorian America." In Journal of Interdisciplinary History; Vol. IX; No. 1, PP. 19 – 46; 1978.

Bartis, Peter. Folklife and Fieldwork: A Layman's Introduction to Field Techniques. Washington; Library of Congress. 2002.

Beals, L. Ralph and Harry Hoijer. An Introduction to Anthropology. Los Angeles. University of California. 1958.

Bedaux, M.R. "Some Aspects of Present-Day Dagon Pottery: An Ethno-archaeological Approach." In Clay and Fire: Pottery in Africa. Roy, D. Christopher's (ed.); Iowa Studies in African Art. Vol. IV; pp. 109 – 128; 2000.

Bender, M.L. et.al., eds. Language in Ethiopia. London. Oxford University Press. 1976.

Bronner, J. Simon "Folk Objects." In Folk Groups and Folklore Genres: An Introduction. Elliott Oring, ed., Logan, Utah: Utah State University Press. 1986.

Cleary, Ann Mc. "Methods and Theory of Material Culture Studies." Course note –Online at-URL: http://www.blinklist.com/ artaide/ theories/(n.d.).

CSA. Federal Democratic Republic of Ethiopia. Statistical Abstract. Addis Ababa. 2006.

Dorson, M. Richard (ed.); Folklore and Folklife: An Introduction. Chicago and London; The University of Chicago Press. 1972.

Dunkan, Dorothy. The Artifact: What Can It Tell Us about the Past? Online.http://www.people.stfx.ca/istanley/material/Guidelines. html

Emerson, M.Robert. et.al., Writing Ethnographic Field Notes. Chicago. University of Chicago press. 1995.

Fleming, E. McClung. "Artifact Study: A Proposed Model." Online at; URL: http://www.jstor.or/view/00840416/ap04009/04a22260/0

Georges, A. Robert and Michael O. Jones. Folkloristics: An Introduction. Bloomington and Indianapolis. Indiana University Press. 1995.

Glassie, Henry. Material Culture. Bloomington and Indianapolis. Indiana University Press. 1999.

Hetzron, Robert. "The Classification of the Ethiopian Semitic Languages." A Paper Contributed to the Survey Monograph of the Language Survey of Ethiopia. University of California, Santa Barbara, California, April 1969.

Illinois State Museum. "Heartfelt/Handmade: 19th Century Folk Art." Online. At, URL: http// www.museum. state.il.us/ muslink /art/ htmls/hh.html

ITO, Nobuo. "Intangible Cultural Heritage Involved in Tangible Cultural Heritage." Paper at 1994 ICOMOS General Assembly. Online. Available at-URL: http://www.internatinal.icoms.org/ victoriafalls 2003/papers.

Jackson, Bruce. Fieldwork. Urbana and Chicago. University of Illinois Press, 1987.

Leslau, Wolf. "A Preliminary Description of Argobba." In Annals d' Ethiopie. Vol. 3, 1952.

Musello, Christopher. "Objects in Process: Material culture and communication." In Southern Folklore: UCLA, Vol. 49; No. 1; 1992.

Nahu Senay. "Social Organization and Status of Artisans In Emdibir Area (Gurage)." Addis Ababa University, Department of Sociology. Unpublished M.A. Thesis. 1998.

Osman, A O S "Philosophical Approach and Research Methodology for the Contextual Study of Architecture. Online. available at: URL. http://www.research.up.ac.za/2004/Faculties/EBIT/AGRT/ Researcher/23266.html

Prown, J. David. "Mind in Matter: An Introduction to Material Culture Theory and Method." Online. Available at: http:// www.jstor.org/about/ terms.html

Roberts, E. Warren. "Folk Crafts" In Folklore and Folklife: An Introduction. Dorson, Richard's ed.; Chicago and London; The University of Chicago Press. 1972.

Schlereth, J. Thomas. "Material Culture Research and Historical Explanation." Online. Available at: http:// www. jstor .org/ journals/ ucal.html.1985.

_____ "Understanding the Nine Models of Material Culture Interpretation". Online. Available at: http://www.btnep.org

Silverman, A. Raymond. Ethiopia: Traditions of Creativity. East Lansing, Michigan State University Museum, 1999.

Somjee, Sultan. Material Culture of Kenya. Nairobi. East African Educational Publishers. 1993.

Sophia, Thubauville. "Maale Material Objects in Their Social and Cultural Context". German. Johannes Gutenberg University; Institute fur Ethnologie und Africkastudien. Unpublished MA. Thesis. 2004.

Stitz, Volker. "The Western Argobba of Yifat, Central Ethiopia." In Proceedings of the First United States Conference on Ethiopian Studies. 1973, Harold, G. Marcus, ed., East Lansing, Michigan State University, 1975.

Tilley, Christopher. Material Culture and Text: The Art of Ambiguity. Lampter. St David's University College Press. 1991.

Ullendorff, Edward. The Ethiopians: An Introduction to Country and People. London, Oxford University Press. 1960.

Waugh, Daniel. "Material Culture – Objects." Online. Available at – URL: http:// www.chnm. gmu.edu/ world history sources/ unpacking /objectsmain.html

Weeks, V. Richard. Muslim Peoples: A World Ethnographic Survey. 2nded, Greenwood Press, West Pot, Vol. 1, 1984.

Yodor, Don. "Folk Cookery." In Folklore and Folklife: An Introduction. Chicago and London; The University of Chicago Press. 1972.

_____ "Folk Costume." In Folklore and Folklife: An Introduction. Chicago and London; The University of Chicago Press. 1972.

_____ "The Folklife Studies Movement." In Folk Art and Art Worlds. Viach, M. and Simon J. Bronner's, ed; Michigan; Library of Congress. (n.d).

አባሪ - 1

የአርጎባ ብሄረሰብ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶች ስብስብ

አገልግሎት	የቁሱ ሥያሜ	ተጨማሪ መግለጫ	መሠረያ ንጥረ-ቁስ	አማካይ ዋጋ	በናሙናነት	
					ተመር ጧል	አልተ መረጠ ም
ለእህል መፍጫ	ወፍጮ	-	ድንጋይ	30.00		√
	መጀ	-	ድንጋይ	5.00		√
	የወፍጮ ቋት	የእህል ማጠራቀሚያ	ድንጋይ + አፈር	-		√
	መራ	የእህል መጥረጊያ	ሣር	1.00		√
	ወንፊት	-	ሽቦ/ግራምጣ	4.00		√
	ሰፊድ	-	ሣር + ሰበዝ	2.00		√
ለእህል መውቀጫ	መጎጫ	የመውቀጫው እናት ይባላል	እንጨት	35.00		√
	መውገጫ	የመውቀጫው ልጅ ይባላል	እንጨት	5.00		√
ለምግብ ማዘጋጃ	ዳያ	የሊጥ ማበኪያ	ሸክላ	3.50		√
	የቡሆ ቅል	የሊጥ መያዣ	ቅል	2.00		√
	ምጣድ	-	ሸክላ	6.00		√
	መጎድ	የምጣዱ ክዳን	ሸምበቆ + አፈር	3.00		√
	ማዞሪያ ቅል	ሊጥ ማፍሰሻ (መቀቢያ)	ቅል	1.00		√
	ጉልቻ	-	ሸክላ	1.00		√
	ለጠብ	የእንጀራ ማውጫ ሥፌት	ሰበዝ	2.00		√
	ማሰሻ	የምጣድ መወልወያ	ሸማ	-		√
	ቶፋ	ሥጋ መቀቀያ	ሸክላ	2.50		√
	ወጫት	-	ሸክላ	2.00		√
	እቶን	ሥጋ መጥበሻ	ድንጋይ	-		√
	ብረት ድስት	-	ብረት	14.00		√
ለመመገቢያ	ሞሰብ	-	ሰበዝ	25.00		√
	እግርያ ሌማት	ባለ እግር ሌማት (ስፊት)	ሰበዝ	3.50		√
	ቆሪ	የወጥ ማቅረቢያ	እንጨት	8.00		√
			ሸክላ	2.50		√
	ማንኪያ	-	ብረት	5.00		√
			እንጨት	3.00		√
	ሰሀን	-	ኒኬል (ቸርቸር)	12.00		√
	አገልግል	ስንቅ መያዣ	ሰበዝ + ክሌ	7.00		√

... ከአባሪ 1 የቀጠለ

አገልግሎት	የቁሱ ሥያሜ	ተጨማሪ መግለጫ	መሠረያ ንጥረ-ቁስ	አማካይ ዋጋ	በናሙናነት	
					ተመርጧል	አልተመረጠም
ለመጠጫ	ፎሌ	-	ቅል	1.00	√	
	ከባያ	-	ጎማ	2.00		√
	ጣሳ	-	ቆርቆሮ	-		√
	ቃባ	ለወተት	ቅል	1.50	√	
	እብሪቅ	ማንቆርቆሪያ በመባል ይጠራል	ጎማ	-		√
ለወተትና የወተት ውጤቶች መያዣ	አኮሌ	የወተት ማለቢያ	ሰበዝ/ሣር	2.00		√
	ማርጊያ ቅል	የወተት ማርጊያ	ቅል	-	√	
	መግፊያ ቅል	የአጓት መግፊያ	ቅል	-	√	
	ናርጅ	ለቅቤ መያዣ	እንጨት	4.00		√
ለሌሎች ፈሳሾች መያዣ	ጋን / እንስራ	-	ሸክላ	7.00		√
	ቅል	-	ቅል	-	√	
	ጀሪካ	-	ጎማ	5.00		√
ለቡና ማፍሊያ፣ መጠጫና ለስርዓቱ መከወኛ	ረጀት	ብረት ምጣድ	ብረት	13.00		√
	መቁሊያ	-	እንጨት/ሸቦ	-		√
	ቡን መውገጫ	-	እንጨት	6.00		√
	ጀበና	-	ሸክላ	1.50		√
	ሥኒ	-	ብርጭቆ	2.00		√
	ረከቦት	የሥኒ መዘርጊያ	እንጨት	10.00		√
	ማጨሻ	-	ሸክላ	1.00		√
ለእህል መያዣ	አቅማዳ	ከፍየል ከሉ ብቻ ይሰራል	ከሉ	30.00		√
	ማዳበሪያ / ኬሻ	-	የማዳበሪያ/የኬሻ ገመድ	3.00		√
	ጉድጓድ	-	አፈር/መሬት	-		√
	ጎታ	-	ሸምበቆ፤ ሀረግ፤ አፈር	-		√
ለእህል መሥፈሪያ	ቀርቀቦ	-	ከሉ	12.00		√
	ዳውላ	-	ከሉ	15.00		√
	ዘንቶ	-	እንጨት	3.00		√
	እንቅብ/ጥባዎት	-	ሰበዝ/ሳር	2.00		√
	ጣሳ/ቆርቆሮ	-	ቆርቆሮ	1.00		√

... ከአባሪ 1 የቀጠለ

አገልግሎት	የቁሱ ሥያሜ	ተጨማሪ መግለጫ	መሠሪያ ንጥረ-ቁስ	አማካይ ዋጋ	በናሙናነት	
					ተመር ጫል	አልተመ ረጠም
የተለያዩ ነገሮችን ማሰሪያ	ገመድ	-	ቃጫ	1ሜ=0.50		√
			ጠፈር/ክሌ	1ሜ=3.00		
			ሲባጎ	1ሜ=1.00		
መብራትን /ብርሃንን/ ለማግኘት	ቀንዲል	-	ድንጋይ/ሞራ+ሸማ/	-	√	
	ኩራዝ	-	ቆርቆሮ፤ ሸማ	3.00		√
ጭስ መሞቂያ	ቦለቅያ /ወይባ ጭስ/	-	አፈር፤ እንጨት፤ የቅባት ድፍድፎች	-	√	
ለመተኛና ለመቀመጫ	ሃልጋ/አልጋ/	-	እንጨት+ክሌ	100.00		√
	መደብ/ወ·ጫሌ/	-	ድንጋይ+አፈር	-		√
	ክሌ	-	የፍየል ክሌ	25.00	√	
			የከብት ክሌ	90.00		
			የግመል ክሌ	110.00		
	ብርኩማ	ለትራስነት ያገለግላል	እንጨት	22.50	√	
	ወንበር	-	እንጨት+ክሌ	25.00		√

አባሪ 2

የአርጎባ ብሄረሰብ የማጌጫ ቁሶች ስብስብ

ጌጦቹ የሚውሉበት የሰውነት ክፍል	የቁሱ ሥያሜ	መሠሪያ ንጥረ ቁስ	አማካይ ዋጋ	ተጨማሪ መግለጫ	በናሙናነት	
					ተመርጧል	አልተመረጠም
ፀጉር	ወለባ	ብር	45.00	ቁንጢና ጥምዝ የሚባሉ ዓይነቶች አሉት		
		ኒኬል	8.00			√
	መንቀሻ/ማበጠሪያ	እንጨት/ሸቦ	1.00	ያላገቡ ወንዶች ያጌጡበታል		√
ግንባር	ወገሮ	ብር	27.50			
		ኒኬል	9.00			√
		ነሃስ	4.00			
ጆሮ	ጉትቻ	ብር	60.00			
	ጨልጨሌ	ብር	22.50			
		ነሃስ	5.00			√
		መዳብ	3.00			
አንገት	ብር ብስ	ብር	125.00		√	
	ብር ቁርጥ	ብር	120.00			
		ነሃስ	15.00			√
	ብር ገረዴ	ብር	225.00	በአሁኑ ጊዜ አገልግሎቱ እየቀነሰ ነው		
		ኒኬል	30.00			
		ነሃስ	25.00			
	መስብሃ	ብር	110.00			
		እንጨት	15.00		√	√
		ፕላስቲክ	6.00			
	ሳላ ፍሬ	ብር	110.00			√
	ክዳዋ/ንፍኦ፣ ሀደዴ	ብር	140.00			
		ኒኬል	50.00			√
	ድሪ/ቡርፋፍ	ብር	600.00	በአሁኑ ጊዜ አገልግሎታቸው እየቀነሰ ነው		√
	አሸን ክታብ	ብር	225.00			√
		ኒኬል	30.00			√
		ነሃስ	20.00			√
	ድንብል	ብር	210.00	ከሁክ ማውጫ ጋር አይነጣጠሉም		√
		ኒኬል	50.00			√
		ነሃስ	30.00			√

... ከአባሪ 2 የቀጠለ

ጌጦቹ የሚውሉበት የሰውነት ክፍል	የቁሱ ሥያሜ	መሠሪያ ንዋይ-ቁስ	አማካይ ዋጋ	ተጨማሪ መግለጫ	በኖሙናንት	
					ተመር ጫል	አልተመ ረጠም
አንገት	ኩክ ማውጫ	ብር	60.00	ከድንበል ጋር አይነጣጠሉም		√
		ኒኬል	20.00			
		ነሃስ	12.00			
	ተመ·ን	ብር + መዳብ	1.00			√
	መሐልቅ	ብር + መዳብ	1.50			√
እጅ	አምባር	ብር	1700.00	ልመ·ጥ፣ጥርጥርና ጥምዝ የሚባሉ ዓይነቶች አሉ·ት	√	
		ኒኬል	340.00			
ጣት	ቀለበት	ብር	40.00	ማገጃ፣ ፍዝ እንዲሁም ጨረቃና ክክብ የሚባሉ አይነቶች አሉ·ት		√
ወገብ	መ·ቅዳድ	ክር	15.00	በእጅና በማሽን ይሠራል	√	
	መቀነት	ሸማና ቀለም	13.00		√	
እግር	አልቦ	ብር	135.00	ብቸኛው የእግር ጌጥ በመባል ይታወቃል	√	
		ኒኬል	25.00			
መ·ሉ ሰውነት	ቀሚስ /ኩ·ብራ/	ሸማ	60.00			√
		የማሽን ክር	100.00			
	ኪታ	ሸማ	80.00	ታላላቅ ወንዶች ያጌጡበት ነበር		√
	ጃኖ	ሸማ	70.00	ታላላቅ ወንዶች ያጌጡበት ነበር		√
	ጉፍታ	የማሽን ክር	30.00	ያገቡ ሴቶች ያጌጡበታል		√

አባሪ 3

የእጅ ባለሙያዎች የሚገለገሉባቸው ቁሶች

የሸክላ ባለሙያዎች የሚገለገሉባቸው ቁሶች

የቁሱ ስም	መሰሪያ ንጥረ ቁስ	አገልግሎት
ደንገራ (መቆፈሪያ)	ብረት + እንጨት	አፈር ለመቆፈር
ኬሻ (ማደበሪያ)	ከኬሻ /ከማደበሪያ ገመድ/	አፈር ለመያዝ
ቀርቀቦ	ከሌ (ቁርበት)	አፈር ለመያዝ
ዋዳት	ሸክላ	አፈር ለማበጥጥ
ቆረቆንዳ	ቆረቆንዳ	የሚሰራውን ሸክላ ቅርጽ ለማስያዝ
ድንጋይ (ለስላሳና ክብ)	ድንጋይ	የሚሰራውን ሸክላ ለማለስለስ
ማሰሻ ጨርቅ	ሸማ	የሚሰራውን ሸክላ ለማለስለስ
ቢላዋ	ብረት + እንጨት	የሚሰራውን ሸክላ ቅርጽ ለማስያዝ

የሽመና ባለሙያዎች የሚገለገሉባቸው ቁሶች

የቁሱ ስም	መሰሪያ ንጥረ ቁስ	አገልግሎት
መዘውር	ሸምበቆ + እንጨት	ጥሰትን ማፍታቻ /ለማቅለም ማዘጋጃ/
ማድሪያ	ሸምበቆ + እንጨት	ድር ለማድራት
ማዳወሪያ	ሸምበቆ + እንጨት	ጥሰት ለማቅለም
እንዝርት	ቀርቀሃ + ቅል	ማግ (ጥሰት) ለማቅለም
መጠቅለያ ዘንግ	እንጨት	ድር ለማሰር
መጠቅለያ	እንጨት	የሚሠራውን ሸማ ለመጠቅለል
ደንፍ	እንጨት + ሸምበቆ	የተዘረጋውን ድር በመስመር ለመጠበቅ
መወርወሪያ	እንጨት	ቀለም (ማግ) ከግራ ወደ ቀኝ ለማመላለስ

የጌጣጌጥ ባለሙያዎች የሚገለገሉባቸው ቁሶች

የቁሱ ስም	መሰረያ ንጥረ ቁስ	አገልግሎት
ወናፍ	ከሌ+ እንጨት+ብረት	አሳት ለማንደጃ
ቀሳጭ (መቆንጠጫ)	ብረት	ብረት ቆንጥጦ ለመያዝ
ማቅለጫ ብረት	ብረት	ብር ወይም ብረት ለማቅለጥ
ማፍሰሻ ብረት	ብረት	ለተለያዩ ጌጣጌጦች ቅርጽ ማውጫ
መዶሻ	ብረት+እንጨት	ብረቶችን ወይም ብሮችን ለመቀጥቀጥ
መቀስ	ብረት	የተለያዩ ንጥረ ቁሶችን ለመቆራረጥ
ቡርሽ	እንጨት+ቀጫጭን ሽቦዎች	ጌጣጌጦችን ለማጽዳት

አባሪ - 4

የአውራ መረጃ አቀባዮች ፕሮፋይል

ሙሉ ስም	ፆታ	ዕድሜ	ብሔር	መኖሪያ አካባቢ	ቀበሌ	የሥራ ድርሻ
ሸህ አብዱራህማን መህመድ	ወ	54	አርጎባ	አሞዬ ሠርጤ	04	የሃይማኖት መሪ እና ታሪክ አዋቂ
ሸህ መህመድ አህመድ	ወ	60	»	»	»	አበጋር (አስታራቂ ዳኛ)
አቶ መህመድ አሉ	ወ	45	»	»	»	የብሄረሰቡን ባህልና ታሪክ አዋቂ
አቶ ከማል ሲራጅ	ወ	40	»	»	»	የብሄረሰቡን ባህልና ታሪክ አዋቂ
አቶ የሱፍ መህመድ	ወ	40	»	»	»	የብሄረሰቡን ባህልና ታሪክ አዋቂ
ሸህ መህመድ አሚን	ወ	55	»	»	»	የሃይማኖት መሪ እና ታሪክ አዋቂ
አቶ ሳኒያ አረባ	ወ	40	»	»	»	የቀበሌ ተጠሪ
ሸህ አህመድ ሁሴን	ወ	50	»	»	»	የሃይማኖት መሪ እና ታሪክ አዋቂ
አቶ ዑመር መሃሊ	ወ	61	»	አሬራ ነቸሮ	02	የብሄረሰቡ ተወላጅ (ነዋሪ)
አቶ አብዱ አህመድ	ወ	28	»	»	»	የብሄረሰቡ ተወላጅ (ነዋሪ)
አቶ መህመድ አቡሃምዛ	ወ	34	»	»	»	የብሄረሰቡ ተወላጅ (ነዋሪ)
አብዱ ሰይድ	ወ	22	»	ኪልኪሎ	05	የብሄረሰቡ ተወላጅ (ነዋሪ)
ጀማል አብዱልቃድር	ወ	22	»	ጎበራ	07	የብሄረሰቡ ተወላጅ (ነዋሪ)
መሬም አብዱ	ሴ	15	»	ጮምዬ	03	የብሄረሰቡ ተወላጅ (ነዋሪ)
አንሻ መህመድ	ሴ	15	»	»	»	የብሄረሰቡ ተወላጅ (ነዋሪ)
እንድሪስ አብዱ	ወ	18	»	»	»	የብሄረሰቡ ተወላጅ (ነዋሪ)
መህመድ ጁሃር	ወ	22	»	»	»	የብሄረሰቡ ተወላጅ (ነዋሪ)
ወ/ሮ አንሻ አህመድ	ሴ	40	»	»	»	የፋጢማዬ ሰርዓት አስፈጻሚ
ወ/ሮ ከሚያ አብዲ	ሴ	45	»	»	»	የፋጢማዬ ሰርዓት አስፈጻሚ
ወ/ት አሚናት አብዱ	ሴ	25	»	»	»	የብሄረሰቡ ተወላጅ (ነዋሪ)
ሸህ ጀማል የሱፍ	ወ	36	»	»	»	የቀበሌው የወጣቶች አደረጃጀት ቡድን መሪ

... ከአባሪ 4 የቀጠለ

ሙሉ ስም	ፆታ	ዕድሜ	ብሔር	መኖሪያ አካባቢ	ቀበሌ	የሥራ ድርሻ
ወ/ሮ ከድጃ ይብሬ	ሴ	35	አርጎባ	አሞዬ ሠርጤ	04	የሽንኦ ሥራ ባለሙያ
አቶ ይማም ሲራጅ	ወ	29	»	አሠኔ አገር	06	የሽመና ሥራ ባለሙያ
አቶ አህመድ መሐመድ	ወ	28	»	አሞዬ ሠርጤ	04	የጌጣጌጥ ሥራ ባለሙያ
አቶ አህመድ ሲራጅ	ወ	33	»	አፈራ ነጭሮ	02	የሽመና ሥራ ባለሙያ
ወ/ሮ አሚነት አብሪ	ሴ	35	»	አሞዬ ሠርጤ	04	የሽንኦ ሥራ ባለሙያ
ወ/ሮ ፋጡማ ሁሴን	ሴ	40	»	አሞዬ ሠርጤ	04	የሽንኦ ሥራ ባለሙያ
ወ/ሮ ዚነቱ ሸሁ	ሴ	40	»	አሞዬ ሠርጤ	04	የሽንኦ ሥራ ባለሙያ
ወ/ሪት መሪማ ሲራጅ	ሴ	28	»	አፈራ ነጭሮ	02	የሽመና ሥራ ባለሙያ
አቶ ሲራጅ አብደላ	ወ	45	»	አፈራ ነጭሮ	02	የሽመና ሥራ ባለሙያ
ወ/ሮ ፋጡማ መሀመድ	ሴ	40	»	አፈራ ነጭሮ	02	የሽመና ሥራ ባለሙያ
አቶ ተማም ሀሰን	ወ	38	»	አሞዬ ሠርጤ	04	የጌጣጌጥ ሥራ ባለሙያ
አቶ መሀመድ ሰዒድ	ወ	40	»	አሞዬ ሠርጤ	04	የጌጣጌጥ ሥራ ባለሙያ
አቶ ሰይዱ ያሲን	ወ	35	»	አሞዬ ሠርጤ	04	የጌጣጌጥ ሥራ ባለሙያ
ወ/ሮ የውብዳር ዓሊ	ሴ	40	»	ጮምዬ	03	የብሄረሰቡ ተወላጅ
አቶ ታሪኩ ገበየሁ	ወ	35	አማራ	ሃርቡ	-	የባህል ቢሮ ሠራተኛ
ወ/ሮ አረጋሽ ይመር	ሴ	40	አርጎባ	አፈራ ነጭሮ	02	የብሄረሰቡ ተወላጅ
ወ/ሪት መሪማ ሁሴን	ሴ	30	»	ጎበራ	07	የብሄረሰቡ ተወላጅ
አቶ ኢብራሂም እንድሪስ	ወ	40	»	አሰኔ አገር	06	የብሄረሰቡ ተወላጅ
ወ/ሮ ዘውዴ ሙሄ	ሴ	45	»	አፈራ ነጭሮ	02	የብሄረሰቡ ተወላጅ
አቶ ሰይድ አህመድ	ወ	40	»	ጎበራ	07	የብሄረሰቡ ተወላጅ
ወ/ሮ አንሻ እንድሪስ	ሴ	35	»	አሠኔ አገር	06	የብሄረሰቡ ተወላጅ
አቶ ሲራጅ እስማኤል	ወ	35	»	ፊጠቆማ	01	የብሄረሰቡ ተወላጅ
መምህር አህመድ መሃመድ	ወ	30	»	ፊጠቆማ	02	የብሄረሰቡ ተወላጅ
ወ/ሮ እመቤት አህመድ	ሴ	25	»	አፈራ ነጭሮ	02	የብሄረሰቡ ተወላጅ
አቶ አብርሃም ሙሉጌታ	ወ	30	አማራ	ፊጠቆማ	01	መምህር

አባሪ 5

የአጋዥ መረጃ አቀባዮች ፕሮፋይል

ሥም	የሥራ ድርሻ
አቶ ጀማል መሐመድ	የአርጎባ ወረዳ ምክትል አስተዳደርና የግ/ገ/ል/ጽ/ቤት ኃላፊ
አቶ ንጉሱ አቦሠጥ	የቃሉ ወረዳ የማስታወቂያ ጽ/ቤት የባህል ቢሮ ተጠሪ የነበረ
ዶ/ር መሐመድ ኃቢቢ	በአ/አ/ዩ/ የድህረ ምረቃ ት/ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት
ዶ/ር ዮናስ በየነ	በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ቢሮ የአርኪዮሎጂና ፖሊዮንቶሎጂ መምሪያ ኃላፊ
አቶ ተስፋዬ ኃይሉ	በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ቢሮ የባህላዊ አንትሮፖሎጂ መምሪያ ኃላፊ
Andreas Wetter	የሥነ ልሳን አጥኚ (Linguist)
አቶ ዘይኑ ዑመር	የተጠኚው አካባቢ ነዋሪ
ሲራጅ ኢብራሂም	በአርጎባ ልዩ ወረዳ የአስተዳደርና ጸጥታ ቢሮ ኃላፊ

አባሪ 6

የጽሑፍ መጠይቁን ሞልተው የመለሱ
የልዩ ወረዳው የመስተዳድርና የባህል ቢሮ ኃላፊዎች

ሙሉ ሥም	ጾታ	ዕድሜ	የትውልድ ቦታ	ብሄር	የሥራ ድርሻ	ተጨማሪ የሥራ ድርሻ
አቶ መሀመድ የሱፍ	ወ	33	ጮምዬ	አርጎባ	የልዩ ወረዳው የጤና ቢሮ ኃላፊ	የልዩ ወረዳው የሚሊኒየም በዓል ዝግጅት ኮሚቴ ተጠሪ
አቶ መሐመድ ጀማል	ወ	27	አንቻሮ	አርጎባ	የልዩ ወረዳው የሕዝብ አደረጃጀት ቢሮ ኃላፊ	የልዩ ወረዳው የሚሊኒየም በዓል ዝግጅት የኮሚቴ አባል
ሸህ ቡሸራ ሠይድ	ወ	45	ጮምዬ	አርጎባ	የልዩ ወረዳው ዋና አስተዳዳሪ	----
አቶ አህመድ እንድሪስ	ወ	27	አሠኔ አገር	አርጎባ	የልዩ ወረዳው የባህልና ማስታወቂያ ቢሮ ኃላፊ	የልዩ ወረዳው የሚሊኒየም በዓል ዝግጅት የኮሚቴ አባል
አቶ ኢድሪስ መሐመድ	ወ	30	ጮምዬ	አርጎባ	የል ወረዳው የጥቃቅን ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ኃላፊ	የልዩ ወረዳው የሚሊኒየም በዓል ዝግጅት የኮሚቴ አባል

አባሪ - 7

ለአርጎባ ልዩ ወረዳ መስተዳድር ኃላፊዎችና ባህል ቢሮ ሠራተኞች የቀረበ የጽሁፍ መጠይቅ

ስም ---------- ብሄር ----------

በልዩ ወረዳው ያለዎት ቆይታ---------- የትውልድ ቦታ ------- የአድገት ቦታ ------- የስራ ድርሻ ---------- ተጨማሪ የስራ ድርሻ ----------

1. በልዩ ወረዳው ስር ምን ያህል ቀበሌዎች አሉ?
2. በየቀበሌዎቹ ያሉት ነዋሪዎች የሚተዳደሩት በምንድን ነው?
   ሀ. ግብርና ለ. ንግድ ሐ. ሽክላ ስራ
   መ. ሽመና ሠ. ብረታ ብረት ስራ ረ. የእንጨት ሥራ
   ሰ. ሌላ ካለ ይገለጽ ----------
3. የእጅ ሙያ የመተዳደሪያ ስልት ነው ብለው ያምናሉ?
4. በእጅ ሙያ (በተለይ) የሚተዳደሩት ቀበሌዎች እናማን ናቸው?
5. ለጥያቄ ቁጥር ሶስት አዎንታዊ ምላሽ ካለዎት የእነዚህን ሰዎች ኑሮ ለማሻሻል እስካሁን በወረዳው ምን የተለየ ድጋፍ ተደርጎላቸዋል?
6. ድጋፍ ከተደረገላቸው ለምሳሌ ምን?
   ሀ. የሙያ ማሻሻያ ስልጠና፣ ለ. የገንዘብ ድጋፍ፣
   ሐ. ታታሪ ሰራተኞን የመሸለም መ. ገበያን የማመቻቸት
   ሠ. የእቃ አቅርቦትን የማመቻቸት ረ. የማስተዋወቅ ስራ የመስራት
   ሰ. ሌላ ካለ ይገለጽ ----------
7. ድጋፍ ካልተደረገላቸው ለምን?
   ሀ. ለእጅ ባለሙያ አሉታዊ አመለካከት ስላለ
   ለ. የእጅ ሙያ ለውጥ ሊያስገኝ አይችልም ተብሎ ስለሚታመን
   ሐ. ባለሙያዎች አሉ ተብሎ ስለማይታሰብ (ስለማይታወቁ)
   መ. የበጀት እጥረት
   ሠ. ሌላ ካለ ይገለጽ ----------
8. ወረዳው በመንግስት በጀትም ሆነ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ተነጋግሮ የእጅ ባለሙያዎችን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል የመስራት እቅድ አለው?
9. የባህል እንዲሁም የቅርስ ጥናትና ጥበቃ የተባለና ለዚሁ ተግባር የቆመ የስራ መደብ (ክፍል) በዚሁ ልዩ ወረዳ አለ?
10. ለጥያቄ ቁጥር 9 መልስዎ አለ ከሆነ እስካሁን ምን ምን አበይት ስራዎችን አከናውኗል? የአሁኑ እንቅስቃሴውስ ምን ይመስላል?

11. ለጥያቄ ቁጥር 9 መልስዎ የለም ከሆነ ለምን? ለወደፊትስ ይህንን የስራ መደብ በማዋቀሩ ረገድ ምን የታሰበ (የታቀደ) ነገር አለ?
12. በሚሊኒየሙ የብሄረሰቡን ባህል (በተለይ ቁሳዊ ባህልን) ለማስተዋወቅ ልዩ ወረዳው ምን እቅድ ይዛል? የተጀመሩስ ምን ጅምሮች አሉ? ካሉ ይገለጹ::
13. ልዩ ወረዳው የብሄረሰቡን ባህላዊ ቅርሶች የሚያከማችበት ቤተ-መዛግብት አለው?
14. ቤተ-መዛግብት ካለው የስራ እንቅስቃሴው ምን ይመስላል? ያከማቻቸው ቁሶች ብዛትስ እንዴት ይገለጻል?

ሀ. በጣም ብዙ ለ. ብዙ ሐ. መጠነኛ
መ. ትንሽ ሠ. በጣም ትንሽ ረ. ምንም

15. ቤተ-መዛግብት ከሌለው ይህንን ክፍል ለማቋቋም ብሎም ለማደራጀት ምን እቅድ ተይዟል? (በመጀመሪያ ግን ይህንን ክፍል ማቋቋሙ ይታመንበታል? ካልታመነበት ለምን?
16. የብሄረሰቡ ቁሳዊ ባህል በአሁኑ ወቅት በሚገባ ተለይቶና ተጠብቆ ይገኛል ብለው ያምናሉ?
17. ለጥያቄ ቁጥር 16 አሉታዊ ምላሽ ካለዎት ቁሳዊ ባህሎችን ለመለየትና ለመጠበቅ የሚደረጉ ግላዊም ሆነ መንግስታዊ ጥረቶችን (ለምሳሌ፤ የምርምር ጥናቶች) በማነሳሳቱና ድጋፍ በማድረጉ ረገድ ምን እየተሰራ ነው?

አባሪ 8

የታሪክ አዋቂ የሃገር ሽማግሌዎችን ለማወያየት የተዘጋጁ መጠይቆች

1. የተሳታፊዎች ሙሉ ሥም፣ ዕድሜ፣ የመኖሪያ አካባቢ፣ የሥራ ደርሻ
2. አርጎባ የሚለው ሥያሜ ምን ማለት ነው? ሥያሜውስ እንዴት ተሠጠ?
3. የአርጎባ ብሄረሰብ ምንጩ የት ነው?
4. የአርጎባ ብሄረሰብ ከአረብ ነው የመጣው ይባላል። ይህንን በተመለከተ ምን አስተያየት አላችሁ?
5. የአርጎባ ብሄረሰብ ከአረብ ከመጣ መቼ? በየትኛው የኢትዮጵያ ክፍልስ ወደ ውስጥ ገባ?
6. የአርጎባ ብሄረሰብ ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ በወቅቱ መጡ ከተባሉት በስም የሚታወቁ ሰዎች ካሉ ብትጠቅሱልኝ?
7. የአርጎባ ብሄረሰብ በኢትዮጵያ የተከለተው የአሠረጫጨት ሁኔታ ምን ይመስላል? በምን ምክንያት? (ተያይዞ የሚጠቀስ ታሪክ ካለ)

አባሪ - 9

የእጅ ባለሙያዎችን ለማወያየት የተዘጋጁ መጠይቆች

1. የተሳታፊዎች ሙሉ ሥም፣ ዕድሜ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የቤተሰብ ብዛት፣ የመተዳደሪያ መንገድ፣ የመኖሪያ አካባቢ
2. በእጅ ሙያው የተሰማራችሁት ከመቼ ጀምሮ ነው?
3. በሙያችሁ ተገልግላችሁ ምን ምን ቁሶችን ትሠራላችሁ?
4. የሙያው ባለቤት የሆናችሁት እንዴት ነው?
5. የተለያዩ ቁሶችን ለመሥራት በአጋዥነት የምትጠቀሚቸው መሳሪያዎች ምን ምን ናቸው?
6. የተለያዩ ቁሶችን በምትሰሩበት ጊዜ የምትከተሏቸውን ሂደቶች ብትገልጹልኝ?
7. የምትሠሯቸው ቁሶች ዋጋ ምን ያህል እንደሆነ በዝርዝር ብትገልጹልኝ?
8. ቁሶችን ለመሥራት ከምታወጡት የተለያዩ ወጭዎች አንጻር ቁሶችን ሸጣችሁ የምታገኙት ገቢ አዋጭ ነው ብላችሁ ታስባላችሁ? የገበያውን ሁኔታ እንዴት ትገልጹታላችሁ?
9. ተመሳሳይ ሙያ ያላችሁ ሰዎች ከአሁን በፊት ተደራጅታችሁ ታውቃላችሁ? ከሆነ እንደቅስቃሴያችሁ ምን ይመስል ነበር? ካልሆነስ ለምን? ወደፊትስ ለመደራጀት ታስባላችሁ?
10. ቁሶችን ስትሰሩ በሂደቱ ጎን ለጎን የምትከውኗቸውን ቃልግጥሞች፣ ተረቶች፣ ምሳሌያዊ አባባሎች፣ ታሪኮች፣ ወ.ዘ.ተ. ብትገልጹልኝ?
11. በሙያው ውጤታማ እንዳትሆኑ እንቅፋት የሆኗችሁን ችግሮች በዝርዝር ብትገልፁልኝ?
12. የአካባቢያችሁ ሰዎች ለእናንተና ለሙያችሁ ምን ዓይነት አመለካከት አላቸው?

መግለጫ

ይህ ቴሲስ (የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ) የእኔ ወጥ ስራ (Original) ሲሆን፣ ከዚህ በፊት በማንኛውም ዩኒቨርሲቲ የድግሪ ማሟያ ሆኖ አልቀረበም። ለጥናቱ በምንጭነት የተጠቀምኩባቸውን መረጃዎችም በሙሉ በተገቢው መንገድ መጥቀሴን አረጋግጣለሁ።

ዐሌዩ አስማማው ጌጋቱ

ስም

ፊርማ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

ሰኔ፣ 2000 ዓ.ም.